# እንኳን ደህና መጡ!!

# ወደ ብሑረ መፃሕፍት ዘ-ኢትዮጵያ

# @ETHIO_PDF_BOOKS

አዳዲስ መፅሐፍትን በ
የሚያገኙበት ምርጥ የቴሌግራም ቻናል ነው፡

እናም ቤተሰብ ካልሆኑ ቤተሰብ ይሁኑ! ብዙ መፅሐፍት
እየመለጠ ነው ይፍጠኑ!



16ኛ ዕትም

# ትንቢተ ሸህ ሑሴን ጅብሪል



ከቦጋለ ተፈሪ በዙ

Scanned with CamScanner

# ትንቢተ ሼህ ሁሴን ጅብሪል

[illegible]

‹‹የዛሬን ለነገ ካላኖሩት ጽፈው
ከዋለ ካደረ ቅሬተ አካል ነው፡፡››

አባ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን


| | |
|---|---|
| ለሶስተኛ | ጊዜ በ1994 ዓ.ም ታተመ |
| ለአራተኛ | ጊዜ በ2002 ዓ.ም ታተመ |
| ለአምስተኛ | ጊዜ በ2006 ዓ.ም ታተመ |
| ለስድስተኛ | ጊዜ በ2006 ዓ.ም ታተመ |
| ለሰባተኛ | ጊዜ በ2007 ዓ.ም ታተመ |
| ለስምንተኛ | ጊዜ በ2008 ዓ.ም ታተመ |
| ዘጠነኛ | ጊዜ 2009 ዓ.ም ታተመ |
| አስራሁለተኛ | ጊዜ በ2011 ዓ.ም ታተመ |
| ለአስራ ሶስተኛ | ጊዜ በ2011 ዓ.ም ታተመ |
| ለአስራ አራተኛ | ጊዜ በ2011 ዓ.ም ታተመ |
| ለአስራ አምስተኛ | ጊዜ በ2012 ዓ.ም ታተመ |
| ለአስራ ስድሰተኛ | ጊዜ በ2012 ዓ.ም ታተመ |



መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
© All rights reserved


Scanned with CamScanner

# ማውጫ

መግቢያ ........................................ 1

ክፍል አንድ

ሸህ ሁሴን ማን ነበሩ........................................ 19

ክፍል ሁለት

የግጥሞቹ ይዘት ........................................ 29

የግጥም ስብስበ በተራ ፊደል ........................................ 81

ተጨማሪ ግጥሞች ........................................ 101

ዐምደ ቃላት ........................................ 231

የሕዳግ መዘክር ........................................ 233

ዋቢ መጻሕፍት ........................................ 234

Scanned with CamScanner

1. በጽሑፍ ያልቀረበ በመሆኑ፤
2. ያውቃሉ የተባሉት ከግጥሙ ይልቅ ታሪኩን ብቻ ማወቃቸው፤
3. የሸሁን መናቁብ የቃሉ የተባሉት ዓይናቸው የፈዘዘ፣ ጆሯቸው የደነዘ፣ ጉልበታቸው የዛለ፣ አንደበታቸው የተሳሰረ የመሆኑ፤
4. አንዳንዱም አንዱን ስንኝ ጠርቶ ሁለተኛው ላይ ማቆሙና ሌላም ሌላም፤

ስለዚህም ግጥሞቹን እጠቃሉ አለማቅረቡም ነበር ሌላው ችግር። ቢሆንም በደሴ ከተማ ሰው የሚመጀንባቸው የጠንገጉው ሸህ ዘንድ ቀረብኩ። እንደ በሽተኞቻቸው ከመራመሩኝ ከታሪኩም ከስንኙም ከወራወሩልኝ በኋላ ሸኩኩ አሉኝ። "ምነዋ! ምናልኩሃ! በወይት መጣህብኝ?" አሉና አበረሩኝ። ሰቀቀን ነበር። ሌላው በኪታብ መልክ አሳቸው የተባሉትም ለባለጋሪና ለባለካሚዎን ረዘቁኝ። ነገሩ አጀብ! የሚያሰኝ ነበር። እኔም የጀመርኩትን ከሐቁ ዝንፍ ከውበቱ ዘንበል ሳይል አቀርባለሁ በሚለው እምነቴ ቀን በሐሩር ጧት በአመዳይ በየሰው ቀየ ከመገተር አላቋረጥኩም። ሱቢህ ለማኝ ወገቡን ሳይፈተን፣ ዶሮ ጩኸት ላይ ከአባወዴ በመጋፋት፣ ዝሁር ላይ በየዛውያው፣ ከሶለት መልስ በየባቡሩ መንገድ፣ መቅረብ ላይ ከብት ሲያለቃቅሙ ለዓይን ሲይዝ በየዛኒጋባው በመንከላወስ ነበር። ሙመለሻዬ።

የሸሁን ታሪክ ሲጠይቋቸው በይህም በይህም ስለይህም ተናግረው አልፈውታል። አቦ ምን ያላሉት አለ? በማለት ይደመድማሉ። እኔም ጥንብ እንዳየ ሳቢሳ፣ መውሊድ እንደሚያሳድድ ደረሳ፣ በየቦታው ክስ ክው ስል፣ ባለአውሊያ ቤት ዘው ስል፣ ቁርዓን በሚያስቀሩበት አረፍ ስል፣ ሲሸከኩም በመሸሽ ነበር ያቋትኩት። አሉ ከተባሉት ዘንድ እሄዳለሁ። በመቆጨት ወየኔ ይኸን እኮ እነሸህ እገሌ ያቁት ነበር። ምን ይሆናል? በቀት ሄዱ እንጂ! በማለት ያን በወሎ የወረደ የሰቀቀን፣ ያን የዋይታና የጣር ቀን፣ ያን ምድር የተቧጠጠበትን፣ እንባ ጐርፍ የሆነበትን ቀን፣ በእንባ ጭጋግ እየተመለከቱ ቢጠሯቸው ወይ ይሏቸው ይመስል ዓይናቸውን ጣራ ላይ ሸጠው፣ በትዝታ ገመድ ወደኋላ ተስበው በእንባ ጭጋግ ታጅበው፣

"የነበር ቢያወጉት ይመስላል ያልነበር፣
ከዚህ ዘመን በፊት ወሉ ጥጋብ ነበር።" ያሉት።

ይህንም አሉና!! ዓይናቸውን ባይበሉባ ዳጡና፣
እናንት ዘመዶች ወለጋ ያላችሁ፣
እናንት ዘመዶች አሰሳ ያላችሁ፣
ዝናቡ ዘነበ ግቡ አገራችሁ
ደጋሲቱ በቅሉ ቢፈለግ አጣችሁ"

የምንልበት ወቅት ሩቅ አይሆንም አሉኝ። እንባ ዓይንን ሰርቅታ ስሜትን በሚሰቀጥጥ አባባል።

ሌላውም ይኸን ማንቁብ ብሉት በማለት ይሸነግሉኛል። ሌላው ደግሞ ጌታው! እንዲህ ዓይነት ጀምሬ ነበር ቢነዩቱኝ ስላቸው "እይህ ሥርፋ እንገናኝ" ይሉና የውኃ ሽታ ይሆናሉ። አንዳንዱም "አንተ አቅልህን ስተሃል? ጨርቅህን ጥለህል እንዴ? ዛሬ ሳይንስ አብቦ፣ ቴክኖሎጂ ዳብሮ፣ ሰው የምድርን ሆድቃ ዘንትሮ፣ የጨረቃን የማርስን ምንነት በሚፈታተንበት፣ ሰው ልጅ በጉነት በሚያስብበት ሰዓት፣ አንተ ሕዝቡን ልቡን ሰልበው፣ አእምሮውን ሰውረው፣ ዓይኑን አውረው፣ አንደበቱን ዘግተው፣ ያቆዩትን ጠንቋዮች ቃላት የምትጽፈው? ይልቅስ የኅብረተሰቡ ዕለታዊ ኑሮ የሚቃናበትን፣ በአካል ጠንክሮ በአእምሮ በስሉ መሬት አሰስልሶ፣ ተራራ አፍልሶ፣ ጠላቱን ድሶ የሚኖርበትን አትጽፍም? ይሉኛል። ሳይንስ ተገንጥሉ ከሌላ ነገር እንደመጣ ሁሉ። ሳይንስም የነገሮችን ምንነት አጠናቅቆ በውሳኔ ዶሴውን እንደዘጋ ሁሉ። እኔ ግን የአንዳንድ አስመሳዮች ጋሬጣነትና፣ የነገሩ አለመገኘት ቅር ቢያሰኙኝም ይኸን በቃል ተነግሮ ካፍ አፍ ሲተላለፈ የቆየውን መሰብሰቤ የሕዝቡን የመያዝ ችሎታና የነገሩንም ታሪካዊነት በማሳየት ሰፊ ጥናትና ምርምር እንዲደረግበት ይገፋፋል በሚል ነው። የሕዝቦችም ጥረት ከታከለበት ለዚህም ሆነ ለመሰል ጥናት ይረባል በማለት ነበር ችግሮቹን ቀብ ሳልል የገፋሁበት።

የአበውን ንግግር ካለማወቅ በስመ የጥንት ግጥም በስመ የሽማግሌ ንግግር ሥራው ሁሉ ከሳይንስ ውጭ ነው ማለቱ ራስንም የሳይንስ መናፍቅ ከማድረጉም በላይ፣ ከአባቶች ምንም አይገኝም እንደማለት ይሆናል በማለት ነበር የጀመርኩት፡፡ የአበውንም ንግግር ጠለቅ ብለን ብናየው በስመ ነጻነት ባርነት፣ በስመ እኩልነት የበታችነት፣ እንዳለም የጠቆሙበትን ለማሳየትም ነበር ያቋትኩት፡፡

እኛም ሆን መጭው ትውልድ መጥፎውን ለቅርስነትና ለትምህርት፣ በጐውንም ለዕድገት በር ከፋችነት መለየትና መጠቀም የምንችለው የጥንታዊቷንና ታሪካዊቷን ኢትዮጵያ እምነትና ሥርዓት፣ ታሪክና ዝና ለማወቅ ካለፈው ስንነሳ ነው፡፡ ቀን ካለቀሙ ሌሊት አይቅሙ ነውና! በሌላ በኩልም ለዚህ ችግር መፈጠር ምክንያቶች አሉ፡፡ ባጠቃላይ ግን አባቶች እንደ ጓያ ነቃይ የፊት የፊታቸውን ከማየታቸውም በላይ የቅኔ ቋንጣ፣ የወሬ የሰው ፍሬ በማለት ብቻ እንዲህ ዓይነቱንም ፋይዳ ቢስ ነው እያሉ ስለሚተዉት ወይም ጽፎ ደጉሶ ለማስቀመጥ ብራና የመዳመጥ፣ ቀለም የመበጥበጡ ጣጣ ፈንጣጣ ጉዳይ ስማይ በመሆኑ፣ ትምህርትም ጸሐፊም ያለመኖሩ ነገሮችም ድብቅ በመሆናቸው ነበር፡፡ ጸሐፊም ክብር አልነበረውም፡፡ የዕምነት ጉዳይ አለና! የዚያን ጊዜ ኀብረተሰብም ከጽሕፈት ይልቅ ወደ ቃሉ ያጋደለበትም ምክንያት ሊኖረው ይችላል፡፡ ስለእንዲህ ዓይነቱም ነገር አቶ አጽመ ጊዮርጊስ "የጋላ ታሪክ" በተባለው መጽሐፋቸው በመቅድሙ ሳይ የዚያን ጊዜ የጽሕፈት ሥራ ሲያስቀምጡት እንዲህ ይላሉ፡፡

> *የጽሕፈት ልማድ በኢትዮጵያ ካህናት ዘንድ፣ እጅግ አልነበረም፡፡ ቢኖርም ለነገሥታት፣ ለመኳንንት ይጻፋል፡፡ የሚጽፏቸው ለቤተክርስቲያን፣ የሚሆን ነገር ነው እንጂ፣ የጊዜውና የወራቱን ታሪክ፣ ለመጻፍ የሚከለክሏቸው ይመስላል፡፡ ብዙ ጸሐፊም አልነበረም፡፡ አንዳንድ ቢኖርም ክብር የለውም ወራዳ ነው፡፡ ማዕረጉም ከሰው በታች ነው፡፡ ጸሐፊ ለጥፊ ብለው ያስንቁታል፡፡ እንዲያውም ጠንቋይ፣ ምትሐተኛ፣ አስማተኛ ይሉታል፡፡ ስለዚህም፣ ታላላቅ መምህራንና አጨጌዎችም፣ ጽሕፈት አያውቁም፡፡ ጻፉልኝ፣*

*አንብቡልኝ እያሉ ጠንቋይ የሚሉት፣ በጻፈው ይጸልያሉ፣ ይተረጉማሉ እንጂ/ይላሉ::*

ስለዚህ ነበር፣ የሸሁን ግጥም ለመሰብሰብ ያስቸገረው:: አሁንም ወፍ የያዘ ሰው ያችን የያዛትን ሰዶ ሳይሆን ሌላ የሚሻው፣ የያዘውን ይዞ እንጂ! እኔም ይኸን በመረዳት ነበር ለሌላ ማሽኰበኰቢያነት ይህን ማቅረቤ:: ቀደም አድርጌ እንደጠቀስኩት ብዙ እንቅፋቶች አንገደውኛል:: ቢሆንም አልፌአቸዋለሁ:: በመጠኑ ብጠቅሳቸው፤

1. ሸህ ሁሴን ገጥመው አልፈዋል የተባሉበት ጊዜ የት እየለሌ በመሆኑ እውቃቸዋለሁ ባይ ያለመኖሩ፣
2. የልጅ ልጅ የተባሉት ሆኑ፣ በኪታብ መልክ አላቸው የተባሉት በየምክንያቱ ለማግኘት ባለመቻላቸው፣
3. የሚያቁ ቢገኙም "ምን የሰው ታሪክ ባህር አደል! ቢሆንም እንዲሁ እየኑሱ:: ቡን ተፈልቶ፣ አድሩስ ተጭሶ፣ ዳሚ ከሴ ተቀንጥሶ፣ አርቲና አሸኩቲ ተነስንሶ፣ ቁጤማ ተጉዝጉዞ፣ ረከቦት ተዘርግቶ፣ ፊንጃል ተደርድሮ፣ ጀበና ተገትሮ፣ አወገረድ ተንበርክኮ፣ እጅ ተዘርግቶ፣

   "አባል ጀባ ቀሃ ጀባ፣
   እማይበጀን ገደለ ይግባ
   ዳውዶ ረግረጉ አዛዋገደል ቁልቁለቱ፣
   ዱበርቲ መራቀቱ፣
   በቀቅሳ ምንጩቱ:: መጀን!!" ተባብሉ ተመራርቆ ታልሆነ

አያዋጣል ይሉና መልስ ይሰላሉ::

4. ከቴም አንዳንዶች "ከወይት መጣህ አይዋ!" ይሉና ተማሪነቴን ስነግራቸው "እስዎ"

   "ሰማንያው ያልቅና ቲሆን ሦስት ዓመት፣
   ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት":: ቲሉ ጨርሰውት የለ!

 በል ከይር ተመለስ ይሉኛል::

5. በእምነት እንጻርም ያየን እንደሁ በዕድሜ የገፉ ትምህርት ያላዩ ከመሆናቸውም በላይ ባለህ እርጋ በሚለው የጸኑ ስለሆኑ እንዲህ ዓይነቱን አደባባይ ማውጣቱ ቅር የማሰኙቱም ነበር።

6. ባጠቃላይ የእኒህን እንደ ዐረቂ መርፌ የሚወጋ ዓይን፣ እጅግም የተባ ጆሮ ነበራቸው የሚባሉትን ሽህ ግጥሞች ለማግኘት ያልፈነቀልኩት ድንጋ፣ ያልገረሰስኩት ጉቶ፣ ያልበጠስኩት ቅጠል፣ አልነበረም። ግን ቂሉም ዝም መጣፉም ዝም እንደተባለው ሆነ። ያም ሆነ ይህ ቅዋየ የፈቀደውን ቀራርሜ አቅርቤአለሁ።

7. የቋንቋውንም /የዘየውን/ ሁኔታ እንዳለ አገሬው እንደሚናገረው በተፈጥሮው ያለውን ለዛ የታሪክ አተራረክ ባለቤትነት በመረዳት ግጥሞቹ ሳልከልክ ሳልኮላ ወጥነታቸውን በመጠበቅ አስቀምጫለሁ፤

8. ለአንዳንድ ከመደበኛው አማርኛ ለወጥ ይላሉ፣ የወሎኛ ቃላት ናቸው ብሎ ለምላቸው በዐምደ ቃላት ማብራሪያና ፍቺ ሰጥቻለሁ።

ወሎ! ታያ! ተቁቶ የማያልቅ ተዝቆ የማይጨረስ፣ አነሁልሎ የሚያስቀር፣ አወዛውዞ የሚያስለቅስ፣ ልብን ስልቦ፣ አእምሮን ሰውሮ አቤት ወዴት የሚያሰኝ ጨወታና ቁም ነገር የሚመነጭባት ናት። ይህች የቀዘቦች መፍለቂያ ወሎ፣ ዋሽቶ ልከበር፣ ቀላምጄ ልፈቀር፣ የማይሉ የነገሮችን ምንነት እንደ እሸት ፈልፍለው፣ እንደ ጣዝማ ሰርስረው፣ የሚያቀርቡ በሰው ጀምበር ዘልቀው የሚናገሩ፣ ቢመጅኑባቸው የሚያሽሩ፣ ቢሽሿቸው የሚያቀርቡ፣ ቢጠንቸው የሚያከብሩ አያሌ ባለአራት ዓይና ሰዎች ትታወቃለች። ለአብነትም የአርሲዋን እመቤት /የጁዬ/ የመርሳውን አባ ገትዬ፣ የየጁውን ልጅ /ኂሳ ቀኛዝማች/ ታየንና የጠንገጉዋን ሽህ መጠቃቀሱ ያስኬዳል።

እነኝህ ትምህርት በማይታለምበት፣ ብዕር ባልተጨበጠበት፣ ፊደል ባልተቆጠረበት ዘመን የተኸልቁ ሰዎች በመንጉል ሳይከትቡ፣ ወረቀት ሳይገልጡ፣ ፊደል ሳይገጣጥሙ አያሌ ቁም ነገሮችን አስጨብጠዋል።

ስለዚህ እነዚህ ቃላትን ከቃል አጋጭተው ሐቅን አውጥተው ጥንት

1. በሥነ ጽሑፍም ሆነ በሌላ ሌላ ልዩ መስክ ተሠማርተው ለሕዝባቸው አንድነት፣ ለሀገር ደህንነትና ብልጽግና ለድሆች ልዕልና የተናገሩ የጻፉትን የወጡ የወረዱትን በማከማቸት ያለፈው ከአሁኑ አባባል ጋር ይቀራረብ፣ ይራራቅ እንደሁ ለማሳየት፣
2. ያሁኑም ሆነ የወደፊቱ ትውልድ አበው በጀምበራቸው የሠሩትን፣ ስለሌላ ጮራ ያሉትንና በዘመናቸው ከመጣላት ይልቅ መፈቃቀርን፣ ከመነጣጠል አንድነትን ያስተዋሉበትን ለዚህ ጠብን በጄ ነገርን በጉንጩ ለያዘ ትውልድ ማመላከቱ እስቲ? ሊል ይችል ይሆናል በሚል፣
3. የአበው እልፈት በውሉድ እንደሚተካ ሁሉ የጥንቱም አጻጻፍና ንግግር ባዲሱ መተካቱ ስለማይቀር ምን ይዞ ጉዞ እንዳይሆን የጥንት ሰዎች የተናገሯቸው ንግግሮች፣ የደረደሯቸው ግጥሞች የተቀኟቸው ቅኔዎች የጻፏቸው ጽሑፎች ተሸክፈው ቢቀመጡ ሥራቸው እንዳይረሳ፣ ተግባራቸው እንዲወሳ ለማድረግ ስለሚረዳም ነው።
4. በዚያ ቢጣሩ በማይሰማበት ጀምበር የታየ የተሰማው፣ የተነገረው፣ የተተረከው፣ የሕዝቡን ሳቅ ልቅሶውን፣ ዘፈን እስክስታውን፣ ማኅበራዊ ገጽታውን ባጠቃላይ አኗኗሩ ደብዛው ሳይጠፋ፣ የትውፊትነት ሐያቱን ለማቆየት ጭምር ነው ጨለፍ ተደርጐ መቅረቡ፣
5. ያገራችንም ሰው ነገሮችን በጠባሳ ጐናቸው ብቻ ከማየትና ከመሰቅጠጥ አልፎ የጉድም ይበላቸው የእርግማን ሥራዎች የጋኔንም ይሁን የውቃቢ ጠቦች ያሻውን ስም ይሰጣቸው ለምርምር አቅርቦ አጥፊውንና አልሚውን ለይቶ የመያዝ ልምድ ቢያዳብር በማለት ነው።
6. ደራሲ መንግሥቱ ለማ "ባገራችን በኢትዮጵያ ደግሞ የታሪክና የባህል መዝገብ የሆኑ ሽማግሌዎች ከመምህራኑም ከማይሞቹም ወገን አሁንም ሞልተዋል።

ቶሎ ቶሎ፣ ብለን ከዓለሙ አላፊነት ተሻምተን መዝገብነታቸውን ካላስቀረነው ነገ አይገኙም እንዷሉት ሁሉ ምን ይዞ ጉዞ እንዳይሆን ተሻምቶ ለማስቀረት ያህል ነው፣ እንዲህ ዓይነቱን ለአብነት ያህል አለፍ አለፍ እያደረግሁ መጠቋቆሜ።

አንድም ሥነ ቃል ከቃል ወደቃል እየተሸጋገረ የመቆየት ኃይሉን ያሳይ ይሆን ለማለት ቢረዳ በማለት፣ ሁለትም የቀደምት አባቶች ክህሎት በዘመነ ሮቦት ገኗል ወይስ ደብዟልን እንዲያጤኑበት፣ በሌላ መልኩም አፍአዊ ኩነተ ቃል ቢሰበስቡት የቆየን፣ የመንደርን፣ የደብርን፣ የአካባቢን እንዲያም ሲል የሀገርን ሥርወ አመጣጥ፣ የቋንቋውንም ዕድገትና ውድቀት ለመጠቆም ማስቻሉን ለማዘከር፣

⇒ በሌላ ጀምበር የተነገረ ኀልፈት ሳይዳብሰው፣ አፈር ሳያበላሸው፣ ዛሬው በዋቢነት በመገኘቱ ዘመነ ሳይንስ እንዴት? ብሎ ይጠይቅ ይሆን? ለማለቻነት፣

⇒ በዘመነ ሽበቱ ከመጣል አልፎ የአንድነት ባህታዊ የታሪክ ሐረግ አመራማሪ፣ ይህም አለ ለካ አሰኚ በመሆን በመለያየት ፈንታ መቀራረብን ጠቃሚነቱንም ለማሳየት ያግዝ ይሆን ለማለት ጭምር ነው። ስለሆነም ለመንቀፍም ለመደገፍም ቸር ንባብ።

## ጽሑፉ የቀረበበት አካባቢ

ወሎን በሰሜን ትግራይ፣ በደቡብ ሸዋ፣ በምዕራብ ጐጃምና ጐንደር፣ በምሥራቅ አሰብና ሐረርጌ ያዋስኗታል።

ወሎን በራስጌ በግርጌ በቀኝ በግራ እትፍ ክቡብ እንድትደረግ ተፈጥሮ እድላታለች። ጥንትም ሆነ ዛሬ ወሎ የጉብሉች፣ ወሎ ያይናማዎች፣ ወሎ የቀዘቦችና የእንጉርጉሮ መፍለቂያ ትባላለች። ስመ ጥር ጀግኖቿን ፈፋ ወንዟን፣ ወዳ አውራጃዋን፣ አንጡራ ገንዘቧን በሆነው ስንኝና ጣዕመ ዜማ በማውጣት ትጠራለች። ወሎ ሴቱ እንዳላማ ሰንደቅ ክሩቅ የሚታይበት፣ በእደሉ በቁኒው፣ በጥራቱ በውበቱ ሳይበላ ይጠገብ የነበረባት የፍቅርና የትዝታ ማፈሻነቷን መግለጫው፡-

መጣች የወሎ ልጅ እንዳረግ ተመዛ

ሳይበሉ እሚያጠግብ ትዝታዋን ይዛ የሚለው ነው።

ወሎ በናፍቆት አወዛዋዥ ናት። በጉብሉች ማራኪ ናት። የቆንደ ሳቅ ፈገግታ የሚሰነቅባት ሀገር ናት። የጥንቷ ላኮ መልዛ የዛሬዋ ወሎ ጥንቅሽና ሽንኩራ ደጋሊትና ዘንጋዳ የሚቆረጥባት፣ ገብስና ስንዴ የሚታፈስባት፣ ማኛ ከሠርገኛ የሚታጨድ የሚወቃባት፣ የባቄላ፣ የምስር እሸት የሚፈለፈልባት፣ ብርቱካን መንደሪን የሚበቅልባት፣ ዘይቱን ከሎሚ የሚያፈራባት፣ ትርንጉና ሙዝ የሚገመጥባት፣ ጥንቅሽና ሽንኩራ የሚመጠጥባት፣ ፓፓያ ለውዝ፣ ማንጉና ጥጥ የሚለቀምባት፣ አሳም የሚረባባት ከመሆኗም ሌላ፣

ከገበሬው ጋር ምርቱ እንዲያ ሲያምር

የጉብዞች አገር ወሎ እንዴት ይቅር፣ የተዜመላት ናት።

ወሎ፣ ደጋ፣ ቆላና ወይና ደጋ የአየር ጠባይ ያላት፣ በአስራ ሁስት አውራጃ የተከለለች ናት።

ወሎ፣ በሎጋ ሐይቅ ደሴቷ፣ በጃሪ ፍልውሃዋ፣ በደንቆሮ ዋሻዋ፣ በግሸን ማርያም አጣብቂኝነቷ፣ በግማደ መስቀሉ መቀመጫነቷ፣ በላሊበላ ፍልፍል ሕንፃዋ ጠቅላል ሲል፣ በታሪካዊ ሥራዋና ቅርሳ ቅርሷ ዕውቅና

ሲናራት፣ በንግግር ዘየዋ በሕዝቧ የዋህነት በሌማት እንጀራ፣ በፎሌ ጠላ፣ በአንኮላ ወተት ለጋሽነቷም ትታወቃለች። ወሎ ገብሱም ይሰኛል ሕዝቧ።

ወሎ፣ ቀድሯን አቃ የተሠራ የተመራባትን ተቀባይ ናት። ከምሬትና ከተፈራረቁባት መከራና ብሶቷ ባፈራቻቸው ክልላዊ ፍቅሯና ዜማቀ አዝማሪው በመሰንቆ ኮበሌው በዋሽንት፣ አረሆ ከቁርበት ወልይ ከድቢ ሳዱላ ተድምጽ እናቶች ተወፍጮ ባዋሐዱት አንጀት በሚባላ ሆድን በሚያባባ፣ ትከሻ በሚያዝል እስክስታ፣ ድምብል በሚያዘልል የዋንጫ ልቅለቃ!

በናቷም ባባቷም ወረሂመኖ ናት

እንደ በልጅግጥይት ትመታለች አናት።

አረጉ አፋፉ ላይ ያገኘናት ልጅ

በጅ አትንኩኝ አለች በከንፈር ነው እንጅ።

ባቂላ ምርቱ እንጂ አያምርም ከምሩ

ይምጣ የወሎ ልጅ ተነምንሽሩ። የተባለላት ናት።

ጉበዝና ጉብዝናም ዱላ ማናሳት ታቅበታለች። በጀግና ሞት በእኔና ባንቺ ሞት አዘካሪ ኧኸይ ወለሌዋም።

ተው ስደድልኝ የጅህን ሉሚ
በሽተኛ ነኝ ልቤን ታምሜ።
ለሉሚው ነው ወይ ለምቧዩ ፍሬ
ሰው ለወደደው ይሰጣል በሬ። ትለዋለች።

ወንዱም፡- አቧራ በሚያምስ፣ ልብን በሚያፈርስ ድልቂያ፣

አይዘለዘልም የጅብ ኩላሊት
እስቲ እንከስ እንደዜ የፊት የኒሊት።
በጊቱን ጅብ በላይ እረኛው ወስልቶ
ዘልቆ ለወሎ ልጅ የሚነገር ጠፍቶ።
የመዋጣ ዱላ አልፎ አልፎ ጅን አለው

እንዲያውም አደለ እየሙቱበት ነው።
ማማው ደብረታቦር ማማው ደብረታቦር ደጋሲቱ የጁ
ወንጭፉ አጠረና ወፎች እህል ፈጁ።
አንወሻሽና እውነት እንናገር
አይደለም ወይ ወሎ የነሰበር አገር። ይላል።

እም! የወሎ ዕውቅና መች በይህ ብቻ! የዘመን መደፍረሱን የአዝማሪ ማሸት መምከኑንም በመናገር ጭምር እንጂ። ታዲያ! ያ! የየጁ የደጋሲት ክምር! ያ የጨፋ የጤም ቁልል ያ! ስጋምበ ቅበና፣ ያ ማር፣ ያ! የሰገሃዲ የጉብስ ሽክም፣ በፈረስ ጉግስና በጥይት አልሞከር ያላሰውን ያህል፣ ሰው እንደሚችገር አዝመራም እንደሚመክን የጊምብ እረጃ ማር፣ ያ! የሰገሂዳ የጉብስ ሽክም በፈረስ ጉግስና በጥይት አልሞከር ያላሰውን ያህል ሰው እንደሚቸገር አዝመራም እንደሚመክን የጊምባ እረኛ፡-

አህያ መጣች ተጭና አሻበ
ክፉ ቀን መጣ በስተሰጋምቦ
ሰማይ ይደፋል የነሐሴ - አቦ።
አህያ መጣች ተጭና ማቅ
እንግዲህ ቀረ እህል መዛቅ።
አህያ መጣች ተጭና እብቅ
ሁሉ ተማጧል የለም ርዝቅ።

ሲል ፍራ ጠርጥር ይላል። ሰው እንደገደል ላይ አፈር በቃል ያለመርጋቱን፣ የድሃ ፍቱን መድኃኒትነቱ የተናገሩበት።

አህያ መጣች ተጭና እንዶድ
ክፉ ቀን መጥቷል የሚያካክድ።
አህያ መጣች ተጭና ቅማል
የዘንድሮ ቀን ጫት ያቃቅማል። የሚል ነበር።

ችግር ደህና ሰንብች። አዝመራው አሸተ። ጥጋብም ነገሠ፣ ያሉበት ሰንኙ፡

አህያ መጣች ተጭና እንቅብ
ችግርም የለ ሆኗል ጥጋብ።
አህያ መጣች ተጭና እበት
አምላክ መጣልን ተኸደበት።

ድንገት ባጋጠማትም ዱብ ዕዳ፡-

ራሴን ወገቤን ብሉ ሳይናገር

ታሞ ነበር እሱ ወሉን ያህል አገር፡፡ ተብሉ የሚዜምላት ነበረች፡፡ ያ ማኛ ከሠርገኛ ምስር ከባቄላ ያመርት የነበረ ኩሩ ሕዝብ ምነው ይጠወልድ እንዴትስ ለራሱ ቅቤ፣ ለሆዱ ቂጣ ይጣ በማለት የተናገረው የስንኝ ቋጠሮም፡-

ወሉ ጠቅላይ ግዛት ገብሱ ጥሩ ነው

ያለም ምርት ፈጣሪ ብትሰጠው ምነው፡፡ ነበር አምራችነቱን ያዘከረው፡፡

ሠርቼ ለሰው የለበትም፡-

እናበቅል ነበር ሠርገኛ ተነጭ

መኪና ወሰደው በላው ተቀማጭ፡፡ የሚል ነበር፡፡

ይቺ ወሉ ፊት በጦርነት ኋላም ለከሰብ አሁንም በድርቅ ፍልሰት የደረሰባት ናት፡፡ ሰዋ ሥጋው ተፍቶ ባጥንቱ የሄደባት፡፡ ነዋሪዋ ቀባሪ አጥቶ ያውሬ ራት የሆነባት፣ የሬሳ ጡት የጐረሰባት፤ ሰዋ ረግፎ ሌላው የሰመሰመባት፡፡ ህልቆ ታርዞ ሌላው የለበሰባት፡፡ ጉብልና ሶታዋ ጠንዝሉ ሌላው የወዛባት፡፡ ድፍን ዓለም ያነባ ያዜመላት፡፡ ያለ የሌለውን የነየታት ወሉ ናት፡፡

ሕልቋም ስደት ልማዱ ተብሉ የተተረተ የተሳቀባት፡፡ በውድቀቱ ሻፓኝ በደሙ ውስኪ የተጠጣባት፡፡ ታዳ ወሉ አወዳደቁ ያለማማሩ ቢያስገርመው አያል ሰው አቃለሁን ድፍን ዓለምን አጣቅሳለሁን የተናገረበት፡፡

አላማጣ ውዬ ዞብል አቀናለሁ

አታርገኝ ጣል ጣል አያለ ሰው አውቃለሁ ነበር፡፡ ይህ ነበር እህህ የሚያሰኘው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ነበር በእንባ ጭጋግ የሚያመላክተው፡፡ እንዲህ እህህ በተፈራረቁባት አገር ነበር የጽሑፌ መነሻ! እንዲህ! ቁም ስቅን ባየችው አባት ልጁን፣ እናት ቤተሰቧን በጣሉበት አካባቢ ነበር ጽሑፌን ያየሁት ማየቱ ደግ ነውና! ብዙ ስለታየባት ብዙ ጥናትና ትምህርት

ሲገበይባት ይችላልና! ጠጠርም ሆነ ዘንግ የሚወረወረው በሚበላ ፍሬ ላይ ነው እንደተባለው እጅም የተዘረጋው ዓይንም ያረፈው ወሎ ላይ ነው። የእሸት-ና የዓይነ ግቡ ጉብሉች መብቂያ በመሆኗ። ወሎ! ለሀገር ሰላሙን፣ ለገዥም ልብን ይስጠው በበረኛ በሠርጠኛው የሚባልባት መልካሙን የሚመኙባት ለመሆኗ ስንኞች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

እዘይው በጉር አንቀልባ
አማን ውሎ አማን ሊባ
እነየ ሐጃሽ ይሁን
ያውም ዛሬ ያውም አሁን፡፡
አማን ነው ምንም የለበት
እነነየ የሚውሉበት

ወሎ ያጣ የሚያገኝበትን፣ የደከመ የሚበረታበትን፣ የታመመ የሚሽርበትን፣ የሚያሳብሱ የእስልምና እምነት ተከታዮችም መኖሪያ ናት፡፡ የደረቀን በሚያረጥቡ፣ የራቀን በሚያቀርቡ ቱፍታ ሰጪዎች ከመጠራቷም ሌላ በአፋዊ ኪነተ ቃል አዝመራዋም ጉልህ ሥርፋ አላት፡፡ ወሎ በውበቷ ኪነት ሁሉ የሚያረግድ የሚያዜምላት በአምባሳል በባቲና በአንቺ ሆየ ቅኝት ከአንደበቷ የማይለዩዋት ናት፡፡

ወሎ እንደ እህል ዓይነት የሰውና የግብር ዓይነት የሚታይባት ያጣ ያገኝብኝ የራበው ይጥገብብኝ፣ የታረዘው ይልበስብኝ የደከመው ይረፍብኝ፣ የቸኮለው ይለፍብኝ ብላ ደረቷን የዘረጋች ውብና ስመ ጥር አገር ናት፡፡

ወሎ! ሚናኢዝ /ክፉ/ ሲገጥማት አንሳልኝ የምትለው፡፡
የወሎ ደመና አይሆንም ለየኛ
እባክህ አንሳሰን ተነንግዶ ልጅ በሚል ነው፡፡
ተንኮል ሲበዛም ቀምበጥ ይዛ ሙላቃን የምታደቀው
እደግ እደግ ብለን ያሳደግነው ቀጋ
ይላል ጉንበስ ቀና እኛኑ ሊወጋ
አርግልን ያልንህንአረክልን ለካ
በነካካው እጅህ እኒህንም እንካ፡፡ በማለት ነው፡፡



Scanned with CamScanner

ከዚህም ሌላ ወሎ ይኸን በዋል ፈሰሱንና ቀልብ የነሳውን፣

የተቸበቸበው በሶረኔ ግንድ

በየደረሰበት ይባላል ወጊድ።

የተቸበቸበው በሶረኔ ቀምበጥ

በየደረሰበት ይላል መጠጥ መጠጥ። እንደምትልሁሉ።

ከአቅል የሆነውን አሁንስ ደስ ደስ አለኝ

ያሲ ቦሩ ልጅ መጣ መሰለኝ።በሚል የዱበርቲ ምረቃ ነበር የሚያሞካሹት አያት ቅማያቶቹ ዘርተው ተቃሙበት፣ ወልደው ከሳሙበት፣ ሠርገው ከዳሩበት ቀየው ሲያነሱትም እርር ድብኑን የገለጸው፡-

ለኩርማን እንጀራ ለስሙኒ ጠጅ

ኸደ አሉ ሰፌራ ይህ የወሎ ልጅ።

ደርግና ኢሠፓ የሠሩልን ሥራ

በሬያችን ለሞስኮ እኛን ለሰፈራ።በሚል ነው።

ወሎ ሲበደል የሚጮኸው መከረን የሚከላከለው ስማይን ያለ ዋልታ ምድርን ያለካስማ ላቆመው አምላክ ነው። ይህም በመሆኑ መርጉ ሲጫነው ሰሚው ባያዳምጠው፡-

አሻቅቤ ባየው ሰማዩ ቀለለኝ

አንተንም ሠፈራ ወሰዱህ መሰለኝ። በማለት ጮኸ።

ፍትፍት ያሳበላን ጠጅ ያላጠጣን እንዳስቸገሩ ያጋስጠበትም

እባክህ አምላኬ ነፋሱን መልሰው

ወንድሙን ወንድሙ ሸጦ ሳይጨርሰው

የኛ ሊቀመንበር ቃልቻ ነበረ

ብሩንም እንደ ጫት ይቅመው ጀመረ። በሚል ስንኝ ነበር። ወሎ አሳዛኝ ነው። ጠንካራ ሠራተኛም ነው። ታማኝና ሰው አክባሪም ነው። የክልሉ ፍቅር ከግምት በላይ ነው። ታዳ ይኸ ኩሩ ሕዝብ ነው እትብቱ ከተቀበረበት፣ ውኃ ተራጭቶ ካደገበት ቀየ ሲያነሱት፡-

ዋድላና ደላንታ ሁሉም አገር ነው
እንዴት የጁን ትቶ ይባክናል ሰው።
አንድ ቀን ቢጨልም ሌላ ቀን ሲነጋ
እንዴት ይሰወጣል የጁ በወሰጋ። ብሎ ያለው።

ሁሉም ጉርፍ ነው ያልፋል ስንችም፡-

እስቲ አቦል ቀደሙን ቃሉ ደህና ይሁን
ችግር ጭቅቅት ነው ይራገፋል አሁን።
አንቻሮ ቀረና ባቲ ተገበየ
ሰው ሁሉ ቀረ እንደተለያየ ነው ያለው።

ይቺ ወሉ ያላለችውና ያልተባለላት አልነበረም። ያልሆነችውና ያልተደረገችው ነገር የለም። አዎ ወሎ ቴዎድሮስን ያዋጋች ከተዋበች ያጋባች ናት። ምኒልክንም ከጣይቱ፣ ቀ.ኃ.ሥላሴንም ከመነን ያገናኙች። ዘውድ አስጭና ዘውድ ያስጣለች። የበጐም የክፉም ተምሳሌትነቷን በዘመን ሽበት ያሳየች ናት፣ ወሎ አያሌ ትምህርት የሚቀሰምባት የሰው ዘ_መገኛነቷ የተመሰከረላት ናት። የእኔም የጽሑፌ መነሻ የሆነችው ይቺው በሰው ጀምበር ዘልቀው የሚናገሩባት ወሎ ናት። ከመከራና ከፍቅር የበቀለ ትምህርት ይገበይባታልና። በመሆኑም የሸህ ሁሴን ጅብሪል አባባል ምን እንደሚል ይመልከቱት።

# ክፍል አንድ

## 1. ሸህ ሁሴን ማን ነበሩ?

### የጌታው የሸህ ሁሴን ጅብሪል ውልድና ግጥሞቻቸው/መንዙማ/

በንግግር ስልታቸው ክፉና በጉን በመለየት በባለሙያነታቸው በወሎም ሆነ በሌላው ክፍለ ሀገር ሕዝብ እንደበት የማይለዩት የነገረን ብልትና ምስጢራዊነት እንደ ቆሎ አፍሰው እንደ ዳቦ ሸርፈው ለሰው የሚናገሩት ሸህ ሁሴን ጅብሪል ብሒረ ልደትና አስተዳደጋቸው በምን ሁኔታ ላይ እንደነበረና እንዳለፉ እነሆ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች ቀርቧል።

ጌታው ሸህ ሁሴን ጀብሪል ከአባታቸው ከሸህ ጅብሪል በወሎ ክፍለ ሀገር በወረሂመኖ አውራጃ በባዙራ ምክትል፣ በባሆች ቀበሌ ልዩ ስሙ እምበለ ሴዳ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በአስራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በ1811 ዓ.ም. ገደማ ተወለዱ።

አባታቸው በዘመኑ አሉ ከሚባሉት ወገንም ባይሆኑ የአገሩ ልማድ የዘመነ ጥያቄና ዕውቀት የሚፈቅደውን መንገድ በመከተል ከትውልድ ስፍራቸው ወጥተው በቃሉ አውራጃ በሚገኘው ገታ ከሚባለው ስፍራ ሄደው ለገታው ሸህ ቡሽራ አድረው ለሰላሳ ዓመታት ያህል በመውረድነት ያገለገሉ ነበሩ። በማገልገላቸው በወቅቱ የሚከፈለው ዋጋ ምርቃን በመሆኑ ለሥራቸው ክፍየ ላአገልግሎታቸውም በረከት ይሆን ዘንድ እኛ ላይ ያለውን በይፋ የሚናገር ልጅ "ጀባ ሀድ ጉጆ ውጣ ሸዋትህ ይሰምልም፣ ሀያትህ ይቆይ" ብለው ነበር የሸኙ ያሰናበቷቸው። ይህም የዘመኑ የነፍስ መዳኛ፣ የሥጋ መጠገኛ ታላቅ ስጦታ ነበር፣ እንዲሉ አበው!

ጅብሪልም ከዛ እንደመጡም የቀድሞው ሙሐመድ አሊ የኋላው ንጉሥ ሚካኤል አባት ከሰጧቸው ኮሬብ ከተባለው ከገጠር ከተማ ወጣ ብሎ ልዩ መጠሪያ ጨቀጨቅ ከሚባለው ርስት ላይ መኖር ጀመሩ። በኋላም ታላቅ ወንድማቸው ሼህ ሰይድ ያህያ የተባሉት በዛው አውራጃ ስስይ እሚባል ቦታ ይኖሩ ስለነበር ይኸዳሉ።

ሁሴን ጅብሪል በልደተ ሥጋ ከተገለጹበት ጀምሮ ከናት ካባታቸው ቤት ማደግ እንደጀሩ ወዳጅ ዘመድን መጠየቅ ይወዱ እንደ ነበረ ይወራላቸዋል። ይህን በማድረጋቸው የቅርብ የሩቅ ይንከባከባቸው ነበር። አቅፈው ደግፈው ካሰደጓቸው የቅርብ ዘመዶቻቸው አንዱ አጐታቸው ሸህ ሰይድ ያህያ ነበሩ።

ሸህ ሁሴን የልጅ ዐዋቂ፣ ትልቅን አክባሪ፣ ትንሽንም አፍቃሪ እንደ ነበሩ በሰፊው ይነገርላቸዋል። በቀልድ ዐዋቂነታቸው ባካባቢው ከመወደዳቸው የተነሳ ስማቸው በትንሽ በትልቁ ዘንድ እንደተጠራ ነበር ይላሉ። ከዚህም የተነሳ ሲናገሩ ለማዳመጥ ልጆች እጅብ እርገው እንደ ከዋክብት ከበው በመቀመጥ ተከትለዋቸው በመሄድ ቤታቸው ሰው አጥቶ አያውቅም ነበር ይባላል። ሸሁም እሸታን እንጂ እምቢታን ባለማወቃቸው የአገር ሽማግሌዎች ራሳቸውን በማሸት ሲመርቋቸው ዱበርቲዎች ቱፍታቸውን ሲሰጧቸው እደግ ተመንደግ፣ እንደ ቅጠል የለመለመ እንደ ዋርካ የሰፋህ ሁን ሲሏቸው ማየት የሰርክ ተግባር ነበር ይላሉ፣ ከዚህም፣ የተነሳ ይመስላል ሁሴን እሩቅ ዘመንን የሚያይ ነገር-የገባው ይመስላል እሱ የሚባሉ አንድ ሸህ። ምክንያቱም ልጆቹ ሲፈነድቁ ከልፍ ክልፍልፍ ሲሉ እሳቸው የሶበሩ ሴሎች ሲንቀለቀሉ እደብ የቀሩ የጨመቱ ነበሩና!! ለዚህም ነው ምርቃትም ነው ያስከናቸው የሚባለው። ሐጃህ ይሙላ፣ ዑምርህ ይርዘም፣ ጉዳይህ የሞላ ዕድሜህ የረዘመ ይሁን ከሚሏቸው አንዱ አጐታቸው ሼህ ሰይድ ያህያ ነበሩ። ምክንያቱም ሁሴን ጅብሪል አጐታቸውን ባካዳሚነት ያገለግሉ ነበርና ነው ይባላል።

እንደውም አንድ ቀን የአጐታቸውን ሰጋር በቅሉ ተከትለው ሰው ለመጠየቅ ይሄዳሉ። በቅሉ ይዘው እደጅ ይጠብቃሉ። በዚህን ጊዜ ዝናብ ይጥላል። በጊዜያቸው የዚያ አገር ሰው ሸማ እንጅ ሌላ አያውቅም። እጅ ጠባብ ከስንት አንድ ነው። ሁሴንም እንዲሁ ነበሩ፣ ኮርቻውን ዝናብ እንዳይመታው ሸማቸውን ያለብሱና ይቆያሉ። አጐት! በዋቸውን ጠያይቀው ሲመለሱ ኮርቻው ሳይረጥቡ ያገኛሉ። ዝም ብለው እየተሳበች ይጓዛሉ። ነገሩ ደንቋቸዋል። ያውጣሉ። ያወርዳሉ እሱ። በኋላም እንዴት ነው! ዝናብ ያልመታው ብለው ሲጠይቁ፣ ሁሴን ጅብሪልም "የኔን ሸማ አልብሸው ነው" ይላሉ። በዚህ ጊዜ አጐትየው "እኛን ሰው ብለህ ሁሴን" ብለው ካንጀታቸው ይደነቃሉ። ልባቸው ይነካል። መንፈሳቸው ይረካል።

ተጭሶም አልነበረም፡፡ ይህ ሁሉ መጨነቅ መጠበብ በሳቸው ዘንድ ስፍራ አልነበረውም ይባላል፡፡ ግጥሞቻቸውንም ሲያንቆረቁሩ ሰው እለ ሰው የለም ብለውም አልነበረም፡፡ ለሰውም ቢሆን የሚናገሩት ስለ ሰው ቁብ የላቸውም፡፡ ገለልተኛ ቦታም አይመርጡም፡፡ ብቻ ሲታቸው መናገር ነው፡፡ እንዴት እንዲህ መናገር እንደሆነላቸው ሲጠየቁ፣ እሳቸው እንደሚሉት ከሆነ፣ "እኔ አልቀራሁም፣ አልከትብምም፡፡ ግንባ በወርቅ ቀለም ተጥፎ ወለል ብሎ ይታየኛል፡፡ ያንን ዝም ብየ መቅራት ነው" አሉ ይባላል፡፡ በእርግጥም እንደ ግጥሞቻቸውና እንደ ሰው አባባል ዝናብ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

የሸህ ሁሴንን ግጥሞች ለመረዳት ዘመኑን ማወቅና በወቅቱ የነበሩትን ሰዎች መገንዘብ ሲያስፈልግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዓቱንም ጠብቆ የሚመጣና የሚፈጸም እንደሆነም ማጤን ይገባል ይላሉ ተናጋሪዎቹ፡፡ ሸህ ሁሴን ጅብሪልን እነጋግሬያቸዋለሁ የሚል አልተገኘም፡፡ ሸህ ሁሴን የነቢዩ መሐመድ እምነት ተከታይ ናቸው፡፡ ቢሆንም እንደ እስላሞቹ ጫት አይቅሙም፡፡ ሶላት አያደርሱም፡፡ መስገጃ ቁርበት፣ ውኃ መያዣ ጡሴ ኣያንጠለጥሉም፡፡ እንደ ዓባይ ጠንቋይም መጽሐፍ አይገልጡም፡፡ ጠጠር ለይጥሉም፡፡ ግን ሱሪቅ /ሐቀኑር/ ያሸታሉ፣ ብርዝ ይጠጣሉ፣ ፍርድም ሲፈርዱ ማለት የሚታያቸውን ሲናገሩም ብርዝ ይጠጣሉ፣ ፍርድም ሲፈርዱ ማለት የሚታያቸውን ሲናገሩም ብርዝ በፎሌ /በሸክና/ ይዘው ነው ይባላል፡፡ እርግጥ ብርዝ ሳይኖርም እንደሚፈርዱ ተነግሮኛል፡፡ በፍርዳቸው ከሲህቅ እስከ ደቂቅ ያልተደነቀ የማይደነቅም አልነበረም ይላሉ፡፡ ሐቁን የሚናገሩ የሚሆነውን የሚተነብዩ በመሆናቸውም ነበር ሁሉም እንደ በኒ ኳስ ይቃለባቸው የነበረው፡፡ ሌላው ከሚያስደንቀው ባህርያቸው አንዱ ደግሞ በፍርድ ሰዓት የጠጡትን ቢጠጡ ውኃ ሽንት የሚባል አያውቃቸውም ሲሉ የሚመላለስና የሚሸናው ግን መውረዱ ነው ይባላል፡፡

ሸህ ሁሴን ፍርድ የጀመሩት ገና የሰባት ዓመት ቃሪሳ ሳሉ ሮጠው ሳይጠግቡ፣ ዘለው ሳይሰለቹ እንደነበር ይባላል፡፡ በዚህም ይደነቃሉ፡፡ አሐዱ ወይም ቢስሚላሂ ብለው ፍርድ የጀመሩት በእጼ ዮሐንስና መምሬ ግርማ በተባሉ ቄስ ነው የሚባል አለ፡፡ የለም ስለ አጼ ቴዎድሮስ የተናገሩትም ነው የሚሉም አሉ፡፡ እኔ ግን ስለ አጼ ቴዎድሮስ ከተናገሩት ውስጥ ያገኘኋት ቅንጣት በመሆኗና ዝርዝር ወጉንም የሚነግረኝ በማጣቴ ተወት

በጎጃም በትግሬ በሸዋ በጎንደር ሳገሳ ሳገሳ

ስብርብር አረገኝ የጥቅሳ* አንበሳ፡

በማለት ተናገሩ የተባለው። አባባላቸውም ሁሉን አሜን፣ አሜን፣ አሜን፣ ሳሰኘው ድፍን አበሻን አቤት ወዴት ሳስብለው ሳስረግደው ሳሽርጠው የነበርኩትን፣ የጥቅሳ ወልይ በአልጋ ቁራኛ በሕመም ዳኛ ያዘኝ። ልጤ የተራሰ ጉድጓዴ የተማሰ አረገኝ ማለታቸው ነው ይላሉ።

መችም የታመመም እድናለሁ፣ ጤነኛም እኖራለሁን እንጅ እሞታለሁን ስለማያቅ፣ ያገርም ልማድ ስለማይቀር፣ ሣር ተጎዝጉዞ ረከቦቱ ተዘርግቶ ወሰማው ተነጥፎ ሰራት ብቻ ዘጠኝ በሬ ታርዶ የግራ የቀኙ ሸህና ደራሳ ተጠርቶ ወዳጃ ይገባል አሉ። ተበልቶ ካበቃ በኋላ፣ ቀምበጥ ቀርቦ ሲቃም፣ ዱአውን ኃይበል ሲሉ ሲሉ መሻር መሞታቸውን ትንፍሽ የሚል /የሚናገር/ ጠፋ። በመሐል ሸሀ ሁሴን ጅብሪል አላሣ ኩበር መባያው ላይ ዶሮ ደጋግሞ እንንደ ጮኸ ቀበሮም ጅብም ሲያውካካ፣

እናንተ ባታቁ እኔ ልንገራችሁ

ትልቅ ሰውተጠራ ተመሐከላችሁ። ይሏቸዋል አሉ።

ሁሉም ቅጠል በጉንጩ ይሆንና፡ አንገቱን ወደ ጣራ አቅንቶ ዝም ሲል ጊዜ በማያያዝ ነገሩ ይባስ ብለው ደህን ይላሉ አሉ

እነሱ ባያቁ እኔ ልንገራቸው

ሐርሽ አደባባይ ላይ ሁሴን ጅብሪል ይምጣ ሲሉ ሰማኋቸው። በማለት ወቅታቸው ማለቁን ዕለተ ሞታቸው መቃረቡን በቃው የሚል ውሳኔ መተላለፉን ለዘመድ ለወዳጅም በወዳጃው ዕለት ያረዳሉ። መቼም ሁሉ ነገር እንደ መስተዋት ጥርት ወለል ብሎ ይታያቸዋል አይደል የሚባለው፣ የሰዎቹን አለማወቅ የሳቸውን የዕድሜ ገደብ ማለት ተናገሩ ይባላል። በዚህም ቤተሰቡ ተደናግጦ ሐዘን ገባው። ሆዱን ባር ባር አለው። ራስን ዳስሶ ግምባር ሳስሞ የሚያስተኛ አባት እንዲህ ሲል አንጀቱ የማይበላ፣ ሆዱ የማይባባ ልጅ አይኖርምና፣ ሴት ልጃቸውም አባዬ እኔ ልለወጥ ብትላቸው፣ መለስ አርገው መች እንዲህ ሆነና ብለው መላከ ሞት

* ጥቅሳ የሚባለው የወልይ አገር ነው

ከመጣ ማቁን ጨርቁን የለም ጉዜን ሳሰናዱ። ደግሞስ መላክ ሞት መጥቶ ቢይዘው ቀኝ እጅወን ሳታጠባው ሄደች የምትወደው ልጅዋን እንዲሉ፣ በኔ ፋንታ ሌላ ይሆድ ማለትም ሆነ ይኸ ቀርቶኛል፣ ያ ዘግይቶብኛል ማለት እንደማይቻልና ከሩ የተከረረለትን ውኃም የተቋተለትን ሰው ማስቀረትም መለወጥ የማይቻል መሆኑንም በሌላ በኩል ሲናገሩ፡-

እንዱ በተጠራ መች ይኸዳል እንዱ

ተዘጋጅቶለታል የነገው መንገዱ

ተወዳ ተወዲህ ቢመጣ ዘመዱ ብለው ነበር አሉ።

ይህም ማለት ማንም ምንም ማድረግ አለመቻሉን ገልጸው ለልጃቸውም ጭምር ማስረዳታቸው ነበር ይባላል።

ከዚህም ሌላ አገር የማያውቅን ወንዝ የማይሻገርን ሰው ልሽኝ የሚል በሰ ያበሰበሰ፣ ዳቦ ቆሎ የያዘ ካልሆነ ዋጋ እንደሌለው ሁሉ እሳቸውንም መሸኘት የሚችለው የተጠናቀቀ ሰው መሆን እንዳለበት ሲያስረዱ እንዲህ ብለው ነበርአሉ።

ማነው የሚሸኘው የነገን እንግዳ

የተጠራ ሰው ነው ስንቁን ያሰናዳ። በማለት አጠቃለው ከመለሱላት በኋላ ማንምሰው አፈር ከመልበስ ድንጋይ ከመንተራስ ያለመትረፉንና አንቺም ብትንሰቀሰቂ፣ ብትብከነከኚ ፋይዳ የለውም በማለት በሷ በኩል ያለውን እልባት ሲያሲዙት፡-

ምን ያስለቅስሻል ከድሻ ልጃችን

ትከተይን አለሽ በስምንት ቀናችን። ነበር ያሉት ይባላል። ከዚህ እንደምንረዳው እሷም ባለሳምንት በመሆኗ አንጀቷ በሐዘን ተበልቶ ጉሂ ቀብሯ ሳያርፍ የምትሸኝ መሆኗን መናገራቸው ነበር ይላሉ፣ ይህም ስለዚህና ከተፈጸሚነቱ አንጻር ሲታይ አንዱ አስገራሚው ነገር ነው ይላሉ ተጠያቂዎቹ።

ቀደም ሲል ለቤተሰቡ ዕረፍተ ሥጋቸው መቃረቡን በቁማቸው ሳሉ ሰምቻቸው ከል ሳያለብሱ፣ ፊት ሳይነጩ፣ ደረት ሳይጥሉ እንዲወጡት

በማድረጋቸው በእንባ ሲራጭ እንገቱን ሲቀልስ፣ ዓይኑን ሲድጥ፣ አፍንጫውን ሲያብስ እንደ አመሻሽ ሰማይ ደም መስሎ ጎህ እንደመቅደድ ሲል እህታቸው "እንደው ምን ይበጀን?" እያሉ ሲያስቅሱ መለስ ብለው፡-

አላህ ይሶብርሽ የናቴ ልጅ እቴ

እኔስ መሄዴ ነው ወደ ቀሪ ቤቴ

በይ እስተዛው ድረስ አላህ ይሁንሽ

ትከተይን አለሽ በስድስት ወርሽ።

በማለት ወደ ሐቻው ቤታቸው ሲሄዱ እንኳ ዘመድ የሚወዱት በቁማቸው ብቻ ሳይሆን ሲሞቱም መሆናቸውን ለማሳየትም እንደሆነ እንጃ ልጅና እህታቸውን አስከትለው እንደሚጓዙ ይናገሩና ምናልባትም በሩ እንዳይዘጋ ዘበኛ እንዳይከለክላቸውም አዝነውም እንደሁ እንጃ ወይም አማላጅነት የሚከተለውን ብለው ነበር ይላሉ።

ያላህ መላክተኛ ተሉ ተቀበላት

ተጠርታ ነው እንጅ ሴላም ተከር የላት

አጀብ ተደረሰ ዑርሂኤል ተመጣ

እታመልጥም ጠጣ ተዛፍ ላይ ብትወጣ።

በዚህም ጊዜው ካለቀ ማንም ማጀት ይግባ በርናስ ይልበስ ከሞት ሲያመልጥ አለመቻሉም ከዕድሜውም መቀጠል እንደማይሆንለትና እህታቸውም ባለተራ መሆናቸውም ቂምሃ በገቡት ሰዎች ፊት ተናግረው እንደጨረሱ አሸደው ፊታቸውም መለስ በማድረግ ወዳውም፣ ለሰዎቹ፡-

ዘመኑን ወራቱን የሚያጫውታችሁ

ሁሴን ጅብሪል ኸደ ተመሐከላችሁ

ና ቢሉህ አትመጣ ቅር ቢሉህ አትቅር

እሰላማላይኩም ሰይድ ዑርሂኤል።

በማለት በተወለዱ ወደ 97 ዐመት ዕድሜ ገደማ ሰገሌ ሲዘመት አንድ

ሌላው እንደዘበት ጣል ያደረጉት ከተፈጻሚዎቹ አንዱ መሆኑ ነው ይላሉ አዛውንቶቹ።

ያም ሆነ ይህ እኒህ በንግግራቸው ሰውን ያንጹ የነበሩ፣ ከሞት የሚቀር የለምና ሰገሌ ሲፈርስ ዓመት ሲቀረው በዚህ ዓለም በኖሩ በ97 ዓመታቸው የሐሙስ ከሚስ ዕለት አፈር ቀመሱ ግብአተ መሬታቸው ተፈጸመ ይባላል።

# ክፍል ሁለት

## 2. የግጥሞቹ ይዘት

የአንድን ግጥም ይዘት፣ የአንድን ግጥም ዝንባሌ ለመረዳት ነገሮችን ተንትኖ ምሥጢራቸውን ፈልፍሎ ማወቅ የአንድ አንባቢ ወይም ሐያሲ ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይገባዋል። ስለሆነም የሸህ ሁሴን ጅብሪልን የግጥም ሁናቴ ዘለሰኛ እና መዲና አሊያም ሌላ ብሉ ለመተንተን ከማጋደል ይልቅ ታሪክነቱን ተመርኩዞ ስለማን ምን ያወጋሉ? ለምንስ ይህን አሉ? ማለቱ በተቀዳሚ አስፈላጊ ይመስለኛል። ስለዚህም፣ እኔ የሸህ ሁሴንን ግጥሞች በመጀመሪያ ለማየት የሞከርኩት ለምን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው።

እነኝህን የሳቸውን ግጥሞች ጠለቅ ብሉ ምንነታቸውን ለመረዳት ጊዜን ቆጥሮ፣ ዘመንን ሰፍሮ፣ አበውን ጠይቆ፣ ሲወርድ ሲዋረዱን አጠናቆ መሆን ይኖርበታል። ከዚህም የተነሳ ነው፣ እኔ ምንን ለማን ለምንስ እንዳሉ ለመግለጽ የሞከርኩት። ምን ማለታቸው እንደሆን ለማወቅ ከስረ መሠረታቸው ፈልፍሎ ማውጣት የሻሁት። እንደውስ አበው፣ "ነገርን ከሥሩ ውኃን ከጥሩ" ያሉት ያለምክንያት የሆን አይደለም። እኔም ግጥሞቹን ብቻ ከማስፈር ይልቅ ከነ ምክንያታቸው ያቀረብኩት ያለምክንያት አይደለም።

1. ጊዜው የት እየለሌ በመሆኑ ሰው ያልሆነ ነገር በመዛበት ተሳስቶ እንዳያሳስት በማሰብ፣
2. የተደበቁ የሰውም ሆነ የቦታ ስሞች ታሪካዊነት እንዳላቸው

## 2.1. ስለ አጼ ዮሐንስ

የዚህ ጥናት መነሻ የሆኑት ሸህ ሁሴን ጅብሪል ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች መናገራቸውን ቀደም አርጌ ጠቁሜአለሁ። እዎ እኚሁ ሸህ ፍርድ የጀመሩት ገና በልጅነታቸው እንደነበር ይወራል። አብዛኛውንም ጊዜ በዘመኑ ለነበሩት ኃያላንና ትላልቅ ተብለው ስለሚጠሩት ሰዎች ከታሪክ ጋር ያላቸውን ቁርኝት ነበር። ባጭሩ ንግግራቸው ሁሉ ራቅ ወዳለ ወደኋለኛው ጊዜ ይመልሰናል። ለሁሉም መነሻው የኋላ ነገር ነውና፣ ታዳ ግጥሞቻቸውን ለማየት ስንነሳ በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ስለሆነው እናውሳ።

በአጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ሕዝቡ በክርስትና ያመነ ፈጣሪና መሪውን ያከበረ ነበር ይባላል። ታዳ በዚያን ወቅት ምንም እንኳ ሕዝቡ በክርስትና እምነት የተጠመደ ቢሆንም "ተመልከት ዓላማህን ተከተል አሲያህን" ነውና፣ በመጽሐፍ ገላጭ፣ በዛጎል አፍሳሽ፣ በደብተራ፣ በቃልቻው፣ በንግር፣ ያምን ነበር አሉ። ንጉሡም አጼ ዮሐንስ እህ ሲሉ መንግሥትህን አጥፊ እልጋህን ተጋፊ እስላም ነውና እስላም ያጠፉሃል ተብለው ነበር ይላሉ። እህሳ ቢባል ባቅራቢያ ያለው የስላም አገር ወሎ ነውና እስላም ይጥፋ ዱር ይገፋ ብዬ መሄድ አለብኝ ይሉና ምታ ነጋሪት ክተት ሠራዊት ብለው ካባላንቃ አሲዘው ጥላና ከበሮ አስጭነው በቀሳውስት በዲያቆናት ታጅበው በፊታውራሪዎቻቸው በነደጃች አርአያና በደጃች አጎስ አዝማችነት በመምሬ ግርማ ቡራኬ ሰጭነት ተነስተው የወሎን እስላም ሐብተወልድና ስም ክርስትና በመስጠት አጥምቁ አቁርቤ የንጉሥነትና የሐዋርያነት ሥራ አከናውኘ እመለሳለሁ ይሉና ይገሰግሳሉ አሉ። ይህንንም ሸህ ሁሴን ጀብሪል ቀደም አርገው ስም ጠርተው ባለብዙ አጀብ ባለብዙ አጋሰስ ባለ ብዙ ጥና ወሎን ከቦ ሰውን አንቆ እንደሚያጠምቀው ክር ባንገቱ እንደሚያብትበት፣

ወንጭፌን አምጡልኝ እምበለው ዋነስ

ወረደ ጨጨሆን አጤ ሑዋንስ

ሐሩን ጭኖ ጭኖ በብዙ አጋሰስ

ፊት ፊት እየመሩ አርአያና አጎስ። ነበር ያሉት ይላሉ።

ይህም እሺ ያለውን በጠበል፣ እምቢ ያለውን በሾተል፣ በማስፈራራት በጋሻ ጃግሬዎቻቸው አማካይነት ለማጥመቅ ነበር የመጡት። ሸህ ሁሴን ግን ከነገሪ ቀደም አርገው "ፍራ ጠርጥር በሰኔ ጦር አለ" ብለዋል እንዲሉ ሰው ተዘጋጅቶ ነቅቶ እንዲጠብቅ ዘዴ እንዲፈልግ ነበር ይህን ያሉት ይባላል። ከዚህም ሌላ ኧረ ስማኝ አገሬ፣ ኧረ ስማኝ ወገኔ ሲሉ አሉ አሁንም የአጤ ዮሐንስ መምጣት ወይም ደግሞ በጉልበቱ ተመክቶ በኃያልነቱ ኮርቶ ስመ እግዚአብሔርን ለማስፋፋት አንድ ባለ አጀብ እንደሚመጣና አገር ምድሩን እግዚአብሔር ይመስገን እንደሚያሰኘው ቀደም አርገው ይናገሩና፣ ይኸም ቢሆን አፈር ፈጭተን ውኃ ተራጭተን ካደግንበት ካገራችን፣ ከወንዛችን፣ ከቀያችን፣ የት እንደርሳለን? ምንስ መሸሻ ሜዳ፣ መሸሸጊያ ዋሻ ይኖረናል። የመጣውን መቀበል ነው እንጅ ብለው ሲሉ አሉ።

መሬቲቱም አለች እግዚአብሔር ይመስገን

ወይት እንደርሳለን ተኮሬብ በርግገን። ነበር ያሉት።

ይህ እንግዲህ ባንድ በኩል የሸሁን አርቆ ተመልካችነት በማንም ልብ ያልተከተበውን በማንም ሐሳብ ያልተመላለሰውን ጉዳይ በገሃድ ለማሳየትና ለማሰማት መቃጣታቸውን ሲያሳይ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከመጣብህ መከራ ማምለጫ የለህም ሲሉት ብሶቱን ሲናገሩለት የቻለ ያመልጣል ያልቻለም ይዘቅጣል ማለት ነው ይባላል።

የሸሁ ንግግር የዮሐንስንም ይመጣሉ ማለት በዚህ አላበቃም። ከላይ በተለያዩ ገፆች እንደተጻፈው ሁሉ አጼ ዮሐንስ የወሎንም ሕዝብ እንደደረቆት ካመሉት በኋላ ቦሩ ሜዳ ጉልቦ ሚካኤል ላይ ሕዝቡን ሰብስበው በነፍስ አባታቸው አማካይነት ማጥመቅ ይጀምራሉ አሉ። መቸም አውራው ከተያዘ ጀሌው ምንም አይል ነውና፣ ያኔ የወሎው ባላባት ድፍን ወሎን በሥፍራቸው ያደረጉትን ኮረቤ መሐመድ አሊን ክርስትና በማንሳት ሚካኤል ይሏቸዋል አሉ። መቸም ለነፍስም ለሥጋም ተብሉ ስለሆነ ያጠመቋቸው ወዳው ካባ ላንቃ አጥልቀው ዘውድ ደፍተው እንደ ጀንበር በድፍን ወሎ ላይ አበሩበት አሉ። ከዛም አገር ምድሩ የሥላሴን ልጅነት አገኘ። አመነ። ተጠመቀ ይላሉ። ነገር ግን ሁሉ ሲጠመቅ ከአገር መሐል ሸህ ጅብሪል ሳይጠመቁ ይቀራሉ። በዚህ አድራጎታቸውም ንጉሥ ፊት

ይቀርቡና፣ “አንተስ ለምን አልተጠመቅህም? ልጅህንስ ለምን አላመጣህም?” ይባላሉ። መልሳቸውም፣ “በነፍሴ አልጠመቅም፣ በልጅም አላዝም” እንዳሉ ይታሠራሉ ይባላል። ያኔ ገና ዱሮ ዮሐንስ ሳይመጡ ነገሩን ሁሉ ተናግረውት ነበር። ያባታቸውን መታሰር ይሰማሉ። ገና በሶታነታቸው ሸህ ሁሴንም ተይዘው ንጉሡ ፊት ይቀርባሉ አሉ። “ለምን ራስህ አልመጣህም?” ቢሏቸው፣ “አላህ ታላቅህ ወይት አመልጣለሁ ብዬ” ይላሉ አሉ ሸሁ። እንግዳው “አንድነቱን ሦስትነቱን አምነህ በመጠመቅ የሥላሴን ልጅነት በቁርባን ታገኛለህ ሥጋም ትበላለህ” ቢሏቸው አሉ፣ “ዛሬ አምኛልና የዛሬን እድሬ አላህ ያቃል” ቢሏቸው ታዳ አሁን ምን ይሻልሃል ሲባሉ አሉ፣ “ተሥጋው ይልቅ ብርዙ ቢገኝ ደግ ነው” ይላሉ አሉ። ብርዝ ቀርቦ ሰው አረፍ ብሉ እየተጉነጩ ሳሉ የሸሁ ፍርድ ይመጣል። በዚህም ቂምሃ /ወዳጃ/ እንደ ገባ ያንጎራጉርና እንዲህ አሉ ይባላል።

ጊዜ ያነሳውን ጊዜ እስቲ መልሰው

ሥጋ ጠጅ አይልም ቡዳ የበላው ሰው። ሲሉ ጊዜ ንጉሡ ይናደዱና ቂስ አስጠርተው ሥጋ አቅርበው ለማብላት ሲሞክሩ መልሰው እንዲህ ብለዋቸው ነበር አሉ።

ደጋውም ቁንጫ ቆላው ረሞጫ

የሰይድ አሽከሮች አጣን መቀመጫ።

ይህንም በማለታቸው ንጉሡ አሁንም ይጠፉሉ አሉ። እምነቱን አስሰውጩ ሥጋ ወደሙን አቅምሺ እሄዳለሁ ይሉና በመጀመሪያ ሥጋ ይቀርብና ተባርካ ይብሉ ይባላሉ። ይግረማቸው ብለው፡-

ሰጥቂት ቀን ብዬ አልነካም ነጃሳ

ወንዝ ለወንዝ ሀጀ እበላለሁ አሳ። አሉ ይባላል።

ይህንም ሰምች ሲፈቱት፣ የዘመነ መንግሥትህ ማለፊያው ጊዜ የቀረው ጥቂት ነው። ያለቀ የደቀቀ ነው። ለዚች ቀን ብዬ የረከሰ ነገር አላበላም። እስከዛው ወንድ ወርጀ አሳ አስግሬ እየተመገብሁ ህልፈትህን እያለሁ። በሃይማኖቱ የሚመጣውን ብሩኅ ቀን ጠብቄ እንደሠራኝ እሞታለሁ ሲሉ

ነው ይላሉ።

በዚህ አባባላቸውም ንጉሡ አጼ ዮሐንስ ነደው ጡፈው ሲያበቁ፣ በል ሂድ ደሴ ጠብቅ መምሬ ግርማ ያጠምቁሃል ሲሏቸው ጊዜ፣ እኔ የስንት እስላም ልጅ እንዴት እንዲህ እባባለሁ በማለት ይደመሙና እሱ "እጃኢቡቱ" ካሉ በኋላ፣

ያላየህም እየው ያልሰማህም ስማ

ቆቡ ተቀደደ የመምሬ ግርማ። እሱና ከንጉሡ ተለዩ ይባላል።

መምሬ ግርማ የተባሉት መነኩሴ ደሴ ከደብረ ቤቴል ሥላሴ ባሻ ገር ከካራ ጉቱ ወዲህ ካለው ቦታ ሕዝቡን ይሰብኩ ነበር እሱ። ወዳው ብር ብለው እንደነፋስ ደሴ አዘዋ ገደል ከተባለው /ገደል/ ተንኮታኩተው ሞቱ እንደሚባል ሰዎች ያስረዳሉ። አጼም ነገሩን ሰምተው የቻሉትን አጥምቀው በነገሩም ተደንቀው ወደ መናገሻ ከተማቸው ተመለሱ ይላል።

ጌታው ሸህ ሁሴን ጅብሪልም ሃይማኖት የሚያፈርስ እምነት የሚያፋልስ እንደሚመጣ አስቀድመው ተንብየው ነበር። ይሉና ሸህ መሐመድ ጌታ፣ ሆኖም ነገራቸውን ቁብ ያለው አልነበረምና ያ ሁሉ መታመስ፣ ያ ሁሉ መጉላላት መጣ። ያመነም ተጠመቀ። ያላመነም እንደዛው ቀረ። ከዛ በኋላም ንጉሡም ወደ ግዛታቸው፣ ሸሁም ወዳገራቸው ከተመለሱ በኋላ ድርጊቱን ሲያጠነጥኑት እንዲህ ይላሉ ብለውን ነበር።

ደረሰብን እንጅ መች ደረስንባቸው፣

ቀረቡ ይሉናል የነፍስ አባታቸው።

በማለት አገር አቋርጠው ጋራ ዙረው እናጥምቃችሁ አሉ። እኛ ግን ካልነኩን የማንነካ፣ ካልደረሱብን የማንደርስ፣ ተነኩን ግን ከሃይማኖታችን ሳንዛነፍ ከእምነታችን ሳንቀንስ ተርብ መሆናችንን እመላከተናቸው ብለው ነበር ነው የሚሉ የተጠየቁት ሁሉ።

ሸሁ ስለ ራሳቸውም ሆነ ስለ አጥማቂዎቹ ያላቸውን በዚህ ያካትቱና ያኔ በሰም ጠርተው በሠራዊት ታጅበው ወሎን ቁም ስቅሉን አሳይተው ሰለሄዱት፣ ስለ አጼ ዮሐንስ የተናገሩትን ታሪካዊ ትንቢት ተጠያቂዎቹ እንዲህ ሲሉ ይናገሩታል።

ሸህ ሁሴን፣ አጼ፣ አባታቸውን በማሠራቸው ሕዝቡን በማመሳቸው እሳቸውንም በማንኳታታቸው ቁርሾ ይዘው ስለነበርና እንዴትስ በቀየው እርሜ በኖረ ንብረቱን በከወነ፣ እምነቱን ባጠነከረ እንዲህ ይንሳቀሳል? በማለትም ይመስላል፣ ስለወደፊቱ የዮሐንስ መዳረሻ የታያቸውን እንዲህ ብለው ነበር የሚሉት፡፡

በመተማም በኩል እምጢሰው ጢስ

የምትከነክን ናት የምታስነጥስ

እምብዛም አትበጀው ኣጤ ዮሐንስ

በማለት በመተማ በኩል የሚመጣባቸውን ከባድ ነገር በመጠቆም ያ! ይፈሩት የነበረው ተጋፊ ያ! ይሳሉለት የነበረው የመንግሥት ተቀናቃኝ መምጣቱን መናገራቸው ነው ይላሉ፡፡ የዚህ ታሪክ ተጠያቂዎች፣ ሸሁ ነገሩንም በማያሻማ ቃል ሲፈቱት እንዲህ ነበር ያሉት፡፡

የዮሐንስ በቅሉ ብረኪ ብረኪ፣

አሳህ ታመጣብሽ የደርቡሽ ማራኪ፣

መተማ ላይ ወርደሽ እንድትማረኪ፡፡

አዛውንቶች እንዲህ ይላሉ፡፡ ነገሩ የሚያስገርም ነው፡፡ ያ ይጥለኛል ያሉት የቅርቡ እስላም ሳይሆን የወንዝ ባሸገሩ ደረሰ፡፡ ጉዳዩ "የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል" ዓይነት መሆኑ ነው፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ ይላሉ፣ ያው አጤ ዮሐንስ፣ መቸም እምነታቸው ከጅማት የጠና ነውና፣ አረመኔውን ድርቡሽ እድሳለሁ ብለው፣ ምታ ነጋሪት፣ ክተት ሠራዊት፣ በማለት በእምቢልታና በመለኸት ታጅበው፣ እጉታቸው ራስ አርአያን፣ የወሎውን ንጉሥ ሚካኤልን፣ ራስ ኃይለማርያምን፣ ራስ አሉላን፣ ራስ መንገሻንና ራስ ሐጐስን አስከትለው ዘመቱ፡፡ እዛም በ1881 ዓ.ም መጋቢት 2 ቀን ማረፋቸውን አልቃሿም ግጥም መደርደሯ ይታወሳል፡፡ እሷም እንዲህ በማለት አለቀሰችላቸው፡፡

አጼ ዮሐንስ ይዋሹሉ

መጠጥ አልጠጣም እያሉ፡፡

ሲጠጡም አይተናል በርግጥ
ራስ የሚያዞር መጠጥ::
በጉንደር መተከስ
በደምቢያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ
ደሙን አፈሰሰ እንደ ክርስቶስ::
እንዳያምረው ብሎ ደሃ ወዳጁን
መተማ አፈሰሰው ዮሐንስ ጠጁን::
የጉንደር ሃይማኖት ቆማ ስታለቅስ
አንገቱን ሰጠላት ዳግማይ ዮሐንስ::

ብላ ገጠመችላቸው አልቃሽ:: ስለዚህም ሸህ ሁሴን ጅብሪል ያሉት መፈጸሙ፣ መተማ መውረዳቸው፣ በደርቡሽ መማረካቸው ነው ይላሉ:: ይህ እንግዲህ እንደተናጋሪዎቹ አባባል ነው::

አጼም በደርቡሽ ጥይት ቆስለው መተማ ከወደቁ በኋላ፣ ያ የሚሳሱለት ንግሥና ከልጅ ልጅ እንዲተላለፍላቸው፣ መኳንንቱም እንዲታዘዙ፣ ሕዝብም እንዲገዛ፣ ሲናዘዙ እንዲህ ብለው እንደነበር የታሪክ ማኅደር ይናገራል::

ንጉሠ ነገሥቱም ወዲያው የወንድማቸውን የደጃች ጉግሣን ልጅ ራስ መንገሻን አስጠርተው፣

*ወራሼ ልጅ ራስ መንገሻ ነውና ለኔ ያደረጋችሁልኝን አገልግሎት ለእርሱም እንዳትነፍጉት ብለው ለነራስ አሉላ አደራ ብለው በነገሡ በ17 ዓመት ከሁለት ወር በ1881 ዓ.ም. መጋቢት ሁለት ቀን አረፉ::*

ንጉሡ ይክን ተናዘው ከዘራቸው እንዳይወጣ ቃል አስገብተው መሞታቸው እሙን ነው:: ነገር ግን ሰዎች እንደሚሉት፣ ሸህ ሁሴን ንጉሡ ያሉት የሀልም እንጀራ እንደሚሆን በሚከተሉት ስንኞች:-

የዮሐንስ በቅሉ ጠፍታ በሌሊት

ቀን ወደምኒልክ ትትሄድ አየናት። ብለው ነበር ይባላል።

እንዳሉትም ይላሉ ብዙዎች፣ ነገሩ በተግባር ተገልጾ መገኘቱ የአደባባይ ምሥጢር ነው። ሸህ ሁሴን ጅብሪል ካሉት ውስጥ ከፍጻሜው የደረሰው ይኸ ብቻ አልነበረም። አሁን እንኳ በዘመናችን ብዙ አሉ የሚሉት የሁሴን ጅብሪል የልጅ ልጅ ጓደኛ ነኝ የሚሉት ሸህ አድሪስ፣ ለምሳሌ ከጦርነት ከተረፉት መሀል አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ቴዎፍሎስ የንጉሡን ራሳ በሳጥን ከተው ትተው እንደሸሹ ታሪክ ይነግረናል። በአንጻሩም ሸህ ሁሴን ንጉሡ እንደማይቀበሩ ቀደም አድርገው ከተናገሩት ውስጥ ትዝ የሚለኝ፡-

ጣይ መውጫ ጣይ መግቢያ የገዛው ንጉሥ

ታይቀበር ቀረ አጤ ዮሐንስ ብለው ነበር።

ይህንንም ተክለ ጻዲቅ መኩሪያ ከጻፉት ጋር ስናስተያየው ደህና ማመሳከሪያ ይሆናል። እሳቸውም ይህን ይላሉ።

*ከዚህ በኋላ ደርቡሾች በድንኳኑ ውስጥ ያለውን ሳጥን ከፍተው የአጼ ዮሐንስ ራስ ይሆንን እያሉ ሲያመነቱ፣ በዚያ ከቆሙት ምርኮኞች አንዱ አዎን ብሉ ካረጋገጠላቸው በኋላ እንደ ስመ ሞክሼያቸው እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ራሳቸውን ቆርጠው ራሳው አጠገብ ካገኙት የወርቅ ሰዓትና በወርቅ የተለበደ ወንጌል ከንግሥት ቪክቶሪያ ከመጣላቸው የሰላምታ ደብዳቤና መነጽር ጋር አንድነት ወደ ኦምዱርማን ለኸሊፋ አብዱላሂ ላኩለት።*

እንግዲህ፣ ቀደምት እንደሚሉት ከዚህ መረዳት እንደቻልነው፣ የሸህ ሁሴን ትንቢት የሰመረ መሆኑን ነው ይላሉ። ከዚህም በቀር አጼ ዮሐንስ ያሰቡት ቀርቶ ያልተዘጋጁበት እንደሆነና፣ ከዛም ወዲህ በትግሮ ንጉሥ እንዳልተነሳና እንደማይነሳ ከተናገሩት ውስጥ የሚከተሰውን የመሰለ ነበር ይላሉ።

ምድር ተዘርግታ እስክትካተት

እንግዲህ ለትግሬ የሰው ወንድነት።

በማለት ገና ለገና በጣም ሩቅና ረጅሙን ጉዞ ተናግረው ወዳገራቸው ተመለሱ ይባላል፡፡

## 2.2. ሙሐመድ አሊ

አብዛኞዎቹ ግጥሞች የሕዝቡን የኑሮ ጉዳና የሚናገሩ ናቸው፡፡ ብዙ ገጣሚዎች የኅብረተሰቡ ኑሮ አቃኞች ናቸው፡፡ የሕዝቡ የኑሮ አቋም የሚመራበትን ፍልስፍና የሚቀይሱ ናቸው፡፡ በወሉም በመጠኑም ቢሆን የኅብረተሰቡን የኢኮኖሚ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ አቋም የሚጠቁሙ በብዙ ቃልኞች እጅ እንደሚኖሩ ይነገራል፡፡ ታዲ ስለ ሸሆች ስናወሳ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ለአጼ ዮሐንስ የተናገሩትን ያህል ለወሉው ባላባት ለሙሐመድ አሊ የተናገሩትም ነገር እንደነበር ይወራል፡፡ ይህም እንዲህ ነበር፡፡

የቀድሞው ሙሐመድ አሊ የኋላው ንጉሥ ሚካኤል እናት ገይቲ በመባል ይጠራሉ፡፡ አገራቸው ጉሻም ነው ይባላል፡፡ እንዳንዶቹም የለም ሴትየዋ አገር ሲቀና በነበረበት ወቅት በግንደ በረት በኩል ተማርከው ለአሊ አገልጋይ ነበሩም ይባላል፡፡ ታዳማ የአሊ ባለቤት ገረዳቸውን ገይቲን አስከትለው ሸህ ሁሴን ጅብሪል ቤት ይሄዱና ሥጋ ጀባ ይላሉ አሉ፡፡ ሸሁም እንደ አገሩ ልማድ ቱፍታ ይሰጡና በይ ከማምሽ ሲሉ ጊዜ የአሊ እውገረድ /ባለቤት/ ይጸየፉና ካዳሚት ገይቲ ትበላለች ይላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ምን ይታያቸዋል እንዲህ ዓይነት፡፡

ልጅስ ይወለዳል ተገረድ

ስሙን ማን ልበል ሙሐመድ

የመዲናን ዲብ የሚንድ አሉ ይባላል፡፡

ሰዎች ይህን ሲፈቱት እንዲህ ይላሉ፡፡ ሙሐመድ አሊ የተባለ ልጅ ይወለዳል፡፡ የኋላ ኋላ ግን ስመ ክርስትናን ሐብተ ወልድናን ይቀበላል፡፡ እስልምናን ይተዋል፡፡ ያፈርሳል ማለታቸው ነው ይላሉ፡፡ ያው እንደ ተባለው ሙሐመድ አሊ ከገይቲ ይወለዳሉ፡፡ ሙሐመድ አሊ በተወለዱበት ወቅት አጉታቸው አባ ዋጠው ወሉን ያስተዳድሩ ነበር ይባላል፡፡ ታዲ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ቤት ለመጠየቅ ሠንጋ አስነድተው ይሄዳሉ አሉ፡፡ ሙሐመድ

አሊ ያኔ ገና ሙጫ ነበሩና አጐታቸውን ተከትለው ሄደዋል፡፡ ወዳው አጐት ሰንጋ ጀባ ይላሉ እሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ሁሴን ጅብሪል ያን ሙጥቅላ፣ ያን እምቡጥ ልጅ ትኩር ብለው ይመለከቱና እሉ፡-

ተንዠርጓል ፍሪው እንደ ቀንዶ

አሰለማላይሉም እያ ሰባት ቀንዶ

ይሉና ቀኝ እጁን ይይዛሉ እሉ፡፡ ይህም እንደሰዎች አፈታት ርዝቅ አሰህ፣ ጊዜህ ብሩኅ ነው፣ ዕድልህ የተቃና ነው ሲሏቸው ነው ይላሉ፡፡

እንደዚሁም አንድ ጊዜ ገይቲ የሙሐመድ አሊ እናት ወዳጃ አስገብተው ያስቅማሉ እሉ፡፡ ውድቅት ላይ የእባታቸው ቡላ ፈረስ እህህ ይላል እሉ፡፡ ሁሴን ጅብሪል እቤታቸው ከሰው ጋር በዛ በውድቅት ሰሊት ጨዋታ ይዘው ነበርና ከጨዋታው ነቅነቅ ብለው እሉ፡-

ቡላ ያሌ ፈረስ

ራሱ ሰው ሆነ ዛሬስ

ማለት! ይህንም ሰዎች ሲያብራሩት አሊ በከራብ ብዙ ባላንጣዎች ብዙ ጠላቶች ነበሯቸውና ያ! የአሊ ፈረስ ተነስ ተቀናቃኞችህን እርገጥ ተነስ ባላንጣዎችን ደምስስ ብሎ መጠቆሙ ለድል ማቆብቆቡ ነው ይባላል ይላሉ፡፡

ሸህ ሁሴን ጅብሪል ስለ ንጉሥ ሚካኤል ወይም ሙሐመድ አሊ ብዙ ተናግረዋል፡፡ መነሳት መጡደቃቸውንም አውስተዋል፡፡ መቅደላንም ጠቃቅሰዋል፡፡ ሙሐመድ አሊ ቶራ መስከ ማሸነፋቸውን፡፡ ሰገሌ ግን እንደማይቀናቸው ደጋግመው ነግረዋቸው ነበር እሉ፡፡ ምንም እንኳ ይህን የሚሆን መሆኑን ቢያወሱም እንኳ አንድ ዘመን ዘውድ ደፍተው ንጉሥ ሳይባለ እንደማይቀሩ፡-

ቲጋልብ አየነው በሐመር ፈረስ

ምንም ምን አይሆንም እንደዜ ታይነግሥ

ነበር እሉ ያሉት ይላሉ፡፡ ያው ንጉሥ መባሉ እውቅ ነው ብለው ይላሉ

Scanned with CamScanner

ቤሳ ምላጭ ጅራፍ አምጣ" አሏቸው ይባላል። ከመጣውም ላይ ቱፍታ ይሰጡና "በል እንግዲህ ህደህ እንዲህ በል፤ ይኸ እያለ የሰምን ንብረት መድፈሬ እያደር ይገርመኛል ብለህ ሳትሸሽግ ንገረው" አሏቸው ይባላል። በዚህን ጊዜ ሚካኤል "እረ እኔስ ሸከኩ" ሲሏቸው ጊዜዘ እንዲህ የሚል ነገር ተናገሩ አሉ።

ባዳራሹ ገብተህ በልፍኙ በር ውጣ

አንድ ነገር ብትሆን እኔ በጉድ ልውጣ

ይሰጥሃል ጊደር ትተህ እንዳትመጣ

የቀኝህን ትተህ የግራህን ጠጣ

ይልቅ ቶሎ ብለህ ሸዋረጋን አምጣ

ይህን ካሏቸው በኋላ ጫነን ፈረሴን ያዝ ልብሰን ብለው በአህያ ፈጅ መንገድ ገሠገሡ። እንጦጦ እንደገቡም አድርግ ያሏቸውን የሸሁን ሲያደርጉ ጊዜ "ይኸማ ሳንተ መግዣ መንጃ ይሁንልህ" ብለው መረቁላቸው ይባላል። ይህ ከሆነ በኋላ ዋል አደር እንዳሉ የሸወው፣ የጐንደሩ፣ የትግሬና የጐጃሙ መኳንንት አፍ እስከ ገደፉ ባለበት አዳራሽ ሚካኤል ይላሉ ሉ ምኒልክ፣ "አቤት" ብለው እንደቆሙ "በል ሸዋረጋን ሰጥተንሃል" እንዳሏቸው ነው አንድ አዛውንት የነገሩኝ።

አሁንም ተክለጻድቅ መኩሪያ ይህን በሚመለከት እንዲህ ሲሉ ይገኛሉ። "አጼ ዮሐንስ ዐርፈው አጼ ምኒልክ በነገሡ ጊዜ አካሄዳቸውን ሳይለውጡ በዐድዋም ጦርነት ጊዜ ሞያ ስለ ሠሩ ልጃቸውን ወይዘሮ ሸዋረጋን በ1884 ዓ.ም. ድረው ባለሟል አደረጓቸው።"

ያ ሁሉ መኳንንት እኛ ስንት ዓመት ደጋ ወጥተን ቆላ ወርደን አገልግለን ያልተሰጠን ጸጋ እንዴት አሁን መጥቶ ድሮ ከድቶ የነበረ አገኘ በማለት ተብላላ። ሚካኤልም ጫማ ስመው ወርቅ በወርቅ ሆነው እንደ ቅዳሴ መስቀል እያበሩ በልፍኝ ባዳራሹ ቿ! ቿምቡዋ ብለው ሸዋረጋን አሳጅበው ወሎ ከግዛታቸው ሲደርሱ ወንዱ በሆታ ሴቱ በልልታ ጭብጨባ ቀልጦ እንደገቡ ብዙ ሽማግሌዎች አውግተውኛል።

መቸም ሰው ካገባ መውለድ የት ይቀራል ይባል የለ ሚካኤል አሲም በዓለም በደስታ እንደተቀመጡ አንድ ቀን ሸህ ሁሴን ምን ይውጣቸዋል፡፡

ልጅም ትወልዳለህ የሚባል እያሱ

እንኳን ለሰውና አይረባም ለነፍሱ የሚል ይላሉ፡፡

ይህንንም ሲተነትኑት እንዲህ ማለት ነው ብለው ይላሉ የአገሩ ሽማግሌዎች፡፡ መውለዱንስ ትወልዳለህ ነገር ግን እንኳን ሰው ሲጠውር / ሲረዳ/ ይቅርና ለራሱም አይሆን፡፡ ምክንያቱም እያሱ ከምኒልክም ሆነ ካንተ የተወለደ በሥጋ እንጅ በጠባይ ስላልሆነ ፋይዳ የለውም ሲሉ ነው በማለት ይናገራሉ፡፡

ከዚህም ጋር በማያያዝ የሸዋረጋን ክፋትና እመቲቱ ቀደም አርገው ሙተው ቢሻል ናሮ በበጀ ብለው ነበር ይሉና ምክንያቱም የዘሩት የማይበቅል የወለዱት የማይበረከት መሆኑ ግልጽ ነበርና ይሉና ይህንንም፣

ያቺ ሸዋረጋ ከሞችስ አይቀር በሞተች በርጉዟ

በመላው ሐበሻ ሳይነዛ መርዟ

በማለት የገለጹት ሲሆን የእያሱንም ከንቱነት የእመቤቲቱንም ክፋት ያጠቃልሉታል በማለት ያስረዳሉ፡፡

አሁን ገና ልጅ እያሱ ሳይወለዱ ለሙሐመድ አሊ ሲናገሩ እንዲያውም ግዛት ማስፋፋት ሕዝብን መምራት ቀቶ በሥርዓተ ተክሊል አግብቶ ሃይማኖቱን ጠብቆ መኖር ይቅርና ያባት የናቱንም ደጅ አስከብሮ የማይኖር መሆኑን ቀደም አርገው ሲናገሩ፣

እያሱ የሚባል አንድ ልጅ ተወልዶ

ያባቶቹን ቀየ አደረገው ባዶ ብለውት ነበር ይሉሉ፡፡

ይህንም በዋል ፈሰስ ነው መጨበጫ ልጓም መወጣጫ ርካብ የለውም፡፡ ስም አያስጠራም፣ ጋሻ አያሳም ብለው ሲሉ ነው በማለት ይናገራሉ፡፡ ከዛም ሸሁ መለስ አርገው መቸም ማምቡተር አይቀርምና ለጊዜው ለጥቂት ቀን በየግዛታቸው መዘዋወራቸው ከምኒልክም ውርስ ማግኘታቸው የማይቀር

መሆኑን ስሚካኤል አሊ ሲነግሯቸው፣

ተሸዋረጋ የሚወለድ ልጅ

እምብዛም አይከፋ እምብዛም አይበጅ

ትንሽ ወደ ኋላ ይቀረዋል እንጂ ብለዋቸው ነበር።

በማለት ይናገሩና ተጠያቂው፣ ሸሁ በማከታተልም ልጅ እያሱ ይዞ ሟች ናቸውና ከሳቸው ጋር ማበር መቃጠል ስለሚሆን አባትም ሆንክ የዳር አገር ወዳጅ እንዳትረዳ ያሉበት ግጥም፤

ዓባይ ደፈረሰ ጣናንም ያሙታል

እንዳትከተሉት ሙት ይዞ ይሞታል ነበር ይላሉ።

ነገሩንም ሰፋ አድርገው ሲያብራሩት እም! ሸህ ሁሴን ይህን ቀደም አድርገው በመናገራቸው ሆነ ወይም የታሪክ ሰዎች እንደሚሉት "ከአብርሃና ከአጽብሐ ጀምሮ በኢትዮጵያ ጸንቶ የኖረውን የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ጠብቆ ባለመኖር ይሁን አለያም መኳንንቱን ሹማምንቱን በማጉላላት ወይም ደግሞ የጀርመን የጦር ጓደኛ በመሆናቸው እንጃ ንግሥናቸው ሳይሳካ እሳቸውም ሳይደላደሉ ቀርተው አልጋቸው በ1909 ዓ.ም. ሲፈርስ በቅቷል በማለት ይመልሱና፣ ስለዚህ በዦም ሆነ በዚህ ሸህ ሁሴን ካሉት ጋር መገጣጠሙን መመልከት ይበቃል ይላሉ።

ሸህ ሁሴን ጅብሪል በጥንት ሰዎች ዘንድ በነገሥታቱ በመሳፍንቱ ዘንድ እንደ ብርቅ ዕቃ እንደ ወደፊቱ በር ከፋች ሆነው እንዴት ይታዩ እንደነበር ባሰፉት ገፆች ካሉት ግጥሞች ማየት ይቻላል። እንዲሁም ስለሙሐሙድ አሊ አወላለድና መዳረሻ የተናገሩትን ደረጃ በደረጃ ማቅረቤ ግልጽ ነው። አሁንም ከዚህ በመነሳት ሸሁ ስለሙሐመድ አሊ አሉ የተባለውን አቀርባለሁ።

ቀደም ባሉት ገፆች ባንደኛው ላይ ራስ መኰንን የምኒልክ ባለሟል በነበሩበት ጊዜ የተናገሩትንና ወደ ምኒልክም ይሂዱልኝ ባሏቸው ጊዜ ያሉትን መናገሬ ግልጽ ነው። አሁንም እንደዛው ወደፊት በጠቅላላ ነገሮች እንደሚገለጸው ሁሉ፣ ራስ መንገሻ አቲከም ይሂዱልኝ ቢሏቸው አሉ፤

እስላማላይኩም አያ ሰባት ቀንደ

ሱባህን ረኪብ እንግዲህ መሐመድ ነበር እሉ ያሏቸው::

ይህም ማለት ከእንግዲህ ወዲህ እንጀራህ ከሰመ፣ ማጀትህ ተሟጠጠ፣ አድባር ራቀችህ፣ ሐጃህ ተዳፈነ ማለት ነበር ይላሉ::

## 2.3. እያሱና ዘውዲቱ

ቀደም ሲል ሙሐመድ አሊ በሚለው ክፍል፣ የልጅ እያሱን አወላለድና የወደፊት ሁናቴ በመጠኑ ማቀራረቤ ይታወሳል:: ምክንያቱም የአባትና የልጁ ዕድል የተያያዘ ነውና! በዝህኛው ክፍል ደግሞ ልጅ እያሱ ካደጉ በኋላ ምን ሆኑ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ከአባቶች የተገኘውን በሚከተለው መልስ አቀርቤዋለሁ::

አጼ ምኒልክ ታህሣሥ 3 ቀን 1906 ዓ.ም. እንዳረፉ ልጅ እያሱ አልጋ መውረሳቸው ይታወቃል:: ልጅ እያሱም መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም. ከመንግሥት ሥልጣን ተሽረው ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ በዙፋን ላይ መቀመጣቸው የሚታወስ ነው:: በዚህም የተነሳ ንጉሥ ሚካኤል ተቆጥተው ጦር አስከትተው ቶራ መስክ ላይ ድል ማድረጋቸው ገሃድ ነው::

ይህም ማለት ይላሉ ሸህ ኢድሪስ ምንም እንኳ ቶራ መስክ ላይ ራስ ልዑል ሰገድን፣ ሊቀ መኳስ አበበ አጥናፍ ሰገድን፣ ደጃዝማች ተሰማ ገዘሙን፣ ፊታውራሪ ዘውዴ ጉበናንና ሌሎችንም ድል በማድረጋቸው ቢደሰቱም የማያዳግም መሆኑን በመዘንጋት ግፋኖቻቸውን ገሰገሱ:: ይህም ሸህ ሁሴን ጅብሪል ያሏቸውን በመዘንጋትም ይሁን በደራ ወይም በሰው ተገፋፍተው ለመግጠም ሄዱ:: ቢሆንም ሸህ ሁሴን እንደማይሳካላቸው ገና ድሮ በተለያየ መንገድ ነበር የገለጡት:: አንዱም ይህን ይመስላል ይሉና ሲናገሩም፣

ሰገሌ ሜዳ ላይ የመጣብን መርዶ

በቀኝ እጁ ካራ በግራው ብርንዶ

በማለት ወሉዬ በፈረስ ኃይ በል ሲል፣ ሸዬ ደግሞ በብልሃት ድል እንዳደረገው በታሪክ ማኅደር የሰፈረ ነው ብለውኛል::

መቅደላ ሄዱ"፡፡

ስለዚህም ጉዳይ ሁሴን ጅብሪል ቀደም አድርገው ጦርነቱ መቅደላ ላይ በምንም ዓይነት /ጦርነት/ የማይቀር መሆኑን ተናግረውት ነበር የሚሉት ይህን በመሰለ ግጥም ነበር ይላሉ፡፡

ሥትሠራ አየኋት መቅደላ ራሱን
ጉንጉንም አይደለ ሹርቢ ቀጭን
ወሎ ግድግዳዋን መንዝ ማገሩን
ይህም ምድር ይጤሳል ማለታቸው ነው ይላሉ፡፡

ምንም እንኳን ከወደቁ ወዳ መንፈራገጥ ለመላላጥ ቢሆንም፣ ልጅ እያሱ፣ አሁንም እልሞት ባይ ተጋዳይነታቸውን እልተውም ነበር፡፡ ንጉሥ ሚካኤል ሰገሌ ላይ በጦር ሠራዊቱ እዛዥ በልዑል እልጋ ወራሽ ራስ ተፈሪ መኩንን አዝማችነት ድል ቢሆኑም መቸም ልጅስ ተወለደ ተመኩንን ጉያ... ብለውላቸው የለ ዳሩ!፡፡ ያም ቢሆን ልጅ እያሱ ከሰገሌ ጦርነት የተረፉትን ይዘው ደሴ ገቡ፡፡ እዛም ጦርነት እንደሚያደርጉ ሁሴን፣

የመተማን ትተን የደሴን እናውጋ
ሦስት ቀን ጨልሞ ባራተኛው ነጋ

ብለው ነበር እሉ፡፡ በእርግጥም የክረምቱ፣ የማለዳ የጸሐይ የጨረር ላንቃ ላንድ አፍታ ብቅ ብላ በደሴ ከተማ ባሉ ታላላቅ ኮረብታዎች ላይ እርፋ ስታንጸባርቅ የሰጠችው የብርሃን ጨረር ልዩ ትርኢት ነበር፡፡ ባንድ በኩል የተፈጥሮው ውበት እጅግ የሚያስደንቅ ሲሆን ያለ ወትሮው በዚያ ሰዓት የከበደ ነበር፡፡ የማለዳው ትርኢት ጨረቃ በመሰለና በሚያቅራራ የሁካታ ውሎ አመሸ ተራኮተ፤ ተብላላ፡፡ በዚህን ጊዜ ነበር፣ ደሴ ላይ ጦርነቱ ተፋፍሞ ለሦስት ቀን የቆየው፡፡ በጦርነቱ እነ ሥራህ ብዙ፣ እነራስ ይመርና ሌሎቹም እንደሞቱ ልጅ እያሱ መቅደላ ምሽግ ይገባሉ ሲሉ ዘውዱ መንገሻ የዳውደው ያጫወቱኝ፡፡ ስለ ደሴውም ጦርነት ቢሆን ተከለጻድቅ መኩሪያ፤ በዚህ ጊዜ በክረምቱ ወራት አደጋ ለመጣል መጥተው ደሴ ላይ ጦርነት ተጀምሮ ሁለቱም ወገኖች በብርቱ ከተዋጉ በኋላ አቤቶ እያሱ ድል ሆነው

መቅደላ ሸሹተው ገቡ በማለት አስፍረውታል፡፡

እሁንም አቶ ዘውዱ መንገሻ ስለ ልጅ እያሱ የተባለውን እንዲህ ሲሉ ይቀጥላሉ፡፡ ሸህ ሁሴን ግን አሁንም ቢሆን መቅደላ ያቺ የንብ ቦታ፣

በመቅደላ በኩል ጨኸት በረከተ

የሴቱን አናውቅም ወንድ አንድ ሰው ሞተ

የተባለበት የጦር አውድማ እንደምትሆን እንዲህ ብለው ነበር ይላሉ፡፡

እየጉድ መቅደላ እየጉድ ሰንጋላት

ሲምች እለቁና ዝንጀራ ወረራት

እኛ እንኳ እንደርስላት እንዳንጋላግላት

ልጅ እያሱም ነፍስ የያዘውን ጦራቸውን ይዘው ገብተው ስለነበረ ሸዌ ተከታተላቸው፡፡ ይህንንም ደጃዝማች ከበደ ተሰማ በሚከተለው ዓይነት አቅርበውታል፡፡

*"ከዚህ ሁሉ በኋላ ልጅ እያሱ እንደገና ጦር ሠርተው መቅደላ ስለአምባቸው ገብተው የጦር ሚኒስትሩ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዋና አዝማች ሆነው፣ ራስ ደምሰው ነሲቡን፣ ደጃች ብሩ ወልደገብርኤልን፣ ደጃች ወሰኔ ትርፌን፣ ደጃች ወልደጻድቅን ከነጦራቸው አስከትለው ከአዲስ አበባ ወደ መቅደላ ተጓዙ፡፡ ደሴ ላይ ሲደርሱ ከሰገሌ ድል በኋላ የወሎ አገረ ገዢ ሆነው የተሾሙት ራስ አባተ ቧያለው አብረው እንዲዘምቱ ተደርጎ መቅደላን አምባውን ከበው ተዋግተው በ1909 ዓ.ም. ነሐሴ 21 ቀን ድል አድርገው መቅደላን አስለቀቋቸው፡፡ ልጅ እያሱም ወደ አውሳ በረሃ ገብተው ተደበቁ፡፡"*

ይህ አባባል እንግዲህ ከሸህ ሁሴን አባባል ጋር ገጠመ ማለት ነው ይሉና ሸህ ሁሴን ከመቅደላ ምሽግ ማምለጣቸውን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሰው የሚፈልግ የራሱን የሚያጣ

በቆቂት በር ገብቶ በሹልኪት በር ወጣ፡፡

የዚህ መነሻ ደግሞ እንዲህ ነው፡፡ ንግሥት ዘወዲቱ መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም. ዘውድ ደፉ፡፡ ከዛም የካቲት 11 ቀን ለራስ ወልደጊዮርጊስ የንጉሥነት ዘውድ ሰጥተው የበጌምድርና የሰሜን ንጉሥ አድርገው ይሾሟቸዋል ይባላል፡፡ ታዳ ወልደጊዮርጊስ ደሞ የጉንደሩ ደጃች ይማም ተፈሪ ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስን በሰገሌ ጦር እንዲረዱ ያዟሉ፡፡ ይማም ተፈሪም፣ ንጉሥ ሚካኤልን ከኂላ ለመውጋት አምባሰልን ረግጠው ሲሄዱ መተሳሰፊያ ሲያደርጉ ይመጣሉ፡፡ አምባሰሌም ይማም ተፈሪን ገጥሞ ሲጠዘጥዝ ይማም አምባሰል "እን" ምትባል ቦታ ላይ ይሞታሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ከላይ የተነገረው ለፍጻሜ ቢቃ፡፡ አምባሰል ተነዳ፤ ተጨፈጨፈ፤ እንደማሽላም ተዘለሰ በማለት ነገሩኝ፡፡ በተጨማሪም ስለዚህ ነገር መሆን ቀደም አርገው በዚህ ዓይነት ነበር ይላሉ የተናገሩት፡፡

ድንኳን ተተከለ ስንዴ ምድር ላይ

ሲሆንም ጭለጋ አለያም ሳይንት ይህ ቢያቅታቸው

ን /እን/ ሜዳ መሻገር እንዳያቅታችሁ

ከብዙ ተጠያቂዎች እንዳገኘሁት፣ ከሸህ ሁሴን ፍርድም ይሁን ወይም ከንጉሥ ሚካኤል ዘር የትግል ስልት አቀያየስ፣ የልጅ እያሱ መከራ ሁሉ ከሸፈል፡፡ አውሳ ገቡ፡፡ ከዛ በረሩ፡፡ ትግራይ መያዛቸው አልቀረም፡፡ ተያዙ፤ እንደገናም በራስ ኃይሉ ተከለሃይማኖት ርዳታም ቢያመልጡም አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም ከታሪክ ማኅደር እንደምናገኘው ልጅ እያሱ ፍቼ በልሁል ራስ ካሣ ኃይሉ ጠባቂነት ታስሩ ይላል በማለት አንድ ቃዲ ነገሩኝ፡፡ ይኸንንም ቢሆን ሸህ ሁሴን ጅብሪል፣

ሲጠነሰስ አየር በትልቅ ጋን ኮሶ

አሊ ቤት ዐበይ ቤት ሶስተኛ ለጃርሶ ይሉታል፡፡

አሊ ቤት፣ ዐበይ ቤት፣ ያው የንጉሥ ሚካኤል ወረሂመና መሆኑ ነው፡፡ ጃርሶም የተባለው ሰላሴን ማለታቸው ነው፡፡ ስለዚህ የንጉሥ ሚካኤል ዘር ሰላሴ ሂዶ እንደሚጋዝ፣ በቁሙ እንደሚሰቃይ እንደሚመረው መናገራቸው ነው ሲሉ ቃዲው ያካትታሉ፡፡

በመጨረሻም ልጅ እያሱ የመቅደላው ምሽጋቸው ከተናደ፣ ሐውሳ በረሃ እንደገቡ ከዛም እንደጠፉ ቀደም አርጌ ገልጬዋለሁ፡፡ ቢሆኑም ከብዙ ጊዜ

በኋላ በ1913 ዓ.ም. በራስ ጉግሳ አርአያ ግዛት ትግሬ ውስጥ ተያዙ። ይጥፉም ይያዙም ብቻ ሸህ ሁሴን ልጅ እያሱ ፋይዳ ቢስ እንደሆኑ ነ በሟት፣

ተወንዝ ዳር ቆመን የምንጠብቀው

ባህር ሰምጦ ቀረ ይወጣል ያልነው

ብለው ተዘፍቀው እንደሚቀሩ ገና በጦርቃነታቸው መና እንደሚሆኑ ተናገረው ነበር፣ ተፈጽሟል፣ አይተናል ይላሉ አዛውንቱ አመዴ ይመር። እንግዲህ የጊዜም ይሁን ያጋጣሚ ጉዳይ፣ የልጅ እያሱ ጉዳይ አከትሟል። እዚህም ላይ በእልባት ይታሰፋል።

ዘውዲቱ በ1909 ዓ.ም. መስከረም 17 ቀን ንግሥት ዘውዲቱ እንደ ዘመኑ አባባል /የዚያን ጊዜ/ በሕዝብ ምርጫ የንጉሠ ነገሥቱን ዙፋን መውረሳቸውን በተለያዩ አጋጣሚዎች ጠቋቁሜአለሁ። እነሆ ከዚህ በታች ከኩቡት እልቂት፣ ከእህል እጦት፣ አይቶ ከማጣት፣ ጠምዶ ከመፍታት፣ የሚያድኑን ይባሉ የነበሩትን እንደ አንዳንዶቹም አጻጻፍ "እግዚአብሔርን ፈሪ ሕጉን አክባሪ፣ በጾም በጸሎት በዓለሙ ተቀምጠው በተባህትዎ እንደሚኖሩት መናንያኖች ዓይነት የሚኖሩ ቸርና ርኅርኅት ንግሥት" ከመወሰዳቸው በፊት ሸህ ሁሴን ጅብሪል ብለውላቸው ነበር የሚባለውን ጠይቄ ያገኘሁትን አሳያለሁ።

በዚህች ዓለም ላይ አንዱ ሲሞት ሌላው መተካት የማይቀር ነውና ምኒልክ ሲሞቱ እያሱ፣ ከእያሱም ዘወዲቱ መንገሳቸው ግልጽ ነው። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ከሆነ ሸህ ሁሴን ጅብሪል የንግሥት ዘወዲቱን ንግሥ አመላከተው፣

ኩብልል ኩብልል አለች የሸዋ ሙዳይ

እኛም ይሁንልን ነፍጣችን ገዳይ

ብለው ነበር ይላሉ። በእርግጥም ከታሪክ ማስታወሻ ላይ እንደሰፈረው "መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም. በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ንግሥተ ነገሥታት ተብለው የዳግማዊ ምኒልክን ዙፋን ወሱ" ብሉ ያወራል።

አንዳንዶቹም አንድ ጊዜ ቃሉን ሌላም ጊዜ ድርጊቱን በመከለስ /መልሶ በማለት/ ነገሩ መልካም ማስተማማኛ ሳይሆን ይቀራል? በማለት የሚናገሩም አሉ።

ንግሥት ዘውዲቱ ከነገሡ በኋላ እልጋ ወራሹና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከነበሩት ተፈሪ መኮንን እንደሚጋጩ ያደባባይ ምስጢር ነበር። እነሱም የራሳቸውን አማካሪዎች ይዘው በየፊናቸው ድብብቆሽ መጫወት ጀምረው እንደነበረ ታሪክ ምስክር ነው። ስለዚህም ከዱብር እስከ መተማ ይገዙ የነበሩት ተፈሪን በአገር ውስጥም ይሁን ከውጭ አገር ተከትለው የሚዘዋወሩት ራስ ካሣ ኃይሉ ነበሩ። ከዚህም የተነሳ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ቀደም አርገው እነዚህ ሰዎች ዘውዲቱን ለማሰናከል እንደሚያሴሩ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል ይላሉ አባቶች።

የሴቲቱ ንጉሥ ጓዟን ስታነሳ

ይማከሩባታል ተፈሪና ካሣ

ተፈሪና ካሣ የቋጠሩት የማይፈታ፣ የነከሱት የሚያመረቅዝ፣ የወጉት የሚያጨልጥ መሆኑን ሸህ ሁሴን ጅብሪል፣

የሴቲቱ ንጉሥ በሏታ ትትነሳ

የከፎ ብር እሉት ተፈሪና ካሣ

ብለው ነበር በማለት ይናገራሉ። ይህም ማለት ልጅ ያለው ሁሉ ልጁን ከቱንና ደጉን የሚለይበትን የንባብና የጽሕፈት ትምህርት ያስተምር። ያገራችንም ሰው ከእጅ ሥራ ልቡ የፈቀደውን ቀልቡ ያረፈበትን ይማር። ያሳስተማረ በእካል ጉዳይ ካሣ መቀጫ ሐምሳ ብር ይቀጣል ያሉትን እንስተው መቾም ነገር ማዋሰብ ልማድ ነውና። "የከፎ" እንደዜ "የካሣ" እያሉ ከሰው ከሀገር ከባላገር ያጋጯቸው ነበር ሲሉ ይደመድማሉ።

## 2.3. ስለ ተፈሪ

ንግሥት ዘውዲቱ በ1909 ዓ.ም. መስከረም 17 ቀን ሲነግሡ ተፈሪ መኮንን ደግሞ ልዑል እልጋ ወራሽ ተብለው መቀመጣቸው ተደጋግሞ ተነግሯል።

ስለዛ ጨቅላ ከተወለደ በኋላ አጼ መባል ብቻ ሳይሆን ዕድል ፈንተው፣ ጽዋ ተርታው፣ ምን እንደሆነና ድፍን አበሻንም በጁ ጨብጦ በግሩ ረግጦ በመያዙ ሕልቁ አባቱን ከዶ በሱ እንደሚምል በሱም ዘመን እኔ ነኝ ባይ ሱሪ ታጣቂ የሚያንበረክክ መሆኑን ልቅም አርገው እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል።

እናገረዋለሁ አርጌ ተልክ

ሸዋ ላይ ይብሳል በተፈሪ አምላክ

ተፈሪ የሚሏት እለች አንድ ኩዛ

ጀግናም አያመልጣት ታልሆነ ፈዛዛ

ልበል እሽሩሩ ልበለው እቡቡ

አርባ ዓመት ይገዛል ብሩህ ነው ተልቡ

ተብሏል። ከዚህም ሌላ ከወሉ ተጋብተው ባህር ተሻግረው የብስ አቋርጠው ኢትዮጵያ አገራቸውን ከባህር ማዶ አገሮች ጋር አስተዋውቀው በመጨረሻም አዛኝ አጥተው እንደሚቀሩ የተናገሩት ይኸን ይመስል ነበር ይላሉ።

ወይፈኑ ታረርጌ ጊዶሪቱ ተኛ

ተወፃ ሰው ጋራ ሆነ ማበርተኛ

እመጨረሻው ላይ ሆነ ወሰንተኛ

ይህም ማለት ብለው ሲያብራሩት ማለት ከፈረንጅ አገሮች ጋር ማኅበርተኛ ለመሆናቸው በንግሥት ዘውዲቱ መንግሥት ጊዜ ገና በአልጋ ወራሽነታቸው ጀምሮ የማኅበርተኛነት መጠየቂያ "በ1915 ዓ.ም. ነሐሴ 6 ቀን የኢትዮጵያ መንግሥት በደጃች ናደውና በቶ ፋሲካ እጅ ወደ ዓለም ማኅበር መላኩ፣ ሁለተኛ ደግሞ ሚያዝያ 7 ቀን 1916 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ራስ ተፈሪ መኰንን የአውሮፓን መንግሥታት ከተሞች ለመጐብኘት መሄዳቸውን" ነው በማለት ነግረውኛል።

ሌላው ደግሞ ሼህ ሁሴን ጅብሪል መሬቲቱ ተፈሪን ተፈሪን እለች እልል



Scanned with CamScanner

ይላሉ በትግሥ ይላሉ በገና

እኛ እንደርስበትም እዛ ሽምግልና የሚል ነበር።

ያው ነገሩ ሆነና ታህሣሥ 17 ቀን 1928 ዓ.ም. ጦርነት ተጀመረና ማይጨው ተዘመተና ሰውም እንዳይሆን ሆነና ተለያየ። ከዛም ያለቀ አልቆ የተረፈ ተረፈ። ሽሁ እያይዘውም የቦምብ ከምር ተሸከመ የጋዝ መርዙን አስጭና መሬቱን በታንክ ሰማዩን ባይሮፕላን እያረሰ እቀጭ እምቧ እያሰ እንደሚመጣ፣

ተሰማዩ በታች ተምድሩ በላይ

ቲንዙ እየናቸው ሻሸና አምባላይ

ሲሉ ነበር የተናገሩት ይላሉ። ታዳ ይላሉ፣ ታዳ እነኝህን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያስበው በላይ ታጥቀው አሸብርቀው የመጡትን ሕዝቡን ከትዋው በላይ በሆነ በቦምብ ነበልባል ሲቸበችቡት፣ በመርዝ ሲያንፍሩት፣ በመድፍ ፍላጻ የሚያንገበግቡን ጉዶች በምን ይቋቋማቸው? ምንም ሰው በትግሉ ምንም ሰው በጉብረቱ ባንዲራውን ዳር ድንበሩን ማስከበር ቢችልም ከመሣሪያቸው ንግግራቸው ግራ የሚያጋባ ከመሆኑም በላይ እንደዘመኑም ከጉብረቱ ጋርም እምነት አለና፣ ሽሁም ያሉት ፈጣሪ አንተ መልሳቸው ነው ይሉና ይህንንም፣

ተወዳ የመጡ ተባህሩ ዳር

አነጋገራቸው እንደጉንጉንቸር

አካሄዳቸውም በሰማይ በምድር

መሣሪያቸው እንኳ አልቢን ምንሽር

መልሳቸው አንተ ሣሙኤል በሲር በሚል ነበር ያጠቃለሉት

ይላሉ።

ኢጣሊያ ከዓለም ሕግና ደምብ አፈንግጣ፣ በታንክና በቦምብ፣ በጋዝ መርዝም ተመከታ፣ ወላድ እንዲመክን፣ ጀግና አልባ እንድትሆን እናት አገራችንን መጨፍጨፏ የማይረሳ ነው። ስለሆነም ሽህ ሁሴን እነዚህ ከልማት ይልቅ ጥፋት የሚቀናቸው ከርጎራጌ ጭካኔ የተቀሃዳቸው

ሶላቶዎች እንደሚመጡና ሲመጡም ሽሁ የማይገኙ መሆናቸውን የገሰጹበትን ሌላውን አባባል ሲያቀርቡት ደሞ ይህን ዓይነት መልክ ይኖረዋል።

የእሬ ፈረሶች ሻሾና እምባሳይ
ቲመጡ እየናቸው በሰማዩ ላይ
እነሱም እያዩን እኛም እናያቸው
የእሬ ፈረሶች እንእምባላይ ናቸው።

ከዛም ሰው ተጠናክሮ በተጋድሎው ድልን ተቀዳጅቶ የፋሽስትም ጦር የሶላቶው ሳገሩ አፈር አለመብቃቱን በሰው አገር አሞራ መብላቱን የቆረጠውም ጅብ ሲጮህ ከማይሰማበት ተልከስክሶ መቅረቱን የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል እንደሚባለው ሁሉ አገሩን ሳያይ መቅረቱንም ሲናገሩ፣

መች ይወጣል ነበር ኮርማ ተበረቱ
እንደወጣ ቀረ እስተሰማየቱ ነበር ያሉት።

ሰወሬ ነጋሪ እንኳን ሳይቀር የኢትዮጵያ አርበኛ አመድ አድርጎ እንዳስቀረው ነበር የተናገሩት አሉ።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ ንጉሡ ድል እንደሆኑ ወደ እንግሊዝ አገር መሄዳቸው አይዘነጋም። የኋላ ኋላም አናስገባም በሩን ያን ፈርጣጩን ሲል የነበረ ሁሉ ቀርቶ መሬቱቲም በአበባ ወንዱም በሆታ ሴቱም በልልታ የሸዋ አበባ ያብባል ገና እያለ እንደሚቀበላቸው ሸህ ሁሴን የሚከተለውን ብለው ነበር ይባላል።

ቁሜ አልሃምዱ ቁጭ ብዬ አታሂያቱ
ተፈሪን ተፈሪን አለች መሬቲ

በማያዖዝም ኢትዮጵያ አገራችንን ቱርክም ሮማውያ'ንም ተመኝተዋትም መሬቷንም ረግጠው አፈሯንም ዘግነው፣ ከውኃውም ተጐንጭተው፣ ሰዋንም ፈጅተው፣ ገዥዎቿንም አሳደው ለመኖር ተመኝተው ሞክረውም ነበር። ነገር ግን ሳይሆንላቸው ቀረ የሚሉት ባሳምባራስ አባተ ይመር አሁንም ሽሁ ያለተፈሪ ባዕድ አይሆናትም ያሉበት ቃል፣

ኢትዮጵያ አገራችን ራሷን ተሠርታ ሩብሳ ልክክ

ተቀብታዋለች በሀምበር በምስክ

ትሸታቸዋለች ሰሮማ ለቱርክ

በሰማይ አውሮፕላን በመሬት ላይ ታንክ

እየመጡ ቀሩ እያሉ ልክክ

ኃይለ ሥላሴ ነው ባሏማ በልክ

እኛም ዱእ እርገናል ሥላሴ ይባርክ የሚል ነበር።

እንግዲህ ይኸን በተለያየ ጊዜ እሉት የሚባለው ጣሊያን መውረሩን፣ ንጉሡ ስደት መሄዳቸውን፣ ከዛም ተመልሰው አገር አረጋግተው ጠላት ተድሶ፣ ሕዝብ ተሰባሰባ፣ ሽብረብ ያሰችውን መሬት ጸጥ እርገው ለመግዛት የሚበቁ መሆናቸውንና ወደቀ ያሉት እንደሚነሳ ፈረስ ያሉት እንደሚጠጋን፣

የሐበሻ መሬት ምን ያሽብርሻል

ይመጣል ተፈሪ አሁን ያረጋሻል

በታችኛው ደሴ በጠባሲት ኮሶ

ኸደ ያሉት ዕቃ መጣ ተመልሶ

ተወደቀ ወዳ ተፈሪ አባነፍሶ

ሲሉ ነበር የተናገሩት ይባላል። ሲመለሱም ጭፈራው ቀልጦ ቀረርቶው ነዶ ነበር እሉ። ለዚህም እንደማስረጃ ይሆን ዘንድ ከታሪክ ማስታወሻ የሚከተለውን እጠቅሳለሁ።

"በሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም. ሰኞ ከፍቼ ተነስተን አዲስ አበባ ስንገባ በሕዝቡ ዘንድ የነበረው የናፍቆት አቀባበል እልልታውና ጭብጨባው ሆታው አሰልክ ይቀልጣል። ግርማዊነታቸው ባጠገቡ ሲደርሱ ደግሞ እንባው በፊቱ እንደጐርፍ ይወርዳል" ማለታቸው ከሽሁ ንግግር ጋር መግጠሙን የዚያ ጊዜ ወጣቶች የዛሬ አዛውንቶች ነገሩን ወደ ኋላ መለስ ብለው በትዝታ ገመድ በእንባ ጭጋግ እያስተዋሉ ስንት አለፈ በማለት

ይናገራሉ፡፡

ያ! ቀውጢ ቀን አልፎ ያ! የሰቆቃ ዘመን ተወግዶ፣ ጀግናም እምቢ ላገሬ እረ እምቢ ለወንዜ ለጸነቴ ብሎ ጤዛ ለብሳ ደንጊያ ተንተርሶ ፍሽሽትን ገርስሶ፣ ነጻነት መልሶ፣ ለመኖር መብቃቱ በኋላም ቢሆን ኃይለ ሥላሴ እንደወጡ ሳይቀሩ ተመልሰው መግዛታቸውንም ቢሆን ሽሁ በማያዳግም ሁኔታ ይህን በመሰለ ግጥም ነበር በወቅቱ ያበሰሩት የሚሉት ፊታ አባተ ይመር ሲናገሩ፣

ሳይሙት ሳይሀይ ሁሉን ሸኘ ቀዲር

ተመልሶ ገዛት ያበሻን ምድር ነበር፡፡ ያሉት ይላሉ፡፡

ደም የጠማው፣ ደግነት የራቀው፣ ክፋት ያጠለቀው፣ የኢጣሊያ ጦር በግፍ ገብቶ፣ አገር አልምቼ ሰውን ፈጅቼ፣ ወገኔን በሰው ለምለም መሬት አራብቼ እኖራለሁ ብሎ ጉዙን ጠቅሎ መድፉን አንጠልጥሎ የመጣውን የጀግናን እናት ማን ይደፍራታል ብሎ ዱሩ ቤቱ ያለው አርበኛ ግፋን ጨርቁን ሳይል ኮተቱን አራግፎ አፈር አልብሶ የሸሸውን መልሶ ጣሊያን አባሮ እንደሚኖር የገለጡበት ሌላው ግጥም ደግሞ፣

ኋሊህ በክብረቱ ፈረንጅ ተግዛቱ

ተመልሶ ኼደ ባምስተኛ ዓመቱ

የሚል እንደነበር ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ ይኸ ሁሉ ባርበኞች ትግል መወገዱን የነጻነት አየር ሕዝቡ መተንፈሱን ቢሆንም ለአምስት ዓመት ያህል መታፈኑን ቀደም አርገው በተናገሩበት ወቅቱ ንጉሡም ሲመለሱ ከውጭ ሰዎች ጋር ተነጋግረው እንደሚመጡና አብረዋቸውም የውጭ ሰዎች እንደሚከተሉ ተናግረው ነበር ይባላል፡፡ ይህም እንዲህ ነበር፣

ተወዳ የመጡ ባለቁምጣ ሱሪ

ተነጋግሯቸው ንጉሡ ተፈሪ

እንዲህ ይህን ሲያብራሩት፣ ያነጋገሯቸውም እንግሊዞችን እንደነበርና፣ እነሱም /ጦቢያ አርሚ/ የኢትዮጵያ አርሚ ብለው ማሰልጠናቸውን ገዳዳ መላዮ የሚያደርጉ መሆኑን ሲናገሩ ነው ይላሉ ሰዎች፡፡

እንግሊዞች መጥተው ወታደር እንደሚያስለጥኑ! ከዛም ሌላ ፈረንጅ በአማካሪነትና ባሠልጣኝነት እንደሚኖርና በደጅ በግቢውም እንደሚያዙበት ሲናገሩ፣

በሰማይ በራሪ በምድር ተሽከርካሪ

እኛስ ይመስሉናል የንጉሡ መሪ

ነበር እሉ ያሉት፡፡ ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ በሰው መጨከንና ሴራ ማድረግ የጀመሩት ከልጅ እያሱ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኂላም በ1921 ዓ.ም. የጉንደር ንጉሥ ተብለው የግብር ሥርዓት ከለወጡ ጀምሮ ነው፡፡ ለዚህም ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ስለሆነም ሽህ ሁሴን ጅብሪልም የኃይለ ሥላሴን አይምሬነት ሲናገሩ፣

ራስ ዘናና እግረ ውትርትር

መች እሱ ይሞታል ሕልቁን ሳይመትር

ብለው ነበር፡፡ በእርግጥም ብዙ ሰዎች አለቁ፡፡ ብዙዎችም ተሰደዱ፡፡ ከላይ እንደገለጥኩት ለአድመኛነታቸው አንድና ሁለት አይባሉም ነበር፡፡ ይኸንንም ማድረጋቸው የልጅ እያሱን መንግሥት መናዳቸው ከዛም በንግሥት ዘውዲቱ ዘመነ መንግሥት ጊዜም ቢሆን ንጉሥ ይባልልን የሚሉ ሰዎች አስነስተው ስለነበር እነደጃዝማች አባውቃውም እንዴት ተደርጉ ብለው ግርግር ሲነሳ እንደነበረና ሴራቸውም እንደ ያዘ ያደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ታዳ እንዲህ ሰውን በማነካካትና አንዱን ባንዱ ላይ በማስነሳት፣ ያቺም ተፈሪ፣ ተፈሪ ያለችው እንደ ጥላ ስታልፍ ጭንቅ ጥበብ እንደሚሳቸው፣ ያቺም ተፈሪ፣ ተፈሪ ያለችው መሬት አንቅራ እንደምተፋቸው በዚያን ጊዜ ዙሪያው ገደል ሆኖ ማጣፊያው እንደሚያጥር የተናገሩት ይህ ነበር ይላሉ፡፡

ቲገዛ ቲነዳ ቲመከር ቲያስመክር

ቲያጣላ ቲያዋቃ እንዱን ታንዱ ጋር

ይደርሳል ወቅቱ ለማንያ ቲሞላ

ወይት ይደርስ ይሆን ተፈሪ አባመላ

ሴት እንደዶሮ ጧት እንደ ቁራ፣ ዝሁር እንደ ሰዓት እሬ ሎ ሎ ያገር ያለህ ባዩ የድል እምቢልታ ነፊ በዳይን ተጋፊ ጧጊ ረጋፊ የሆነው ተማሪ የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ገዝግዞ አደንዝዞ እንደሚጥለው የተናገሩት ቃል የሚከተለው ነበር ይባላል።

ሰማንያው ያልቅና ቲሆን ሦስት ዓመት

ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት

ለሁሉም ጊዜ አለው እንደሚባለው ሁሉ ሁሉም ነገር ጊዜውን ቆጥሮ ለከቶ መድረሱ የማይቀር ነው። ስለሆነም ታዲያ! ዳር እስከዳር የገዙት ንጉሥ እኒያ ከሐበሻ መሬት አልፈው ፈረንጅ አገር ማኀበር የተጣጡት ጽዋ ያጋጩት፣ የተጐነጩት መንግሥት፣ እኒያ ምድራቱን አስጨንቀው አበሻን ጨፍልቀው ጀግናውን መርዘው ያዙ የተባሉት መሪ እምጥ ይሁን ስምጥ እንደሚገቡ እምን እንደሚደርሱ የትስ እንደገቡ የሚያውቅ የሚያስረዳ እንደማይገኝና ይህም እንደሚሆን ሽህ ሁሴን እንዲህ በማለት ተናግረውት ነበር ይባላል።

በሰማይ በራሪ በምድር ተሽከርካሪ

ውት እንዴት ደረሰ ልጃችን ተፈሪ

ይህን ካሉ በኋላ የአጼነት መንጠፊያው የአጼነት መቁረጫና ጡት መጣያው በዘመኑ ኃይለ ሥላሴ መሆናቸውን ቀደም አርገው አስተጋብተው የነበረው የሚከተለውን ዓይነት ግጥም በመሰለ ነበር በማለት ይነገራል።

ግባ በቀላጤ ውጣ በቀላጤ

ከተፈሪ ወዲ አይባልም አጤ

ይህንንም ይበሉ እንጅ ከዛ በፊት ግን ወሎን ድሰው ከወሎ ተጋብተው ባህር ተሻግረው የብስ አቋርጠው አገር አስተዋውቀው እሳቸውም ገነው እንደ ጤዛ በነው የሚቀሩ መሆናቸውን የተናገሩበት እንደነበር አይዘነጋም።

ከዚህም ሌላ ውበትና ጥራት ባለው አነጋገር የአገዛዙን ስልት ከየት ወዴት አርገው እንደሚያገኙትና ዓለምን ማየት ደስታውን ጨብጠው በድሎት ተንደላቀው እመጨረሻም ላይ ሥልጣኑም ንብረቱም እንደ ቀትር

ጥሳ እልፍ የሚል መሆኑን ተናግረው ነበር የሚባልበት ግጥም፣

ኃይለኛው በኃይሉ ዘውዱን አጠለቀ
እንኳን ተአበሻ በአርባ ዘለቀ
ዓለሟን አግብቶ ጉድ ተደላቀቀ
በሰማንያ ዓመቷ ሰማንያዋ አለቀ
እኔስ ይገርመኛል ስተኛም ስነቃ
የአበሻ ቆቡ በተፈሪ አበቃ
ዘውዱም ይመለሳል አራት ዓመት ጭቃ* የሚል ነበር።

እንግዲህ ነገሩን ስናጠቃለው፣ በቀደምትነት ነገሥታት መሳፍንት የመላለሱበት፣ በሌላው ጐኑ እንደ ንጉሡ እጐንብሱ ነውና ምሳሌው ሕዝቡም በመጽሐፍ ገላጭ፣ በዛጐል አፍሳሽ፣ መወጠሩን ሲያመለክት፣ ዋነኛው ገጽታው፣ ግን የያንዳንዱን የግጥም ትርጉም ከታሪኩ ጋር አዋህደን ስናየው አባቶቻችን ኀሊናን በሚነካ፣ መንፈስ በሚያረካ ባንድና በሁለት ቃል እንደ አመልማሎ ሸብልሉ የማቅረብ ችሎታ ማግኘታቸው የሀገራችንን ባለሙያነት ከማጉላቱም በላይ፣ ያቆዩልን የባህል ቅርስ ልጆቻቸውን የሚያኮራ ስማቸውን የሚያስጠራ ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም። ስለሆነም ቅርስ ነውና ለመዘክርነት ወዲህም ለጥናት ይረባል። /ሊጠና ይገባል/።

## 2.5. ጠቅላይ ነገሮች

ቀደም ባሉ ገፆች በቆራጥነትና በጀግንነት እንዲሁም በድፍረት ስለ ዘመኑ ሰዎች መወለድና መውደቅ የተናገሩትን ተመለካከተናል። ከዚህ ቀጥዬ ደግሞ በተለያዩት ገፆች ላይ የኢጣሊያን ፋሽሽት የግፍ ወራሪነት ከመረዳት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው እንደሚገሉ እንደ ተናገሩት ሁሉ አሁንም ሽህ ሁሴን አሌት ለይተው ጉራ ለከተው በሕዝብ ላይ የሚመጣውን በግለሰቦች መካከል ያለውን ቅራኔ ሆነ ችግር ቁልጭ አርገው ያሳዩባቸውን ግጥሞች በቅደም ተከተል አቀርባለሁ።

* በወሎ አራት ዓመት ጭቃ ማለት በየአራት ዓመቱ የሚሸመው ጭቃ ሹም ነው ይባላል

ሸህ ሁሴንም በከራማ ሰምተውት ኖሮ፣ ሴትዮዋን ከነስሟ ጠርተው፣

ጆሮዬ ከፉ ነው ነገር እያልፈኝ

ትዳሬን አደራ አስችኝ የልፍኝ አሉ ይባላል።

ወ/ሮ የልፍኝም ሐጃዋ ሞልቶ፣ ደህና ተደላድሎ ልብስ ተጋፋፊ አግኝታ እንደ ቆየች ተነስታ ኩራብ ትወርዳለች። ብትመጣ ምነዋ! የጉደሰ አሰ ቢሏት "እረ /ሞልቷል/ ቲፍ ብሏል! ተርፏል አለችና ቀየዋን ታረግጥ አልቀር ብየነው ብትላቸው "ሴት ልጅ ለበርኖስ ወንድ ልጅ ለፈረስ ብለው" መርቀው ላኳት ይባላል።

መቼም ሰው ሁሉን ማስደሰት አይችልም። ባገራችን አነጋገር እንኳ ካንድ አካል እንኳ ቀኝ የሚሰጠውን ግራ አይይ ይባለ የለ? ታዳ ሸህ ሁሴንም ሲናገሩ አንዱ መደሰቱ ሌላው መከፋቱ እንደማይቀር ግልጽ ነው። ሰለዚህም ድፍን ኮራብ በሳቸው ጉሜ ይይዛል አሉ። ምነጋ ቢሉ እሳቸው ላሰው ቅንጭብ ያረግዳል እንዲሉ ጉተራው ለሞላ ማጀቱ ለተትረፈረፈ ቱጃር ሰድሃ አይፈርዱ ሲሉ ሣር የሚያጭዱላቸው፣ እንጨት የሚፈልጡላቸው ጉረቤቶቻቸው ሲያልፉ በነገር ጉንጥ ያደርጓቸዋል። በነገታው ሸሁ እንደምን አረፈዳችሁ? ሲሉ ዝም። ምነው ሲሉ ሁሉም በአንድ አፍ ያብሰለሰላቸውን ይነግሯቸዋል። በዚህን ጊዜ እሜሐከላቸው አረፈ ይሉና፣ ጨዋታ ደርቶ ወጉ ደምቆ እንዳለ "እረ ተው እቦ እኔ ሐብታም ድሃ ሙሃቻ ሞላ ጉደሰ እምልበት ምን ቅዋ አለኝና ሐብታሙስ ምን ቲፈይድልኝ ነው? ይልቅስ እናንተው የምትከጅሉኝ የምከጅላችሁ አትሻሉም? ታላችሁም መርሃባ" ብለው ቆየት እንዳሉ፣

ፍረድልኝ አሉ ምን ልፍረድላቸው

ማጭድ ተወገቡ ምሳር ተከንዳቸው

እኔን የሚታየኝ ያው ድኅነታቸው

ብለው እርፍ በማለት ወሽመጣቸውን ቆምጥ፣ አንጀታቸውን ቁርጥ አደረጓቸው ይባላል። እንዲሁም ደግሞ ጉረቤታቸው የሆነ ገበሬ ከሚስቱ ጋር ሆኖ ሁልጊዜ ያሟቸው፣ ሁሌ ያነሱ ይጥኋቸው ነበር አሉ። ከዚህም የተነሳ ሸሁ ከይር አደራችሁ ብለው ሲያልፉ ሲያገድሙም ዝም

ይኂቸዋል። አሁንም ዝም ብለው ያልፋሉ። ጉዳያቸውን ተከራቸውን ተክረው ሲመለሱ መቸም ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጐረቤት ነውና የሰውየው ደጃፍ /በር/ ገርበብ ብሎ ያዩና እንገታቸውን መለስ ሲያደርጉ አባዋራ ከጐሮ ሆኖ ያይና፣ እውገረድን ተጣርቶ "ቶሎውን፣ ቶሎውን፣ ይኸውይ ሰውዬ መጡ" ይላል አሉ። እውረገረድም ያን ማር የያዘ ዕቃ ወስዳ ከንስራ ውስጥ ትደብቃለች። እሳቸውም ገብተው መደብ ላይ አረፈ እንዳሉ እቶ አባወራ አፈሩን አረጋግፎ ይገባል። ቡንም ምንም እየተባለ ማጀት አለመሙላቱን የቋቱ ጠብ አለማለቱን ባጠቃላይ የእዱንያ አለመሙላቱን እያወጉ ሳሉ አቦሉን ልፈው ቶናው ሲቀዳ፣

ምን ይሆንልሃል ይኸ ሥራ

ማርክን ሸሽገህ ተንስራ

ፍረድልን አሳችሁ ምን ልፍረድላችሁ

ለኔ የሚታየኝ ያው ድኀነታችሁ ብለዋቸው ቡናቸውን አክትመው እብስ አሉ ይባላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሳይንስ እውነትን ለመፈለግ ነጻነትን የሚሰጡትን ባህላዊ ሁኔታዎችን መፈለጉን እነዚህም በሳይንስ ውስጥ ያሉ ነገሮች ሰብአዊነት ካልተጨመረባቸው ፍጹም መሆን የማይችሉ መሆናቸውን የሳይንስ ብቃት ከፍቅር ጋር ሲገናኝና ሳይገናኝ መቻሉን የጠቋቆሙበት እንደነበረ ይወራል። ታዳ አጼ ዮሐንስም እስላም ይጥፋ ዱር ይግፋ ብለው ያልተነሱትን ያህል፣ ዮሐንስ አገሬን እንኳን ደርቡሽ ሌላም አይደፍራት ያላሉትን ያህል፣ በጊዜ መለዋወጥ፣ በትምህርት ዕድገት መምጣቱ ያልታያቸውን ያህል ሸህ ሁሴን ዐረብ በከረሜላ እየደለለ፣ በቃላት እየሸነገለ፣ በገጠር በከተማው ዳር እስከ ዳር በመሰማራት፣ በሐበሻ መሬት እንደሚፈስ በሐበሻ ምድር እንደሚሰገሰግ የዐረብ ሹማምንቱ መልክተኛው እንደሚሰራጭ ከሳፍንቱ ከልዕልታቱ ጋር እንደሚወዳጅ ቀደም አርገው ተናግረው ነበር ይባላል። ይህ ሁሉ ሲሆን ታዳ እሳቸው አፈር የሚለብሱ የማይሰሙ የማይላወሱ መሆናቸውን በሚከተሉት ዓይነት ስንኞች ነበር የተናገሩት በማለት አባቶች ያጫውቱናል።

እኛ እንደርስም እንጅ አዛለደረሰ

የዐረብ ፈዛይን ሐበሻ ፈሰሰ

እንዲህ እንደዛሬው ሰው ተራብቶ ከተማው ከትሞ ባልነበረበት ወቅት፣ እንዲህ እንዳሁኑ በትምህርት ገፍቶ መድኃኒት ባልነበረበት ሰዓት ሰው ከቆላ ይልቅ በደጋው ፈሶ ደጋውን ነበር ሙጥኝ ብሎ የነበረው፡፡

አሁን ግን እንኳን ደጋው ቆላውም የዘመኑ ደጋ ባደለው የው ልጅ ጥረት በወለደው ቴክኖሎጂ በመደገፍ ለብልጽግና ተፈላጊ ሆኖ ሰውም ሰፈኖበት ሁሉም ተሟልቶለት ይታያል፡፡ እንደዚሁም በወሎ ክፍለ ሀገር ከደሴ ከተማ ሃያ ሦስት ኪሎ ሜትር ላይ የምትገኝ ኮምቦልሻ የምትባል የአውራጃ ከተማ አለች፡፡ ይህች ከተማ ከአሥመራ ለሚምዘገዘገው፣ ከአሰብ በአሳይታ ብሎ ሽቅብ ለሚያዘግመው ከአዲስ አበባ ለሚሽቆለቆለው ባለካሚዎን ነጋዴም ሆነ ተመላላሽ የሰጠች ናት፡፡ ታዳ ምን ይሆናል እንኳን ሲያድሩ ሲያመሹባት ሲያልፉባትም ታስፈራ ነበር፡፡ ለመናኸሪያ አመች እንደመሆኗ ሁሉ ወባዋም ከመቅጽበት እንደ ቅጠል እርግፍ ነበር የሚይደርገው እሉ፡፡ ሽህ ሁሴን ግን ስለዚች የአውራ መንገድ ከተማ ዕድገትና ብልጽግና ስለዚች አውራጃ መሻሻል፣

እስቲ ተነስቼ ልህድ ወደማሻ

የኋላ የኋላ ስለማላይኩም ኮምበልሻ

ነበር እሉ ያሉት፡፡ እነሆ አሁን ትንቢቱ ይዞ፣ ነገሩ ሰምሮ የንግድ እምብርት፣ የሰው እረፍት ማግኛ ሆነች ይሉና አልፋ ተርፋም ፋብሪካው ተቋቁም ሰው ከትሞ ከኑሮ አመቿ ሆና በመታየቷ ዛሬ የማየሳለማት ነጋዴ ይሉ ጸሐፊ፣ ዛሬ የማይመላለስባት ፈረንጅ ይሉ ሐበሻ፣ ዛሬ የማይከትምባት ዓረብ ይሉ የወዳሰው የታሰና! እንዳውም ፋብሪካው ተንጣሉ፣ ካሚዎን መንገድ ተዘርግቶ፣ ትምህርት ቤቱ /እስኮላው/ ተከፍቶ፣ መብራቱ ሲንቀለቀል፣ ውኃው ሲንጨለጨል፣ ሲታይ ምነው የክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ኮምበልሻ በሆነችው የማይል ምሑር የማይመኝ ወጣት ሽማግሌ አይገኝም በማለት የጥንቱን ከዛሬው ጋር በማወዳደር ዐዋቂዎች ይናገራሉ፡፡

ወልይ የሚናገረው ሂደው ሲጠይቁት እንዲህ ሆንኩ ሲሉት ነው ይባላል። ሽህ ሁሴን ግን ተጠርተው ሲሄድ፣ አሰያም እንዳው በምንም ቀን ሲታያቸው፣ ሰውም ሲያነሳቸው ነበር እሱ የሚናገሩት። ታዳ ንጉሥ ሚካኤል ወደ ምኒልክ ልከዋቸው ያ! ሁሉ አባይ ጠንቋይ በሽታውን አጥቶት የባጥ የቆጡን ቀበጣጥሮ ሽህ ሁሴን የትርንጉውን ነገር ነግረዋቸው ሲመለሱ ሲሉ ምኒልክ ሰፊ መሬት ልስጥህ ቢሏቸው "ለኔ ቀርተ ላንተው እጅ በነሳልህ" ብለዋቸው ኮሬብ ወርደው ብዙ ነገር ሲያደርጉ ሲናገሩ ቆይተው ሳለ በሌላ ጊዜ ወ/ሮ ሽዋረጋ እንዴት ብዙ ወታደር የሚያሳድር መሬት ላንድ ሰው ልስጥ ብሰው እሱ ብሰው ንጉሡን ሲናገሩ ኮሬብ ሁነው ይሰማሉ እሉ። በዚህን ጊዜ ምን እሉ ይባላል፤

ያቺን የኛን ወፍቅ /አንድ ማሳ/ አሻግራ ትታይ

ያቺ ገዲ ተነሳች ተንቁሳሏ ላይ

በማለት ወ/ሮ ሽዋረጋ እንደሚሞቱ ተናገሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ሐረርጌ ወርደው ብዙ ነገር ተናግረው በምኒልክ በኩል ሲመለሱ መሬት እምቢ ሲሉ፣ በግድ ፈረስና በቅሉ ተሸልመው በማሻ ሲያልፉ ደጃች ሲበን ያኔ ማሻን ይገዙ ነበርና ሲዘዋወሩ በሩቅ ባጀብ ሰው ሲሄድ ይመለከታሉ። ማነው ሲሉ ጊዜ፣ ሽህ ሁሴን ጅብሪል ናቸው ይሏቸዋል እሉ። ሲበን ይገሰግሱና ጥላ አብርደው፣ አርፈው እንዲሄዱ ይለምኗቸዋል ይላሉ። ጉዳዩ ደግ ተመኝ ደግ እንድታገኝ አይደል፣ ሰው የሚለው እሳቸውም መልካም ይነግረኛል በማለት ያስገቧቸዋል። እዛም እንዳረፉ የእግር ውኃ ቀርቦ፣ ምግብ እስኪቀርብ ቡን ተፈልቶ፣ ከዛም ማድ ተነስቶ የፈላው ተነሳስቶ ከቆያዩ በኋላ፣ ወደ ምሽቱ ላይ እንዲህ ይላሉ እሉ።

እንዲህ ቅሜ ቅሜ ላልወጣ ዘመድ

ማሻ ተፈረደ ለበሽር መሐመድ።

ይህም ይላሉ ተነጋሪዎቹ፣ የደጃች ሲበን ግዛት ሲዳሞን ይገዙት ለነበሩት ለደጃች በሽር መሐመድ ለማሻው ተወላጅ እንደሚሰጥ ሲበንም ምንም እንኳ ተወልደው ያደጉበት፣ አትብታቸው የተቀበረበት ደግሞ መቀመጫቸውን አሰለል ላይ አድርገው ሚስታቸውን ጉድበይ ብሪቱ እያሉ፣ በዘንግ ቃሉን፣ ተሁለደሬን፣ አልቡኮንና ርቄን ለአርባ ዓመት እንደገዙት የቃሉው ባላባት

እንደ ብሩ ልቦ ለአርባ ዓመት እንደሚገዙ ሲናገሩ፣

በሸርን እንበለው አበባ ከበቦ

አርባ ዓመት ይገዛል እንደ ብሩ ልቦ

ወዳጀ ወዳጀ ወዳጀ ሲበን

እሰው አገር ሀጾ ከረመ ድልባን

የመጣሁበቱ ተወጣ ሐጀቴ

ዝናቡ ታይዘንብ ሳይሞላ ቱልቴ

አንተም ወደሸዋ እኔም ወደቤቴ።

በማለት ቀልጠፍና ጠፍ ባለ አማርኛ ነግረዋቸው ወደቤታቸው ሄዱ። ሲበንም አዝነው ተክዘው ቀሩ። ራስ በሸርም በንግሥት ዘውዲቱም ባጼ ኃይለ ሥላሴም ጊዜ ነበሩ። ደጃች ሲበንም እንደ‐ት ከዘር ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ግዛት በኔ ጊዜ ይደፈርሳል? እንደ‐ትስ ትሰቃለህ ሸዋም ትሄዳለህ አሉኝ በማለት ቂም ይዘው እንዳሉ እህህ እንዳሉ ወደ ሸዋ ሄዱ ይባላል፣ እዛም ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላ ሸሁ ያሉት ተፈጽሞ ሲበንም ተመልሰው ኵሬብ ይገባሉ። እንደመጡም ሸህ ሁሴንን ከመሬታቸው ይነቅሏቸዋል አሉ። እሳቸውም በፋንታቸው እንገታቸውን ደፍተው ብርዛቸውን ይዘው ሐቀኑራቸውን ሳብ እያረጉ "እስቲ አንተ ታውቃለህ" ሲሉ ብዙ ጊዜ ቆዩ አሉ። ከዛም በኋላ አንድ ቀን እንደተቀመጡ፣

ያንተ ሞልቶ ተርፎ የኛን ታየሃት

አንተም ትነሳለህ ታዱኛ መሬት ማለት፤ እያይዘውም

ይዘጋ ታላችሁ መህራባ ይዘጋ

እዳራሹ ባጋም እልፍኙ በቀጋ

እንዳሉ ደጃች ሲበን ይሰሙና አሉ፣ ዝም ቢሉ ይሻላል ብለው ለአሽከር ይልካሉ አሉ።

ይህን እንዳሉ ያ ደጅ የጠኑለት ያ ለስንት ጊዜ ወድቀው የተነሱለት

የቋመጡ፣ የባንለት ግዛት ያን ያህል መከራ ያዩለት ቤት ወና እንደሚሆን ነገሯቸው፡፡ ያም ሆነ ይላሉ ከዚህም ሌላ አሁንም ወሉን በዓይነ ህሊና የተመላለስንበት እንደሆነ ይህን የመሰለ ወግ እናገኛለን፡፡ መንገሻ አቲከም ዋድላን ሲገዙ ሲበን ደግሞ ድፍን ኩራብን ይገዙ እንደነበር በላይኛው መሥመር ተገልጿል፡፡ የኋላ ኋላ ግን ሁለቱ በኩራብ እንደሚያያዙና ሹመትም በሸዋ እንደሚመጣ ሁለቱም በትውልድ እንደማይተናነሱ ሸሁ ሲናገሩ፣

ከሸዋ የመጣች አንዲት ትንሽ ጋሻ

ቲቃሰቧት አየን አሲና መንገሻ

እንደምንም ብሉ አላቸው ውሃርሻ /ረዳት/

ብለው ነበር ይባላል፡፡ እንዳሉትም ያው ከመቅደላ በኋላ ራስ አባተ ቧያለው ሲሞቱ ራስ ከበደ መንገሻ ወሉን ተሾሙ፡፡ ያው ሹመቱ ከሸዋ መጣ፡፡

መቸም የጥንት ሰው እምነት ካንጀቱም ቢሆን እንደ ዘመኑ ሁናቴ አይደል ሰው የሚናረው በንግርት ምን ተባለም በማለት ያምን ነበር፡፡ ታዳ ራስ መንገሻ አቲከም ሳይንትን ሲገዙ በነበረበት ወቅት ከንጉሥ ሚካኤል ጋር ደኅና ነበሩና "እባክዎን እኒያን ወልይዎን ይላኩለኝ" ሲሏቸው ግዜ "ምን ከፋኝ" ብለው እንዲሄዱ ይለምኗቸዋል አሉ፡፡ ሸሁም በዚህ ቅር ይሰኙና አሉ ወደ ምኒልክ ሲሄዱ እንዳሏቸው ሁሉ አሁንም ደግመው "ቲሆን ቲሆን የወግ ዕቃ ተደብቆ በከበሬታ ይቀመጣል እንጅ እንደ ፋቅራ ጡሴ ለዛም ለዛም፣ እዛም እዛም አይንጦለጦልም፡፡ መቸስ ምን ይደረጋል" በማለት ሲነሱ የተናገሩት፣

ተሰደድከኝማ ሰውጁ ሰውጁ

አገርክን ወሰዳት የመንገሻ ልጁ

ነበር ያሉት አሉ፡፡ እዛም እንደደረሱ መንገሻ አቲከም በሦስት ሰዎች ተከበው እልፍኝ ውስጥ ተቀምጠው እነኛ ሰዎች አምን አቦ አምን ድፍን ወሉን ትገዛለህ ያረግድልሃል ያሸረግድልሃል ሲሏቸው ሸህ ሁሴን መስማት በዚህን ጊዜ መለስ አርገው ሸሁ፣

እማይሆን እማይሆን እየፈረዳችሁ

እንማን ነበሩ ታስኙናላችሁ ማለት፣

በዚህ ወቅት ራስ መንገሻ አቲከም ተቁነጠነጡ አሉ፡፡ ሽሁም ይኸን ዓባይ ጠንቋይን፣ መጽሐፍ ገላጩን፣ ይኸን በግራ ገብተህ በቀኝ ትድሳለህ ባዩን፣ ያን ለምሲም ሣር እያንቅፍህም ባዩን ያን ጠላትህ እንደጢስ ተኖ እንደጉም ተጉማምዶ ይጠፋልሃል የሚለውን ሁሉ ሲያጋልጡት፡ አመስካከታችሁ ካፍንጫችሁ ያልራቀ፣ ዓላማችሁ ቀላፍቶ ለመብላት እንጅ ራቅ ያለውን የሚሆነውንም አታዩ ያሉበት ቃል፣

እናንተ እምታዩት የለቱን የለቱን

እኛ የምናየው የሰማንያ ዓመቱን ነበር አሉ ያሉት፡፡

እንግዲህ ከላይ ያለውን ቃል አሉ የሚባለው እዛ ደርሰው መንገሻ አቲከም በሦስት ሰዎች ተከበው ሲዋሹ እንደነበር ሁለት ስንኞች ገልጠዋል፡፡ ወዳውም ያኩተቱልናል አሉ፣

እስቲ እንናገረው ሰውጁ ሰውጁ

ባባትየው ቢቀር ይገዛዋል ልጁ አሉ አሉ፡፡ ሰዎቹን መለስ አድርገውም መንገሻ አቲከምን፣

ቲሆን ባንተ አለያ ለልጅህ

የሰባት ቤት ወሉን አደረግናት በጅህ

አሏቸው ይባላል፡፡ ይህም ማለት መንገሻ አቲከም እንደማይሆንላቸው ነገር ግን ልጃቸው ራስ ከበደ መንገሻ እንደሚገዙ ተናገሩ አሉ፡፡ ሽማግሎችም ግጥሙን አስልተው ሲያገናዝቡት እንዲህ ይላሉ፡፡ ራስ አባተ ቧያለው ወሉን ይገዙ በነበረበት ወቅት የልጅ እያሱ ጦር ደሴና መቅደላ ላይ እንደ ተመታ ራስ አባተ ከሞቱ በኋላ ራስ ከበደ መንገሻ ወሉን ተሹመው ገዙ ይሉና ለዚህም ታሪክ አሌ አይልም ይላሉ፡፡ ስለዚህም "የሰባት ቤት ወሉን አደረግናት በጅህ ያሉትና ባባትየው ቢቀር ይገዛዋል ልጁ" የሚለው ፍጻሜ ስማማትን የታሪክን ማኅደር መመልከት ነው በማለት ያጠቃልላሉ፡፡

ድርጊቶችን ሁሉ ታሪክ እንደሚመዘግባቸው ሁሉ የሰውም አእምሮ



Scanned with CamScanner

ያሰፉትን ቀርዖ በመያዝ ሲያብላላቸው ይኖራሉ። እንደዚሁም ሁሉ ቀደም አድርጌ ከታሪክ ጋር በማያያዝ ልጅ እያሱ ፍቼ በልዑል ራስ ካሣ እጅ ታስረው ሳለ ከልዑል ራስ ኃይሉ በተሳካላቸው ገንዘብ ሰውን ሸነጋግለው ሲያመልጡ፣ በዚህ የተነሳ ራስ ኃይሉ ከጃንሆይ ጋር ይጡሉና ይጋዛሉ አሉ። ኋላም ይጠራጠሯቸው ነበርና ይሞታሉ አሉ። መቸም በዚህ ዓለም ላይ ያንድ ሞት ላንደኛው ሠርጉ ሲሆን ስለሚችል ለጊዜው ጃንሆይ ደስ አላቸው ይባላል። ነገር ግን የመጨረሻውን የሚያውቀው ፈጣሪ ነው በማለት ሁሴን ጅብሪል፣

ቲሰበር አየነው የጉጃም ተራዳ

ዛሬም ደስ አላቸው የኋላውን አንጃ

አሉ ይላሉ። ሰው ያላንድ ነገር አይፈጠርም ይባላል። አንዱ ጉብዝ ሠራተኛ ይሆናል በሌላ በኩል ሰካራም ይሆናል። ሌላው ደግሞ ዝም ያለ ይሆናል አልፎ አልፎ ሲናገር የሚያስቅ የነገርን ደርዝ የሚያውቅ ሆኖ ይገኛል። እንደዚሁም ከጥንቶቹ ባለታሪኮች አንዱ የጦር ሚኒስትሩ የነበሩት ፊታ. ሀብተጊዮርጊስ በመኳንንቱ ዘንድ ከስማቸው ቀድሞ ይገኝ የነበረው “አባ መላ” የሚለው ቅጽል ነበር አሉ። ምክንያቱም በጣም ዘዴኛ በጣም ብልሃተኛ እንደነበሩ በሰፊው ይወራል። ታዳ ሸህ ሁሴን ጅብሪል የኒህን ሰው መለኛነት ያውቁ ይመስለኛል፣

ቲሰበር አየነው ጉራቻው በሬአቸው

እንግዲህ ለሽዎች ብላትም የላቸው

ነበር አሉ ያሉት ሲሞቱ ይኸም ማለት ይላሉ ሰዎች፣ ይኸም ማለት አባ መላ ከሞቱ ሸዬ ዓይነ በሥር ሆነ ቀኑ ጨለመበት ነው ነገሩ።

በድሮ ጊዜ ባልና ሚስት የሚባሉት ሲጋቡ ትውልድ ቆጥረው ዘራቸውን ጠርተው አጥንተ ጥሩነታቸውን አስመዝነው ወንዝ ማሻገሩን አስመስክረው ነበር ይባላል። በዛን ጊዜ በዚሁ ዓይነት የራስ ኃብተማርያም ልጅ ወ/ሮ አበበች ኃብተማርያም የየጁውን ገዢ የንጉሥ ሚካኤልን የእህት ልጅ ደጃች ቃሲም መሐመድን ያገባሉ አሉ። የማሻው ፊታውራሪ እመዴ በሽር ደግሞ ደብሪቱ ንዑስ የሚባሉትን ያገባሉ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ደጃች ቃሲም አንድ ዕለት ገታራ ወንዙ ደብሪቱ ንዑስ ባጅብ ሲሄዱ ያዩና ቡና ጠጥተው

ከጸሐይ አግልለው በረድ ሲሰ /ጥላ ሲዞር/ እንዲሄዱ ይጠይቁና ፈረስና በቅሉ ይራገፋል፣ ባል እንዳያዩ እንዳይሰሙ አሽከሮቻቸው ደሴ ተዝናንተው ዘመድ ጠያይቀው እንዲመለሱ ይላካሉ። ከደጃች ቃሲም ጋር ይሰነባበታሉ። በዚህን ጊዜ አበበች ኃብተማርያም ለአመዴ በሽር "ቃሲም የያዘውን አልያዘም ወይ" ሲሉ ይልካሉ አሉ። ይህን ጊዜ አመዴ በሽር አመር ዘራፍ ብለው ይመጡና ይከሳከሳሉ። ይህ ነገር እንደሚሆን ግን ሸህ ሁሴን ጅብሪል ገና ሴቶችም ሆነ ወንዶቹ ሳይኸለቁ እንዲህ ብለው እንደነበር አቶ ዘውዱ መንገሻ ይህን ይላሉ፣

ትውልድ ትውልድ አሏት አበበች ኃብቴን
እንቅፋት የመታት ግራ ቀኝ እግሯን
ወይ እነሱ አያቁ ወይ ሰው አይጠይቁ
ቃሲምና አመዴ ባንዲት ሴት አለቁ።

ሌላው ጉድ ደግሞ እንዲህ ነበር። ፊታውራሪ አመዴ በሽር ጋቢ ቤት የሚባለውን ያዙና ሹም ሽር ያደርጋሉ። በዚህን ጊዜ እነ ቀኛዝማች ይመር ወሉ እነ አሰን መሐመድ፣ እነ አባ ጥቁር እነ ግራዝማች መንገሻ ሁሉ ለመሾም አቆብቁበው ለኔ ለኔ በማለት ይያያዛሉ። ነገር ግን ይህ እንደሚሆን ጌታው ሸህ ሁሴን ጅብሪል ቀደም አርገው በሚከተለው ዓይነት አንቆርቁረውት ነበር።

ምን ያጣላችኋል እነ ይመር ወሉ
መሬቱን ወስደው ያባቱ የጃዴ ነው ብሉ።

በማለት ፊታ. አመዴ በሽር እንደሚሽሯቸው ተናገሩ ይላሉ። ቀጠል አርገውም ሸበሽ አመዴ የሚባለውም ያባቴ ነው ብሎ እንደሚሳና ተቀባይ እንደሚያጣ አገሩን የዐበይ ቤትን የራሱን ወረሄመኖን እንደሚያምሰውና እንደሚሞትም ሲያወጉ፣

ባለቡላ ፈረስ ባለ ዐረብ ጉራዴ
ሞተ ተቀበረ ያ ሸበሽ አመዴ

ነበር አሉ ያሉት። በዚህች ዓለም ላይ የሚኖር ሰው ወዳጅም ጠላትም እንደሚኖረው እሙን ነው። እንደዚሁም ሁሉ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ሁሉም

ቃሴ ነው ካሰ በኋላ ወሰም ዘሰም አይልም ነበር እሉ። ካሰም ሙግት ቢገጥምም ያገር ሽማግሉቹ ባሉበት ዛፍ ስር ተቀምጠው ማር እሰጥ በቅሉ ከነግላሷ እሰጥ በማለት ነበር እሉ የሚነጋገሩት። ሽህ ሁሴን ግን ይኸ ይኸ ተረስቶ ወረቀት ባሙጣው ጣጣ ማመልከቻ በመጻፍ ፍርድ ቤት ሰፍርድ ቤት በመወዛወዝ ናላው እንደሚዞር በቃሉ ተናግሮ ባንደበቱ አስረድቶ ፍጻሜ ማግኘት እንደሚቸግረው ነገር እንዳከርማ በመሰንጠቅ እንደሚናውዝ ሲናገሩ እሉ።

እሰጥ አገባ ነበር ሙግታችን

ራቦር በመጣፍ ሰላሳ ዓመታችን

ነበር ያሉት። እንግዲህ ሰነገር መነሻ እንዳለ ሁሉ ሰዚህ ሁሉ መንከራተት ቀን በጸሐይ ሌት በቁር መጠበስ ምክንያት የሆነው ያገር ሹሙ የሰፈር ዳኛው እንደመሆኑ መጠን ይኸንም ያደረገ በሰፈረው ቁና መሰፈሩ የማይቀር እንደመሆኑ ሁሉ ያ በጊዜው ያጉላላ፣ ያ በዘመኑ በሰው ይቀልድ የነበረ ሁሉ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የጁን እንደሚያገኝ የተናገሩት ቃል የሚከተሰው ነበር ይላሉ።

ምጣዱ ተጥዶ እጃ እየተቆላ

ምነው አይጠረጥር መኪንንቱ ሁላ

መድፉ ታይተኩስ ቦንብ ታይፈነዳ

መኪንንቱ ሁሉ እንደበግ ተነዳ

በተሰያዩ ገፆች ላይ የሰገሌንም፣ የመቅደላንም፣ ሁናቴ በልዩ ልዩ መንገድ አቅርቤያሰሁ። እዛ ሰው እንደሚያልቅ አሞራ ተጸይፎት፣ ጅቡ ንቆ እንደሚተወውና ፈረስና በቅሉው የሚያራግፈው አጥቶ መሣሪያና ልብስ ሸካፊ ወንድ ጠፍቶ መንገዱ በሬሳ ተዘግቶ ጭነቱን ሴቱ እንደሚያቃልል ብረትና ልብስ እንደሚሰቀም ሽሁ የሚከተሰውን ነበር እሉ ያሉት።

ተቦሩ ያነሳ ወረኢሉ ድረስ

ቲሰቀም እየነው ብረትና ልብስ

ይሉና ሰውም እሴቱ አንድ የሆነው ሳይሰይ እንደሚባቃ የውጭ ቢሆን



Scanned with CamScanner

ከባህር ማዶ የተነሳ ባለ ጋራ ቢሆን ባንድ ላይ ተረባርቦ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን ተጉራ ጉራ ተጠራርቶ በደብርና በሰቦካ ተከልኩሉ ከዛም ወንዝ ደፍቶ አሳዶ እንደሚመሰስ ሲቻል፣ ነገር ግን ይህን በመልከም ይሁን በእፍ አንድ የሆነው ሰገሴ ላይ ሆነ ሴላም ቦታ እንደሚዋቃ ሲናገሩ፣

ፈረንጅ ፈረንጅ እለኝ አበሻ መሬቱ

የፈረንጅ ነገር አሰው መመለሻ

እኔን የቸገረኝ አበሻ ላበሻ

ነበር አሉ ያሉት። አሁንም እያሱ ከመቅደላ ካመለጡ በኋላ ደሴን ለመያዝ መገስገሳቸው ባሸንጉ ከተጋለጡ በኋላ የፊ. ኃብተጊዮርጊስ ጦር ደሴ ደርሶ ሦስት ቀን መዋጋቱ ተገልጧል። ይህ ከሆነ በኋላ ግን ወሉ ያረሰውን እንደማይበላ፣ የከተተውን እንደሚቀማ፣ ጋላ መሬት ተብሉ እንደሚወሰድበትና ቀላድም እንደሚጣልበት ጉድ እንደሚልም፣

ምን እለች ታች ደሴ ምን እለች ታች ጢጣ

ምድር ሰፋሪዋ ቀጣሪዋ መጣ

ብለው ነበር ይባላል። ባንጻሩም ሰው እየተዋለደ እህሉም እየተወደደ በሚሄድበት ወቅት ሁሉም ሥራውን ትቶ እርሻ እርሻ ብሉ እንደነበር ሐቅ ነው። ይህ በተባለበት ወቅት ደግሞ፣ የመሬት ዋጋ የት እየለሴ እንደነበር አልፈነው የመጣነው ነው። በሌላ በኩልም ሕዝባዊ እመጽ እሰበሰበ እየገነደሰ ድልን በድል ላይ በመቀዳጀቱ መሬትም ለባለቤቷ መመለሷ ግልጽ ነው። ስለዚህም ሁሴን ጅብሪል የሚከተለውን ተናግረው እንደነበር ይወራል።

ወቅትያዋ እሊቃ ትትቀጥን እንደ ድር

እውሩ በመሪ አንኳሳው በምርኩዝ ይላል ምድር ምድር

መኸልቁታ ሁሉ ይላል ምድር ምድር።

ከዚህም በቀር ምድር ቀላድ እንደሚጣልባት መጫኛ እንደሚዘረጋባት፣ ያ! ድካህ፣ ይህ ወሰንህ፣ የሚባልበት ዘመን የሚያልፍ መሆኑን፣ መሬት

ሲወርስ፣ አጥር ሲጥስ፣ ድንበር ሲያፈርስ፣ የነበረው ሁሉና በሰፈ
በመያዝ የሚያጣበው እንደሚቆጭ፣

ሁለት ነጭ አልፎ ሦስተኛ ቲመጣ
ምድር ሰፋሪዋ ቆጣሪዋ መጣ
ሁለት ነጭ አልፎ በሦስተኛው ነጭ
ሜዳ መሬት ያለው እንደምን ይቆጭ

ነበር ያሉት ይባላል፡፡ ጊዜን ጊዜ ሲወልደው ነገሮችም ሂደታቸውን በዛ
ልክ እንደሚያስተካክሉ ግልጽ ነው፡፡ የታሪኩም ሂደት ይኸው ነው
ስለሆነም ነው ምድር ቃጤ ሆኖ ምስኪኑ ገበሬ የሰባውን ለባላባት
ያደነደነውንም ለጭቃ ሹም ሰጥቶ የጉፈየ እንኳ አጥቶ አንጀቱ አሮ ቆሽ
ደብኖ ይኖር የነበረበት ዘመን አልፎ ራሱ አስቦ ለራሱ ስቦ አድልቦ መብላ
የሚጀምርበት ዘመን እንደሚመጣ በዚህም ጊዜ የራሱን መሪ ከመሐ
መርጦ መኖር ሲጀምር መኳንንቱ የድመት ዕውር መሆናቸውን በሊ
አባባል የገበሬ ማኅበራት ተቋቁመው በሹመኛና በመልከኛ ከመጉላላ
ተርፈው እንደሚኖር የተናገሩት፣

ለሰው ይገርመዋል ይህንን ትናገር
ርግቢቱ በራ ገባች ተባላገር
ታልጋ ተወላጆች እየ መደናገር

በሚል ነበር ይላሉ፡፡ እንግዲህ ይህን ንዑስ ክፍል ስናጠቃለው ዘመኑ ጊ
ቀር፣ ሰው ባሽከር ባጀብ የሚታበይ ከትምህርት የራቀ ላባይ ጠንቋ
የታጠቀ እንደ ነበር እናያለን፡፡ ሽሁም ቢሆኑ ስለማለሰባች ሹመት ሽረት ስ
አልኩባይ ቅጥፈትና አጠቃላይ ጉዳዮች ሲናገሩ እናገኛቸዋለን፡፡ ስለዚ
በዚህ ክፍል የተለያዩ ጉዳዮች መጠቃቀሳቸውን ለመገንዘብ ያስችለናል፡፡

## የግጥም ስብስብ በተራ ፊደል

ቋንቋ ከባህል መግለጫ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ እንዲሁም በልዩ ልዩ
ብሔረሰብ ቋንቋዎች ውስጥ ልዩ ልዩ ባህላውያን አነጋገሮች መገኘታቸውም
ሐቅ ነው፡፡ እኒህም በቃል ብቻ በሚገኙበት ጊዜ በጽሑፍ እንዲሰፍሩና
እንዲጠኑ ይደረጋል፡፡

ታዳ በቋንቋ በኩል የሸህ ሁሴን ጅብሪልን የአማርኛግጥም ያየን እንደሆን ልዩ ልዩ የተውህቦ ቃላት እሉበት:: ይኸም ከመስሎቻቸውም ሆነ በአካባቢው ጋር የሚግባቡት መሆኑ ነው:: ይህም በመሆኑ ለሌሎች ግር የሚያሰኙ ቃላት በግጥሙ ውስጥ ይገኛሉ::

የሸህ ሁሴን ጅብሪልም አነጋገር ተወላጅ ለሆኑና በዛ አካባቢ ለሚያንዣብቡ ሁሉ ብርቅና ድንቅ አይሆንም:: ስለዚህ በዚያ ላሉ ውበትና ስሜት መስጠቱ አያጠራጥርም፡

የሸህ ሁሴን ጠቅላላ ግጥሞች ባለመሰብሰባቸው ዓይነታቸው ከዚህ በታች የቀረበው ብቻ ነው ብሎ ለማለት ያዳግታል:: ቢሆንም ለዓይነት ያህል አቅራቤአለሁ ይህንንም ሳደርግ ግጥሙ ከሰው የሚተላለፈው በቃል በመሆኑ የተናገሩ ግጥሞችና ቅኔዎች ሳይረሱና ሳይጠፉ እንዳልቀሩ ለማስገንዘብም ጭምር ነው::

*ተውህቦ የተሰጥዎ ቃል በአንድ ሙያ ላይ የተሠማሩ ሰዎች ሊግባቡት የሚችሉበት ቃል::*

ይህንም ሳደርግ በአብዛኛው የወሎ ክፍል ሆሄ መጉረድና ለውጥ ያለ ቅርጽ ማምጣት የተለመደ መሆኑን ሳልዘነጋ ነው:: በወሎ የሆሄ መጉረድና የአንዳንድ ቅርጽ ለውጦች ጉዳይ የሚከተለው ዓይነት መልክ ይኖረዋል::

ለምሳሌ፣

እህቴ ለሚለው ቃል እቴ

አጼ ዮሐንስ ለሚለው ቃል እጤ ሐዋኒስ

ከገረድ » » ተገረድ

እስኪመስለው » እስቲ መልሰው

ሙሐመድ » ማመድ

ሲጋልብ » ቲጋልብ እና ሌላም ሌላም መጥቀስ ይቻላል::

ኡኡ ለሰበርያ ኡ ኡ ለቀለቴ

አስቀለቀለባት ላይ ታቼን ላመንቴ

እነደጃች መርድ እንደ ደጃች ብሩ

ተሸዋ ገስግሰው ሬጣ ላይ ሰፈሩ
ሁሉንም የሚያዘው ሀብተጊዎርጊስ
ድል አርጐ ይገባል ደሴ ላይ ቲደርስ
እቺ የወርቅ አገልግል እቺ የወርቅ ሙዳይ
ክብልል ኩብልል በይ ሰገሌ ሜዳው ላይ
ተፈሪ ታይጠፋ ታሰ በሕይወቱ
አልጋውን ይወርሳል የጦር ሠራዊቱ

ሀ. ሀርሽ አደባባይ ገና ሲጫወት
ውሴን ጅብሪል ሞተ ሲሉኝ ሰማሁት
ሁለት ነጭ አልፎ ሶስተኛው ቲመጣ
ምድር መስፈሪያዋ መቁጠሪያዋ ወጣ
የጨረፈ መሬት እንዴት በጉድ መጣ
ወንዱ በቦላሌ ሴት ሴቱ በቁምጣ
ያንን ቀን እንጀ ነው ኢማን የሚያወጣ
መሬት አይገባ ሰማይ አይወጣ
ሁለት ነጭ አልፎ በሶስተኛው ነጭ
ሜዳ መሬት ያለው እንደምን ይቆጭ
ሃይማኖት አክባሪ ዳዊትም ደጋሚ
የማታ ጣይ ወጣች ሁለት ዙር ጋሚ
ካሳህ የተሰጠኝ ያመት ዓመት ዕድሜ
ሂዱ ሂዱ የሚል ክፉ ጋኔል ገብቶ
ተው ተው የሚል አንድ ገልጋይ ጠፍቶ

ሚካኤልን አየን ሰገሌ ላይ እንደጨው ታኩቶ
ሀብቱ ዘሙተ እሱ ደንቢያና ፎገራ

የኔ የሆናችሁ እንዳትሄዱ አደራ
ሐሙስ ተሰቅልቆ ዓርብ ተበራየ
ሹመት አይለምንም ማሙድ አሊን ያየ
ሐበሻን ሲገዛ ቲመጣ ልጃችን
እንደወጡ ቀሩ ወታደሮቻችን
ኃይለኛው በኃይሉ ዘውዱን አጠለቀ
እንኳን ተአበሻ ባርባ ዘለቀ
ዓለሟን አግብቶ ጉድ ተንደላቀቀ
በስማንያ አመቷ ሰማንያዋ አለቀ
እኔስ ይገርመኛል ስተኛም ስነቃ
የአበሻ ቆቡ በተፈሪ አበቃ
ዘውዱም ይመለሳል አራት ዓመት ጭቃ /ምርጫን ያመላክታል/
ለ. ለሚካኤል ልጆች ይዣለሁ ትግያ
ልጅስ ተወለደ ተመኩንን ጉያ
ለሰው ይገርመዋል ይህንን ትናገር
ርግቢቱ በራ ገባች ተባላገር
ለጥቂት ቀን ብሎ አልነካም ነጃሳ
ወንዝ ለወንዝ ህጆ እበላለሁ አሳ
ላይሙት ላያህይ ሁሉን ሸኘ ቀዲር
ተመልሶ ገዛት ያበሻን ምድር
ለኔ ማለት ቀርቶ ቲባል ለኛ ለኛ
በባዶ ምስክር በጉራዱ ዳኛ
እባክህ አድነን አታድርሰው ተኛ
ልበል እሸሩሩ ለበለው እቡቡ
ዐርባ ዓመት ይገዛል ብሩን ነው ተልቡ

ልጅም ትወልዳለህ የሚባል እያሉ
እንኳን ለሰውና አይረባም ለነፍሱ
ልጅስ ይወለዳል ተገረድ
ስሙን ማን ልበል ማሙድ
የመዲናን ዲብ የሚንድ

መ. መሬቲቱም አለች እግዜር ይመስገን
ወይት እንደርሳለን ተኩሬብ በርግገን
መች ይቀራልና የታዘዘው ፍርድ
እሾህ ይወጋል ወይ በጫማ ቲኬድ
መድፉ ታይተኮስ ቦንብ ታይፈነዳ
መኪንንቱ ሁሉ እንደበግ ተነዳ
ማነው የሚሸኘው የነገን እንግዳ
የተጠራ ሰው ነው ስንቁን ያሰናዳ
ምን ያስለቅስሻል ከድጃ ልጃችን
ትከተይን አለሽ በስምንት ቀናችን
ምን አለች ታች ደሴ ምን አለች ታች ጢጣ
ምድር ሰፋሪዋ ቆጣሪዋ መጣ
ምድሩን አልብሶት ጀርመንና ካሳ
ዕድሜ ለሰጠው ከዚህ ይበቃል አንድ ማሳ
ምን ይሆንሃል ይኸ ሥራ
ማርከን ሸሸገህ በንሥራ
ፍረደን አላችሁ ምን ልፍረድላችሁ
እኔን የሚታየኝ ያው ድኅነታችሁ
ምድር ተዘርግታ እስክትካተት
እንግዲህ ለትግሬ የሰው ወንድነት

ምጣዱ ተጥዶ እጃ እየተቆላ
ምነው አይጠረጥር መኪንቱ ሀይ
ሞሰቡ ተጥሎ ማዱ ታይነሳ
በአውሳ ዘለቁ ጀርመንና ካሳ

ሰ. ሰማንያው ያልቅና ቲሆን ሳስት ዓመት
ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት
ሰገሌ ሜዳ ላይ የመጣብን መርዶ
በቀኝ እጁ ካራ በግራው ብርንዶ
ሱማሌን ይዘልቃል ማመድ ሲራጅ
ለሰላሙ ላማራው ለሁሉም አይበጅ።
ሰፋ አርገህ ለቅልቃት የርብን ዓውድማ
ይጋጠሙበታል አሥራ ሁለት ኮርማ
ቲሰበር እየነው የጉጃም ተራዳ
ዛሬም ደስ አላቸው የጊላውን እንጃ።
ቲገዛ ቲነዳ ቲመክር ቲያስመክር
ቲያጣላ ሲያዋቃ አንዱን ታንዱ ጋር
ይደርሳል ወቅቱ ሰማንያ ቲሞላ
ወይት ይደርስ ይህን ተፈሪ አባመላ
ስትሠራ እየጊት መቅደላ ራሷን
ጉንጉንመ አይደለ ሹርቤ ቀጭን
ኗሊህ በክብረቱ ፈረንጅ ተግዛቱ
ተመልሶ ኸደ ባምስተኛው ዓመቱ
ራስ ዘናና እግረ ውትርትር
መች እሱ ይሞታል ህልቁን ሳይመትር

ይዛው ትጠፋለች የሐበሻን ምድር
ርብማ እሚሉት የደረሰለት
ህልቁ ይታደላል ብጣሽ ወረቀት
ሮጥ ፎጥ አለ ወታደር ወጣት
በታተነውሳ የተፈሪን ቤት።

ቀ. ቁሜ አላሃምዱ ቁጭ ብዬ አታሂያቱ
ተፈሪን ተፈሪን አለች መሬቲቱ
ቁጭ ብዬ አላሃምድ ቁሜ አተሂያቱ
እንቅፎቅብ እንቅርቅብ አለች መሬቲቱ

በ. ቤሐረርጌ በኩል የወጣች ወጠጤ
እምብዛ እንዳትንቋት ትባላለች አጤ
በመከና በኩል በስተእውሳ ከተማ
ወሎን ወርሶት አየን ትልቁ ጨለማ
በሰማይ በራሪ በምድር ተሽከርካሪ
እኛስ ይመስሉናል የንጉሡ መሪ
በሰማኝ በራራ በምድር ተሽከርካሪ
ውት እንዴት ደረሰ ልጃችን ተፈሪ
በመተማም በኩል እምጤሰው ጢስ
የምትከነክን ናት የምታስነጥስ
እምብዛም አትበጀው ላጤ ሖዋኒስ
የሐወኒስ በቅሉ ብረኪ ብረኪ
ይላሉ ታመጣበሽ የድርቡሽ ግራኪ
መተማ ላይ ወርደሽ እንዳትማርኪ
በትሌቀ ምጣድ ይታመሳል ሕልቅ
አማሽም አይደለም ታማሽም አያልቅ

Scanned with CamScanner

በዘመን ባውንድ በዘመን ሞዴል
አንድ ላይ ይውላል ቁርአንና ፊደል
በእንዲህ ያለው ጊዜ በተመናመነው
እውጣኝ አውጣኝ ብለህ ጌታህን ለምነው
በሽርን እንበለው አበቦ ከበቦ
ዐርባ ዓመት ይገዛል እንደ ብሩ ልቦ
በንባብህ ሳሊህ በነይማም ሩም በሸሪአው ሹም
አባትህን መርቅ አባትህን ርገም
በጉጃም በትግሬ በሸዋ በጉንደር ሳገላ ሳገላ
ሰብርብር አረገኝ የጥቅላ እንዝላ
በሬን ለኮርቻ በትሉን ለቀንበር
እንዲህ ሁኖ ቀረ የኛማ ነገር
በዘንግ ይገቡሉ ተየሩሳሌም ያበሻ ተወላጅ የመሳፍንት ዘር
ንጉሥ የሚሆኑ ባበሻ ምድር
በግሮቹ ጣት ንብተን ባናቱ ብንወጣ
ከትርንጎ ሌላ በሽታዎ ታጣ
ቤታችኛው ደሴ በጠባሲት ኮሶ
ኸደ ያሉት ዕቃ መጣ ተመልሶ
ተወደተ ወዳ ተፈራ አባነፍሶ
በይ አስተዛው ድረስ አላህ ይሁንሽ
ትኩተይኝ እሰሽ በስድስት ወርሽ
በጥቋቁር ጫማ በጥቋቁር ጥላ
ይሄዳል መተማ ይኸዳል ዳንገላ
የኛ የሆናችሁ እንዳትሄዱ እደራ
እኩሉም ሳፈር ነው እኩሉም ሲበላ

ቡላ ያሌ ፈረስ

ራሱ ሰው ሆነ ዛሬስ

ባሽከሮቹ ክፋት ደግሞ ባጋፋሪ

ዘውዱ ቲዞር አየን ወደ ልጅ ተፈሪ

ባባቱ ወልደየስ በናቱ ፋጡማ

ጉቢሳን ዘለቀ ድምጡ ታይሰማ

ባሰጌው ልጅ ሁላ ማዱ ታይነሳ

በአውሳ ዘለቁ ጀርመንና ካሣ

ባለ ቡላ ፈረስ ባላረብ ጉራደ

ሞተ ተቀበረ ያሽበሽ አመደ

ባባቱ ገብረሕይወቱ በናቱ ፋጡማ

ይዘልቃል በጧቱ ጣይ ድምጡ ታይሰማ

ባዳራሹ ገብተህ በልፍኙ ብትወጣ

አንድ ነገር ብትሆን እኔ በጉድ ልውጣ

ይሰጥሃል ጊደር ትተህ እንዳትመጣ

የቀኝህን ትተህ የግራህን ጠጣ

ብረቱን ቀጥቅጠው ይሉታል ማረሻ

መገን ወረኢሉ የጉድ መጨረሻ

- ተሰማዩ በታች ተምድሩ በላይ ላይ መንገድ አበጅተዋል

ተጠንቀቅ አንተ አላህ ወዳንተ መጥተዋል

ተሰደድኸኝም ለወጁ ለወጁ

አገርክን ወሰዳት የመንገሻ ልጁ

ተሰደድከኝማ በውጁ በውጁ

መኩንን አልጋውን አሆረ ለልጁ

ተቦሩ ያነሳ ወረኢሉ ድረስ

ቷሰቀም እየነው ብረትና ልብስ
ቀንገርጋል ፍሬው እንደ ቀንዶ
እስላማላይኩም እያ ሰባት ቀንዶ
ተስማዩ በታች ተምድሩ በላይ
ቲጓዙ አየናቸው ሻሾና አምባላይ
ተመከና እንሰቶ ወረኢሉ ድረስ
ተልክስኮሶ እየነው በቅሉና ፈረስ
ተናግሬአለሁኝ እኔ ለሐበሻ
አንድ እንኳ ታይቀረኝ እስተመጨረሻ።
ተወንዙ ዳር ቆመን የምንጠብቀው
ባህር ሰምጦ ቀረ ይወጣል ያልነው።
ተወዳ የመጡ ባለቁምጣ ሱሪ
ተነጋገራቸው ንጉሡ ተፈሪ
ቀወዳ ተወዲህ ቢመጣ ዘመዱ
አሚያውሰው የለም ተነገው መንገዱ።
ተዚያማ ወዳ እዱኛ ታልቅና ትትሆን ምልፊት
ይበረካከታል የመንደር ሹመት
ጭቆች ይቀራሉ ፊት የነበሩት
ሐበሻን ይመራል ተማሪ አሚሉት።
ተፈሪ ታትሞት ታለች በሕይወት
አገሯን ወሰደው የጦር ሠራዊት፡
ተፈሪና ካሣ ሽዋ ተቀምጠው እየተቃሰሙ
ቀይ ባህርን ተሻግረው እንሻሾ መጡ።
ተፈሪ የሚሏት ትንሿ ወጠጡ
የኗላ የኗላ ትባላላች እጤ

ቲሆን ባንተ አለያ ሰልጅህ
የሰባት ቤት ወሉን አደረግናት በጅህ
ቲጋልብ አየነው በሐመር ፈረስ
ምንም ምን አይሆንም እንደዜ ታይነግስ።
ቲጠነሰስ አየን በትልቅ ጋን ኮሶ
እሲ ቤት ዐበይ ቤት ሶስተኛ ለሻርሶ
ታረርጌ ተነስቶ መተማ ድረስ
ዳንኪራ ይመታል የመስኮብ ፈረስ።
ታረግልኝ እንደሁ አርግልኝ ዘንድሮ
እንደ ፍርድ ቤቱ ምንድነው ቀጠሮ።
ትውልድ ትውልድ አሏት አበበች ሹሜን
እንቅፋት የመታት ግራ ቀኝ እግሯን።
ተነገሠ ወዳ አይውጣ ተቤት
እክል ያገኘዋል አልባሌ መሬት
ና ቢሉህ አትመጣ ቅር ቢሉህ አትቀር
እስላማለይኩም ሰይድ ዐርሂ ኢል።
አሁንም ልናገር ጉዱን ያየሁት
ብረት ይለቀማል እስከ ሶስት ወቅት።
አሁንም ሊመለስ ከተማሪ ዘንድ
[illegible]ርቼ እሄዳለሁ ያየሁትን ጉድ።
[illegible]ቾም ሳይገት እንደተጠበበች
[illegible]ናት ሳሊ አባዙሳ ልጅ ጢስ እያፈለቀች
[illegible]ሰሪ አገር የለው
[illegible]ጫጫረው
[illegible] መዶሻ

ይጠቅመን ይሆን ወይ ለኛ ሲሐበሻ
እየናት መቅደላን ነበር ሲያንገላታት
እኛ እንኳ እንደርስላት እንዳንገላግላት
አሁን እያችሁ ወይ የርብን ሳቢላ
ያላረባችውን ያላሰበችውን ስጋ ስትበላ፡፡
አሰቀስች አለቀሰች የሸዋ ወይዘሮ
የሰባት ቤት ወሎ ዙሩ በሷ ዙሮ፡፡
አላህ ይሶብርሽ የናቱ ልጅ እቱ
እኔስ መሄዴ ነው ወደ ቀሪ ቤቱ
አላህም ይርዳችሁ እናንተም ዱአ አርጉ
ስብሰባ ይበዛል ተሜዳ እስከ ጥጉ
አስላማላይኩም አያሰባት ቀንደ
ሱባህን ረቢክ እንግዲህ ማመደ
አነጋገራቸው እንደ ጓጉንቸር
አገራቸው ወዳ ተባሀሩ ጻር
አስረዳን እባክህ ሣሙኤል በሲር
መሣሪያቸው እንኳ አልቢን ምንሽር፡፡
እንበሳው ታረርጌ ጊደሪቱ ተኛ
ታሰም መንግሥታት ጋር ሆነ ማበርተኛ፡፡
እንዱ በተጠራ መች ይኼዳል እንዱ
ተዘጋጅቶለታል የነገው መንገዱ፡፡
አንድ ዘመን አለ የተልወሰወሰ
ወይ ጠርቶ አላረፈ ወይ አልደፈረሰ፡፡
አንድ ዛፍ ይመጣል ተየሩሳሌም
ሸታው እሚጣፍጥ ቁመተ ረዥም፡፡

የንን ያልተከለ እንጁ·ተ· ይሰድም
እየጉድ መቅደላ፣ እየጉድ ሰንገላት
ሰሥች አሰቁና ዝንጀሮ ወረራት
ጸኛ እንኳ አንደርስላት እንዳንነላግላተ
ኣይተናል አሽከሮች የሚጥበሰበሱ
ከወደ ቤጌምድር ወደ ወረኢሉ።
አዱኒያ ታልቅና ትትቀጥን ተጭራ
አሳሀ ይጠብቀን ተዛንለት መከራ
አባ ሀሩ ሜዳ ሬጣ ሆነ መልካው
ተሰባሰቡበት እካካ መካካው
አዱኒያ ታልቅና የማታ የማታ
ገዚያ ይውላል የማህን ሽመታ ፡፡
አዱኒያ ታልቅና ትትቀጥን እንደ ጭራ
አንድ ላይ ይበላል እስላምና አማራ
አዱኒያ ለማለቅ ትትል ዘንበል ዘንበል
እንድ ላይ ይቀራል ቁርዓንና ፊደል
አዱኒያ ታልቅና ትትቀር እተላዋ
ደጋት ይጠራል ተላይዋ ተላይዋ።
አዱኒያ ታልቅና ትትቀጥን እንደ ድር
መሀሉቃታ ሁሉ ይላል ምድር ምድር።
እንዱኒያ ታላቅና ትቂት ቲቀራት
ሕልቁ ይታደላል ብጣሽ ወረቀት።
እጀብ ተደረሰ ዑርሂኤል ተመጣ
እታመልጥም ጠጣ ተዛፍ ላይ ብትወጣ።
እንዳ ቲመጠጥ እሽቱ ቲቆረጥ



Scanned with CamScanner

እልናገረውም ተሆዶ ይቀመጥ
እሚዳረጉትን አጣጥና ቀረጥ
ኢትዮጵያ አገራችን ራሷን ተሠርታ ተብላ ልክክ
ተቀብታዋለች በሀምበር በምስክ
ትሸታቸዋለች ስሮማ ሰቱርክ
በሰማይ አይሮፕላን በመሬት ላይ ታንክ
እየመጡ ቀሩ እያሉ ልክክ
ኃይለ ሥላሴ ነው ባሏማ በልክ
እኛም ዱአ አርገናል ሥላሴ ይባርክ።
አየር መኪናውም ታንክም የሚሉት
ተሰባብሮ ወድቋል አንዱም አይመክት
እማይሆን እማይሆን እየፈረዳችሁ
እንማን ነበሩ ታሰኙን አላችሁ
እራስ ዘናና እግረ ውትርትር
መቸ እሱ ይሞታል ሕልቁን ሳይመትር
እስቲ ተነስቸ ልሀድ ወደ ማሻ
የኋላ የኋላ ስላማላይኩም ኮምበልሻ
እንዲህ ህዶ ህዶ አዱኛ ትታልቅ
አማሹም አይደክም ታማሹም አያልቅ
እሰጥ አገባ ነበር ሙግታችን
በር በመጣፍ ሰላሳ ዓመታችን
እስቲ እንናገረው ለወጃ ለውጃ
ባባትየው ቢቀር ይገዛዋል ልጃ
እነሱ ባያቱ እኔ ልንገራቸው
ሐርሽ አደባባይ ላይ ሁሴን ጅብሪል ይምጣ ሲሉ ሰማኋቸው

እነ ባሻ ሷሊሀ እነ ይማም ሩም
የሐበሻን መሬት ታይረግጧት አይቀሩም
እነ ይማም ሩም የዘለቁ ለታ
መስጊድ ይተከላል ዋድላና ደላንታ
እናንተ እምታዩት የሉቱን የሉቱን
እኛ የምናየው የስማንያ ዓመቱን
እናንተ ባታቁ እኔ ልንገራችሁ
ትልቅ ሰው ተጠራ ተመሀከላችሁ
እናገረዋለሁ እርጌ በልክ
ሸዋ ላይ ይባላል በተፈሪ እምላክ
እኔም ተናገርኩኝ አላህ ያውቃል መሌ
እስንት ከፈሏት ያበሻን ቀበሌ
እንዲህ ቅሜ ቅሜ ላላወጣ ዘመድ
ማሻ ተፈረደ ለበሽር ማመድ
እንዲህ ያለ ዘመን የዘመን ፍድልድል
እንድ ላይ ይውላል ፊቅዝና ፊደል
እንዲህ ዋዛ ነው ወይ መድረስ እዛ ቦታ
እዛ ጭር ሳይል ሙቅቢል ሳይንገላታ
እንዲህ ብሎ ብሎ ሲደርስ ጊዜያቱ
ይከቡብ የሰም ወይም በጦር ሠራዊቱ
እንዲህ ያለዘመን የዘመን ጉልድምድም
ወንድ ወንድ በቀሚስ ሴት ሴቱ በግልድም
እኔ ታባትየው አሳዘነኝ ልጁ
ታይበላ ተሥጋው ታይጠጣ ተጠጁ
እኛ አንደርስም እንጅ እዛ ለደረሰ

የዐረብ ፈዛይን ሐበሻ ፈሰሰ
እያሱ የሚባል አንድ ልጅ ተወልደ
ያባቶቹን ቀየ አደረገው ባደ
እጥር ቅጥን ያለ አባጣ ጉባጣ
ፈረንጅ አገር ሀዶ ማበር እሚጠጣ
ከምራት መርዝም የገበሬው ጥናት
ርብ ላይ ተጠምዶ ወረኢሉ መፈታት
ከሞፈሩ መርዝም የበሬው ጥናቱ
ሱዳን በር ጠምደው ወረኢሉ መፈታት
ከሞፈሩ መርዝም የበሬው ጥናቱ
ሱዳን በር ጠምደው ወረኢሉ ፈቱ
ከሱዳን የመጣች አንዲት ትንሽ ጋሻ
ቲቃልቧት አየን አሊና ማ"ገሻ
ከሸዋረጋ የሚወለድ ልጅ
እምብዛም አይከፋ እምብዛም አይበጅ
ትንሽ ወደ ኋላ ይቀረዋል እንጅ።
ከወረኢሉ እንስቶ መኪና ድረስ
ሴቷ አራግፈችው በቅሎና ፈረስ
ኩበልል ኩበልል አለች የሸዋ ሙዳይ
እኖም ይሁንልን ነፍጣችን ገዳይ
ወ. ወልይ የፈረደው አይቀርም ዓዋጁ
መንገሻ እንኳን ቢቀር ይገዛዋል ልጁ
ወንጭፉን እምጡልኝ እምበለው ዋነስ
ወረደ ጨጨሆን አጤ ሐዋኒስ
ፊት ፊት እየመሩ አርያና አንኮስ

ሐሩን ጭኖ ጭኖ በብዙ አጋሰስ
ክፈፉ እያለ ነገር ሊሰውስ
ወቅትያዋ እልቃ ትትቀጥን እንደ ክር
እውሩ በመሪ አንካሳው በምርኩዝ ይላል ምድር ምድር
ወይፈኑ ታረርጋ ጊደሪቱ ተኛ
ተወዳ ሰው ጋር ሆነ ማበርተኛ
እመጨረሻው ላይ ሆነ ወሰንተኛ
ወይ ጨርሶ አልጠፋ ወይ አልደፈረሰ
በመሬት አረጀ መሀልቁ ታመሰ
ወዳጀ ወዳጀ ወዳጀ ሊበን
እሰው አገር ሀዶ ከረመ ድልባን

ዐ. ዐረብ በሐበሻ ትደባለቃለች
ደሞ ተመልሳ በሱ ትረጋለች
ዓይን ያለው ያለቅሳል
ዓይን የሌለው ያርሳል
አዲኒያ ልትሞት ጉድጓዷ ይማሳል።
ዓባይ ደፈረሰ ጣናንም ያሙታል
እንዳትከተሉት ሙት ይዞ ይሞታል።

ዘ. ዘመኑን ወራቱን የሚያጫውታችሁ
ውሴን ጅብሪል ኸደ ተመሐከላችሁ።
ዘመኑ ያልቅና አጉል ላይ ቲሆን
ትልቅ ሰው ቶጠልቶ ትንሽ ሰው መሆን።

የ. የሐዋኒስ በቅሉ ጠፍታ በሰሊት
ቀን ወደምኒልክ ትቷድ እየናት
የመጣሁበቱ ተወጣ ሐጀቱ

ዝናቡ ሲጥል ነው ሲሞላ ቁልቴ
አንተም ወደ ሸዋ እኔም ወደ ቤቴ፡፡
የሐበሻ መሬት ምን ያሸብርሻል
ይመጣል ተፈሪ አሁን ያረጋሻል፡፡
የሚያዝያ ጊደርጊስ የግንቦት ልደታ
ይደረጋል አዛን መቅደላና ተንታ፡፡
የእሬ ፈረሶች ሻሾና አምባላይ
ቲመጡ አየናቸው በሰማዩ ላይ
እነሱም እያዩን እኛም እናያቸው
የእሬ ፈረሶች እነ አምባላይ ናቸው፡፡
የዮሐንስ በቅሎ ብረኪ ብረኪ
መተማ ሽመል በር ቁመሽ ተማረኪ
የሰው የሚፈልግ የራሱን የሚያጣ
በካፊር በር ገብቶ በቆቂት በር ወጣ
የሰኔ ሚካኤል የግንቦት ልደታ
ሕልቁ ግብር በላይ መቅደላና ተንታ
የሸዋ ፈረሶች ሐመርና ጉሬ ወዲህ ገሰገሱ
የወረኢሉን ድግስ ቀምሰው ሊመለሱ
የሴቲቱ ንጉሥ ጓዟን ትታነሳ
ይግከሩባታል ተፈሪና ካሣ
የሴቲቱ ንጉሥ በልታ ትትነሳ
የከፎ ብር አሏት ተፈሪና ካሣ
የጀዛ ቀና ናት የደሴ መሬት
አንድ ቤት ይገኛል ዐሥር ዐሥር ሴት
ያላህ መላክተኛ ቶሎ ተቀበላት

ተጠርታ ነው እንጅ ሌላም ተከር የላት
ያላየሀም እየው ያልሰማህም ስማ
ቆቡ ተቀደደ የመምሬ ግርማ
የርብ ጦርነት አሰው ምልክት
ሕልቁ ይታደላል ብጣሽ ወረቀት
የደሴ የሸዋ ሸርሙጣ ራሷን ተፈታች
ትላጫለች እንጅ መች ትሠራዋለች
ያንተ ሞልቶ ተርፎህ የኛን ታየሃት
እንተም ትነሳለህ ታዱኛ መሬት
ያቺን የኛን ወፍቅ አሸግራ ትታይ
ያች ገዴ ተነሳት ተንቁላሏ ላይ
ያቺ ሸዋሬጋ ተሞተችስ አይቀር በሞተች በርጉዷ
በመላው ሐበሻ ታየነዛ መርዟ
ይሉታል ተማሪ ይሉታል እንክላ
ይላሉ በትሣሥ ይላሉ በገና
እኛ እንደርሰበትም እዛ ሸምግልና
የሚካኤል ልጆች ሁላችሁ ባል አልባ
ስህኔ ብቻ ናት ጥቂትም ብትረባ
የተጋጠመሰት ሸልሞና መጣ
እባክህ ጀሲሉ የዛን ቤት ዘር አውጣ
ይዘጋ ታላችሁ መህራባ ይዘጋ
አዳራሹ ባጋም እልፍኙ በቀቃ
ይኸ ማመድ እሊ ያመጣው ነገር
እንገቱ ላይ አየን ጥቋቁሮች ክር

ደ. ደረሱብን እንጅ መች ደረስንባቸው
ቀረቡ ይሉናል የነፍስ አባታቸው
ደሴ ስገሌ ላይ ዐውደማ ልቅላቀ
እሚወቃበትን አለሱ ማን አቀ
ደጋውም ቁንጫ ቆላው ረሞጫ
የሰይድ አሽከሮች አጣን መቀመጫ
ደግሞም ልናገረው ሰው ይበለኝ ጉድ
ሳይንት ልግባና ካማሮቹ ዘንድ
አምባም ጭቅማም ይሠራል መስጊድ
ደግሞ እምናወጋው እስ እዚህ ላይ
ተሱዳን ተነስቶ ለሐበሻ ጠቅላይ
ድርቅ ባለው ጠሐይ በሐሩር በጋው
እኔንስ እምቢ አለኝ እደጃፍ ጭቃው
ድንኳኑን ይተከላል ሱዳን ምድር ላይ
ያሣር መጩሻ ወረኢሉ ነሽ ወይ
ድንኳን ተተከለ ስንዱ ምድር ላይ
ሲሆንም ጭለጋ ሲሆንም ሳይንት ይህ ቢያቅታችሁ
ጓ! ሜዳ መሻገር እንዳያቅታችሁ
ድንኳኑ እሚመስለው የሰማይ ኮከብ
ጥይቱ ይመስላል የጠራራ ንብ
በምሥራቅ ይዘልቃል የሚባል ሞስኮብ
ጀ. ጀበብ ጀበብ አለ ወታደር ፈረስ
ጨንቃት ጠበባት የተፈሪ ነፍስ
ጀሮዬ ከፋ ነው ነገር እያልፈኝ
ትዳሬን እደራ አለችኝ የልፍኝ

ጀንበሩ በጉጃም ጨረቃው በአውሳ
ምድሩን ጋሰበበት ጀርመንና ካሣ
እንዲህ ያለ ምስጢር ይታየኛልሳ
እጠፈው ይበቃል መነጠሩ መንሳ።
ግባ በቀሳጤ ውጣ በቀሳጤ
ተተፈሪ ወዳ አይባልም አጤ
አየ በዛ ዘመን አየ በዛ ወቅት
አየ መበሳቆል አየ መጉዳት
ደሞ የሽረኛው የጦር ሠራዊት
አየ ያች ዘመን አሳህ አይታወቅ የሃይማኖት ሞት
ባንድ አርዶ ይበላል ያለው ሠራዊት
ወይ አማራ አይባል እስላም አይሉት
ጆሮዬ ንቁ ናት የራቁ ትሰማለች
ገ. የተፈሪ አንበሳ የሺ ትወልዳለች
ገና ልቁረጥና ልበል እምባሶሌ
መከራ መጣበት ዘንድሮስ እምባሰሌ
ጊዜ ያነሳውን ጊዜ እስቲመልሰው
ሥጋ ጠጅ አያልም ቡዳ የበላው ሰው
ኦሮሞ ቅቤውን በጌምድር ላሙን ትግሬ ሸማውን
ተጉዣም ማሩን ሸዋ በርኖሱን ተወሎ ገብሱን
ትተሠራ እየኗት መቅደላ ራሷን
ጠ. ጣይ መውጫ ጣይ መግቢያ የገዛው ንጉሥ
ታይቀበር ቀረ አጤ ሐዋኔስ
ጨለማው አግሎ ሲነጋ ሌሊቱ
ሥልጣኑን ይይዛል የጦር ሠራዊቱ

ጩረቃና ጀምበር ርብ ተገናኝተው

ደህና ተለያዩ ሰውን አስፈጅተው

ፈ. ፈረንጅ ፈረንጅ አሰኝ አበሻ መሬቱ

የፈረንጅ ነገር አሰው መመሰሻ

እኔን የቸገረኝ አበሻ ላበሻ

ፊቱን እንዳላየው ዛገ መስታይቱ

ማን በጠረገልኝ እመዱን ተፊቴ /ተፊቴ/

ፍረድልኝ አሉ ምን ልፍረድላቸው

ማጭድ ተወገቡ ምሣር ተክንዳቸው

እኔን የሚታየኝ ያው ድህነታቸው

ዕውቀና የወረኄመና ተወላጅ ሸህ ሁሴን ጆብረል

ትምህርት እንደሌላቸው አሊፍ ባታ እንዳላሉ ገልጸነዋል፡፡ ሆኖም የያዙትን ጸጋ እንዴት እንደተጐናጸፉት ቲናገሩ እንዲህ ነበር ያሉት፡፡

ዋሪዳው መጣና ቆየኝ አሰኝ ዓመት

ጫትክን እየቃቃምክ ታትወሳልት

ደረሳህን ይዘህ ትትጫወት አቤት

እኔም ከሰዋ ገባሁ ቆየሁ አንድ ዓመት፡፡

ዓሰሙን እየሁት ተዳር እስተዳር፣

ንጉሥ እየፈራን ታየጣላን አሸክር፣

ወዲያው በሙ ታቆ ሸዋና ሐረር፣

እኔም በመስታይት ዓይኔን ማባመር፣

ቃሊ ታይዛነፍ ታልደናገር፡፡

አላህ ቲያሳምረው ሰው ዕጣው ቲወጣ

ዓመት አስቀመጠኝ ከከልዋ ታልወጣ፣

ወዳው ምናብ እየሁ አንበሳ ቲመጣ

ኑብር ተጊላየ ጅብ ተፈቱ መጣ
ግመል ተሸክማ የሆነ ባላንጣ፣
ምናቡን አይቶ ለሰው ታላወራ
በሰባተኛው ቀን መጣ አንድ ቀብራራ፣
መሰንቆና ዋሸንት በጁ ይዞ ጭራ፣
እኔው ጋር አደረ ጫት ቲቅም ቲያወራ፣
ማሲቆ እየመታ ቲዘፍን ቲያቅራራ፣
ዶሴ ተሸክሞ መጣ አንድ ቀብራራ
እሳህ ቲያሳድበው ነገሩ ቲሰላ
በስምንተኛው ቀን ጫት ትንቅም ትንበላ
ሑስየ ቡን አፍላ ነገሩ እንዲሰላ፡፡
ስምቀን አደብኩኝ ታትናገር አፈ
የቤቱን ግድግዳ ግንዱን ተደገፈ
ፊቱን እያጠብኩኝ እንዳይመጣ እንቅልፈ
እንዲቀመጡበት ጋቢዩን አንጥፌ
አይገርማችሁም ወይ ታልነገድ ማትረፈ፡፡
ምናቡን ሰፈርነው አንተ ትትናገር
ጠጅና ጉማሬ ጫት ትትቅም እንዲምር
ጀባ ብለንሻል እነሆ በዛሑር
ሐሲድ የሚመታ አንድ እንኳ ሹም ታይቀር፡፡
አሳህ ታደረገኝ የሀልቁ ወዳጅ፣
መሰንቆ እየመታሁ ልወዛወዝ እንጅ
በጭራ በዋሸንት ሰው ባልነካው እጅ፡፡
አውልያ እምጠራበት ዱላው እንዲበጅ
ጫት በጃችን ይዘን ጠጅ እየጠጣን

ጥቁር ጭራ ይዘን ድቢ እየመታን
ሐሲድ እንዳይነካን አውልያ እየጠራን
እምስት ወቅት ሳላት እየስጋገድን
ሰው ያሰነካው ዕጣ ጀሊሉ ሰጠን
መጭውን እየነው ጉድ አጃኢቡን
ዓለም ትትስቅብኝ እኔም ሳኩባት
ታልፋት በተቀር ያሉት በሐያት
ተከትቦ እየዋለሁ ስሙን ወደፊት።
ገና ተሆድ ታለ ታይኸለቅ በፊት
ስሙን ይነግረኛል ወረዳው ቲመጣ
ምንድን እንደሚሆን የዛ የሰው ዕጣ
ምን አስሰፈሰፈን ሊታይ ወደፊት
እንቢ በል ቲሉኝ ነው የምወሻከት።
ሃምሳ ዓመት ትናገር ትሞት ጉድ እያሉ
ትሞት እንዳልሰሙ አሳየንም እሉ
እንደ ፍልፈል አፈር ሰው ቲፈለፍሉ።
እኛም ሰደድናቸው ባፈር እንዲተሉ፣
ቀሪው እንዲፈራኝ ውሸት እንዳይሉ።
ሃምሳ ዓመት ካደመኝ መሐመድ ንኢሳ
መዲና ወረቀት ተጁ ታይነሳ
ይከተሰው ነበር ዋረዳው ቲነሳ
በጉ እፈርጃለሁ ዓለሙ እስትትከሳ
ቃልቾቹም ጠሉኝ ጠጅ ይጠጣል ብለው
ደብተራውም ጠላኝ ሹም ተጠጋው ብለው
ባለዛሩም ጠላኝ ሰው ኸደለት ብሉ

ፍቅራውም ተጠጋኝ ምን ይፈርዳል ብሉ
እኒህን ችየ ነው የሰጠኝ ጀሊሉ
እስቲ ሁላችሁም መጀን መጀን በሉ።
ላላህ ትቸው ነበር በዱኒያ እንዳልፍ
እንግዲህ ዘላለም መሬቱን ይቆፍ
በቅሉ ገላገለኝ ሰው እንዳያልፍ።
በንቂስ ወርቅነህ በነ መምህር ግርማ
በነእሰቃ ውብነህ ነስር ባላገኝ
እኒህ ተዋርደው ነው ንጉሥ የፈራኝ።
ባሰቃ ቀለመወርቅ በነ ይመር አደም
በነ እሰቃ ኢዮብ ባውገረድ አሰማሽ ነስር ባላገኝ
እየሰደድኳቸው እንቅልፍ ቢነሱኝ
ነግሬያቸው ነበር ፊት ታልታመም
አሁንም እየነው አላህ ቲፈርም
አፈሩን በጥብጦ በጥቁር ቀለም
ቃልቻ ይንፈስር እንዳትታመም።
ክፉ ዱካ አለኝ የሚያምር ስሱቱ
አስተውሰው እሚመቱ በሩቅ የማይስቱ
እኔም ሹም አልፈራ ጉድ ታሁበት
እንዲት ጥንብ ሰጠኝ እያውቅ መስሉት
ማነው ያሳሳተው ያገባው እሳት
ሰክሮ ታላወቀ አያስርም ተቤት
ዛፍ ያልተቆረጠ አይወድቅም መሬት
እያሱ አደብ ግዛ እንዳትሳሳት
ቆጥረህ ድረስበት መነን ምንህ ናት

ሚካኤል ተው ቶበት ክፈር አትቀጣ
እንዴት ያለች ሴት ነፍስ ባል አምጣ
ደብቀሃል የሚል ታላቅ ዐዋጅ መጣ
በጥፊ ብትመታው ባፍንጫው ደም ወጣ
ጊዜው ተቃረበ ሩት ልትወጣ።
ምኒልክ ክፉ ነው በስንቱ ፈተነኝ
እንዳለፋት ሾይጣን እሳት ሊያቃጥለኝ
በሰው እጅ አልጠፋ እሳህ ታልገደለኝ
እንኳን ተመምር ፊት ሊቅ አደረገኝ
አፈራው ነበረ በእጁ እንዳይጠልፈኝ።
የምኒልክ ጠንቋይ ዋና ደብተራው
ይሠራው ነበረ ጅኑን እንደሰው
በርበሬ ነበር የሚያቋድሰው
ጅኑን እየላከ ስቱን ሰው ፈጀው
መምሬ ሐዲስ ነው ሰመጀ፡ ፊያው።
የዝህ የጠንቂይህ ፍቅር ይቅርብህ
ላንተ ሥራ አላጣም ይኸው ነገርኩህ
ቢያጣ ኩሱን እያጣም እንዳይጥልብህ
ስታልፍ እንዳትረግጠው ሰው እንዳይርቅህ
ዐሥር ዓመት ብችል ሊያርዱኝ ተሰለፉ
ሰካ ለዚህ ጉሯል እምቢያለኝ እንቅልፉ
የሸዋረጋናት አለቴን ያቃሌ
ሁሴን መጣ ቲሉ ጋትን ያጣጥባሉ
ቂጠማ ጉዝጉዘው አደስ ያቀርባሉ
መጋረጃ ጋርደው ቀጥ ብለው ያድራሉ።

መሞቴንም ሰምተው ልደር ታሉ ቂሱ
ሀሴን ያቃሉ ጣይቱን ያስታውሱ
እደሴ ቡስ ብለው እንዳይወስውሱ
ጠጅ ባፋችን ይዘን ደጁን እንዳይቀምሱ
የረዳው ይሞታል አይወድም መጅልሱ
ቂጭ ብለው ይደሩ ተኛ ጋር መጅልሱ
ነፍስ አባት ተሆኑ መምሬ እኒህ ቂሱ፡፡
ዕድሜውን በሙሉ ተኜ ተተጣላ
ደንዳናው ኢማኑ ይሆናል ነሁላላ
ባዶውን እንዳይቀር ተጭኖ እየሰላ
ቃልቻን ተው በሉት ጠምብቶ እንዳይተሳ፡፡
እባክህ ጌታዬ አታጣላኝ ተሰው
ታይደርሱት ይደርሳል መቸም የተሳሰው
ኢማኑ እንደቁላል ፈርጦ የፈሰሰው
በየደረሰበት ቀልብ እየጠበሰው፡፡
ሸዋ መርዙን ጣዛ መሪውን ታይተካ
ወያኔ አስፈራርቶ ንጉሥ እንዳይተካ
መዝረፍ እንዲመቸው ቦታና ፈረንካ
እንዴት ሰው ባገሩ ደም ሰውሶ ያቡካ
ጥይት እህል ሆኖ ሐሽ ላይ ቦካ
ቦታና መሬቱ ተተወሰደበት ይወርዳል መአት
ያልታሰበ እልቂት የርስ በርስ ጦርነት
በተሰይ አሥመራ ትሆናለች ዱቄት
ሸዋ ጠላት ገዛ ጥይት ደጉሰበት
ብዙ ጉድ እየሁኘ መጅሊስ ተጠርቼ

ቁፍታ ልትመታ ጆስሚንም አይቼ
ጡቷንና ጠጉሯን ቲይዟት አይቸ
ሰው ነገረኛ ነው እሜቱን ፈርቸ
ራቅ ብየ ቆምኩኝ እንዳልነካት በጀ
አልተናገርኩትም ወትም ወትም ህጀ።
ጠጅ ጠጣ እያሉኝ ሲሩን ታያቀው
እኔ ስጠጣሁት ምን ቅናት ያዘው
አላህ ቲያስተው እንጂ ለሰው ብየ አልተው
እነ መምር ግርማ ስሰበላቸው
ምክሩት ቃልቻን ኂላ እንዳይለምደው
አምስት ወቅት ሶላት ስገድ ብንለው
መርቅኛለሁ አለኝ እውት ይኸን ሰው
ሜት ሐራም አድርጉ ዲኑን ሲያጠፋው
ሜቱን እየቃመ ቢሰግድ ምነው
በዲን ዋዛ የለም ትንሽ ቀን ሳየው።
ሶላት ታልሰገደ አብሮኝ እንዳይቅም
ሀድራ ይበላሻል የሰውም ጥቅም
አይሰግድም ተመባል ሞት አይሻልም
አላህም አይሰቀው እስተዘላለም
ነግሬው ታልገባው ይጠይቅ ዓለም።

በዚህ መጽሐፍ ላይ አጤ ዮሐንስ እስላም ይጥፋ ዱር ይገፋ ብለው ወደ ወሎ መዝመታቸው ተጠቅሷል። የታሪክ መጻሕፍትም እንዲህ ሲሉ አስፍረውታል።

“ከቦሩ ሜዳ ጉባኤ በኂላም እስላምና ያልተጠመቀ ሁሉ እንዲጠመቅ የሚያስገድድ ዐዋጅ በ1870 ዓ.ም. አጤ ዮሐንስ አሳውጀው የቦሩ ሜዳን

Scanned with CamScanner

ጀግና አጤ ሐዋንስ የጀግኖች ወንድም
የዛሬን ማርልኝ እንንዲህ አለምድም
በነገረ ሠሪ ሰው አይታረድም
እየደነገጠ ይበትናል ወይትም
እንዲህ ተሆነማ አንድ ሰው አይተርፍም።
ዓባይ በጣና ላይ መኸዱ ለምነው
ትንሹ ቲያጠፋ ትልቁ ቲችል ነው
ቢከፋም ቢበጅም እያዩ ማለፍ ነው
ተምክሮ በስተቀር በቀረ ከንቱ ነው።
ማረዱ ከንቱ እንጂ ጀግንነት አያጣም
እስላም የሚያርድ እንጂ የሚወድ አይመጣም
የፈራህ ሰው ግፋ አኔ መልስ አላም
ይዘገያል እንጂ ሰው የጁን አያጣም
መተማ ተኸደ ተመልሶ አይመጣም።

ሸህ ሁሴን ጅብሪል በመዘታተናችን ግር ቅጠሉ አልቅሶልናል። በመሞታችን ሁሉ አንብቶልናል። በቤታችንም ላይ የታሪክ ጠባሳ አርፎበታል። የሽማግሌ ወቀሳም አስነስቶበታል። በትዝብትም አስመልክቶታ፣ አባባል ከማስተሳለፋቸውም በላይ እንጀታችን ጭስ ሰዎችን አልቅሶ የማይቀር መሆኑን፣ ደማችን በደም ይመሰሳል።

አጤ ዮሐንስ መተማ ይወርዳሉ ግን አይመለሱም ያሉት ሀረፍተ ነገር አሳክተው ስንኝ ቋጥረው ነበር ሲነበብም እንዲህ ይላል።

እንትም ዕድሜህ አጭር ወይ ፍሬህ አይገዛ
ጉርፍ ደርሶ አይወስድህ አለቅጥ ታልበዛ
እንጨት ተደረቀ ቢቀቡት አይወዛ
ሐበሻ ክፉ ነው አይምሰልህ ዋዛ
መተማ እስቲጠራህ በብልት ግዛ።

እነግርህ ነበር መች እሽ ትላለህ
እሳብህ ብዙ ነው መንገድ ታስባለህ
መተማ ስመዝመት መሽድ ትኸዳለህ
መመለስከን እንጃ እዛው ትቀራለህ
በደርቡሽ ጕራዴ ራስክን ታጣለህ
በደም አጨማልቃ የምትቆራርስ
ራስ የምትቆርጥ ያውም የንጉሥ
እንደዜ ተመታች የማታላውስ
አንድ ዓመት ቲቀረው ምኒልክ ሊነግሥ
እሳህ መተማ ላይ ይስላል መቀስ
በመተማ በኩል ትጨሳለች ጢስ
እጅግም አትበጀው ላጤ ሑዋንስ
እሳህ ሽቶበታል እንገቱን ሊቀምስ
እሷም በራስ ገብታ የምታስነጥስ፡፡
ብለው ተሳደቡ ደብተራና ቄስ
ሀጅ ልናገረው ላጤ ሑዋንስ
ፈረጅለት ነበር መቅደላ ቲፈርስ
እንዴት የነቢ አሽከር ይሆናል ርኩስ
የሰማም ስምቶኛል ያልሰማም ያልቅስ
መቸ እኔ እፈራለሁ ደብተራና ቄስ
መተማ ታልኸደ እኔም ጫት አልቀምስ
ጦሩን አስከትቶ መተማ ቲደርስ
ከበቅሉ ወረደ አጤ ሑዋንስ
የጦሩን መከታ ጋሻውን ሊለብስ
እሱ ራሱን ሰጥቶ ሰውን ሊያስጨርስ

ቢጠሩት አይድንም ጥፋ ያሰው ነፍስ።
እንዴት በጉራዴ ሞት ይመኛል ሰው
መተማ አትድ ብየ ምነው ብነግረው
መች ይመለሳል ያዘዘበት ሰው
ደሙ እየሸተተው ሞት እየጠራው
እንደምን ሳንገቱ አያስብም ሰው።
ፈረሱን መጭ ብሎ ድርቡሽም ዘለቀ
ከሊፋና ዑመር ደባጢን ዘለቀ
ተዛም ተዛም ብለው ተደበላለቁ
ሑዋንስ ተነጭፍራው ፈርተው ተጨነቁ
የሚያስታርቅ ጠፍቶ ሰዎች ሁሉ አለቁ።
ያህያ ልጅ በቅሉ በወርቅ ተሸልማ
ሑዋንስን ይዛ ወረደች መተማ
ተጌታዋ ራስ በቁም ልትቀማ
ስንቱን ሰው ፈረጀው ደጉ አገር መተማ።
ስንቱን እርዶት ነበር እስላም እንዳይለማ
ምኒልክ ደስ አለው ምጡን ቲፈረጅ
እኔም ሜት በመቃም ነጃ ወጣሁ እንጅ
እስላምን የሚወድ ወደፊት ይምጣ እጅ
ሑዋንስ ክፉ ነው የሰውም ወዳጅ
መተማ ደጉ አገር ገላገለን እንጅ
አላህ ገላገለን ከዚሑር መከራ
እንግዲህ ምኒልክ አይዞህ በል አትፍራ
ሑዋንስ ሲኸድ ነው ጦሩን እየመራ
ማረድ የለመደ መቸም ሞት አይፈራ

ሞቱም ብላሽ ሆነ እንዲህ ቲንጠራራ፡፡
አንተም ጨካኝ ነበርክ ጨካኝ ወረደብህ
እንደ ፍሪዳ ላይ በቁምህ አረዱህ
በቅሉህን ጊጊ ጋር በቁምህ ማኩህ
ራስህን ቁንጣ አርገው ሥዕል አደረጉህ
አላህምዱላሂ ለዚህ ላበቃህ
ሐዋንስ ራስክን በችካል መቆምህ
አላሉ አግዳሚው እስኪተፋብህ
ሰው የጅን አያጣም እንዲህ አረጉህ
የወሎን መሻኬህ እንዳላረድክ ሰቅሰህ፡፡
አባቱ መተማ ሸዶ አፈር ሲቅምስ
ልጁ ጊላ ቀረ መስሎት የሚነግሥ፡፡
እንኳን የወንድም ልጅ እሱውም አይነግሥ
አጻል ተፈርጂል ምኒልክ ሲነግሥ
አሰቦ ነበር ለሁሉት ሲነግሥ፡፡
ቴዎድሮስ ለጋስ ነው ቸርነት አያጣም
ማንም ያምኑዋል ያሳዝናል በጣም
ለሰላም ደህና ነው እስላምም አይጉዳም
ራሻ ይላል እንጂ እስላም ዘር አያጣም
ሐዋንስ ክፉ ነው የበላ አይወድም
የሰው ያየ ጊዜ ያረጋል ጉርድምድም
ሆዱም አላማ ነው ያየውን አይሰድም
ማረድም ሰብቻው ሰው አያስቀርም
ለጦር ግን ጀግና ነው ቢሄድ አይታክትም፡፡

ከዚህ በላይ በሸህ ሁሴን ጅብሪል የተባለውን ከታሪክ ማኅደር ጋር

ስናስተያየው "ከሬሳው ላይ ያጤ ዮሐንስን ጭንቅላት ቆርጠው ለከሊፋ አብዱላሂ የምሥራች ብለው ላኩለት። ከሦስት ቀን በኋላ የአጤ ዮሐንስ ጭንቅላት በእንጨት ላይ ተሰክቶ በግመል ጀርባ ላይና በሰው ሸክም እየሆነ ገበያ ለገበያና መንደር ለመንደር እየዞረ ለሕዝብ ሲታይ ከረመ።" ሲል እናገኘዋለን።

የሸህ ሁሴን ጅብሪል አባባል ከታሪክ መጻሕፍት ጋር መሳ ለመሳ በመኸዱ እጡብ ድንቅ ያሰኛል። ለምሳሌ ከብዙዎቹ ስለ አጤ ዮሐንስ ከተጻፉት መጻሕፍት ባንዱ ላይ፣

"በዚያ ጦርነት ድርቡሾች ስምንት ሺ ያህል ሰዎች ማረኩ። ጐንደር ከተማ ገብተውም አርባ ሰባት አብያተ ክርስቲያኖች አቃጠሉ። ወደ ጐንደር በሚጉዙበት ጊዜም ሁለት መቶ ያህል ቤተ ክርስቲያን አቃጥለዋል።" የሚለውን ከሚቀጥለው የሸህ ሁሴን ጅብሪል ቃል ጋር ስናያይዘው እውነታነቱን ያጐላልና። አጃኢብም ያሰኛል። ለማንኛውም ስለመተማው ጦርነት እንዲህ ነበር ያሉት።

> እጠቷቆራቸው ከሰል ይመስላሉ
> ተመህልቁ ተሰው በጣም ይጠቁራሉ
> መተማ ድል አርገው ጐንደር ይገባሉ
> ደቀዛና ጋይንት ብዙ ሰው ያርዳሉ
> ተሺ ታቦት በላይ በሳት ያነዳሉ።
> መረድ ተጀመሩ ደንቢያና ፎገራ
> ምን ይበጀው ይሆን የጐንደር አማራ
> ልይተህ የማታቀው መጣብህ መከራ
> ብዙ ሰው ይሞታል ታልሰለመ አማራ
> ይሰበልበዋል ያርደዋል በካራ
> ወደ ሱዳን አገር ዋረዳው ታመራ
> ደፈረኝ ታላሉ ሳይንቀችን ልጥራ
> አሁን ድረሱልኝ ያዙልኝ ደብተራ

ወትሮም የመሄድ ዘር ከሰላቸው አይፍራ
ገላገላችሁኝ አልቅሽ ብጣራ።
ብደፍራችሁ ዕድ ዝም ብል ችግር
ዋሪዳው መጣና አሰኘ ተናገር
እንግሊዝ ተሱዳን ተሰቀቀ አገር
ይዘገያል እንጂ ኋላ አለ ነገር
ሱዳን ብሉ ማለት ተፍሲህ ሽንቅላ
ዘራቸው ልዩ ነው ናቸው ያለህ በላ
ተላቸው ታልሆነ አያገቡም ሌላ
ወዳጅ ይወዳሉ ሐራምም አይጠላ
ሰባት ቋንቋ አላቸው ሁሉም በጠቅላላ።
ድርቡሽና ሱዳን መልካቸው ጥቁር ነው
መልካቸው አንድ ቢሆን ቋንቋው አየቅል ነው
ተዘር ፍጥረታቸው ዘራቸው ልዩ ነው
በሢሒር ቲጠራ ስማቸው እስላም ነው
ቸርነት አይጡም እጃቸው ሲጋስ ነው።
የሱዳንን ነገር ስንቱን ላውጋላቸው
ተኛም ሰው አይጠፋ ነጭ ያስተማራቸው
ደርቡሽ ጥሩ እስላም ነው ልባቸው የጠራ
ሶላትን አይተውም ቢበዛበት ሥራ
ችግርም ቢገጥመው ይችላል መከራ
አገራቸው ሜዳ የሌለው ተራራ
ልብሳቸው ቀሚስ ነው ዳኢም ታጥቀው ካራ።
ተኔ ተመርቀው ሴት ልጅ ተወለዱ
ለጉግሣ ይዳሩት እንዳትዛመዱ
ሌላም አያገባት ፈርዷታል ዘመዱ

እንግዲህ እሜቴ ሜት ቃሚን ውደዱ
አሁን ነው መሸማት ደጉቹ ታይሄዱ።
የወንዱስ መላ እልቋል የሴቱን ያብጀው
ሰንቡል እያጤሰች ባልጋ ገሰጠችው።

ወሎ ሰብኮ የማሳመን ተናግሮ የማሰባሰብ ኃይል አለው። ወሎየ ጉበዝ አራሽ ነው። መልካምም አሳቢ ነው። ማኛ ከሠርገኛ ደጋሊት ከዘንጋዳ ማፍራቱን ለዘመናት አስመስክሯል። ዘሀር ዙሮበት ወዳጅና ጊዜም ዘንበል ብሎበት ተርቧልም፤ ተሰዷልም። ታዳ ያም ቢሆን ምናስ ወሎ ተብሎለት ነበር። አሁንም ምናስ ወሎ ተሚያሰኙት አንዱ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ናቸው። እንዲህ ካሰኙበትም አንዲ አጤ ምኒልክ ንጉሥ ሚካኤልን ያን ጠንቋይህን ላክልኝ ብለው ባሉበት ጊዜ ዐዋቂነታቸውን ያስመሰከሩበትን በመጽሐፉ ገልጸነዋል። እንዳው ለማዘከር ያህል ሙሐመድ አሊንም ምኒልክንም ካሏቸው ይቺን እንበል።

በእልፍኙ ገብተህ ባዳራሹ ውጣ
እንዲያም እንዲያም ብለህ ሸዋሬጋን አምጣ
የተጋዘከ እንደሆን እኔ በጉድ ልውጣ
እኔ ፈርጃለሁ ሌላ እንዳታመጣ
ወንድ ትወልዳለች ግን የለውም ዕጣ።
በግርጌህ ገብቸ በራስህ ብወጣ
ተትርንጉ በቀር ሌላ ነገር ታጣ
ይህ ያልሆነ እንደሆነ እኔ በጉድ ልውጣ
ሆድህን የሚገልጥ ሸማግሌ ይምጣ
ይህንን ጉድ ታላይ ተቤትም አልወጣ
ተው አንተ ሙቀጫ በኔ አትሰወጥ
ጌሾና ቡናውን ውጣና ቀጥቅጥ
በሽታም እንደሆንክ ፈንድተህ ፍረጥ።

ማንን ታምኛለህ እኔ እስወድ ላግጣ
እኔ እሳት አልገባም ነግሬንሃል ቁርጣ
መሠድስ አይወድም ተጳጳስ ተቁስ
ግን አቤ ምኒልክ እንዲለው ደስ ደስ
ሰው ዘብሎ ያድራል እንኳን ሊደግስ
በርባ ጊዜ መጣሁ የልብህ ይድረስ
ፈትም ዱአ አርገናል አንተ እንድትነግሥ
ፊትህ ደህና ቢሆንብትወድ መጅልስ
ገርፊህ ባትሰቅል እንደ ሉዋንስ
ስንት አስላም ወደደህ ስንቱን አለው ደስ።
ጉጃም ተክለሃይማኖት ጉንደር ራስ ተሰማ
እንራስ አላላ አባ ጅፋር ጅማ
ሐረር ራስ መኮንን ዘራችሁ የገማ
እኔ ተናገርኩኝ ያልሰማህም ስማ
ትጉማ ዘር በቀር የለም የሚስማማ።
መች ባንተ ይሆናል ምኒልክ ንጉሡ
አንተ አስበህ ነበር ልትሰጠው ለያሱ
እንኩን ሊነግሥና ይያዛል ለነፍሱ
በራስ መኮንን ልጅ ትጠፋለች ነፍሱ
ተጌታ ተፈርዷል ዘውዲቱ ሊነግሡ
ምኒልክ አሥመራን ለነጭ ተሸጡት
ይዘገያል እንጂ ይመጣል ፍጅት
ስንቱ ይማረራል ተ ወንድም ተሴት
ሸዋ የዛን ጊዜ የለውም ረፍት
ቀኘሎ ይነዳል በጀርባው እሳት

እንኳን ለያሱና ታይታይ አባቱ
ምን ብለናት ነበር ትመሰክር እናቱ
እስቲታሙም ድረስ ጒላም በማሚቱ
ትዝ አይላችሁም በጫት ተመልከቱ
ክፉ ዱአ አለኝ የሚያምር ስለቱ።
ባህር ወዳ ማዶ ዘር መጣ ለጥቅም
ግድግዳው ያማረ ቢሸጡት የሚጥም
ቅጠሉ ለስላሳ ቁመቱ ረዥም
እሱን ያልተከለ እንዴት ይለድም
ሸዋ ታልተከለ እሰሉ አይቆምም።
ያጤ ምኒልክ ዘር ማት ወረደባቸው
የቤታቸው አሽከር እንደ ጤፍ ዘራቸው
ጠንካራ ሰው ጠፍቶ ምች አደረታቸው
ቀብሩ እንዳይታወቅ ሰው እንዳይቀብራቸው
እያሱ እንኳ እንዳይተርፍ በቅናት ፈጃቸው።

አጤ ምኒልክ ከወሎ ጋር በጋብቻ መተሳሰራቸው፣ ወዲህም የሚያምጸውን ለማርገብ ወዲያውም የዛጉየን ሥርወ መንግሥት የትልቁንና የትንሹን ራስ አሊ የዘር ግንድ በመፈለግም ነው። በመሆኑም ሴት ልጃቸውን ወ/ሮ ሸዋረጋን ለንጉሥ ሚካኤል ሲድሩ፣ አጤም የጁየዋን ጣይቱ ብጡል አገቡ። ራስ መኮንንም ከወረኢሉ ባላበት ከተወለዱት የሺ እመቤት አሊ ጋር አጋቡ። ወሎን በዎ ጥልቀት በሥጋ ውህደት ሙጥኝ አሉት።

ንጉሥ ሚካኤል ከሸዋረጋ ኢያሱ ሚካኤልን ወለዱ። ራስ መኮንንም ከወሎየዋ የሺእመቤት አሊ ተፈሪ መኮንንን አገኙ። ተፈሪ መኮንንም ከአምባሰሌዋ ስሂን ሚካኤል የተወለዱትን መነን አስፋውን አገቡ። ዝርያ አፈሩ። ሁሉም በወሎየ ወሎየነትን አተረፉ። እልጋውን ዘውዱን አጠኑ። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ተወሎየ ተጋብቷል። ሥልጣን ተጋርቷል። ወሎ

የሁሉ ነገር ምንጭ ይሏል እንዲህ ነው። ታዳ ሸህ ሁሴን ጅብሪል የዚህን ሁሉ መገናኘት፣ መውደቅና መነሳት ልቅም አርገው ተናግረውታል። ስለ ተፈሪ መኮንን ቀደም ሲል ታሉት ሌላ ይችንም ብለው ነበር።

ምኒልክ ዘሩ ከልቆ መነን ትተርፋለች
ተፈሪን አግብታ ጥቂት ትወልዳለች
የባሏን መከራ ታታይ ትሞታለች
ሐበሻ የሆን ቀን ትነፈልላለች።
መነን ልትሞት ሦስት ዓመት ቲቀር
ሸዋ በተለየ ይሆናል ሽብር
አሊጋውን ለመያዝ ግፊ እስ ወታደር
መቶ ይዘጋጃል ያለበት ነገር /1953 ዓ.ም./
እጃቸው ይያዛል አይገኝም ኸደር።
ተፈሪ መኮንን እሥመሬ እጁን ሲዶ
ትግሬን በበቅሎ አደረገው ባዶ
ተፈሪ መኮንን አሊጋው ደህና ታስ እሸክር ታይለፍርበት
ልጆቹን በተራ እንዲት በማረበት
ሕልቁ ታይደንግጥ ቀን ታይጨልምበት
አበሻ በመላ ምክር ታይመክርበት
ተፈሪ ክፉ ነው ልቡም አይገኝ
ለሰው ይመስለዋል ይናገራል ቀኝ
ኋላ እንዲህ ሊዋረድ ፍጻሙን ሊያገኝ።
እሳት ሰደደበት ዳግሚያ እንዳይገኝ
ዘላለም እማይበርድ በደም የሚቀኝ።
ትግሣና ራስ ወሌ አጤ ሎቅንስ
ሚካኤል ምኒልክ አጤ ቴዎድሮስ

ዘውዲቱ ናት ፈራጅ ተፈሪ ቲነግሥ
በብልሃት ግዛው አልጋው እንዳይፈርስ
መጨረሻው ከፍቶ ጣሉት እንደ ርኩስ።
የትግሬ መከራ የወሎ ችግር
የሚበላው አጥቶ ሕልቁ ቲሸበር
ሐበሻ የዛን ቀን የለውም ቀድር /ቁራር/
ውሸቱ እንዳይመስልህ በወሬ እሚቀር
ያቺን ቀን ያስፈ የለውም ችግር።
ወሎ በራብ አልቆ ሞት የዛ እንደሆን
ተፈሪ የዛን ቀን ምን ይውጠው ይሆን?
የጃን ነው የሚያገኝ የዛን ቀን ሰው አይሆን።
ተፈሪ መኮንን የተያዘ እንደሆን
እንግዲህ አበሻ ምን ይበጀው ይሆን?!
እህል ያልገዛ ሰው ወት ይገባ ይሆን?
አሥመራና ሸዋ ይሆናል እንዳይሆን
ወያኔ ተነስቶ አሥመራ እሳት ቲሆን።
ኦሮሞና* ውራጌ የሸዋ ሙንኪር
ሴት እንቅልፍ የላቸው ቀኑም በነገር
ሸዋን ያመልኩታል አንድ እንኳን ታይቀር
ድንጋዩን በድንጋይ አርገው ንብርብር
አጃኢቡን ታላይ መሬት ቲሆን ብር።
ታሰፋት ይሻላል ተብሎ ነው እንጅ
ተፈሪ መኮንን ለሌላም አይበጅ
እኩሉን ቲያስለቅስ እኩሉን ሊያበጅ

*በዛን ዘመን ጋላ የሚባለው በአሁኑ ወቅት ኦሮሞ ስለተባለ በዚህ ተስተካክሏል

እምሳ ዓመት ይገዛል ሰው የለውም እንጅ
እንደ ቆላል ገምቶ ጠፋ በሰው እጅ።
ተፈሪ መኮንን ትልቁ ልጃቸው
አልጋውን ለመያዝ ያሰባል ልባቸው
የጊላ የጊላ ሐቲማም የላቸው
ሸዋ ክፉ ሰው ነው ተሥር ነቀላቸው
ዳግሚያ እንዳይነሱ ተነልጅ ልጃቸው።
ያላህን ትተው በውሸት የሚመሩ
ቁመታቸው አጭር መልካቸው የሚያምሩ
በሐበሻ መሬት ግፍን የሚሠሩ
አይነግሱም ብላችሁ አትጠራጠሩ
እምሳ ዓመት ይነግሳል አግሬ ውትርትሩ
በ1967 ዓ.ም. ወታደሩ ወርቅ የሚዘንብለት ወጣት
ጉልማሳው ተሰማይ መና የሚወርድለት ሳያሠሬ የሚያፍስበት።
ተበረንዳ ወደ ቪላ የሚሰውጥለት መስሎት ሆ! ብሎ ነበር። እልል በቅምጤ ተብሎ ነበረ። ጊላ እንዲህ ሰማይ ሲቧጥጥ። ሁሉም እንዲህ እንደ እሮጌ ዝሃ ጨርቅ ተበጣጥሶ ሲያልቅ። ይህ እንደሚመጣም ሸህ ሁሴን ጅብሪል ፈደል አጋጭተው ሰንኝ ቋጥረው የሚከተለውን ነበር ያሉት።
አልጋው በወደቀ በሁለት ዓመት
ፈንጠር ፈንጠር ይላል አይሆንም መስሎት
ማሰቁን ታያውው በራብ በጥማት
ጌታውን ይከዳል በታና መሬት
ሐብታም የዛን ጊዜ ይወድቃል ድንገት
ባሪያ ሁር ሆኖ ተሆነ ፈረጅ
ገልጋዩ ማን ይሆን እሰበሱ ቲፋጅ

የድህነት ወቅቷ ቴታወጅ ባዋጅ
ተፈሪዋን ጥላ ጅቡ በቀለ እንቶ
ታህመድ ኒጋሽ አገር እንድ ሰው ተወልዶ
ሸዋ አልጋው ቢናወጥ ኸደ ባህር ማዶ::
መኸዱም ተግር ነው ቢያገኝም አየኑዳ
ሐበሻ ጉድ አየ እንበሳ እባብ ወልዷ::
ቀድሞ በዘሟታም በሁሽት መማል
አቤት ቲሳሳቁ ተሴት ጋር መዋል
ዲኑን ሰማጥፋት ነው የያዙት ትግል::
እሱ ጠጋ ይሳል ባሷ ወጣ ቴል /የቀበሌ ካድሬ/
የሐሳሱን ዕቃ ገብቶ ሲያማስል::
ምክሬን ስምተህ ያዘው የመንደር ጡርጋጥ
መጩን አይተነዋል እንዳትደናገጥ
ሴት ታስበቃሃለች ቀሚሷን ታትገልጥ
እንደ ፍየል ቅሉቱም መንኒውን ትትመጥ::
ተፈሪዋ አውርዶ ተፈሪ ተገዛ
ሰጥቂት ቀን እንጂ እጅግም አይበዛ
ሸሪክ ተጠንቀቀው አይምሰልህ ዋዛ
በብላት ታልሆነ በጉልበት አይገዛ
ሁሉ ግን ሟች ናቸው ነገሩ ተበዛ::
መሣፍንት ተሞተ በሸዋ መዲህ
ችጋር ይፈጠራል አገርም አይቀና
ሐበሻ የዛን ቀን አያኝም ጤና
መለፍለፍ ነው እንጂ ዐዋጁም አይጠና
በላው ቅሉ አይበርድም ተቀብቷልና።

ተዳፍና ትትኖር ያሥመራ እሳት
ማንም እንዳይጭራት ውሃ ቲያጠፋት /ቀይ ኮከብን ይመስከታል/
በግድ እነደዳት የሸዋ ቅርጣት
ኋላ ግን ያራሱ እንደሳት ራት
ሸዋ ጦሯን ሰዳ እጣች ብልሃት፡፡
ተፈሪ መኰንን እንዴት ያለ ሰው ነበር
መረታቱን ቲያውቀው እርቅ ይወድ ነበር፡፡
ተወደቀ ይውደቅ ብሎ ሲደናገር
ምን ይበጀው ይሆን ከተማ ባሳገር
ዲኑን እያጠፋ ዘመድህ ቲታሰር
መሸነፉን ቲያውቀው ጀግና እርቅ ይወዳል
እርቁን እምቢ ታለ እጅ እግሩ ይነዳል
ሰው ያሳየው ውርደት ኋላ ይዋረዳል
ፍቹን ድርስበት ኋላ ይሻሰሃል፡፡
በተፈሪ ይብቃ ማት ይወርድብሃል፡፡

ተ ሱማሌም ጋር ውጊያ መኖሩን ሰው መቸገሩን የሀገራችንን መዳከምም ያሱበት ቃል እንዲህ የሚል ነው፡፡

መውሰድ መልካም ነበር ሸዋ ጥሩ ወልዶ
እንዲህ ወደኋላ ሃገር ሆነ ባደ
እስኮላ ግባ አለ ኋላ እንዲህ ሲነድ
ልጅን መቅጣት ነበር ብልግና ታይለምድ
ምን ይነወራሉ ሰውን ቢያዋርዱ
ያማራ የስላሙን መብላት ተለመዱ
ሐበሻ ሳም ሆና ታሥራ ተታሰበች

ጡቷ መዝገር ሆኖ ጥጃዋን ገደለች::
ላሟም ትሞታለች እየመነመነች
ወተት ቢሉ አይገኝ እንደዜ ሞታለች
ይዘገያል እንጅ ጊኣ ትድናለች::
የሐበሻ መሬት ለት ቀን ቲጨልም
ሐረር ወዳ ማዶ ይፈሳል ብዙ ደም
ቂሙም አይረሳ እስተዛላለም
መንገድ ይፈልጋል ሐበሻን ሊለቅም
ተስንቱ ጋር ይሆን አበሻ እምትገጥም
ቋንቋቸው ተብታባ ዲናቸው እስላም
አገራቸው ቆላ ልብሳቸው ግልድም
ጦራቸው እጥፍ ነው አፈር የሚያስቅም
እኒህ ለሐበሻ መርዝ ናቸው ስም
ተነዚህ መጣላት የለውም ጥቅም::
ስንት ሐጃኢብ ያያል በዱኒያ ለቆየ
እኛ ባንደርስበት የልጅ ልጅ ብዙ አየ
ጥበብ እንዳይሰምድ አሻቅቦ እያየ
የነጮች ሥራ ብልግና ገበየ
አባቱም ገዛም እስ ፈረንጆቹን እየ::

በወሎ ጫት የሚቅሙት የበቁ ኢልም የደቀቁ አለያም ዱበርቲዎች ሸሆች ናቸው:: የሚቅሙትም ስብስብ ብለው ጭር ባለ ለሊት ወይም ቀን የታመመን አሽረልን፣ የወደቀን አንሳልን፣ የተጣላን አስታርቅልን፣ የተጋደለን ደም አድርቅልን ለማለት ነው:: ዝናብ ሲታጣም ለመለማመን፣ ሁከት ሲበዛም ለማብረድ፣ አገሩን እማን ገበያውንም ጥጋብ አርግልን ልመና፣ የወጣም እንዲገባ፣ የከሰረም እንዲያገኝ፣ የተዘራም እንዲያፈራ:: ታደ በነዛ በደጋጉቹ ጊዜ ይኸ ሁሉ የሚደረገው አቅልን ሰብስቦ ጅስምን ሰደድ ተደርጐ ነበር::

ይህን ጊዜ ነበር ከራማ የሚቀርበው፣ ርዝቅም የሚወርደው፣ የተመኙትም የሚደርሰው:: ዛሬ ግን ውሪው እንደ ፍየል ሲቀነጥበው መንገደኛው እንደ ከብት ሲያመስካው ጊዜ ረከሰ:: አልይዝ አሉ:: ቀዲሞቹማ ያሉበትን ዘመን አልፈው የሴላው እስኪታያቸው ድረስ ነበር::

"መቃም ነው ማስቃም ነው መስሎ ጥቁር ማቅ የሚመጣው ዘመን ቁርጡ እስኪታወቅ" የሚሉት:: ታዳ ምን ይሆናል ዛሬ ሁሉም ቅጠል በላ ሆነ:: ነገሩም አላምር አለ:: እንዲህ እንደሚሆን ገና ከሩቁ ሸህ ሁሴን ጅብሪል ብለው ነበር::

የሳዱቶች ቀሰብ ቀምበጥ ታትረክስ
አላፊው ታይቅማት ታትበሰብስ
ትባሆ ታያጥናት ተሸጣ ታትረክስ
ተው አታበላሽት እየቃምክ አታልቅስ
አላህ እንዲያሰብስህ ሸማና ቀሚስ /ኩመት/ ጫንክ
ለሲት ጫትን መትፋት መቃሙን ይተው
መብራት አጥፋ እያሉ ሰው እንዲያየው
እኔ ዝም አልልም ጫትን ቲያራክሰው
እንኳን አላህ ጠልቶት ደስ አይልም ለሰው::
ይሰማኝ እንደሆን ፍቅርን ልምከረው
ለሴት ጫትን መትፋት መቃሙን ይተው

ሸህ ሁሴን ጅብሪል ስለ ንጉሥ ስለ እረኛው፣ ስለመንገድ ሠሪው ስለ ሉቸው /መብራት/ ስለ ፈረንጁ ስለ ፋብሪካው ተናግረው አልፈዋል ያየም አይቷል:: በመጣፍም አንብቧል:: ሰኛም ትምርት በመሆኑ ለአጃኢቡ ከታትበንዋል:: የሚቀራ ይቅራው:: ታዳ የባሕር ማዶ ሰዎች ያመጡት ጅልም ይሁን ጥሩ እንዲህ ነበር ያሉት::

ሥራቸው ባለጌ አህያ እሚበሉ
ባሕር ወዳ ማዶ ከፉ ሰዎች አሉ
አበሻን ሳመውረስ አሳብ ያስባሉ

የጂላ የጂባ መምጣት ይመጣሉ
አምስት ዓመት የዘተው ቶሎ ይወጣሉ።
ድንጋያ ዱቄት አርገው መንገድ የሚሠሩ
ጠብቅ ይመጣሉ ታዘበኝ ቢቀሩ።
ጉመዱን ዘርግተው ምንገድ የሚያበጁ
እሁያ የሚያርዱ አሞራ የሚፈጁ
መጡ እየተማሩ አበሻን ሊያበጁ
ማማሩን እማሩኝ ግን ብዙ ሰው ፈጁ።
እግሩ እንደመቀመጫ የሚንከባለል
ቢሄድ አይታክተው አቀበት ቁልቁል
ጫካ ታሰው መንገድ መሄድ የማይችል
ነደል ሚንሸራትተው የሚንከባለል
ይኸን የገዛ ሰው ለቶ ምንም አይል።
በገባጁ ነድፎ ፈትሉ የሚሠራ
ሰውን የሚያስገርም የሚሠራው ሥራ
ልብሱ ተፈሳ ሰውን የሚያኮራ
የዚህ አይግረምህ አለ ሌላ የሚሠራ።
እፍ ቢሉት አይነድ እፍ ቢሉት አይጠፋ
ቲነኩት የሚገድል ሰውን የሚያጠፋ
ነጮች ያንዱ ታላ ሐበሻ ቲሰፋ
የመተማን ትተን የአውሳን እናውጋ
ሦስት ቀን ጨልሞ ባራተኛው ነጋ
ሰለት ታግሎ ነበር አውሣ እንዳትወጋ
ስሙ የታወቀ ትልቅ ባለጠጋ
ታይያዝ ይመጣል አገር ግን ተዋጋ።

አይጥ ጠመንጃ ይዛ ተገባች ተዋሻ
ታትታይ አትቀርም አሥመራ አላህ ቢሻ
በደም ተጨማልቃ ትሆናለች እርሻ
ብዙ ሕልቅ ይጠፋል ታይገኝ ወጌሻ
ክፉ ንፋስ ገብቶ አልብሷት ቁሻሻ።
ምን ኑሮ ይገኛል ምንግሥቱ ተከፋ
ሰውን ለማስገደል ጦሩን እያስፋፋ
ውሸት እንዳይመስልህ ይሆናል በይፋ
ጠብቀው ዘመኑን እንዳታንቀሳፋ
ወቅታቸው እስቲደርስ እስቲያልቁ በይፋ
ደንግጦ ይሞታል ያሥመራ ቃልቻ
ነገሩ አይታወቅ ሁልጊዜ ጦር ብቻ
ያሥመራ ጦርነት ትግሥ ቲጀመር
ብዙ ሰው ይጕዳል ነገሩ ታይምር
ወዳው ሰደዳቸው በሰማይ በምድር
ወያኔ ይሞታል እያገኘም ነስር።
ተልባቸው ነጃሳ ቲያዩዋቸው እስላም
ንጉሳቸው ጥሩ ይባላል ጀሰማም
ሰደን ተቆርቋሪ ለሁሉ ሚጠቅም
በኬላ ያልቃሉ ቀኑ ቲጨልም
በስሙ እሚፈሩ ዓለም እስታለም
ባህር ወዳ ማዶ አራት ሰዎች አሉ
እነዛ ሁለቱ በቀን ይበልጣሉ
የጌታችን መቃም አያል ነው ይላሉ
ሳደም መህልቁታ በላ ይሆናሉ

ባመጡት አበሻ እነሱ ያልቃሉ፡፡
ሐበሻ ሁለት ነጭ ታይጡም አይቀር /ጣልያንና እንግሊዝ/
አንደኛው በፍቅር አንደኛው በጦር
አለበው ነበረ ሲያረግት አገር
አምስት ዓመት ሙሉ ቲል ድንግርግር፡፡
እኩሉን በሥራ እኩሉን በጦር
ነጭ ቃሳህ መጥቶ ያከስላል ከሰል
በመን ተበሳሽቶ ወደቅደቅ ቲል
ተፈሬ የዛን ቀን ይሆናል ቅጠል
የሚያነሳው ጠፍቶ ይሆናል ከሰል
ሜዳ ላይ ይወድ ቃል ታያገኛ ከልል
አሳህን ስደብኩት ማን አሰው ጠቢቃ
ምን ሥርፋ ኖርት ነው ለስ የሚቢቃ
መሸሸጊያ የሰው ቢኳልም አይበቃ
በዱኒያ እንደሆነ ይበልጣል የኒቃ
ቃልቻ ይመስክር አላህ ያሰው ቡቃ
በሂሐር ላየው ሰው መሳ ደጋጋ ነው
ውስጡን ማን የሚያውቀው ያሁኽ ሲቄ ነው፡፡
ቃሳህ ቤት ገባሁኝ ታየኝ ጉድጓዳው
ሂደ ሂደ መንገድ ማነው ያቢቃው
አንድ እልም የሌለኝ እኔኒ ታውቀው
በይህ እንዳይገርምህ ጉዱ ብዙ ነው
ኒታየን ስደብኩኝ ሐሊቅ ነው ሞሂድ
እኔ ድንጋይ ነው እልኩ ያሰውድ
ታትከፍር ሀድ ጠይቅ ተቃልቾች ዘንድ

መጨን አይተነው ነው ሐጃጅ ቲነግድ
ጊላ ጉድ ይሰማል ሐበሻ መሬት
የትኛው ኪታብ ነው የፈቀደለት
ልኩውን ልክ ሥራውን መሥራት
ሽህውት ተሸከማ ያለ አጃኢበት
ሱብይ ባየች ጊዜ ቀልቧን የሚያስት
ሸዋ እብቁን ዘርቶ አሥመራ እንፈሰው
የጊላ ጊላ ሕልቁን ሊያስለቅሰው
ራብ ትዝ እያለው ጊላ የሚቀምሰው
ሸዋን በጉዱታ የሚገዛው ማነው።
ሸዋን በረድ መትቶት ቢይዘው እንቅልፍ
እንክርዳድ ነው እሱ የሚያምረውን ጤፍ
በየስርፋው ዘሩት እንዲበላው ወፍ
ህደህ ጡብቅ አሉት አስይዘው ወንጭፍ
በታች አይጥ ፈጀው ላዩን ቲሰፈልፍ።
ሐብታም ቀኑ ደርሶ ሊወልድ ቲቃረብ
በወሉ በትጉሪ ይገባል ራብ
በቁም የሚያስቃይ የሚያንገበግብ
ተፈሪ የሣን ቀን ያገኛል አዛብ
ያውም በወራዳ በሌለው አደብ።
ሸዋ ድንገል ሆና ሕን ተፈረሰ
ሐብታም የተባለ ደንገዶ አለቀሰ
ምጡን ታይፈረጅ ሆዱ በሰበሰ
መዳኒት ጡጣ አሉት ደም የተለወሰ
ሺታው የሚያስከፋ እምታስነጥስ

የዛን ቀል ይወድ ቃል እስላምና ቀበ
የዛን ቀን ያሲጋል አገር እንዳይፈርስ።
እኛ ፈሪን በምን ባንድ መቶ ዓመት
ተፈሪ ዓይኑን ቃጥሞ ይምል መሬት
ማር የሳበ ሆኖ ይቀምሳል እሬት
ያሰው ይንገሥታል በገንዘብ ሽፍት።
ሸዋ አባቱን ቃይዝ ምስጢሩን በዘበዘ
ድርቡሽ አገር ዋ የውን ልብ ይዞ
አዳብ ልብ አገኘ መጣ መርገን ይዞ
አረሁ ላይ ተፋው ፖያንን ጅብ ይዞ
አበር እሚበላ እንጀትህን በዘበዘ።
ሱልህና ቃሲም አብደላ በበደር
በወልቃይት ብቅ አሉ ትግሬ ሲበረበር
ኩታበር ጎራዴ ተሆናስቸ ሲሰበር
ጉጃም ትያዛለች ታትወል ታታደር
ብዙ ሰው ይወፋል ያውም በስንበር።
አሥመራ ተዋጊት ወልቃይት መርዝ ተፋ
ሽፊና መቀሴ ይሆናል የከፋ
እንቅልፍ እንዳይወስደህ ርብ ታይሰፋ
ይመስላል ሳየው ቂምን የተደፋ
እሱቱን ስንቁን ማለው ጠብቆ ወረፋ።
ጋይንት ነፋስ መውጫ ደራና ፎገራ
ርብ ላይ ምልቶ ቲህሩን ቲያወራ
ተወዳ ይፈነሃል መቀሌና አሥመራ
ምን ይበጀው ይሆን ጭልጋና ወገራ

ሸዋ ደፈረሰ እህሉን ታይዘራ።
ደህና አርገው ለቅልቃት የርብን አውድማ
ይጋጠሙብታል እሥራ ሁለት ኮርማ። /1982-83ን ያስታውሱ/
መግዛቱንስ ይግዛ የውጠንስ ዘር
ወዲያው ስጥቲት ቀን ይላል ፍጥር ፍጥር
ተፈሪን ጣል አርጉ ቲያሳድድ ቲቀብር
ቢያዝ መልካም ነበር አገሩን ታይቀብር
በቀር ሸዋ አይፈጋም አትጠራጠር።
ሐበሻ ተፈሪን ይዘው ተቀበሩ
እሥመራ በሙሉ ይታጠራል በሩ
መቸም ሳስተዋለው ብዙ ነው ነገሩ
እኔ አልናገርም አያል ነው ምሥጢሩ
ባረሆ አካባቢ መች ቀረ ነገሩ።
አበሻ ልትደኽው ትትቀጥን እንደድር
አዲስ ምንግሥት መጥቶ ይታወሻል ምድር
ሕልቁ የዛን ጊዜ ይሰዋል ድንግርግር
ገንዘብም ተወርሶ እትክልትም ታይቀር
እንኳን የከሰው የበርሃም አይቀር።
ይኸ ቻይና እሚሉት ዘራቸው ልጠፋ
ችግርይኸለቃል ይሆናል የከፋ
ማጥፋት ይሻል ነበር ባገር ታይስፋፋ
ወልደን ታንጥሰው ልጃችን ታይጠፋ
ጠብቀው ዘመኑን እስቲታይ በይፋ።
ሐበሻ ተገባ የቻይና ቀራይሽ
ዲትን ያስፈራዋል እንዳይሆን ብላሽ

በዘበኑ ውጣት በሆኑት ቆሰለሽ ፤
ምን መላ ይገኛል ጦር ቢያከማቹት
እስካሁም ታሪክ ተወንድም ተሴት
ሰው ታልመከረ ይሆናል ወንፊት
መጨረሻ እሳቱ ተቶፋ ይሆናል ፍጆት።
ይኸን እየሰማ እንዴት ገባ እሳት
በድርቡሽ ቂጥርመኛ ባደቀ ጦርነት
መቀሌን እያሁት እረሆ በሌቶት
ሸዋ በገዛ እጁ በጫረው እሳት
ስንቱ ሰው ይንዳል ውቅር አዲግራት
አገኪን ያገበሰ ልጅ እያዘ ቲዘዘው
ጀግና እሚወጣበት አንዱ ወይት ነው
ሥርቆውን አይቶ እኔ ሳላታውቀው
ኸሬ ልጅ እሥመራ ማይጠልው ወያኔው
ምኒልክ ይመስክር ቴዎ ያየው
የወሌዶ ወሌዶ የጀግናም ጀግናው
እኛ እንኳ ላንቀምሰው በሌላው እየነው
በሌተው አይጠጡ ጀሰማቸው ተጭንን ነው
ተፈሪ ያልወፈረው እንሩ በዝቶ ነው
ሸዋ እሥመራን ፈጅተህ እታጥበህ ወለት
ማምሰጫም አታገኝ ታትህን ፋቁት
ገና ታሥመራ ጋር ታትፈተፍት
ማምሰጫም አያገኝ ሁሉን ፈረድኩት
ግን እሥመራ ያልቃል በራብ በጥማት፡፡
ሐበሻ ጠቅላላ በጦር ተተመራ

ውትታቸው ያቢቃል ፋቅራና ደብተራ
ላገር ባይመቹ በሚሆኑት ሥራ
ምድር እያነቁ ቲያስነጥሱ ደንቃራ
ጉዳቸው እያልቅም ቢወራ ቢወራ።
እሥመራ ዉሻ ጋብ ቲበል ቲደነፋ
የልቡን ተናግሮ ፕንዘቡን ቲያጠፋ
ተሰለም ተክርስቲያን ተሁሉም እይጠፋ
ሁሉም ቲከፋበት በራብ ሲያንቀላፋ
ውቅቱ ዘበል ቲል ያስቅኅል በሊፋ።
በርበሬ ቢጋገር እንጀራም አይሆን
እሿራው ማን ይሆን እፍሳሹ ሲጠን
እቡኪሙስ ማን ይሆን የሚሰድ እጁን
ሸዋ ግን አይፈራም ያውቀዋል ጉዳን
በልቶ ሰው ያበላል እስቲገኝ እማን።
የከተማው ወንፊት በርበሬ እያነፋ
ኑሩስ የመጣ እንደሁ ነፋው ዓይኑ ጠፋ
ዓይኑን እስተሚያሸው ነፉ አጥቶ ተደፋ
ኑሩስ እያዩ ነው በርበሬ እሚነፋ
ፍሬው ታልደቀቀ በርበሬ አይነፋ።
የሥመራውን ልቅሶ ሸዋ ታልሰማው
እንደ ጥቅምት ማር ይልሰዋል ሰው
የወገባው ጉበዝ ቀንማን የነፋው
ይጨፈጭፈዋል ዳንሚያ እንዳይለምደው
ቤቱን እስተሚያዩን በጉድ የተማው።
ተቴዎድሮስ እንስቶ ተፈሬ ድረስ

ዘመኑ ይቢቃል የዘውድ ንጉሥ
ንጉሥ እሰ ብስህ አትወሳወስ
በምርጫ ታልሆነ የሰም የሚነግሥ
ግን ሕልቁን አየሁት ብዙ ቀን ቲያለቅስ።
ኢያሱ ተረግሞ ሰክሮ ቲያንቀሳፋ
ተፈሪ ይነግሳል ታይደክም ታይሰፋ
ቀጥ ብሱ ያውጃል እንዲያቁት በይፋ
ፈረንጅ ድል አርጉት ተይዞ ታይጠፋ
ዘላሰም የሱ ናት እስቲሆን እንጋፋ።
አበሻ ክፉ ነው ቆርጦ ተተነሳ
ፈረንጁን አረገው እንደዜ ኮሳሳ
ጦርነት አሰበ ዳግሚያ እንዳይነሳ
አገር መቾ ይቻላል ቆርጦ ተተነሳ
ቲያዩት ምኝ ይመስላል ቲገል እንዳንበሳ።
እንደ እንቁላል ገምቶ ቲፈርጥ እንደብይ
ምን ይበጅህ ይሆን ባሰባር ጠንቋይ።
ታትያዝ አትቀርም ፍዳህን ታታይ
ለሰው ዑምር ትታይ ለራስህ ታታይ
ምን ጠንቋይ ይባላል መጨን የማያይ
እኛ ባንደርስበት ምን ቀረው ሊታይ
እሥመራና ትግሬ ትትል ሸገዳይ
አባብ ከተፍ ይላል መምጫው ታይታይ
ሸዋ የባን ጊዜ ይላል ዋይ ወይ
ጆርባውን መጅ መታው ወደ ትግሬ ቲያይ።
ቲተክሏቸው ጥሩ ቲበቅሉ ጠማማ

ተመጫው ያልሆነ ወይንም ጨለማ
እላህ ያሳያችሁ የወሉ ኡላማ
ደረጃው ምንድው ቃልቻ ሰው ታማ
ግን ኋላ ሳያቸው ይሆናሉ እላማ፡፡
እንግዲህ የኔ ጠጅ ነገር ታመጣሽ
ሌላ ታትነኪ ሀሲድ እያዩሽ
ቃልቻ አይጠጣሽ ይታጡብበሽ
ሰው እስቲ ስቅበት እስቲሆን ብላሽ
እንግዲህ ቃልቻ አትጫወትብኝ
አንተ ተቤት ቁርተህ ምንድን ሊጉልብኝ
ታሜትህ በተቀር ምንም አልቀረብኝ
ብታማም በጠጅ ነው ሌላም ጉድ የሉብኝ
ወድጄ አልጠጣሁት ግንአላህ ፈርዶብኝ
ባላህ ይሁንብህ የመንደር ቃልቻ
ይኸው አርገንሃል የንፍቆ ስልቻ
ተቤት እንዳትወጣ ሁን እንደ ጉልቻ
ሴት ወንዱ ያዋርድህ እታግኝ ፈረጃ
በኔ ቀልደሃል የሚሆንህ እጃ፡፡
አላህ ያሳያችሁ ያበሻ የወልይ ያሰህ
እኔ እከሌ አላልኩም በድፍን ሺሊላህ
መቀመጫ አጣሁኝ በስ ቃልቻ ታማህ
ከፍረሃል በሏሒር አሉኝ ጠጅ ተጠጣህ
ተስንቱ ልጣላ ኧረ ያላህ ያሰህ
አላህ ገላገለኝ ዘላለም ወይኔ ትል
ቢነግሩት አይሰማ ቢጥዱት አይበስል

ቢያስፋ ይኖራል እበሻ ይመስኅል
እሳት ስደድኩበት በጣም እንዲበስል
በኔ ግን ታልመጣ እረግም ለሰው ትል
እሸሙር ነውንገር እንዳትሳሳት
እፈር በገባን ባርባምስት ዓመት
በሐበሻ መሬት ይመጣል ጉዳት
እውልያ የተባልክ በል ደግና ስንብት
ዝሆራው ያስፈራል መከ ቢያወሩት
ወልይ የሰም ታሉ የሕልቁ መብራት
መኮች ባወሩት መንገድ እንዳትስት
በግልጥ ሳሰማህ እንዳትገባ እሳት
ሸሊላ በላቸው ተወንድም ተሴት
በሺሐር ሰሞቱት በድኒያም ሳሉት።
እስህም እንዲልል ሥርፋህን ማን ያቃል
የሰህም እንዲልል ይመሻል ይነጋል
እንዴት ያገተን ሥርፋ ሸይጣን ይደፍረዋል
ወትሮም ጥበብ ሥራ ሰው ያስወነጅላል
ያልሆነውን ሆን እያስ ያሴራል።
/ታማሪክ/ ታሜሪክ ወደ እስ ጥቁር ባህር
ሃያ ዓመት ያስኬዳል በግምት በእግር
እዛ አንድ ጉራ እለ ተተክሎ እንደ ጦር
ኑሙች እዛ በታ ታይደርሱም እዴቀር
ላዩ ግን ሜዳ ነው ያገድ ጋሻ እገር
ታማሪክ ወዳ እለ ጥሩ እገር
ተራራውን ወጥቶ ተተገኘ ቀድር

ላዩ ግን ሜዳ ነው የሚያጥበረብር
ሥርፋውን ግን እያጣም የሆኑ ዛኪር
እዝሀም አይደርሱ እንኳን ሊቀመር፡፡
መኮች ኸዱ ታሉ ነሙች ተጨረቃ
መውሊድ የሰም ታሉ ዝየራ ሰደቃ
ነቢን ተጠሷቸው የሕልቁን ጠበቃ
እንኳን መስማትና ማውራትም አይበቃ
ልባቸው ርኩስ ነው ሥራቸው ጨምላቃ፡፡
እምስተኛው መዝሁብ ተሸጠ ታይሰማ
ኋላ ጉድ ታያሰህ ያሻ ኡሰማ
የማታቀው ነገር ቀርቧል ልትሰማ
ሰምተህ እንዳትከፍር ጆሮህ እየሰማ
ለሚት እንዳትረግምህ እህያ ታሰማ፡፡
ምሥከር ያሰኘ ሰው ተናግሬ አልሸሸ
ዐቋጁን ተከተል ታትከፍር ብላሽ
በሁለት ምንግሥት እንዳትንገሸገሽ
ያሲን መስከሮታል ቁርአኑም አይቀሽ
ሌላ ታልሰፈሩት ሰው እንዳይበላሽ፡፡
ባምስትና ባራት በስስት ቲጦር
ቲከትብ እየሁት ሸህ ሙሐመድ ኑር
ቀንጥሮ ያወጋል ምንደር ሰምንደር
ጠቅላላ ታይዘው ቀርቶ ሳይከርር
ሰውን እያየሁት ጠልፎ ቲናገር፡፡
ፈረስ ደህና ስንብት እላህ ይሁንህ
ነጭ አበሻ ገብቶ ጉድ እሸከመህ /1928/

የሚታቀው ነገር ጭና አስጉተተህ
ጉድክን ወደ ኋላ እንዳታይ ሁነህ
ባንዱ ትታሰቅስ ሶስት ሰው ሜኮህ
ዐረብ አገራችን ታይለምዱም አይቀር
ወልደው ይከብዱሉ ያረጋሉ አገር
ግን ልጁ ሸይጣን ነው የሰውም ኸይር
ሶላትም አይሰግድ አልፎ አልፎ በቀር
መልክ ቀንጆ አይመርጡ ብትሆን ባሪያ ኩፋር፡፡
ሐብታም ወራሽ ምንግሥት ተሹሞ ቲመጣ
ሙግት የዛን ጊዜ ይሆናሉ ቂጣ
ሁሉም ይጉምደዋል ጣይ እስክትወጣ
ታስሮ ተመገደል ምናልባት ቢወጣ
ያሳህ በል የዚያን ቀን እንዲህ ያል ቲመጣ፡፡
ዘመን ተሰውጣ ጥቅምት ቲደርስ
ባሥመራ ከተማ ይነፍሳል ንፋስ
የዛን ቀን እሻ ይሳል ፍርስርስ
ሃምሳ ቀን ይቆያል ሴት ወንዱ ቲያስቅስ
ወንፊት ጉድ እስቲ ወልድ ሁሉ እርስ በርስ፡፡
ምንግሥታቶች አልቀው እሥራራት ቲቀሩ
ተድንጋጤ በቀር ይቀረኛል ኸይሩ
በረካም አይገኝ እስቲ ቁርአን ቅሩ
መድፈሩም አይበቃ ደብድቦ መቅበሩ
ለሰው ግን ጥሩ ነው በእማን ማደሩ
በመካ አንድ ንጉሥ ባረብ ሶስት ቲቀሩ
ሐበሻና ሶማል ታይገጥሙም አይቀሩ፡፡

ድርቡሽ የዛን ጊዜ ያስባሉ ሸር
የዛን ቀን ያየ ሰው እሳት ቲጫጫር
ሰበቡ አምመራ ትሆናለች ኑር፡፡
አፈር በገባን በሥላሴ ዓመት
ንጉሥ የተባለ የሰውም ሂያት
እጁ እየተያዘ ይገባል እሳት
ዘሩ እየታደነ እንዳውሬ እንስሳት
ተኛም ታይመጣ አይቀርም ጊኋ ወደፊት፡፡
አጫኒያ ደህና ሁኝ እኔ ጋሰብኩሽ
ምምክሬ እንዳይው ነሽ ሀዋጅ እንዳትረሽ
በሐቅ መምክሪ እንደኔ እንዳትዋሽ
አሚያውቀኝ ብዙ ነው እንዳትወቀሽ
እኔን በታች አርገሽ በላይ ታረገሽ
እናም ልንወድቅ አሏት ሳትሸሽ
ስሟን ብዘበይተኝ አልሲት ነኝ ብላሽ
ጊኋ እንዲህ ልሰድብኝ ልትለኝ በሰባሽ
በዘጠና ስምንት ግላችን ፈራሽ፡፡
አጀሳችን ቀርቦ አፈር ትታቀፍ
ብዙ ወፍ እየሁኝ አፊቴ ቲረግፍ
ሁሌን አባቴ አለ ወደ መንገድ ቲያልፍ፡፡
ዝም በል እንዳልሰው ሙለፎኝ እንቅልፍ
በዘጠና ስምንት ሂያታችን ሲያልፍ
ታንሸጊጋት አርገን ልቅምቅም
አምሳ ዓመት ጋብቢናት የቀረን የለም
እያየን እንዲረዳ አማራና አስላም

መጨረሻን ተናገርኩኝ አይቶ እንዳረገም
የልጅ ልጅ እንዲያቀው እስተዘላለም።
አውሮፕላን መጣ በሰማዩ በሮ
ደሴ ከተማውን ሠራበት ቀርቀሮ።
ምን አሉብኝ ብሎ ፈረንጅ ተንፈላሰሰ
እንግሊዝ ዘሰቀ በድንጉ... ......
ጀርመንና ጥሊያን አንድ ላይ ሁነው
የሀበሻን መሬት ጉድ ሊያደርጉት ነው።
እነሱ ታይቀዩ ወዲያው ቲመሰሱ
ተመሐል ቦታ ይላል ንጉሥ ኢያሱ።
በሐረርጌ በኩል ይዘልቃል መስካብ
ድንኳኑ የበዛ ተሰማይ ኮከብ
አንዱ ተማመደ አንዱ ባህር ማዶ
የሐበሻ መሬት ያደርጋታል ባዶ
በያሱ አምላክ ይላል የሰማይ ምስለኔ
አውሊያ ሲኸድር እዛው ነበርኩ እኔ።
ድንኳናቸው በዝቶ እንደሰማይ ኮከብ
አሁን ይመጣሉ ጀማልና መስኮብ።
ባባቱ ማመደ በናቱ ፋጡማ
ተዐረብ ይመጣል ድምጡ ታይሰማ።
በነጀማል ጊዜ በነመሐመድ
መቅደላና ተንታ ይሠራል መስጊድ።
ተዛም ተዛም ብሎ ቲያበቃ ዘመቻ
መገን ወረኢሉ የሰው መካተቻ
ያሰለቅሳል እንጂ ይህስ አያስቅም

በሰው ተመከሎ ዝንጀሮ ጫት ቲቅም፡፡
ቢለን አዛን እርጉ ጅሩ ይሰገዳል
የቂሉ ሁሉ ቀብ ያንቀን ይቀደዳል፡፡
ተሳይ ፊጦ ይዞ ታች ተንታ ድረስ
ይሠራል ቆርቆሮ የሚለሰልስ
ንብቶ ይመስለኛል የስላሞች ንጉሥ፡፡
በታችኛው ርብ ዐውድማ ተበጀ /1982-83 ዓ.ም/
እዛው ይበራያል ዕዳውን የፈጀ
ደንቢያና ፎገራ እሳፋ ጣቁሳ
ያፈታህ ያከረም ቱል ሰማሁትሳ
በየወላይ ብሎ በጠባሲት ኮሶ
በላይ ጉባ ብሎ ዃላውን አጋምሶ
ካሚወሉ ገባ ታች ተንታ ገሰግሶ፡፡
ታች እምባ ማርያም ላይ ይሠራል መስጊድ
እስላም የተባለ ጁምእ ቲሰግድ
ዐዋጅ ይነገራል ካፊር ሲታረድ
ነገሩ እንዳይበዛ ልበለው ታግድ
እኔን ይመስለኛል ሸህ ሰይድ መሐመድ፡፡
ሸህ ግመል ሸለከ በመርፌ ቀዳዳ
ላም እሳት ወለደች አህያ ጅብ ነዳ፡፡
በሰንበሲጥ ግዳፍ መዳቀሉ ዋርካ
ወይ ፍካሬ የሱስ ይህም እስ ሰካ፡፡
ከቶን በሰበሰ ደረሰ መፍረሻው
መስጊድ ይተከላል በድፍን አበሻው፡፡
ፍራት ፍራት አለኝ ምነው ሆዴ ባባ

ቁሱም ቃልቻውም አከተማ ገባ፡፡
እንበሰው ስሊላ እንበሰው መጀን
በሰሜን ዘለቀ የሚሉት ጀርመን
አምራ ላምራ በሕዋ ቲፋጅ
የጦሩ ማክተሚያ ርብ ነው እንጅ
ጣይና ጨረቃ ርብ ተገናኝተው
ደህና ተሰያዩ ሰውን አስበቅተው፡፡
በስተ ጠሐይ መውጫ ይመጣል ያሉት
እኔን ይመስለኛል ተማመዶች ቤት
ራስ ዘናና ምንጭረ ዘርባባ
ድፍን አበሻ ይለዋል አባባ፡፡
ዘመቻ ቲታዘገዘ ዐረብ ቲል ክተት
ወታደር ባላገር በውድማው ግብት
በል ግባ ይልሃል የጉበዙ ዳኛ
ያን ጊዜ እንዳትኸድ ተው አድበህ ተኛ
ለድማሚቱማ አሰው ወቅት ሂድ
እሱን የሚገልጠው ስይድል ሐዲድ
ለኛም አሰን ጊዜ ለኛም አሰን ፈንታ
መስጊድ ይተከላል ዋድላና ደላንታ

እንዴ ነው ሳይ ደሴ የሁሉ እኩል አገር መጠጫው ብርሌ መቀመጫው ወንበር እንዲሉ ሁሉም ወሎየ በእኩል ዓይን ነው የሚተያየው፡፡ ስምና ሃይማኖት አይለየውም፡፡ ተባብሮ፣ ተፋቅሮና ተከባብሮ የሚኖር ነው፡፡ ሸህ ሁሴን የቅርብ የሩቁን ሲናገሩ ችግር ሲያቃልሱ ውሰው መቅሪብ ላይ ወደ ቀያቸው ሲገሰግሱ ከብት ከገባ ሰዓይ ተያዘ እንዴት ወንዝ አቋርጠው ጥሻ ጥሰው ይኸዳሉ ተድባብ ማርያም ቅጥር ግቢ ይደሩ ተባሉ ቁጠማ ጉዝጉዘው፣ ስኒ ደርድረሰው፣ ስኒው ተደርድሮ፣ ጀበናው ቲገተር ከተፍ

ከተፍ ይላል ያውልያው ወታደር እያሉ ይጠብቋቸዋል፡፡ ሸሁም ገና ደፉን ሳይዘልቁ እግራቸውን ሰብስብ፣ ቀልባቸውን መለስ አርገው "እስቲ እንህድላት ሰዚች ለወይዘሮ አይሰማምና ድቢና ከበሮ" ብለው ምልስ አሉ ይባላል ፍቅርና ክበሬታን ሲያሳዩ፡፡ በ1966 ታሪክ ነውና ታሪክ ዘግቦታል ሸሁም ጀበብ ጀበብ እሰ ወታደር ወጣት በታተነውሳ የተፈሪን ቤት ያሉለትና ዓለም ኮበለለች በሰድላ ስድስት እሷም አትመለስ እኛም አናያት ያሉበትን የሚያዘክር ወቅት ነው፡፡ በዛን ጊዜ ነበር በ1967 ዓ.ም. ግርማዊ ቀዳማዊ አጤ ኃይለሥላሴን ወታደራዊው ደርግ ከሥልጣን አውርደንዎታል ሲላቸው፣ ግርማዊነታቸውም "የኛ ዘመን እዚህ ላይ ይፈጸማል፡፡ የናንተ ከዚህ ይጀምራል፡፡ የኢትዮጵያን አንድነት ማታቆዩ ከሆነ የናንተ ይወድቅና የኛ ስም ይነሳል" ነበር አሉ ያሏቸው፡፡

አዳኙቱን ውሻ ነክሰቻት በግ

በስው እጅ ያስ ሰው የሰውም ማዕረግ

ሆነና ነበር የግርማዊነታቸው ፍራቻም ይባል ትንቢት የሼሁን፣

ሐበሻ ተፈሪን ይዘው ተቀበሩ

እሥመራ በሙሉ ይታጠራል በሩ፡፡

መቸም ሳስተዋሰው ብዙ ነው ምስጢሩ

ባረሆ አካባቢ መች ቀረ ነገሩ፡፡ የሚለውን ያስታውሰናል ይህም ደግሞ፣

የኤርትራ አሞራ ነፍስሽን አይማረው

ጀግናው ሁሉ ቀረ አገር እንዳማረው

የተባለለትን የርግደ ሙሾ ያዘክረናል፡፡ ምንም ይባል ምን ሸሁ የጊዜን መጥመም የነገርንም መዘበራረቅ እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት፡፡

ባጥፈው ደነዘዘኝ ምላሴን እንደ ግር

ጤናና ንንዘብ ነው የልብ የሚያናግር

እንዲያው የኔ ነገር በጣም ይገርመኛል

ከውሃ ላይ ሁኘ ውሃ ይጠማኛል
ጀቡ ፈረስ ሁኖ ዕውር ተቀምጦት
ከፍቶት ሲያንጉራጉር ይመስላል የቅንጦት
እምኛል እንዳልል መሰሰብኝ ነውር
ደህናንኝ እንዳልል በሽታዬ ሰውር
የሰው ሁሉ ሁዳድ የሰው ሁሉ መሬት ሁሉም እኩል እኩል
ተድንበር እሰፈ ምነው በኛ በኩል
ኮንቦልቾ ዝንጀሮ እይሻ ላይ ዝሆን
ጊንዳ ላይ አንበሳ የሰፈረ እንደሆን
ይሉታል ደህ አውሬ ምን ይሆን ምን ይሆን
ጉኔን ጉልበቴ በላት እየጋዬ
ደህና ነው ይሰኛል የጥርሴን እያዩ
ፈጣሪ ታቃሰህ ሣቅና ጉዳቴን
ጀሊሉ ታቃሰህ መሣቅ መከፋቴን
ራሴን መቻያ አጥናልኝ አንጉቴን
ጀሮ ወንፊት የላት መልስ እታንቆረቆር
ልብ ያወቀ ጊዜ ምነው ባይደነቁር
እመመኝ ብላቸው ባይታይም ቁስሌ
ታንጀቴ መሆኑን ይንገራቸው ምስሌ

ይሉና ሰውም እስበሱ እንደሚናከር ጊዜውም እንደሚብስ የተናገሩበትም ስንኝ

ማሽላ ብዘራው ጉስ ሆነ እረማሞ
እየባለ ኸደ ተዘንድሮው ከርሞ
ውሃ ቁልቁል እዩ እሻቅቦ አይወጣም
የባሰ ቀን እንጂ የተሻለ አይመጣም

ውሽ ቲዘልቅበት ጅብ ዙሮ ይሸሻል
ይነጋል ብንለው እያደር ይመሻል
ላሚቷ ወተታም አባባው ዕውር
እንዴት ያለቀን ነው የሚያደናግር
ፍቅር ታረደና ደሙን ውሻ ላሰው
መነፋፈቅ ቀረ እንግዲህ ሰው ለሰው
የሚመጣው ዘመን ይላል እበት እበት
እንዳንገላግለው እኛም እንደርስበት ነበር ያሉት።

ነገሩ በስምንተኛው ሺህ ሰው በረከሰበት ሽምብራ ቡን ሆኖ ቲረቲብ ተጠጣበት እንዲሉ ሆነና የጊምባ ረኛም የጊዜውን መከፋት የርዝቀንም መጥፋት የህሉንም መወደድ እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት፣

እህያ መጣች ተጭና እብቅ
ሁሉ ተሟጧል የሰም ርዝቅ
እህያ መጣች ተጭና ማቅ
ተንግዲህ ቀረ እህል መዛቅ
እህያ መጣች ተጭና ድገር
እህል በጭብጥ ይሸጥ ጀመር
እህያ መጣች በተሊ ዐውሊያ
ምን ሲሸመት ነው ወጥቶ ገበያ
እህያ መጣች ተጭና ቁና
ጉግ ጉሮ በል ጠብ አይልምና
እህያ መጣች ተጭና ፈረስ
እህል በጭብጥ ዕዳ በራስ
እህያ መጣች ተጭና ቆብ
እንኳን ሊቀና የሰም ቀሰብ

እንተርሱ ባሰፈ መሆኑን በእንደህ ነበር የሚገልጡት፣

ሷ ሂብ ሰሷ ሄሁ አንድ ነው እመሙ

አብረው ይድናሉ አብረው ከታመሙ።

ጥሩ ጓደኛና ባህር ዛፍ አንድ ነው

አይመቀኛኝም ዕደግ እንደግ ነው

የያኔዋ ዘፋኝም አባባሉን ስትደግመው፣

ሲታመሙ ታሞ ሲሞቱ ካልሞቱ

በምን ያስታውቃል ሰው ወዳጅነቱ ነበር ያለችው። የጥንቶቹ ብዙ ብለዋል። ብዙም አስተምረዋል። ሰው ውሉ ከገባ፣ ከስቦ ካሰገባ፣ ኑሮው እንደት እርስ የልብ አድርስ ባይሆንም ችግር ቢያማቅቅም ርሃብም ቢያፍቅም ትዕግሥቱና መተሳሰቡ ካለ እንደ እጅ ጠባብ ይወልቃል፣ እንደ ጭቅቅትም በውሃ ይለቀቃል ያሉት፣

እስቲ ዐቦል ቀደሙን ቃሉ ደህና ይሁን

ችግር ጭቅቅት ነው ይራገፋል አሁን።

በሚል የሰነኘ ቋጠሮ ነበር። ታዳ እንደ መምህር የሚያስተምሩት፣ እንደ ሰባኪም የሚመክሩት ሽህ የኋላ ኋላ የሚሆነውን ገና በሩቁ የታየና ያስፈራቸውን ጉራ ዘለው፣ ዘመን ተሻግረው ሲዋደዱ ከዓይን ጥቅሻ፣ ከክንፈር ንክሻ በፈጠነ ሲካካዱም ያኑ ያክል ነው ያሉት፣

ደመና ቲመጣ ሰማይ ይጨግጋል

ሐድራ ቲቀዘቅዝ ዐወል ሱፍ ያወጋል።

የርብን ምልክት ልንገርህ ጥቂት

እሷ ትትመጣ እሳት ምልክት

ህልቁ ይታደላል ስንጼና መሬት

ደሞ ሁለተኛ ብርና ጥይት

እስ በሱ መሂሰም ድርቅና ክደት።

ይሉና፣ ሰጠቅ እርገውም መልቷሃት እንደሚያይል፣ ወሸከሬነት እንደሚጉሰብት፣ ቀማኛነት እንደሚበረከት፣

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]

[illegible]

[illegible]
[illegible]
[illegible]

[illegible]

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]



Scanned with CamScanner

እቴ ደሀና ሰንብቾ እስትንገናኝ ማስታቸው ፍቅር መከሰመኑን፣ መለያየት መጠንከሩን ሲናገሩ አይደል? አዝማሪውስ፣

አምባሰል ቀረና ባቲ ተገበየ

ሰው ሁላ ቀረ እንደ ተሲያየ ለሳሰም?

ሰውስ ቢገርመው ቢደንቀው አልነበር፣

አሳሁ ሲጣላ በትር አይቆርጥም

ያረጋል እዪ ነገሩ እንዳይጥም ማለቱ:: መቾ ለዋዛ ለፈዛዛ ነው? ፍቅር ቀዝቅዞ፣ ጥላቻ ሞቆ በማየቱ እንጂ!

የሚመጣው ዘመን ይላል እበት እበት

እንዳንበሳ ግለው እኛም እንደርስበት

ሽምብራ ቡን ሁኖ ተርቲብ ተጠጣበት

የሞተውም ሞቷል ያለውም ተጣልቷል

ዝምድና ሱታጠብ ውሃ ተወዝቷል::

በሬ ታረደና ደሙን ውሻ ላሰው

መነፋፈቅ ቀረ እንግዲህ ሰው ለሰው::

ፍቅርና ጤና ምቶ ቲቀበር

ባልሰማ ነውይ ልቅሶዩ ነበር ያሉት::

እንዲህ እንደዛሬው ሰውን ፍቅር ነስቶት ሰላም ርቆት ውሸት ተጠናውቶት፣ ዐቅል አሳጥቶት ባጥንት እንደሚናከስ ውሻ እስበሱ እንደሚባላ በሩቅ ስለታያቸው ነበር ያን ያሉት፣ ታዛቢውስ ወዶ ነው?

ምን ያለ ዘመን ነው ዘመነ ሽፋፋ

ፍቅር ከሰመነ መከባበር ጠፋ ያለው!

ወሎየዎቾ ጥላቻ መንገሡን፣ ጥርጣሬ መጉልበቱን ሲያዩ እደል ገንዘብን ጥግ ያደረግን ዘመድ ጓደኛን የራቀን የናቀን ወገን ያልጠየቀን ሆዱን የወደደን አይተው ገምተው ብላሽ ነው ሲሉ ያስታርቃል ያሉት ሲያጣ፣ ያስማማል ያሉት ሲያፋርስ፦

ይኸ ዘመን ታሟል መድኃኒት ይጠጣ

ወንድም ለወንድሙ ሆድ ለሆድ ተጠጣ፡፡

አፈላለሁ ቡና ታገኝሁ መራቂ

አቀራራጥ እንጂ የሰም አስታራቂ ብለው ያረቁት፡፡ ረምባዎችም ተለት ወደለት ሰው እየከፋ መተማመን እየጠፋ፣ ክፍት እየፋፋ እንደሚሄድ የተናገሩት፣

አህያ መጣች ተጭና አደስ

ክፉ ቀን መጣ የሚያጫርስ ስሱ በደል ያስተጋቡት ታዛቢዎችም፣

ጉጃም ተሸምቶ ይቀናል ቢገምድር

እየከዳ ኸደ ወዳጅና ምድር

አሉ፡፡ ምንም ይሁን ምን ሸሁ ታዳ፣

እሱ ያመጣውን እሱ እስቲመልሰው

ምጋ ጠጅ አይልም ቡዳ የበላው ሰው፡፡

ብሰዋልና እንተው አብጀው አስቤም አልፈጀው ሰማለት እንዲያመችን፣

እንቺ ቡና አፍልተሽ እኔ ልበል ጀባ

አሲድ ምቀኛችን ገደል እንዲገባ

እንባቡል አለ ዐውገረዲቱን፣ ይኸን ሰውን የሚጠየፈውን ከወዳጅ ዘመድ የራቀውን በጉረጥ የሚያየውንም፣

ዝናቡ አልዘነበ ወጨፎ አልመታው

ጥግ ጥጉን አሰፈ የዘመኑ ሰው

ብለን እንታዘበው ሲሉ ታዛቢዎች፣ ሸሐውም እንዲህ ብለው ነበር፣

ትቀታል መሰለኝ ያስው መወደዱን

በወዳ በወዳ አርጉታል ምንገዱን

ወዳጅ ቶሎ ቶሎ ብንገናኝ ምነው

ተዋስ ታደረ ሰው ተረሽ እንጅ ነው አሉ፡፡

ታይን የራቀ ተልብ የራቀ ነው ቲሉ፣ እበውም ወዳጅ ሲያረጅ በጓሮ ይኸዳል ይሉ የለ? በድሮ ጊዜ ወንድም መታፈሪያና መከበሪያ መሆኑ ግልጥ ነበር። መሬት አልረጋጋ ሒሳብም ወልጋዳ ሲሆን እንዲህ ሲሉ ይናገሩታል፣

እንዲህባለው ጊዜ በውራ ውሬው
ወንድም ለወንድሙ መድኃኒቱ ነው።

ሲሉ ወንድም አልባውን ደግሞ፣

ወንድም የሌለው ሰው ጥሳው ከውካዋ ነው
ከንቱን ከተመታ እሞራስ ምን አለው
ወንድም የሌለው ሰው የወንድም አባሪ
ትከሻው ላይ ቀረ የዱላ ስባሪ ይሉታል።

ከጊዜ ጥመት ይሁን ከሰው ጭካኔ የተነሳ ነገሮች እየከረሩ መተዛዘኑ እየቀነሰ መሄዱ ፍራት ፍራት ያላቸው ታዛቢዎች፣ መደበቂያ መሮጫ ሜዳ ያጡት አካላቸውን የነዘረውን ሆዳቸውን የበላውን እንዲህ ሲሉ ይተነፍሳሉ።

አቤት ይኸ ጊዜ ሰንት ጉድ ያሳያል
ወንድም በወንድሙ ቢላዋ ይስላል
ነግ በኔ ተረስቶ ወንድም ይታረዳል
ዝናቡ ጣለ እሉ ሲሞላ ነው ውሃው
እወይ ይኸን ጊዜ ለተሻገረው ሰው
ጉመን ቀንጥሽ አለኝ እንግዲህ ተመሽ
መቸ እገፋዋለሁ ይኸንን ቀን ጥሽ
ምድር ቲጠቀለል እንደ ወረቀት
የቀልቡ ይጠፋል እንኳን የደጅ ክብት
በሮቹ ተጠምደው እምቢ አለ ማረሻው
ይኸን ቀን ያየ ሰው እስተመጨረሻው
በሬቹ ተጠምደው እምቢ አለ ማረሻው

ይኸን ቀን ያየ ሰው እስተ መጨረሻው፡፡
ቢረቱም ዳኝነት ቢረቱም የደስ ደስ
እንደው በዚህ ዘመን ተሰው አሰመድረስ ይላሉ፡፡
አንበሳ እግሩን ታስሮ ደም ቲያሰቃቅስ
ማማው ምስጥ በልቶት ይሆናል ብስብስ
ዑዱኒያ ታልቅና የማታ የማታ
ገበያ ይውላል የማሀን ሽታ
መገን አግራችን መገን ለገዟዳ
ዑዱኒያ አብቂናት መቸም ሀዳ ሀዳ
ተቲዎድሮስ አንስቶ ተፈሪ ድረስ
ዘመኑ ያበቃል የዘውድ ንጉሥ
በምርጫ ታልሆነ የለም የሚነግሥ
ግን ሕልቁን እየሁት ብዙ ቀን ቲያለቅስ
ጆቡ ፈረስ ሁኖ ዕውር ተቀምጦት
ክፍቶት ሲያንጕራጕር ይመስላል የቅንጦት፡፡
እምኖል እንዳልል መሰሰብኘ ነውር
ደህና ነኝ እንዳልል በሽታየ ስውር
አዳኝነቱን ውሽ ነከሰቻት በግ
በሰው እጅ ያለ ሰው የለውም ማዕረግ
ባጥፈው ደነዘዘኝ ምላሴን እንደ እግር
ጤናና ገንዘብ ነው የልብ የሚያናግር፡፡
እንዳው የኔ ነገር በጣም ይገርመኛል
እውሃ ላይ ሁኘ ውሃ ይጠማኛል፡፡
የሰው ሁላ ሁዳድ የሰው ሁላ መሬት ሁሉም አሰው ኩልኩል
ተድንበር አለፈ ምንው በኛ በኩል

ጉኔና ጉበቴ በሳት እየጋዬ
ደህና ነው ይለኛል የጥርሱን እያየ

ሲሉ እንጀቱ የተበላ፣ ይናገረው ያጣ ዘመድ የሌለው ደሞ፣

ቤቱንስ ሠራሁት ዛሬ በልመና
እጠር መከራዬ ሰው የለኝምና
ላምላክ የምንግረው ምሥጢር ስላለኝ
ቀን ያልፋል ብለውኝ በመጠበቅ ላይ ነኝ

ይላል። እንደ ልቧ መናገር ወጣ ብሎ መከራከር የቸገራት ወዳጅን ተመኝታ ማግኘት ተሳናት በዓይን ቁራኛ በባላንጣ ዳኛ ተይዛ መላወሻ ያጣች ጉብል፣

እስቲ ረግ ረጉ ዓይኔ ይንከራተት
እንደ ልቡ አይበላም እረኛ ያለው ከብት
እንደ ራበኝ ውዬ እንደ ራበኝ ባድር
ራቤን እኔ መች ዐወቀው አገር ሲል ያንጕራጕራል።

ሌሎች ደሞ ስገንዘብ የሚጓጉትን ለሆድ ያደረትን በሰው ደም የሚታጠቡትን፣ ለዘመድና ለአብሮነት የማይጨነቁትን በነገረ-ሠሪነት፣ በዋሾቶ አደርነት የሚኖሩትን የሚገልጿቸው፣

እሾህ ብቻ ሆኗል እግሬን ብዳብሰው
እንዴት መላወሻ መሄጃ ያጣል ሰው።
ጊዜ እስ ብላችሁ እንዳትታሰሩ
ተደባልቋልና ሳቤትና ባኢሉ።
እባክህ ጀሊሉ አታጣላኝ ተሰው
ታይደርሱት ይደርሳል መቼም የተሳሰው
ኢማኑ እንደ እንቁላል ፈርጦ የፈሰሰው
በየደረሰበት ቀልብ እየጠበሰው
ያፈሰሰው እንባ እያቅበዘበዘው

ሲሉ ሸሁ፤ ታዛቢዎች ደሞ፣

ምላስ የወጋ እንደሁ ተቸከሉ አይቀርም
መርዝ ስለሆነ ተሆድሁ አይሽርም
የምቀኛን ምላስ ይንቀለው በሰጋው
እያደገ አደለ እሾህ የሚወጋው
ከእንግዲህስ ወዳ ሃገሬን አለቅም
አለች ከአፍ አፍ ነገር የምትለቅም፡፡
ሪከስ ቢባል ጥበብ እንደ ዋዛ
ከተማ ገጠሩ ነጭ ለባሹ በዛ
ጆሮ ጠቢው እንጂ እኔን የጐዳኝ
እየተጐተተ እንደ ቤት ከዳኝ፡፡
ጐረቤት ቢከፋ ይኖራል ሰብቻ
መድኃኒት የጠፋው ለሰባቂ ብቻ፡፡

ነገሩ ባጐረሰኩ እጄን ተነከሰኩ እንዲሉ ዓይነት ሲሆን ሸሁ እንዲህ ይላሉ፣

ተመከራ ሁሉ የጉንዳን ባሰ
የተሸከሚውን ጆሮ እየነከሰ

ሰውም ሲጨንቀው፣

ማንም ሰው አይገኝ ቁስል የለለበት
ልብስ ሽፍኖት ነው እንዳይታይበት

ሲል ሌላውም፤

እመኪና መንገድ የቆምኩት አሁን
ስንቱን አሳልፌ እዘልቀው ይሆን?
መሬቱ የኛ ነው እህሉ የዘመናይ
ፊትክን አዙር ይላል ቲመዘን እንዳናይ
ድመት ተጕታ ላይ አይጥ አይዝ አይጥ አይዝ

ዓይጥ ተጉታ ሥር እኔ አመልጥ እኔ አመልጥ

እንደዚህ ያለ ነው የኛም አቀማመጥ።

ይላል ወዳጅ መስሉ ጠላት ስሆነው ሳያይ ሳይሰማ ለማያውቀው ለሚባጠልቀው በየአዝማሪው ቤት፤

በል ተነሳ ልቤ አስብ ተመራመር

አላዋጣም የዘመኑ ነገር

ጨጓራና ጉበት ሁሉም ምግብ ነው

ሆድ የሚያሻክረው ምላስ ብቻ ነው

ኧረ አገር ኧረ ተወኝ መንደር

እየሰማህ አውራ እያየህ ተናገር

አሳህ የጣለበት ድልባን ያስቀምጣል

ማታ ያወጉትን ጧት ይዞ ይሮጣል።

አንድ ማጥን መርፌ ቀዳዳ ያሰው

ጎልቁን የጨረሰው ጠቋሚው ሰጪ ነው።

ሲሉ፤ ነገረ ሠራን እሾህ አጣሪን ወጋ ያደርጉታል። ጸሐፍትም ቢሆኑ ወዳጅ መስሉ ከሚወጋ፤ ሳሚ መስሉ ከሚነክስ የሳቀ መስሉ ከሚያስለቅስ መጠንቀቅ ነው ያሉት በእንዲህ ዓይነት የስንኝ ቋጠሮ ነበር።

በገሃድ ከመጣ የጥፋት ሠራዊት

በማንባር ከሚታይ የባላንጣ ብዛት

በወደባባይ ወጥቶ ከሚፋለም ጠላት

ወዳጅ መስሉ ቀርባ ስቆ ለሚቀበለው ያስፈልጋል ትኩረት

ዘፋኝም መቸስ ምን ይደረጋል እንዲህ ዓይነቱን በቅሌት ሚዛን ኮስኩስት ከማስቀመጥ ሌላ ያሰው፤

ዕዳም ይከፈላል እየሰነበቱ

ዓይኑን ያፈጥና ይቀራል ትዝብቱ

አርኮም ይኸድና ሰልዲም ያልቅና

ያስተዛዝበናል ይኸ ቀን ያልፍና
ይኸ ዘመን አልፎ ለሚመጣው ዘመን
ስንቱን ክርስትና እናነሳው ይሆን፡፡

በማለት ነበር ያዜሙት፡፡ ገምቢዎችም የዘመኑን ያለማማር የሰውን ቃል አባይነትና ውስልትና የገለጹት፣

እህያ መጣች ተጭና ከስል
እንዴት ዋላችሁ ሊቀር ነው መሰል
እህያ መጣች ተጭና በጥጥ
ጊዜው ወስልቷል አርፈህ ተቀመጥ፡፡

ነገር የሚያደሩን፣ ሥራ የማይሠሩን፣ ለዳቦ ፍርፋሪ ለእህል እራሪ፣ ለማንቲም ድቃቂ ለልብስ እላቂ ሲሉ ነገር የሚያምሱ ወሬ የሚያናፍሱ የትናገሩለት ሰንኝ፣

ማሽላ ቢዘሩት የነቀዝ ዕዳ ነው
ዘንጋዳ ቢዘሩት የወፎች ዕዳ ነው
እስቲ ተልባ ዝሩ የማላጋ ቀን ነው ይሉና
ወጥ በንጤት በቅጠል እየተጋገረ
እንጀራ በምላስ ይበስል ጀመረ እሉ፡፡

ለሆዳቸው ያደሩ በምቀኝነት የታጠሩ መኖራቸውንና የዘመኑ መከፋት የሐቀኛ መጥፋት የበረከት ማጣት ያስጨነቀ ያስጠበባቸው፣ ችግር እንደ መርግ የተጫናቸው፣ ዕዳ ያጉበጣቸው ነገር የመዘመዛቸው የሚያዩት የሚሰሙት ግራ የገባቸው፣

ዓይን የታመመ እንደሁ ማየትን ይጠላል
ጥርስ ተጠናበት ተነቅሉ ይጣላል
ሆድ ብቻ አይቻልም ውስጡን ያቃጥላል
እንዲህ ያለ ዘመን ዘመነ ገለባ
የታመመው አይሽር የወጣው አይገባ

ምን ያለ ዘመን ነው የዘመን ወሊጋዳ
ለፍትንም ማስነንም ሆነናል ባለዳ
እነሱ በበሉ እነሱ በጠጡ በሰማ ጆሯችን
እልወርድልን እሱ ዕዳው ተጀርባችን
በሮቹን እምጡልኝ አርጀ እበላቸው
ደሞ እንደ መሬቱ ሳይካፈሏቸው
ጊደሯም ተሸጠች ሙክቱም ተነዳ
አሳስቀምጥ ቢለኝ የማዳበሪያ ዕዳ፡
እውነትን ፍለጋ የቆፈርነው ምድር
እህል ዘራንበት በሊተን እንድናድር
እዩት ተመልከቱት እኔማ ጉዴን
ምስት እህል ዘራኂት ፀርባ ባምሳዬን
እናበቅል ነበር ሠርገኛ ተነጭ
ወስደው ጉመኛ በላው ተቀማጭ
እኔያ ባላባቶች ደግ ጊዜ ሞቱ
ንባሮቻቸው ጋር ገመድ ሳይጉትቱ
እንዳትመለሱ እምና የሞታችሁ
እዚህ የቀረነው የደላን መስሏችሁ
እምና የሞታችሁ ዝም ብላችሁ ተኙ
ዕዳ በዝቶብሃል ወደኛ እትመኙ
ሲል፣ ጊምባምች ደሞ፣
አህያ መጣች ተጭና በሶ
አከሲ ሞተ እልሄድም ለቅሶ
እናት አባቱን በዳ ለውጦ
ይላሉ፡፡ እበው ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ፣ ውሃ ቢያንቅ በምን

ይወጣ እንዲሉ አባቱ ዳኛ፣ ልጁ ቀማኛ ቢሆንስ፤

ታምናው ተታችምናው ዘንድሮ ይብሳል
ሌባ ዳኛ ቲሆን በማን ይከሰሳል
ሊቀመንበር ውሻ ጠላፊው ቀበሮ
ልቅም አርጐ ነዳው ሸቃዩን ዘንድሮ

እንጀቱ ያረረውም ቅስሙ የተሠበረውም፣ ጉዳዩም ገር ከችሮ የቀረበትም ምሬተኛ እንዲህ ይላል፤

እህሉን ድርቅ መታው ዳኛውም አምጡ አለ
ዛሬስ የሞተ ሰው ምንኛ ታደለ፡፡

ሰወፍ ጉጆ ለከብት ጉርና የጓይጥ ሸርንቁላ ለቀበሮም ጉድጓድ አላቸው ሲታከታችው ማረፊያ ሲያሳድዷቸው መደበቂያ፣ ሰስውም እንደ ቅዋው ጣራዋ የተበሳስ፣ ከጉኗ ያበመመች በባላ የተደገገፈች ደሳሳ ጐጆ በተወነጋገረ የጭራሮ መዝጊያ ገርበብ የምትል ትኖረዋለች፡፡ ሲወጣ ሲወርድ ውሎ ጉጉን ያሳርፍባታልና፡፡ እንጎት ካስገባች ጣይ ከከለለች አውጣ ታሳደረች ምንም አትልምና፡፡ ችግሩ ያቺው በላች ተብላ ከቁምነገር ተቆጥራ ስትኖር ወልዶ የሳመበት፣ ደግሶ የዳረበት፣ ሐዘኑን የተወጣበት ዕድርና ሰንበቴውን ያወጣበት፣ ንፍሮ አንፍሮ፣ ቆሎ ቆልቶ ከስፎ ከጐረቤቱ ጋር የቆረጣጠመበት ናትና መፍረሷ ያቶስለዋል፡፡ ሐዘኑን የከፋ ያደርገዋል፡፡ ሚስቱ ገደል፣ ቀን ሴት ይሆንበታል፡፡ ፊቱ ይበሰሳል፣ አካሉ ይከራማትል፣ ጥርሱ ይፋጫል፣ ይናገረውን ያጣል፣ እርር ድብን ይላል፡፡ ንዴትና ትካዜ ይደበዋል፡፡ ምነው እነ አባ ሰጠማሞች ቢኖሩም ይመኛል፣ ለቅኖች ቢመሸም ይነጋል፣ እሱ የወረረውን የሚያጣፍጥ የጨለመውን የሚያበራ፣ የጠመመውን የሚያቀና፣ የተሰበረውን የሚጠግን ነው ቢሉ ያስተምሩ የለ እንዴ፣ ምነው ታዳ በኔ ላይ ቀኑ ጨለመብኝ፣ ሰማይ ተደፋብኝ ቢል ይቆዝማል፡፡ እንዲህ ቢል ያንጐራጉራል፤

ሴቱም አልፈተለ ወንዱም አላረሰ
ተማረ አልተማረ ከብቱ አልተመለሰ
እንደ ጥምብ አሞራ ቤት እያፈረሰ፡፡

ወይ አልተጣላን አልተነጋገረን
ሰተት ብለው ገብተው ቤት አፍራሱ እሱ
ከነ ልጆቻችን መንገድ ላይ ጣሉት
እህል ስጡን ቢሉን እህል ሰጠናቸው
ሙከት አምጡ ቢሉን ሙክት ሰጠናቸው
ቅቤም አምጡ ቢሉን ቅቤም ሰጠናቸው
ቤቱን ስጡን እሱን ጠገራው ቀርቷቸው
እስቲ ፍርድ ስጡን እነኚህ ሰው ናቸው?
ከመሬት ከቤትም ከልጅ ተሰያይተን
አገር አሰን ልንል መንገድ ዳር ተኝተን
ኧረ ወገኖቸ ለቆመው አልቅሱ
እሱ አሽቃባጮች ጠገራ እሚያፈርሱ
በለት ፍርፋሪ ሰው የሚያስለቅሱ
ጨረቃና ኮከብ በቦታቸው ናቸው
ደርግና ኢሠፓ ባይለዋውጧቸው
ደርግና ኢሠፓ የሠሩልን ሥራ
በሬያችን ለሞስኮ እኛን ለሠፈራ
እንዳላለ ሁሉ ወሎዋ በተራ
ሁሉም ተደረሰው ዛሬስ ምን ያውራ፡፡
ምን ሊሆነኝ ጐጆ ምን ሊሆነኝ ቤት
እንግዲህ በሐብቱ ታሳዘዝኩበት፡፡

ድሮ ድሮ የጉድ አገር የበሩ ገበያ ይሉ ነበር ነገር ተሆዳቸው ሲሰነቀር፣ ሲገረሙና ሲደንቃቸው፣ አካባቢዩ ጉድ ሆነ፣ ቀየዩ ጤቅ ተሠራ ሲሉ፡፡ ምን እነሱ ብቻ አዝማሪም ነገርየው አላማረኝም፣ ቀየውም ቀየ የሚሆን አይመስለኝም ሲል እንዲህ ነበር ያለው፡፡

ከድጃም አበበች ፋጡማም ታጨች
እንዓዲህ አንቻሮ ምን አገር ሆነች

እያያዙን አይተህ ጭብጦውን ቀማው አደል የሚባለው አንቻሮ አገር ያልሆነች በነብየ በነ ፋጤ መሄድ በቀየው ባዶ መሆን ያሰሰው ቢወዱት ምን ያረጋል አገር ማስቱ አደል፡፡ የጊምባም እረኞች የውን ሰደት የቤቱን መፍረስ፣ የከተማውንም ጭር ማለት በማየት ይመስሳል፤

አህያ መጣች ተጭና ትሬ
አዲስ አበባ ብቻሽን ቅሪ

ያሉት፡፡ ሆዱ የሻከረው፣ ነገር የናወዘው፣ በእንባ ጭጋግ የተጋረደው ደሞ እንዲህ አለ፡፡

አልቅሱ እንላቀስ ጊዜ ያመጣውን
ሣቅና ጨዋታ ድሮ የቀረውን
አልቅሱ እንላቀስ ምንድነው ዝም ዝሙ
ያልተጐዳ የለም በልጅ በወንድሙ
ለቅሶ እንዳይለቀስ ተነገረ ዐዋጅ
ቲሄድ ያስለቅሳል እንኳን ሲሞት ልጅ
ኧረ እናንተ ሰዎች ለቆመው አልቅሱ
ሁለት ግሞች አሉ ጠገራ እሚያፈርሱ

አዘንም ተከዝንም አለቀስንም ሳቅንም፤ ተራብንም ጠገብንም፤ ተሰበርንም ተጠገንም፤ ተንገዳገድንም ተቃናንም፤ እንደምንም ተፍገምግመን እምናን ዘልቀነዋል፡፡ የዘንድሮውስ? ስሚሉት ፍራት ፍራት ስሚላቸውና ጥያቄ ስሚያቀርቡት በጥያቄ ሲመልሱላቸው እንዲህ ይላሉ፡፡

እምናንም አለፍነው እንዳይሆን እንዳይሆን
ደሞ መከረሚያችን ዘንድሮ እንዴት ይሆን?

ሌላው ደሞ እንተው ተወው ነገሩስ የሆነው እንዲህ ነው፡፡

ተጐድጓዳ ሥርፋ ይበቅላል ደደሆ
የፈራነው ነገር መጣ ድሆ ድሆ

ያምናን ቀን አማሁት ባፌ ለከት የለው

የዘንድሮው መጣ እጅ እግር የሰለው

ቀን ይወጣል ብየ ብጠብቅ ባስጠብቅ

እንኳን ቀን ሲወጣ ጨለማ ነው ድቅድቅ

የሚል ምላሽ ሲሰጥ እንደዚሁ ትይዘው ትጨብጠው ያጣች ግራ የተጋባች፣ ፍቅረኛዋ የራቃት፣ ኑሮው ያስጨነቃት፣ ብቸኝነት ያጠቃት፣ እንባ ያጠለቃት፣ አይዞሽ ባይ ያጣችው ነገሩ ያስደነቀ ያሳመማት፣

እንዲህ ያለ ነገር የጠፋ ለመላ

እንዴት ይለያያል ሰው ሳይጠላላ

ምነው አምና በምትኩ እንዲያ እንዳማረብኝ

ይህ የመንደር ልክፍት ሠርጾ ሳይገባብኝ

አሞኝ አሞኝ ውሎ አሞኝ ሊያድር ነወይ

ኢትዮጵያዊነቴ ጤና ሳይሆን ነወይ?

አለቅሳለሁ ባይኔ አብሳለሁ በጀ

እንደ ሰማይ ኮከብ ርቆኝ ወዳጀ

እንደ ራበኝ ውየ እንደ ራበኝ ባድር

ራቤን እኔ እንጂ መች ዐወቀው አገር።

እንዳለችው ሁሉ እንዲህ እንደ እሷ ሁሉም ነገር የራቀው ዐመድ ያጠለቀው ጉልቻ የምጣድ ላይ እንጉቻ የሆነው ነገር ያደቀቀው ሐሳብ ልቡን ያወለቀው፣ ሲቃ ያንቀው፣ ነገር ተሰንቅሮ ቀልቡን ሰውሮ፣ እንጀቱ አርሮ እህህን እዝሎ የሚናገረው የአዝማሪ ስንኝ እንዲህ ትላለች።

እንዴት ያረጉታል የሆድን እመም

ማጭድ አይገባበት በጅ አይታረም

ዓይን የታመመ እንደሁ ማየትን ይጠላል

ጥርስ ተጠናበት ተንቅሎ ይጠላል

ሆድ ብቻ አይመችም ውስጡን ያቃጥላል

በማለት እርር ድብኑን ሲተነፍስ፣ ሌላውም ፈጣሪውን ሲያማርር ሰውን ሲሰምን በሰውም ሲተማመን ይቆይና ቀልቡ ሲመለስ፣ በቅሉ ሲታደስ እንዲህ ሲል መሳሳቱን ያወጋል፡፡

ላንተ መንገር ትቼ ለሰው ነገርኩና
ላልቶ የነበረ ጠበቀ እንደገና
ባሳሳውእምቢ እሰኝ ደረቀና እንዝርቱ
ኳታችም አይደለ ከላይ ነው ጥመቱ
እሳቲ እናንተ ብሉ እኛስ እንቆያለን
ያርብ ሮብ ጦመኞች ጊዜ እንጠብቃለን

ይልና የሰውንስ ነገር አየሁት ለየሁት አንተ ሁሉም በጅህ፣ ሁሉም በደጅህ የሆንከው በረከቱን ወረድ ከርዝቁም አየት አርገኝ ያላንተ ማን አለኝ ሲል እንዲህ ይላል፣

አንተ ስጠኝ እጁ ሙሉ ሙሉ ቁና
የሰውስ ስጦታ አያጠግብምና

ይልና ለጠቅ ያረግና፣ እባክሽ እንቺ ቀን ቶሎ ቶሎ እለፊ

እግኝቶ ያጣ ሰው ይመስላል ቀጣፊ
ለታምር ሠራና ለታምር እቆየኝ
ድንቅ ነው ፈጣሪ ይህንን አሳየኝ
አምና ጃኖ ለበሱ ዘንድሮ ገተት
ይኸንን ያሳያል አብሮ መሰንበት

ሲል የሰው መሠረትን የእርስ በርስ መመቀኛኘት ያጠፋቸው ሰዎች፣

አህያ መጣች ተጭና ገሣ

ሸረኛን ሁላ እባክህ አንሳ የሚለውን የጊምባ አረኞች ግጥም እያንጉራጉሩ፣ የቡን ተርቲበኞች የሚመራረቁበትን፣ ዱበርቲዎች የሚያቃቅሙበትን፣ ሸሆች አንሳ የሚሉበትን፣ ካዳሚት ጀሊሳ የምትልበትን፣

የሐረጉን መንገድ ጠመዝማዛውን
ተሻግሬው መጣሁ ቦርከና ወንዙን
እንዲያነሳ ብዬ ያገር አዛውን
ቦርኬ ሙላ ኧረ ወንዙ ሙላ
እንድታነሳልን ሙላቃውን ሁላ
ገላግለን ያልንህን ገላገልከን ለካ
እምቢ አለ መሬቱ ሙላቃ እየተካ
በነካካው እጅህ እኒህንም እንካ
አርግልን ያልንህን አረከልን ለካ
በደረቀው ሰተር አርገው ነካ ነካ
አርግልን ያልንህን አርግልን ዘንድሮ
እንደ ፍርድ ቤቱ ምንድነው ቀጠሮ
የቃሉ ደመና አይሆንም ሰየጁ
እባክህ አንሳልን ተነንግዱ ልጁ

ሲል፣ አንዳንዱም ፍራት ያደነዘዘው፣ ሆዱን ባር ባር የሚለው፣ ከጥላው የሚጣለው፣ የሰውነገር የማይገባው ሙካሲፍ ደም፣

አርግልኝ ያልኩህን ታረግልኛለህ
ግን ትዘገይና ታስጨርሰኛለህ በማለት ጥርጣሬውን ይናገራል።
ቦርኬ ሙላ ኧረ ወንዙ ሙላ መሙላት ይሻልሃል

ያልሞላህ እንደሆን ማንም ይረግጥሃል የተባለውን የዘነጋ ቦርከና የደሴዋ ሰማይ ሲደማምን፣ ሰኔ ግም ሲል፣ ሐምሌ ሲጨላልም፣ ነሐሴ ሲያጉረመርም፣ ሲዘንብ አካቢ ዘራፍ ትልና ተቁልቁል ተንደርድራ፣ ዝቅዝቅ ተወርውራ፣ ዱውዶና ሮቢትን ገምሳ አሮኒማን ታክካ ሸረፍ አርጋ፣ ሆጤና አዘዋ ገደልን ሰንጥቃ፣ ቦቀቅሳን ቾፍ ወንጨፍ አርጋ ሽሮ ደንን ገላምጣ፣ አሰስ ገሰሱን፣ የሰው ንፋሹን የሀፈር እባሹን ጥርግ ጥርግርግ ሽክም ሽክምክም፣ እንቅ እንቅንቅ አርጋ ከቃሉ ዐፈር ደባልቃ፣ ቃሉን ጤና

ይስጥልን ብላ የአየር ማረፊያውን የሻንጓ አይታ የኮምበልሻን የጣሚዎን መንገድ አብሳ መንደሩን ዘልቃ የኮምበልሻን ሜዳ አጥሰቅስታ በባር ማሽላ ሞቃ ደምቃ ዛሬስ ቦርኬ ጤቅ ሠራችን ማሳና ቤቱን አደባለቀችው ሲባልላት ያልሰማ ሳገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ የሆነ፣

ዓባይ ጉደል ብሰው አለኝ በትሜሥ
የማን ሆድ ይችላስ እስተዛው ድረስ

የተባለለት፡፡ እያሞካሽ ጉብሎችን እያሻሽ፣ ሳዱሎቹን አምኝቾ ባባይ በጠና አመላከቸ ሽጬ እላለሁ ባዩን የተመለከተ ቃሉዬ ምነዋ ጃል ስንት ትውልድ የተሻገረበት ዝንት ዓለም የሚጠራበት ወንዝኮ አለን እንደውም፤

ገላህም አይሳሳ ዐዲስ ለመልበሱ
መገን ጥቁር ውሃ አለቀረም መፍሰሱ ይልና፣
ዐባይና ጣናን ወንዝ ነው ወይ ያልኸው
የወንዞቹን ንጉሥ ቦርከናን ባየኸው
ቦርኬ ሙላ ኧረ ወንዙ ሙላ ሳንቲም ይበጅሃል
አልሞላም ያልከ እንደሁ ይቀልዱብሃል
እንዲህ ደምና ደምና የዘነበ እንደሆን
እንኳንስ ሮቢት ሙጋድ ጭቃ እንዳይሆን
አለና ነገሩ ሲትዮዋ ቁጭቱን፤

እመሚትንቴ አድርጉኝ ከሳሳ
ቆይ አሳይሃለሁ ዐመሌ ሲነሳ

በማለት እንደተናገረችው ማለት ነው፡፡ ነገር ያደነዘዘችው ሆዳቸው የቆሰለባቸው ግራ የተጋቡ፣

ማንም ሰው አይገኝ ቀለል የሌለበት
ልብሱ ሽፍኖት ነው እንዳይታይበት ሲሉ ሌላው ደሞ፣
እኔማ ዘንድሮ ሆኛለሁ ጆርጆርቱ
ቢጠሩኝ አልሰማ ጨርቁን ካልጉተቱ ይላል፡፡

ቢነግሩት የማይሰማን፣ ቢያጥቡት የማይጠራውን የሰውን ምክር ዋዛ ፈዛዛ ሲያደርግ የሚታየውን፣

እየነገርናቸው እያረጉት ዋዛ

የተቸበቸበው የተሰጠው በዛ

ይሉታል፡፡ የቀደሞቹን ይዞ እሺ በጆ የሚለው ጠጅ ሣር ጉዝጉዞ፣ ዳማ ከሴ ነስንሶ፣ ቄጠማ በትኖ፣ አርቲ አሸኩቲ ይዞ ረከቦት ዘርግቶ፣ ፊንጃሉን ደርድሮ፣ እድሩሲን አቡንኛ ቡና አፍልቶ ዐቦል ጀባ ቶሃ ጀባ የሚለውን፣

ዐቦል ጀባ

እማይበጅን ገደል ይግባ

ምቀኛህ አንጋዳ ይግባ

ርዝቅና ጤና ይገባ

ቀና መንገድን

የሹም መውደድን ይስጥህ ተብሎ ሸረኛን ሸረረኛን ዓይኑን ጨለማ ጉልበቱን ቄጠማ ያርግልህ፣ ከሙጢ ሥጢ፣ ከቀባጣሪ ከወሬኛ ከሸውከኛ ከስውር መጋኛ ይሰውርህ ቡሃ ቃል የሞላ፣ ምቀኛህ የተኛ ያርግልህ፡፡ የሹም መውደድን ቀና መንገድን ሳንተ ያርገው፣ ሩጠህ የምታመልጥ ተናግረህ የምትበልጥ፣ ምርቃት የያዘለት ርጥማት የወለቀለት ርዝቅ የወረደለት ዐድባር አውጋር የወደደው፡፡

የነዋ ልጅ ቡና ሚያፈላው

አርቲ አሸኩቲ ይሸታል ገላው

አሚን የአሚን ልጅ አሚን የወደደው

የዘራው ይበቅላል ያድጋል የወሰደው ሲባልለት ቀልብ ያነሳውን ውቃቢ የራቀውን ርጥማን የለበሰውን ርዝቅ የራቀውን፣ ዐቅል ያልገዛውን ቀድረ ቀላል የሆነውን ኢማኑ ፈሶ ቀልቡ ተገፎ የሚታየውን ሽማግሌ የሚያናንቀውን ሲያገኙ፣

ገላግለን ያልንህን ገላገልከን ለካ

እምቢ አለ መሬቱ ሙላቃ እየተካ

ሕልቁ ታይደነቅቦ ቀን ታይጨልምበት
አበሻ በመላ ምክር ታይመክርበት
ወሎ በራብ አልቆ ሞት የበዛ እንደሆን
የጁን ነው የሚያገኝ የዛን ቀን ሰው አይሆን
አረኛ እንደሌለው ሜዳ ሙሉ ኩበት
ሕልቁ ይታመሳል በቀን በሌሊት
ሶላት ያበላሻል መብላት መጠጣት
ከት ብሎ መሣቅ ነጃሣ መንካት
ወይ በርሃ አልገባሁ እንደ አዳሉች ጊደር
ወይ በገና አልመታሁ ዐውሊያ ቲደረደር
አልም ብላ ቀረች ወሎን ያህል አገር
ላበሻ ብንቅም ብናስቅም ጠፋ መድኃኒት
ሀጅራው ቲሆን ኸይረል በረካት
እንዴት ያለች ዘመን እንዴት ያለች ወትት
ጭቃና ምስሴ የሚጠፋበት
የወታደር መንግሥት የሚሾምበት
አገር ቤት በሙሉ ሹመት አሚገባበት
ቡና በቢቾሪ የሚሆንበት
እህል በቆርቆሮ የሚቀናበት
በሬ ሽህ ብር የሚያወጣበት
ገበያ በሙሉ የሚጠፋበት
እንኳን ሌላ ነገር ውለታው አድፋስ
ይጠፋው ቲቀላ ሳቦል የሚጤስ
ላሚቷ ወተታም አላቢው ዕውር
እንዴት ያለ ቀን ነው የሚያደናግር

እስቲ ልንሳና ድርበቡን ሳጠንጥን
እየተወጡ ኸደ እያሌውን ውጥን
ማንም ተፈተሰ ሽማኔው ቅጥ አጣ
እስተ መጨረሻው መጠቅለያው ታጣ
በሬ እንደ ማሽላ እሚፈጭበት
በኩረንቲ መውቂያ ኮምበልቻ መሬት
ባንድ ወንድ በሥር ሴት የሚሆንበት
በሰማይ ደመና የሚበዛበት
ያው እንኳ አይገኝም እንዳው ነው ምኞት
ሀጅራው ቲሆን ኸይረል በርኛት
እለቾ ብርቱ ቀን አሰች በቀስት
ኢማሙ ይወድ ቃል ሁና እንደ ኩበት
ጭራሽ ትመጣለች ትቆማ እሚኳት
በነ ሊቀመንበር በሽንጉች ወራት
ያን ጊዜ ይበዛል ጦርና ዱለት
ደላንታም ይዋጋል በኩታ መሬት
እሥመራም ይዋጋል ኤርትራ እሚሉት
በሸዋ በደሴ የሚያልቀው ፍጥረት
ዐይዱን ይወቀው ሐይላ ይሙት
ተማሪ ወታደር የጦር ሠራዊት
የርብን ምልክት ልንገርህ ጥቂት
ሰው ይታደላላ ስንዴና መሬት
ደሞ ሦስተኛው ጀበርና ብረት
ሰው ይያያዛል ሐሲድና ውሸት
እስ በሱ መሂሰም ድርቅና ኩዳት

የኃይለሥላሴ ወታደሮች ወቅት
መከራቸው ትትሆን ዘጠኝ ዓመት
ለድሃ ቢመቹ አላቸው ስምንት
ላኪን ታልተመቹ ይላሱ ብትት
ማከተሚያው ይሆናል በአሥራ ሰባት፡
ምጣዱ ተጥዶ ይታመሳል ሕልቅ
እማሹም አይደክም እምሱም እያልቅ
ዋድላና ደላንታ ቲሠራ ቆርቆሮ
ጥሩ ይመስሰዋል ለልቡ ደንቆሮ
ሱሪ ባንገት አውጡ
የኂሊት ሩጡ
ወይ ድንጋ ፍለጡ
ወይ ሴት ጆምበር አውጡ
ታይሉም አይቀሩ
ሰዎች ይሀን ፍሩ
ዳኞች ይሾማሉ በየአካባቢያቸው
ቀበሌ እሚሏቸው የበላይ አካላት ደርጉች የሚሏቸው
ቲጠፉ አይታዩም እንደ ዳይሪ ናቸው
ደሞ ባገራችን ተንታና ሐዋይት
ተያዘ ሰው በቀር ብጣሽ ወረቀት
መግባት አይቻልም እፈለገበት
ፋና ታይተከል ማሾ እሚሉት
አወይ አሳዳጊ ዓይናቸው እያየ ዋ! ብሉ ወቅረት
ያን ጊዜ ይነዳል ውሃም እንደ እሳት
በቅሉም ትወልዳለች መሐኒቱም ሴት

ሸንበቆም ያፈራል ስጥቆም ቁም እንጨት
የሰው አገር ዛፍ ነው በሸርጥ ጆሃት
ምን ያጣላችኋል በመሬት ጉዳይ
አሁን ዘር ቲጠፋ ይቀር የለም ወይ?
በሰማይ ቀበሌ መሊኮች ቲዋጉ
ባጤ መባል ቀርቶ ይባላል በደርጉ
ያን ጊዜ ተዱአ እንዳትዘናጉ
መሬትና ሹመት እንዳትፈልጉ
እስትትሸልክ ድረስ ርብ የሚሷት
እንዴት ያለች ዘመን የጠናች ወራት
ያን ጊዜ ይበጃል ክልል እሚሉት
እንዳይገናኙ ተንታና ሆርማት
ታልያዘ ሰው በቀር ብጣሽ ወረቀት
ያን ይነዳል ውሃም እንደ እሳት
ያን ጊዜ ይበዛል ጦርና ዱለት
ደላታም ይዋጋል ቦረና መሬት
አላሽም ይዋጋል ኤርትራ ለሚሉት
በሸዋ በደሴ በትግሬ በጉንደር የሚያልቀው ፍጥረት
ሃዲዱን ያወቀው ሃያሱ ይሙት
ያን ጊዜ ከበረ አላህ የሻለት
ቀኑንም ሌቱንም እንዳው መወትወት
ይኸን ተናግረዋል በቁርዓን አያት
የኸንን ነገረኝ በሩስ የሚሉት
የኢፍራት ወንድም ነው በናትም ባባት
አበሻ ላም ሆኖ ወታደር ቲያልባት

ሸንበቆም ያፈራል ሰጥቆም ቁም እንጨት
የሰው አገር ዛፍ ነው በሸርጥ ጀሃት
ምን ያጣላችኋል በመሬት ጉዳይ
አሁን ዘር ቲጠፋ ይቀር የለም ወይ?
በሰማይ ቀበሌ መሲኮች ቲዋጉ
ባጫ መባል ቀርቶ ይባላል በደርጉ
ያን ጊዜ ተዱአ እንዳትዘናጉ
መሬትና ሹመት እንዳትፈልጉ
እስትትሸልክ ድረስ ርብ የሚሏት
እንዴት ያለች ዘመን የጠናች ወራት
ያን ጊዜ ይበጃል ክልል እሚሉት
እንዳይገናኙ ተንታና ሆርማት
ታልያዘ ሰው በቀር ብጣሽ ወረቀት
ያን ይነዳል ውሃም እንደ እሳት
ያን ጊዜ ይበዛል ጦርና ዱለት
ደላታም ይዋጋል በረና መሬት
አላሸም ይዋጋል ኤርትራ ለሚሉት
በሸዋ በደሴ በትግሬ በጉንደር የሚያልቀው ፍጥረት
ሃዲዱን ያወቀው ሃያሱ ይሙት
ያን ጊዜ ከበረ አላህ የሻለት
ቀኑንም ሲቱንም እንዳው መወትወት
ይኸን ተናግረዋል በቁርዓን አያት
የኸንን ነገረኝ በሩስ የሚሉት
የኢፍራት ወንድም ነው በናትም ባባት
አበሻ ላም ሆኖ ወታደር ቲያልባት

ያገር ቤት ሹማምንት ቲያመኑ ተላላት
የነቢ ሰው ጠፍቶ ሃይማኖት ቲሞት
እንዲታደርሰን ተንዲህ ታሰው ወቅት
ይመጣሉ እነዚያ ጨካኞች ደርጉ የሚሏቸው
ብቻ የሚሄዱ አሽከር የሌላቸው
ለንድ ቀን አይቀይም ደም ዐዋጃቸው
ጹኣ እድራጊ በቀር ሌላም አይችላቸው
ዝመቱ ምንገድ ሥሩ መሬት እኩል ከፈሉ
በዋቅ ወደስተፊት አትቁም ይላሉ
ተማሪ ወታደር የገጠር ሠራዊት
አበሻን ሊመራ ይዞ ሠራዊት
ጦርነት ሲያደርጉ በቀን በሰሊት
ተዙፋት ታሊጋው አረፍ ሳይሉበት
ሙማውን በቴና ትንሽ ታይበሉበት
ጠጅ ተዘንበሉ ጥቂት ታይጠጡበት
ተማድ ይነሳሉ አዬ ጉድ መጉዳት
ወሬያቸው ይጠፋል የደረሱበት
ደርጉች ኤርትራ ላይ ሦስተኔ ዘምተው
ሰውም ያጠፋሉ እነሱም ጠፍተው
በጦር ጨፈጨፋት ላይሬጋ መሬት
እንኳን አልደረሰን ትትነድ እንደ እሳት
ኢሥመራ ልጠፋ ገመድዋ ሲላላ
በሸዋ ከተማ ይኸለቃል በዓ
አክሱም በዚያን ጊዜ ትሆናለች ሌላ
ታትታይ አትቀርም ኢሥመራ እሳህ ቢሻ

በደም ተጨማልቃ ትሆናለች እርሻ
የዓለሙ ንጉሥ ዐዋጅ ያደርግና
ከነሠራዊቱ ከተቱ ይልና
ሀልቁ ይበራያል በደብ ይሰባሰብና
ዐረቡም ይመጣል እንግሊዝ ፈረንሳይ ይመጣል
በርብ ዐውድማ ላይ ሁሉም ይራኮታል
እኔ ያየትን እናንተም ባያችሁ
ሌቱን ባልተኛችሁ ቀን ባልዘነጋችሁ
ከርብ ያነሳ ወረኢሉ ድረስ
ምን ረጅም ሞፈር በክንድ አይጨረስ
ጨረቃና ጠሐይ ተራ ተገናኝተው
ደህና ተለያዩ ሕልቁን አስፈጅተው
አላህ ይሁናችሁ አላህ ይሁነን
ባስቸጋሪው ሁሉ እያስቸግረን
በራህመት ደመና ሸፍን ያድርገን
ይኸን የጊዜ ጉድ የጊዜ ዕድል
ይኸው ነገርኳችሁ ሸህ ሁሴን ጅብሪል
የደርጉትን ቂስዋ ታነሳንላችሁ
እንግዲህ ይበቃል አላህ ይሁናችሁ
በራህመት ደመና ሸፍን ያድርጋችሁ
ሸህ ሁሴን ጅብሪል ነኝ እኔ አባታችሁ
ሰው ይታደላል ብረት በነቂስ
አይታኮስበት እንዳው መታመስ
ደሞ ተዛ ወዳ የሚመጣውን
እስቲ ላውጋላችሁ ታልደብቅ ልኩን

ጠጉራቸው ሆጭራራ ጫማቸው ነጠላ
አላህ ይጠብቀን ከሚያመጡት በላ
ራስ ቁጥጥር ልብሳቸው አዳፋ
ቲወስደው ይታያል ሕልቁን እያዳፋ
በቤተል ምንግሥቴ ስተት ብሶ ገባ
እንዱ የማመዶ እንደኛው ተማደ
የሐበሻን መሬት ያረጉታል ባደ
በፊት ቲገቡ በደሴ በር ነው
በሸዋ እሚዘልቁት በሸላ በር ነው
ታቹንም ገደማ በደብረዘይት
ጦሩም ይከፍታሉ በቤተል ምንግሥት
መተኮስ ነው እዩ ምንም አይገኙ በቤተል ምንግሥት
ሁሉም ይጓድናል በየያሻበት
እስቲ ልዘያይር እንጦጦ ልሻገር
አፋቶ ደርሽ በዛው በባላገር
በጉጃም በር ላይ እኒህ የሚሏቸው
ጉተት ጉተት እሱ ሰው ታያቸው
ያንን የድንገት ጦር የሚከፍቱበት
ምኑም አይታወቅ ቅን ይሁን ለሊት
ያልቅበታልና ህልቁ በብዛት
በፈረንላይ ሜዳ በነጋሽ ዳገት
ተማሪው ታስኮላ ቂሱም ተመቅደሱ
ተፎሩጦ ይወጣል አውሰኝ ታይቀምሱ
እስላምም ተመስጊድ አንገዛም ብሰው ሁሉም ያምጣሉ
ኃያላን ምንግሥታት ሁሉም ይሰማሉ

ቲገቡ እንደ ትኋን ቲወጡ እንዳንበጣ ነው የሚሆኑት
ምጋዘን ይበጃል ብረት ማስቀመጫ ጥይት ለሚሉት
አቃጣዩ አይታይ በማዕና ክብሪት
ቲቀጣጠል ያድራል ቀንና ለሊት
አላህ ይጠብቀን ተንዲህ ያለው እልቂት
ጕጃም ተቃጠለ ታባይ እስታባይ
ትግሬ ቅጠል ይዞ ሊያጠፋው ነወይ?
ውሸት ዘረዘረ ሐቅ ዕድሜ ጨረሰ
እሚጠው ቀበሩት ሰባት ጉድጓድ ምሰው
እንግዲህ ሆድ ለሆድ አልተገናኝም ሰው
በቆላ በደጋ ነፋስ የነፈሰው
እየገሸለጠ ቤቱን አፈረሰው
ያን ጊዜ እሚሾመው ውሸት የፈራ ሰው
እባክህ ጌታዬ ሰባራ እንደ ደገና በነበር መልሰው
ምን ያለ እንዝርት ነው ውልቅ የሌለው
ሁሉም ስብስብ ነው ጠባቂው ማነው
ዘሐው ለሰለሰ ሽማኔው ተቆጣ
እየ ጉድ አሬ እስተ ወዳው ድረስ መጠቅለያው ታጣ
ሕመምንም ማውጋት ታመመው ሰው ጋር ነው
ለቦርከና ውሃ መንገሩ ከንቱ ነው
ዓመት ሁለት ዓመት ይቸገራል እንጅ
መልኩ በሠላሳ እንዴት ብሎ ያርጅ
እንደ ሐላ ዘመን እንደ ሐላ ወቅት
ተደባለቀ እሉ ጤፍና ዱቄት
ወይ አይበጠር አይነፋው ወንፊት

እንዴት ያለች ዘመን እንዴት ያለች ወቅት
ጭቃና ምስለኔ የሚጠቁበት
የወታደር ምንግሥት የሚሸምባት
እስቲ ልነሳና ድርበቤን ሳጠንጥን
እየተወው ኸደ እያሌውን ውጥን።
ራያና ቆቦ ሰርሻ ቲመንጠር
ደሴ ይቆረጣል የምባሎ ሞፈር
መሬት ዓይኗ ታሞ ትትደናበር
ባርባ ከንድ ገመድ ትሰካ ጀመር
ዑጋኒያ ታልቅና የማታ የማታ
ግበያ ይውሳል የስዋን ሽመታ
ዓይን ያሰው ያሰቅሳል ዓይን የሌለው ያርሳል
ዑድኒያ ልትሞት ጉድጓዷ ይማሳል።

ሐብትንም ለመንዘግ መብትንም ለመንጠቅ ሰቆ አሳስቶ መስሎ ተመሳስሎ መሆን እንዳለበት ሐቅ ነው። ለነዚማሪም ማሲንቆውን እንደት እንዲበላ፣ ቀልብ እንዲስልብ አርጐ እየመታ ያለው እንዲህ ነበር።

እንዲህ አርጐ ነው የሰው ሚስት ሲቀሙ
እወፍሮ ሥር ሁነው ዱቄት እየቃሙ።

ታያ ወጥታችሁ እትግቡ፣ ተቀምጣችሁ እትነሱ የሚሉ በበዙበት ጊዜ ከገቡ መውጣት፣ ከገኙ ማጣት የሌለበት ፈጣሪ ያዘጋጀው ቦታ መኖሩን የዘነጉ፣ እምላክ አበው ቀደምት አምላክ፣ ነቢያት ወሐዋርያት፣ አምላክ ፅድቃን ወሰማዕታት፣ መዓቱ የራቀ፣ ምህረቱ የበዛ የከብር ባለቤት የለመኑትን የማይረዳ የነገሩትን የማይረሳ መሆኑን ቸል ያሉ የፈጠረውን የማይሰማ የማይረዳ የመሰላቸው ሹመኞች እንደ ሰም እናቅልጣችሁ! እንደ እሳት እንጠፍጥፋችሁ፣ እንደ ሸክላ እንፈርክሳችሁ ሲሉ ድሃ ዘገር ባይነቀንቅ፣ ሳንጃ ባይወድርም እንባ ባቀረረ በሲቃ በተወጠረ ስሙና ፈጣሪውን እየዋ! ሲል ፍላት ከረትና ምጥቀት ባለው ቢቃላት በተዋበ ሰንኝ

በሰመረ እንጋገር፣

አቤት፣ አቤት! የሰማዩ ጌታ የምድሩ ባለቤት
ነገረኛ ካለ አውጣልን ከዚህ ቤት ይልና፣
እሱቲ ጡር ይከማች እሱቱ ጡር ይከማች
አይረባም ያሉት ሰው ቢረባ ምናልባት
እናንት መኳንንቶች ጡር አትናገሩ
ችግር እንደሆነ ቅርብ ነው አገሩ፡፡ ካለ በኋላ፣
አርሶ መብላትና ተኩሶ መሳት
አያደር ይፋጃል እንደ እግር እሳት
ስማይ ሙሉ ከከብ አድማቂው ጨረቃ
አገሩን አጠፋው ምስለኔና ጭቃ
ያምሳሲቀው ምጥማጥ ጭቃው ወደል ውሻ ምስለኔው ቀበሮ
አላስቀምጥ አለኝ ከተተኝ እሮሮ
ኧረ እነዚህ ምንቱ የሚሠሩት ሥራ
ታገርም አያስኖር ቤትም አያሠራ
ጉመኔን በጥሼ እርጥቡን በላሁት
እንዳላበስሰውም የጭቡን ፈራሁት፡፡

ተብሎ ነበር፡፡ መቸም መዓቱ የራቀ ምህረቱ የቀረበ የክብር ባለቤትና ግፍና በደልን እንባና ሐዘንን ቁጥሮና ሰፍሮ እንደ አስታተሩ ስትሮ ስትምህርት ሉተዘክሮ ቢሠራም ብትምህርቱ ሳይመለሱ ከከፋት ሳይታገስ ያየ ያስተዋለ ነገሩሁሉ ቢጠቅጡት እንበጭ የሆነበት ታዛቢ ግራ መጋባቱን እንዲህ በማለት ይተነፍሳል፣

የዛሬ ዘመን ልጅ ይቅር ምናባቱ
መከራው ነው እንጂ አይተርፍም ትልበቱ
እኔን የቸገረኝ አንድ ነገር ብቻ
እኔ የቁስ ልጅ ነኝ እሷ የቃልቻ

ከቾኀፈር፣ ከሹመኛ፣ ከቀማኛ የሚከላከል አለ በማለት ሹቅብ ይሰጣሉ፣ እንባ ይረጫሉ፤ እንዲህም ይላሉ፣

እርግልን ያልንህን እርግልን ዘንድሮ

እንደ ፍርድ ቤቱ ምንድነው ቀጠሮ

እጆብ እኛ እጆብ እኛ

ብቻችንን ቀረን እንደ መንገደኛ

ባንድ ወቅት እጤ ዮሐንስ ወሎንና ወሎዬን እንደ ደረቆት አመሱት፣ እንደ አሻሮ ቆሉት፣ እንደ ባር ማሽላ ሸለቀቁት፡፡ መግቢያ መውጫ ነሱት፣ ቁም ስቅሉን አሳዩት፡፡ ቡሩ ሜዳ ሸከፉት፣ ሐብተ ወልድና ስመ ክርስትና ተቀበል አሉት፡፡ የፈራ ተቀበለ፣ የሸለከ ሾለከ፣ የደፈረ አሻፈረኝ አለ፡፡ የበረታም መንገድ መረጠ፣ ወደ ጉረቤት ፈረጠጠ፣ ያኔ ሽህ ሁሴንም ይያዙና እጤው ዘንድ ይቀርባሉ፡፡ እጤም ቆፍጠን ብለው ኩራትና ንቀት በተሞላው ቃል ደጁም፣ ግቢውም፣ ሜደውም፣ ሸለቆውም፣ ዱሩም፣ ተራራውም የኔ ሳስጠራህ ምነው ቀልጥፈህ አልመጣህ ቲሉት፣ እኔማ አላህ ታላቅህ ወይት እምልጥ ብየ ነዋ! ቢሉምት ይጦፉና በል ወስደህ እጉርልኝ ሲሉ እንደ ጋጣ ከብት ዐጃኢብ ነው ይሉና ወዲያው፣

ሆሆ በሰው ንቡን ይሸፍር እንዳሆን

የሚሠራው ሥራ እንዳይሆን እንዳይሆን

ዝሆንም ቅጠሉን አንበሳም ሥጋውን

እስቲ እናየዋለን ታግሎ እሚጥለውን

ደጋውም ቁንጫ ቆላው ረሞጫ

የሰይድ አሽከሮች እጣን መቀመጫ

እሉና ሰጠቅ እርገውም እንዲህ አሉ፣

እንጉራጉራለሁ በየደረስኩበት

ዐውቁ አለሁና እንዳገኙሁበት

ቢከፋም ቢበጅም እያዩ ማለፍ ነው

ተመምከር በተቀር ድርጊቱ ከንቱ ነው

ማረዱ ከፋ እንጂ ደግነት አያጣም
እስላም የሚያርድ እንጂ የሚወድ አይመጣም
የፈራህ ሰው ጥፋ እኔ ግን አልወጣም
ይዘገያል እዩ ሰው የጁን አያጣም
መተማ ተኸደ ተመልሶ አይመጣም::

ህጀ ልናገረው ሳጤ ዮሐንስ
ፈርጀለት ነበር መቅደላ ቲፈርስ
እንዴት የነቢ አሽከር ይሆናል ርኩስ
የሰማም ሰምቶኛል ያልሰማም ያልቅስ
ዮሐንስ ንፉግ ነው የሚበላ አይወድም
የሰው ያየ ጊዜ ያረጋል ጉርድም ድም
ሆዳም አሳማነው ያየውን አይሰደም
ማዱም ሰብቻ ነው ሰው አያስቀርብም
ለጦር ግን ጀግና ነው ቢኸድ አይታክትም

ካሉ በኋላ፣ መጠንቀቁ ይበጃል ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ ማየቱ መልካም ነው ሲሉ የተናገሩት እንዲህ ሲሉ ነበር::

ያባን በቅሉ እሠሩ አጥብቁ እባካችሁ
ደሞ እንደ ዮሐንስ እንደጠፋባችሁ ሲሉ

ከበሌም፣ አገራችን ወሎ ለኛ መች አነሰን
አስቸገረን እዩ መጭ እየወረሰን አሉ::

እጤ ከዓለማዊው ተድላ ደስታ ርቀው ከሥጋ ድሉት ለነፍስ ብለው ዓለምን ንቀው ረግጠው የፍየል ሌጦ የበግ ደበሎ ለብሰው፣ ዳዋ ጥሰው ድንጋ ተንተርሰው ጤዛ ልሰው አፈር ነስንሰው በጾም በጸሎት፣ በስግደት፣ በውድቅት ተወስነው የፈጣሪን ቃሉን ተቀብለው ትዛዙን አክብረው የሚኖሩ እንዳሉ እያወቁ በሽሁ ላይ በደል መፈጸማቸው መከራ ማጥናታቸው፣ ጌትነቱ ለዘላለም የጸና ቅዱስ ስሙ ገናና፣ ምሥጋናው በሰማይ በምድር

ከምላ ፈጣሪ ጋር መጣላትና መጋፋት መሆኑን መዘንጋታቸውን ልብስ አላሉም፡፡ ፈጣሪ በደጋጉች ላይ አድሮ የሚሠራው የረቀቀ ነውና! ቢሉ ታዛቢዎች፤ ሸሁም ምነው አጤው ሰበር ቢሉ? አባት ልጅ ቲያጠፋ የሚመክር፣ የሚዘክር፣ የሚያስተምር፣ የሚያርም ነው፡፡ ሹምም ጭፍራ ቲያበላሽ የሚያስተካክል፣ ገባር ቲያፈርስ የሚያሳምር ነበር፡፡ ታዲ ምናስ አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ ቢያልፉ ወይስ ነገሩ፣

ገብርበሰው ይገብራል ደሃ
ለሚሞቀው ጠሐይ ለሚጠጣው ውሃ

እንደሚባለው መሆኑ ነው ይሉና፣

ዓባይ በጣና ላይ መኸዱ ለምን ነው
ትንሹ ቲያጠፋ ትልቁ ቲያልፍ ነው ማለት!

የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል ይላሉና አበው ለአጤስ ምነው ርጋታውን ቢሰጥዎ? ዐደብ ቢያከልልዎ? ምነው ቀልብ ባያነሱ የፈጣሪን ነገር ባይረሱ፣ ደሃን ባያምሱ፣ ቀየን ባያፈርሱ ርግማን ባያፈሉ ይሉና፣

ጥንስሱ ፈሳና ሰበረው ጋኑን
አሁን ማን ያቀዋል የሚመጣውን
አንቱም ሽጉጥህን ጠበንጃህን ይዘህ እኔም ጫቱን ይዠ
እጥልሃለሁኝ ገዝግገኼ ገዝግዤ ካሉ በኋላ ሰጠቅ አርገውም፣
ዕድሜውን በሙሉ ተኔ ተተጣላ
ደንዳናው ኢማኑ ይሆናል ነሁላላ
አንተም ዕድሜህ አጭር ወይ ፍሬህ አይገዛ
እንጨት ከደረቀ ቢቀቡት አይወዛ
ሐበሻ ክፉ ነው አይምሰልህ ዋዛ፡፡ ይሉና እክል አርገውም፣
እስላም የሚያርድ እንጂ የሚወድ አይመጣም
የፈራህ ሰው ጥፋ እኔ እንኪን አልወጣም
ይዘገያል እንጂ ሰው የጁን አያጣም

እየጣርህ ክሬ መቼ እጄ ትላለህ

መመለስህን እንጃ እንጂ ትቀራለህ

በደርቡሽ ጉራዴ ራስክን ታጣለህ ነበር ያሏቸው።

እንደ ሸሁ ያሉ በትህትና ልዕልናን የተላበሱ፣ ንግግራቸው የሰመረ፣ ምራቃቸው ያማረ፣ አካሄዳቸው የቀና መንፈሳቸው የጠና፣ ቸርነቱ ትልቅ ትዕግሥቱ ምጡቅ መሆኑን በውል የተረዱ አገር ከጥፋት ሰው ከስደት፣ ሕዝብ ከመቅሰፍት የሚድነው በጾም በጸሎት በምህላ በስግደት መሆኑን ያስተምራሉ ይመክራሉ። እንደ አሊሞቹ ሁሉ የጊዮጊ አረኖችም

አህያ መጣች በቀስታ ብላ

ዱካህን ቀጥል አዳሜ ሁሉ

በማለት ጸሎት ከመከራ እንደሚያወጣ ከአደጋ እንደሚሰውር ሲያውጁ፣ ሸሁም ለሀገር ሰላምን ለሰውም ፍቅርን፣ ለታመመ ሽረትን፣ ለነጋዴ ወረትን፣ ላጣም ማግኘትን፣ ለአርሻ ምርትን፣ ለላሞች ወተትን እንዲሰጥ ጸሎት መጸለይ ደግ መሆኑን ይናገራሉ። ጸሎት እንኳን ከፎከረ ከወረወረ ማዳኑን መአትን ማራቁን፣ ምህረትን ማቅረቡን ያስተምራሉ። ጸሎት ቁጣን ያበርዳል፣ ጥላቻን ያርቃል፣ ፍቅርን ያጠነክራል፣ ኃይልን ይሰጣል፣ በረከትን ይሰጣል፣ ረድኤትን ያወርዳል። ጸሎት ከብዙ ጣጣ ፈንጣጣ ያወጣል።

ስለዚህ እንደ በደላችን እንደ ኃጢአታችንና ስንፍናችን ብዛት ሳይሆን እንደ ቸርነትህ ይቅር በለን ማለት ተገቢ እንደሆነ ሸሁ እንዲህ በማለት ነበር የተናገሩት፣

ዱአን በቀኝ እጅ ጨብጦ መያዝ

የዛን ቀን ያወጣል ከብዙ መዘዝ

እየዋ ልንገርህ እንዳትል ፍዝዝ

የሐበሻ ልጆች ተዉ ዱአ አድርጉ

ተክፉ ተደጉ ያወጣል በወጉ

ለሐቻይቱ ዑዱኒያ ሁሌም አደግድጉ

ዱአን የጠበቀ አያይም መከራ
ነቢ ተናግረዋል የጠይባው ሙሸራ
አየዋ ልንገርህ ሁን እንዳባትህ
በዱአ ተጥናና ሳንተ እንዲበጅህ
ለሰው ትተርፋለህ እንኳን ለራስህ
የዑባዳ ራሱ ዱአ ነው ብለዋል
ምኩል ኢባዲቱ ብለው ተናግረዋል።
በሰማይ ቀበሌ መሊኮች ቲያወጉ
ባጤ መባል ቀርቶ ይበላል በደርጉ
ያኔ ተዱአ እንዳትዘናጉ
መሬትና ሹመት እንዳትፈልጉ።
ቁርባን መድሃኒት ነው
ዱአ መትረየስ ነው
ሙኽፍ አንባ ነው
ዐደብ እንዳጥር ነው
አጥር ተተጣስ ሁሉም መፍረሱ ነው።
በጧትም በማታ ተውራንን አታብዙ
ዱአ መዳኒት ነው አጥብቃትሁ ያዙ።
ዐደብ ራሱ ዱአ ነው ብለዋል
ሙእሚን እንዳት ይኸን ተናግረዋል
የነቢን ሰለዋት ገንዘቤ በሏት
ትደርሳለችና የመከራ ለት
ነገር ቲቅመዘመዝ ቲሻገር እንደ ትል
ምነው ዘመድ ወደጅ ዱአ አትል ዱአ አትል
ዱአ መዳኒት ነው ለጀኒያ ላኬራ

ጴጥሮስን የጠበቀ እያይም መከራ

ነቢ ተናግረዋል የጠይባው ሙሽራ።

ከላይ የተባለው ሁሉ በጾም በጸሎት፣ በፍቅር በትህትና፣ በየዋህነት በትዕግሥት ተጠምዶ መኖሩ ከሐሣር ወደ ክብር፣ ከረሐብ ወደ ጥጋብ፣ ከስደት ወደ አገር ቤት እንደሚያሸጋግርና ዓይን ያላየውን፣ ጆሮ ያልሰማውን ፀጋና በረከት እንደሚያጐናጽፍ የተናገሩት ነው። በተሰሎንቄ 6÷5-17 ላይ ጳልዩ ሳትታክቱ እንዳለው ሁሉ ማለት ነው። ጸሎት የልቦችንና የአዕምሮችን ዝንባሌ ነውና፣ ጸሎት በሙስሊሙም ሆነ በክርስትናው እምነት የመጨረሻው መሣሪያም ነውና!!

እግዚአብሐር እንዴት ያለ አምላክ እንደሆነ ለመረዳት ብትሻ ይህን አድምጥ!!

"እርሱ በክፉዎችና በበጐዎች ላይ ፀሐይን ያወጣል፣ በፃድቃንና በኃጥአንም ላይ ዝናቡን ያዘንባል" ማቴ 5-45

አዎን! ሰማይን ያለ ዋልታ ምድርንም ያለ ካስማ ለዘረጋ ላቆመው አማን አውሎ አማን ለሚያሳድረው፣ ጨለማውን ገፎ ብርሃን ለሚያጐናጽፈው ጌታ አቤት ማለቱ ከመከራ፣ ከኪሣራ እንደሚሰውር ሳይታሰም የተፈታ ነው። በመሆኑም የእህልን መጥፋት፣ የሰውን መክፋት፣ የሚሸመት የሚቀና መታጣት፣ የርሃብን መግባት፣ የሐዘኑን ብዛት ጊምቢዎች እንደተናገሩ እንዳስተማሩ ሁሉ ዝናመ ምህረቱን፣ እህለ በረከቱን ሰጥቶ፣ በረድኤቱ ጐብኝቶ፣ ልመናና ምልጃን ሰምቶ፣ ሐዘንና ስደትን አንስቶ፣ ርሃብ ጠፍቶ ጥጋብ ተተክቶ፣ ምርት ሞልቶ ልቅሶ ቀንሶ፣ ሣቅ ተተክቶ፣ ሜዳ ሸንተረሩ፣ ፈፋ ባይሉ አረንጓዴ ለብሶ በአበባ ተውቦ፣ አዝመራው አሽቶ፣ ፍሬው ጐምርቶ እህሉ በጐታ ምግቡ በገበታ ሞልቶ ሕዝቡ ተደሰቶ፣

እንዴት ያስደስታል የባላገር ኑሮ

ወተቱ ተጓዳ እሸቱ ተጓሮ

እንደምነው ወሉ የጀነቱ ምስል

ያፈራው ቲበላ ያሸተው ቲበሰል።

ይል የነበረበት ጊዜ ተመልሶ መምጣቱን፣ ፈጣሪ ቃል-ኪዳኑን ማደሱን፣ ፊቱን መመለሱን፣ በልግና መኸር መታፈሱን ጊምባዎች የተናገሩበት በምሳሌያዊ ቃል እንዲህ የሚል ነበር።

እሀይ መጣች ተጭና እምቧይ
መኸር ዘለቀ አገሩን ሲያይ
እሀይ መጣች ተጭና ሽኛ
በልግና መኸር ተጋርሮ ተኛ
እሀይ መጣች ተጭና ሞፈር
ቅቤ እንደ ጭቃ እህል እንዳፈር።
እሀይ መጣች ተጭና ኮት
ወደፊት አለ የላም ወተት
እሀይ መጣች ተጭና ወርቅ
ብዛቱ መተጓስ አትጨነቅ
እሀይ መጣች ተጭና እንቅብ
ችግርም የለ ሆኗል ጥጋብ።
እሀይ መጣች ተጭና ቀንበር
ይስመልሷል የሸገሬ አገር
እሀይ መጣች ተጭና ምንበር
የከኔ ሀደም ቤት ፈርሶም አይቀር
እሀይ መጣች ተጭና ከሶ
ችግር ሞቶ አሉ እንኳድ ለቅሶ
እምና ሐቻቸና ብሬን ጨርሶ።
እሀይ መጣች ተጭና ዳቦ
ወቅቱ ዛሬ ነው ቶሎ ቶሎ ረስ
እሀይ መጣች ተጭና ድግር

መሬት የራስህ ተው አትሽበር
እህያ መጣች ተጭና እንጀራ
ተበልቶም እያልቅ ያለው አዝመራ።
እህያ መጣች ተጭና ዛላ
ጊዜው ደግ ነው እያረስክ ብላ
እህያ መጣች ተጭና ርጎብ
እንገት እስካንገት ሆኗል ጥጋብ

ሲሉ ገበሬም በተራው፣

በሬዬንም ሽጬ ጋቢዬንም ሽጬ ሱሪየን ሳስማማ
ኢሕአድግ መጣልኝ በነጠላ ጫማ
ይኸድ የነበረ እስከትሱ ውሻ
ተንግዲህ ቀረለት ሞፈር ዘመት እርሻ
የራበህም ብላ የጠማህም ጠጣ
ተዚህ የተሻለ ምንም ቀን አይመጣ

ብሎም ነበር። ከሰማይ ርዝቁን፣ ከመሬት ወርቁን! ከጉሮ ምርቱን! ከወጪት ፍትፍቱን ማፈስ፣ መዛቅ የሚቻልበት ወቅት መጣ! ሜዳው ገደል! ፍርዱ ገምድል ሆነ እንጂ! ያም አለ ይህ ሽሁም ሆኑ ጌምባዎች ታዛቢም ሆነ አዝማሪ በአገር ላይ የሚወርደውን መዓት፣ በሰው ላይ የሚደርሰውን መቅሰፍት ልቅም አርገው ተናግረዋል። ዝናብ ይጥላል ወይ ቢለው እንደ ደጅህ እየው እንዳለው ሁሉ! የርሃብ የጥማቱን፣ የበሽታ የስደቱን የቤት ማጣት የኑሮ ውድነትና የውሸት መጉልበቱን አሳምረው ጨኽዋል። እያንዳንዱም በቤቱም በደጅም፣ በማጀትም እያየው እየኖረውም እያንጐራጐረውም ነው።

ሽሁም ጌምባዎችም ሆነ ገበሬዎች ያለፈውን በማዘከር ብቻ አልተወሰኑም መጪውንም ጭምር እንዲህ በማለት ነበር።

ቀኑም ወራቱም ተወስነላችሁ
አደራ እንዳትኸዱ በኔ ይሁንባችሁ

የራህመት ደመና ሸፍን ያርግላችሁ።
የርብ መከራ ጉዱ ዐጃኢበት
ነቢ ተናግረዋል በይራል በራይት
ከቶ ነፋስ አለች አበሻ መሬት
ፍጥረት የምትጨርስ በቀን በለሊት
ማፅናውን ልንገርህ ንፋስ ያለበት
ከጦሩ መሐል አለና ድንገት
ሽብርና ጭንቀት የሚበዛበት
የሚደርስበትን በሩቅ ስንናገር
ስንቶችን ምን ይሆን ስንገባ ታፈር
ከጦሩ ወዳንዲያ ሰችው ሰዓት
ጦሩም ከመከራው ከጭንቁ ብዛት
ምናለበት ቢተርፍ ከስምንት ጥቂት
የአንድ ላም ወተት
የአንድ ማሳ እሸት
ይበቃ ነበረ ቢደረስ እዛ ዕለት
ይታይ የነበረ መስሉ እንደ ጠላት
አይገኝም ዘመድ እንደ መድሃኒት
ከላይም ንጉሡ ከታችም ንጉሡ
ከቀኙም ቢነፍሱ ከግራም ቢነፍሱ
መቅረት የለበትም መሐመድ ኢያሱ
በእናቱ ዐረቢያ በአባቱ ሐበሻ
እጅግ ዘመን ኑሮ በጫካ በዋሻ
የባዕድ አገር ሲሆን የሰው መሸሻ
ወላሂ ኢልም ነው የባሮቹ ጋሻ

እባክህ ጠብቀን እደራ በሉት
መድሃኒት ይሆናል የመከራ ለት
ሬሳ ይበዛል የሰውም የከብት
ሴት ትለቅመዋለች ያን ጊዜ ብረት
የርብን መንገድ ስንቱን ልንገርህ
በሰማይ ይዋጋል ምድሩ ሲያጅብህ
የርብን ምልክተ ልንገርህ ጥቂት
ልብ እላህ ቢሰጥህ የምትይዙት
መሬት የሚከጅል ደሞም ልብስ ጉርስ
ጉባዔ እንገናኝ መቅደላ ድረስ
ይህንን ይልና ጡሩንባ ይነፋል
የጡርምባው ብዛት ሦስት መቶ ይሆናል፡፡
እንኳንስ ያለው ሰው ትንሽ ልጅነት
ሽማግሌ ባልቴት በምርኩዝ በከብት
ጡርንባ ነፍቶ ዐዋጅ ያደርግና
ይቆላዋል ከዚያ መሐል ያደርግና
ትንሿ ፍሬ እሰች ባቂላ እሚሏት
ውሎዋን ቢቀቅላት የማይነካት
የርብን መከራ ስንቱን ልንገርህ
ቂያሚይ ቀን ይመስላል ገና ሲቀርብህ
የርብ መከራ ትትመጣ ድንገት
ሀሌቱ ይሸበራል እንደቂያሚያስት
የሚያጉል ዘመድ የናት ልጅ ያላችሁ
ታንጀት የምትወዱት ወዳጅም ያላችሁ
በዱአ ጠብቁት እንደ ኸይባችሁ

ዘመኑ ሲደርሰው የአፍ ኢሉ ማኢሻ
ዐዋጅ ብቻ የሳል ቀን ጠፍቶ ኢሻ
በሱ ይበራል የህልቁ ማኢሻ
ለምቹም አሳዩ እንዲህ ያስ ኑሮ
ይቀሰባል ጤፍ ውሻ ድመትና ዶሮ
ሚዘጅ ሲሞላ የህልቁ ማይሮ
ጥቂት እነሳሁኝ የደርጉችን ቋሳ
ሙሐመድ ንጉሡን እስኪ ጥቂት ላንሳ
ተእሥመራ መሬት ነው እሱ የሚነሳ
ትከሻው ሰፊ ነው ራሱ ከባዳ
የቀሬሶች ዘር ነው የአበሻ ይሁዳ
ከእሥመራ መሬት ድንገት ይነሳና
የዐረብን ዐውሊያ ተራ ይደርስና
መካ መዲና ላይ ሐጂ ያደርግና
ተሻግሮ ይመጣል በጉንደር ይልና
በቤገምድር ብሎ ተንታ ይገባና
ደብሩን እስከፍቶ አዛን ያደርግና
የጃምእን ሶላት እዛው ይሰግድና
ቡናውን ያስፈላል ይፈላልጥና
ለሚያዝያ ጊዮርጊስ ለማንበት ልደታ
አዛን ያደርጋል መቅደሳና ተንታ
ዐውሊያው ሲኸድር እዚያው ነበርኩ እኔ
ደላንታ ይዘልቃል ያረቦች ምስሰኔ፡፡
መሬት ትበጃለች ሆና ባስተራ
ትትሠራ እየናት መቅደላ በኖራ፡፡

በስተፀሐይ መውጫ አለ የሚሉት
እኔን የሚመስለኝ በማመደች ቤት
ያሥመራው ባላባት ሙሐመድ ደያስ
የሚሄድበትም በለቦራ ፈረስ
ያበሻን ሀውሲያ ተራ የሚያደርስ
ዐበሻን አድርሶ መቅደላ የሚያደርስ
ዋሂድ ቀሃር በሃርሽ አደባባይ በራህመት
ሲያወጉ ሰማሁኝ ጉድ ዐጃኢበት
የንፋስ በሽታ ይመጣል ድንገት
ህልቁን የሚጨርስ በቀን በለሊት
በሻርቅ ዝሁር ነው የሚዘልቅበት
መዳኒቱን ንገረኝ ብየ ጠየቅሁት
ሌትም ሆነ ቀን በዱአ መጽናት
ደግሞ ሁለተኛ የቁርዓን እያት
ሰፊእ ነይቶ ሁልጊዜ መቅራት
ደሞ ሦስተኛ ተህሊሊ መጠጣት
ሠላሳ ናቸው የተህሊል እያት
ማር ጋር ድብልቅ አርጉ መጠጣት
ለይተህ ንገረኝ እስተማመሙን
ሲያመን እንድናውቀው ሲፈትል ወስፈን
እኩሉ ራሴን ነው እኩሉ ልቤን
እኩል ጀርባዬን እኩሉ ሆዴን
እኩሉ እንደ ከብት ሽፈኑት ፀቅሉን
እንዲህ አድርጉ ነው ሲያድሰው መናን
እንበላው ንጉሥ ይገዛል ለስድስት ዓመት

ለየቃ ትመሳለች ደግሞ እንዲት ሴት
ቁጥር የሆነ ዘጠኝ ዓመት
ለየ አምዝዘ ማግባር የባ ወራት
ከዛ የደረሰ እሳህ ሽቶስት
ዘንም ሐሳብ የሰው በዚ ጋው ወራት
ጥቂት ከሰብ እርጉ በበዘ ማምረት
ዝሆ እንዳውድማ መብቅ ባባበት
መሐመድ ኢደስ ቁብ የተባለን እሥር ይነግንያል
ያልታወቀውን ሰው እስ ህውቶት ያሰትባል
ችግር ጠፍቶ በስ ሁስ ያፈፈርጎል።
እበን ተዘርግቶ ባላማ ተሰፋፍቶ
ስድስት ዓመት ይገባል ደህና ጤለደ ወጥቶ
ስቃይና መከራ ይታያል አብቅቶ
ያገሬችን ሰምች ህደው በሰው አገር
ጠፍ ትሆናለች ደህች የኛ አገር
ይቆረጥባታል የምባሙ ምፈር
ሰብስም ጉርስም ቢሆን ሞልቷል በዛ ወቅት
ሜዳውን ይሞላል ውዴታና እገዛት
ዛፍ ያዋ እንደሆን እሸግር ድንገት
ና ብሎ ይጠራል የሰው ልጅ መስሉት
ወዳያውኑ ያልፍና ችግርና ጭንቀት
ደጋበሩ ይበል ቃል እህ ብላ ወራት
1300048 ሂጅሬው ሲሆን ለይድ ማዳት
ሙሐመድ የኑር ልጅ ነው ያሰነፍከት
ያበሻ ቀበሌ ደላንታ መሬት።

ግጥም የሰውን ስሜት ወጥሮ ያንባቢና ያድማጭን ስሜት ኮርኩሮ አዕምሮን ሰርስሮ ወስዶ መሰስ አርጉ፣ አንባ አስቀርሮ፣ ልብ ሰውሮ፣ ዐቅል ሰቅሎ፣ በሣቅ ፈንቅሎ፣ ዓይን አስድሶ፣ አፍንጫ አሳብሶ፣ አፍ አስከፍቶ፣ ጥርስ አስገልፍጦ፣ በዐጃ ኢበታ የሚዘመዘም ነው።

በግጥም ሰውም ወንዙም ሣሩም ቅጠሉም ተራራውም ሜዳውም ሽለቆውም ዋሻውም ይሞገሳል፣ ይወቀሳል፣ ይከሰሳል። እጥር ምጥን ባለ አሰኛኘት እጅግ ብዙ ይባላል። ግጥም በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በቃልም ይጠናል። እንደ ዜማም ይዜማል ይንቀረቀራል። በዚህም ሸህ ሁሴን ጅብሪልና የጊምባ ዕረኞች ይጠቀሳሉ። መጪውን አሳይተውበታል፣ ወጪ ወራጁን፣ ሂያጅና ተመላሹን አመላክተውበታል። ረሃብ ጥጋቡን፣ ጥፋት ልማቱን፣ ክፋት ደግነቱን፣ ሞት ሽረቱን፣ ሐዘን ደስታውን አሳምረው ተናግረውበታል።

ፊደል ቆጥሮ፣ ነገርን መርምሮ መናገር ለሚችል ከታሪክ እንዲያመሳክር ከአበው እንዲነጋገር እነሆ! በስንኞቻቸው ሲያንደረድሩት ተመልክተናል። እየሆነ፣ እየተደረገና እየኖርነውም ያለውን አኗኗር ለማጣጣም በሚያስችለው መልኩ እንዲህ ተናግረውታል።

በሰማይ ቀበሌ መሊኮች ቲያወጉ

ባጤ መባል ቀርቶ ይባላል በደርጉ

ቱዎድሮስ አንሰቶ ተፈሪ ድረስ

ዘመኑ ያበቃል የዘውድ ንጉሥ

በምርጫ ታልሆነ የለም የሚነግሥ

ግን ሕልቁን እየሁት ብዙ ቀን ቲያሰቅስ።

ያሉት እጅግ ግርም ድንቅ ያሰኛል። ሁኔታችንንም ቁልጭ አርጎ ያሳያል። እነሆም ነጋ ጠባ እየየ፣ መሸ ባተ ወየው ይላል ማለታቸው ዛሬ ላይ ቆመን ስናየው ካነጋገራቸው ዝንፍ ካባባላቸው ውልፍት የለ ነገር የለም፣ ታዳ ይኸ ዐጃኢብ አያስብል ይሆን?

የሸሁ አነጋገር አስደናቂነትማ መች ከላይ በተባለው ብቻ ተደግቶ ጠላትን ድሰው፣ ነፃነትን አላብሰው፣ ዳር ድንበር አስፋፍተው፣ ሥልጣን

አስገዝተው፣ ትምህርት ዘርግተው፣ ኢትዮጵያዊነትን አፅንተው፣ አንድነትን አጠናክረው፣ በትንሽ በትልቁ ተወደውና ተከብረው ለረጅም ዘመናት ሲመሩ የኖሩት የንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሥልጣን ዘመን አከታተምና ጀምበር አጠላለቅ ሁኔታን የተናገሩበት የስንኝ ቋጠሮ በእጅጉ ዐጀብ! የሚያሰኝ ሲሆን እንዲህ ይላል፤

ትልቅ ሰው ቲናገር የለበትም ውሸት
የተፈራን እሊጋ ተማሪ ጣለበት
ቲገዛ ቲነጻ ቲመክር ቲያስመክር
ቲያጣላ ቲያዋቃ እንዱን ታንዱ ጋር
ይደርሳል ወቅቱ ሰማንያ ቲሞላ
ወየት ይደርስ ይሆን ተፈሪ አባ መላ፡፡

ይሉና እያይዘውም፤

ተፈሪ መኮንን እሊጋው ደህና ታስ አሽከር ታይሰፍርበት
ልጆቹን ቢተካ እንዴት ባማረበት
ሕልቁ ታይደነግጥ ቀን ታይጨልምበት
አበሻ በመላ ምክር ታይመክሩበት

ካሉ በኋላ ሰው የዘራውን ያጭዳል፤ በቆፈረው ጉድጓድ ይገባል፤ በሰፈረው ቁና ይሰፈራል የጁንም ያገኛል ሲሉ ሕዝቡን ያስደነቁበትና የንግግራቸውና የድርጊቱን ተፈጻሚነት ያረጋገጡበት፤

ወሎ በራብ እልቆ ሞት የበዛ እንዳሆን
የጁን ነው የሚያገኝ የዛን ቀን ሰው አይሆን
እረኛ እንደሰሰው ሜዳ ሙሉ ከብት
ሕልቁ ይታወሳል በቀን በሰሊት

ይሉና ለጠቅ አርገውም፤

ቀጥሳ ነገሥቸ ዘውዲቱ እሚቢት
እምሳያ የለሳት መልኪት ትታይዋት



Scanned with CamScanner

የራስ መኮንን ልጅ ተፈሪ አሚሴት

መቃ ሥራ ሠርቶ ገሉ ቀበራት።

እቤት ውስጥ ቀብሮ መደብ ሠራበት።

አበው ቢመክሩ ቢዘክሩ አልሰማ እሰማ የሚሉትን "ምከረው ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው" የሚለውን ይተርታሉ። ምክሩን ቁብ ያላሉትን ምርቃትንም ቸል የሚሉትን ቢመክሯት አመማት ቢያጠምቋት ባለባት የሆኑትን ምክሩን ንቀው አናንቀው እታርጉ የተባሉትን አድርገው ጉዳቱ የደረሰባቸውን እንዲህ ይሏቸዋል።

ሉጋው ሸቦዬ

የሜረው እሳት ሲያጋየው ታዋ የሆኑት ወደ ቀልባቸው ሲመለሱ ጥፋታቸውን ሲያስታውሱ፣

እየየም አትበሉ እንደው ቅበሩኝ

ሳቀው ገብቻለሁ ዘመድ ሲመክረኝ።

የሚለውን ሲያንጉራጉሩ የሸማግሌን አርቆ ተመልካችነትና አሳቢነት መራቂነትና አስታራቂነት ቁብ የማይሉ ከድጡ ወደ ማጡ የኼዱትን ስናይ ከገቡበት ማጥ ከወደቁበት አዘቅት መውጣት ሲሳናቸው ልዳማ ሲጠብሳቸው መውጫ ቀዳዳ መሮጫ ሜዳ መሸሸጊያ ጓዳ ሲጠፋባቸው፣

ጉትተን ጉትተን ያመጣ ነው አሌጋ

ወይ አያስኮረትም ወይ አያዘረጋ

ይሻለኛል ብዬ አሌጋ ብለውጥ

የባሰ ሆነብኝ የሚጉረብጥ

ኮሌጅ እንጨት ስበር ፖሊስ ውሃ ቅዳ

ጉትተህ ጉትተህ ባመጣኸው ዕዳ። የሚል እሮሮ ያሰማሉ። ኑሮ እንደ ሬት የመረረው እንደ ኮሶ ያንገሸገሸው ያባቶቹ ወኔ የቀሰቀሰው ደግ፣

ይሆነኛል ብዬ ያበፋሁት ሱሪ እላራምድ አለኝ

ቀድጆ ቀድጆ ልጣለው መሰለኝ ሲል ይደመጣል።

ሴትዮዋ ወዳጇ ሲለምናት ሲያባብላት ንቃ አመናጭቃ ከሄደች በኋላ

ነገሩ የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ ሲሆንባት፤

ይበለኝ ይበለኝ ይበለኝ በጣም

እንዲህ ታላረጉት ዕብድ አይቀጣም፡፡

እንዳለችው ሌሎችም እንደ እሷው እያልጐመጐሙ አንገታቸውን ደፍተው ጉልበታቸውን ታቅፈው፤ ቁጭታቸውን አፍነው፤ እንባቸውን እያፈሰሱ፤ መሬት በስንጥር እየማሱ ነበርን እያስታወሱ ይኖራሉ ሽሑም የሚነገረውን ያልሰማ፤ አጨብጭቦ እንደሚቀር በኅብረተሰብ ውጣ እንደሚባል በእንዲህ ዓይነት አባባል ነበር የተናገሩት፤

ፍየል ግዛ ቢሉኝ ማዳቋ ገዛቸ

ስንዴ ግዛ ቢሉኝ እንክርዳድ ገዛቸ

ገብስ ሸምት ቢሉኝ ወበሉ ገዛቸ

እንደ ገባህ ውጣው አሉኝ ዘመዶቼ በማለት፡፡

ወቅቱ ዋሾቱ መክበር፤ ቀላምዶ ማደር፤ ጫት ይዞ መዞር፤ የበዛበት በመቃም አቅል የሚሳትበት፤ ጤና የሚታጣበት፤ ቅጠል በጣሽነት ሥር ማሸተት የተወደደበት ዘመን ስመሆኑ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ሆባዎችም ቅጠል የሚበጥስ፤ ዕዳ እንደሚባ፣ ዕድሜውም እንደሚያጥር የተናገሩት እንዲህ ሲሉ ነበር፡፡

አህያ መጣች ተጭና ቆዳ

የቅጠል በጣሽ መጣበት ዕዳ፡፡

አህያ መጣች ተጭና ሉህ

ቅጠል አትብላ ያጥራል ዑምርህ፡፡

ሽሁም የሰው የጫት አቃቃም ገና ከሩቅ አስፈርቷቸው አቃቃማቸው ለአገር እማን ለገበያ ጥጋብ መለመኛነት ያስመሆኑ ታይቷቸው፤ አቃቃማቸው አስደንጋጭ ነው ሲሉ የተናገሩት እንዲህ በማለት ነበር፡፡

ይቅሙት ይሆናል ጫቱን እንደ እንጀራ

ማጣቡቂያው ስኳር ማማጊያው ሲጃራ፡፡

እም፤ ያሉት አልቀረም፤ የተናገሩትም መሬት ጠብ አላለም ሲጃራውም፤

ስኳሩም ጁረ እንዳውም ለስላሳውም ተጨማምሮ አዕምሯቸው ዞሮ፣ ልባቸው ተሰውሮ፣ ዐቅላቸው ተጠቅሎ፣ እድማጭ ሳይኖራቸው፣ ሰው ሳይጠጋቸው እጃቸውን እያወናጨፉ ጠጉራቸውን እያንጨበረሩ፣ ትንጫቸውን ነርተው፣ ዓይናቸውን አፍጠው ሲሄዱ ማየቱ የሰት ተሰት ትርዒት ሆኗል።

የጉሮ ውድነቱን፣ የሰውን ድህነቱን የሚሸጥ የሚሰውጥ የመታጣቱን፣ የእህል ዘር የሚያጥጥበት፣ ችጋር የሚያሽቅብበት፣ የቡኑ ውሰታ፣ የእድሩሱም ሽታ የማይጥምበት ወቅት እንደሚመጣም ያመላከቱበት ስንኝ እንዲህ የሚል ነበር፣

እህል በቆርቆሮ የሚቀናበት

ቡና በቢቾረ የሚሸጥበት

ጫት ተወዶ በሬ የሚረከስበት

ገበያ በሙሉ የሚጠፋበት

እንኳን ሌላው ነገር ውሰታው ያድሩብ

ይጠፋል ቲቀዳ ላቦል የሚጤስ። አሉና፣ አያያዘውም እር እንደሚከፋ፣ ደህና ሰው እንደሚጠፋ፣ ሰው በምቀኝነት እንደሚታወር፣ በውሸት እንደሚታጠር፣ ቀናነት ብሎ ነገር እንደ ዓይን እንደሚጠፋ፣ ሐሰ ውሸት ውሸቱ እውነት ሆኖ የሚሄድበት ዘመን መምጣቱን የተናገሩበት ስንኝ ይህን ይመስላል።

ክፉ ንፋስ አለች በጠቢያ መሬት

ሕልቁን እምት ጨርስ በቀን በለሊት

ማዕናውን ነገረኝ እቡስ የሚሉት

የኢፍራጣ ወንድም ነው በናትም ባባት

አጥሩ መሐከል እለ አይደለም ድንገት

ያስተማማቸዋል ዘይፍያው ብዛት። ካሉ በኋላ ውሸት እንደ ማሰ እሽት ማዘርዘሩን፣ ሐቅ መቀበሩን መልቲ መወደዱን ሆድ ለሆድ መተጣጣቱንም እንዲህ በማለት ተናግረው ነበር።

ውሸት ዘረዘረ ሐቅ ዕድሜ ጨረሰው
እሚጠው ቀበሩት ሰባት ጉድጓድ ምሰው
እንግዲህ ሰው ለሰው አልተገናኘም ሰው
በቆላ በደጋ ነፋስ የነፈሰው
እየገሸለጠ ቤቱን አፈረሰው
ምን ጊዜ እሚሸመው ውሸት ያፈራ ሰው
እባክህ ጌታዬ ሰባራ እንደ ደህና በነበር መልሰው

ካሉ በኋላ እናንተንም እኛንም ሽክፍ ድግፍ ያርገን እሱ ይሁነን ያሉበት ለኛ እንዲህ ይነበባል፣

እሳህ ይሁናችሁ እሳህ ይሁነን
ባስቸጋሪው ሁሉ እያስቸግረን

በራህመት ደመና ሽፍን ያድርገን በማሰት ክፉን እንዲያርቅልን፣ ደጉን እንዲያቀርብልን በመመኘት ሲያበቁ፣ ሸሁ ደጉን ቢመኙ፣ ከደርጉም ሊያልሙ ጀሊሉ ፊቱን ግራዋን ደረቱን በትር መዘርጋቱን ቁጣውን ያለማንሳቱን እንደ አክርማ መቀጨት፣ እንደ ቅጠል መርገፍ እንደሚኖር ሆባዎች እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል::

እህያ መጣች ተጭና ካራ
ይቀጠፍ ጀመር ወጣት ኩታራ
እህያ መጣች ተጭና ጅራፍ
ሞቱ በርክቷል የለም የሚተርፍ::
እህያ መጣች ተጭና ካሊም
ሶብይ ሶብዩ ዘንድሮ የለም::
እህያ መጣች አርቴ ይዛ
በመሐል አገር የለስ በዛ
እህያ መጣች ተጭና ጉፍታ
ወረርሽ መጥቷል የሚያንገላታ

እህያ መጣች ተጭና ጥጃ
የዘንድሮን ቀን ከራሚን እንጃ።
እህያ መጣች ተጭና ኩበት
ሰኛም ይተርፋል እኒያ የሚሩት።

ይህ ሁሉ ወጣቱ ወጥቶ ይገባባት፣ ተምሮ ለሀገር ለወገኑ ይጮህ ይቆረቆር የነበረበት ወርቃማ ጊዜ አልፎ እንደ ቅጠል የሚረግፍበት እንደ ሳባ የሚበንበት፣ እንደ አልባሌ ዕቃ የሚጣልበት፣ እንደ ጥንብ የሚወረወርበት ዘመን መምጣቱን ያመላክተናል። አሁን ላይ ቆመን ስናየውም እውነታው ፍንትው ብሎ ይታየናል። ዘመኑ ተቀይሯል። ልጅ አባቱን በበጐ ሲያስጠራ፣ እሰይ ጀግናው ሲባል ነበር እንጂ እሪ ሲል እናቱ ድረሽ ሲልማ ምን ያረጋል። አባቱን ያሳዝናል። እንዲህም ያስብላል፣

ፈሪ ልጅ ተመውሰድ ፍየል ማርባት ይሻል
የማነው ወጠጤ ሲያስብሰው ያመሻል
ነባሩ የቀረው ከመጀመሪያው ነው
ልጅ አባቱን ትቶ በናቱ ቲምል ነው።
እሰልስል እመንየምን ነፍስህን እይማረው

ወጣት ቁሞ ቀረ ፍቅር እያማረው የሚያስብል ሆኗል። ጊዜው ይሉና፣ የኑሮው ነገር ግራ ማጋባቱን ከቀን ወደቀን መያዣ መጨበጫ ማሳጣቱን፣ ችግር ማናወዙን፣ በነገርም መወዝወዙን በእንጉርጉሮ እንዲህ ይላል የቆዘመው።

ተሐቻምናው አምና ታምናውም ዘንድሮ
ብሰጭቴ በዛ እየባሰ ኑሮ
ዝንጀሮ በገደል አዳልጦት አይወድቅም
እንዲህ ያለ ጊዜ አጋጥሞኝ አላቅም።
የኛ ሙሽርነት እንዲው የግድ የግድ
እንጀራው ዘንጋዳ ሥጋው የጃሮ ግንድ
እኔማ ዘንድሮ ብበላው እልጠግብ ብለብሰው አይሞቀኝ

ይኸው ዐርባ ዓመቴ ውቃቢ ተራቀኝ
ባላጣው ሰው እየኝ ብጋግረው ሳሳ
ብሰክስክ ብሰክስክ አደረገኝና!!

ሲል ሲያዩት ወንጃ ሲናገሩት እንጃ የሚል ካንገቱ ዘንበል ከወገቡ ሰበር፣ ጠንልበቱ ሸብረክ የማይለው ሲነግሩት የማይሰማ፣ ካገር የማይሰማማ፣ ውቃቢ የራቀው ይይዘው ይጨብጠው የጨነቀው ነገሩ ከረር ሁኔታው መረር ሲልበት ምነው ባልተናገርኩ፣ ኧረ ምነው እንደበቴን በዘጋው ምላሴን በቆረጠው ዕድሜዬን ባሳጠረው ሲል ይቆጫል። ያስታራቂ የሸማገለ ያለህም ሲል ይደመጣል። እንዲህም ሲል ያንጐራጉራል፣

ደሴ ደረቆይራ ገራዶ ቢለን

የስንቱ መኸከል ስከፈኝ እኔን በማለት ሙሐቻው የጉደለበት፣ ማጀቱ ወና የሆነበት፣ ከሌማት እንጀራ፣ ከታጨ ሽምብራ ያጣው፣ ዛፍ ያጣ ጉሬዛ የሆነው፣ ቢለስብ ያልተባካለት ርምግኑ ያልወረደለት ምርቃት ያልያዘለት ደም የባሰ እንዳይመጣ በመፍራት፣

ተመስገን ነው እዩ ሰው ባያሌው ታሞ
ያማረሩት እንደሁ ይጨመራል ደሞ።

እያለ ሲቆዛዝም፣ ጊምበሎችም የመጪውን ጊዜ ጨለማነት የጉሮን እንደ ባማ ሰብሳቢነት፣ እንደ በርበሬ አንገብጋቢነት፣ እንደ ቁስል ቆጥቋጭነት፣ እንደ ሬት ጉምዛዥነት፣ እንደ እንቆቆ እንገሽጋሽነት በየመልኩ ይገልጡታል። የገበያውን መስሰብ፣ የሚቀና የሚሸጥ መጥፋት፣ ወቅቱም መቅኖ እንደሚያጣ ይናገሩና እህሉን ተረፍ በላውንም መሰስ እንዲያደርገው፣

መቃም ነው ማስቃም ነው መስሎ ጥቁር ማቅ
የሚመጣው ዘመን ቁርጡ እስኪታወቅ። ማለቱ እንደሚበጅ ይናገሩና የነገሩን አካሄድ እንዲህ ይሉታል።

እህያ መጣች ተጭና ቴልት
የዘንድሮ ቀን መቅናም የላት
እህያ መጣች ተጭና ችካል

የዘንድሮ ቀን ጫት ያቃቅማል።

እም! ያቃቅማል። በላሙን ተበሪድ፣ ሰውንም መሙሪድ እንዲያደርገው፣ የታመመው እንዲሸር፣ ያዘነውም እንዲበስር፣ ሀቅልን ሰብስቦ፣ ልብንም ከፊት አርጐ ከኑሮው አለመሟላት ከነገሮች መጥመም የሰው መከፋት፣ ከምግቡ፣ አለመጣም፣ ከሰውነት ተራ መውጣት ያስጨነቀ ያስጠበበው የሹመኛው አላስቆም አላስቀምጥ፣ አላስወጣ አላስገባ ባይነት አንገቱን ያስደፋው፣ ወገቡን ያጉበጠው፣ ሁሉ ነገር ያንገሸገሸው እህህ የሰባለው ይህን ይላል፦

በላይ ጅቡ መጣ ከታች እንበሳው
በመሀል እሣማ ሊጨርሰን ነው
በላይ ጅቡ መጣ በደጋው እንበጣ
ዳግም መፈጠር ነው ዘንድሮን የወጣ።

ገብሱም በተራው እርር ድብኑን እንዲህ ሲል ይተነፍሳል።

እኔ ባይወማ አባቴ በኢንማ እናቴ ባይኢለማ
የሞተ ሰው መልካም ይህንን ላይሰማ

የተማሩ የተመራመሩ ዐዋቂዎችም፣

መሞት በዚች ዓለም መች ሀዲስ ነውና
ብርቁ መኖር እንጂ ያላንዳች ጭቀና። ይላሉ።

ሼሖችንም፦ ጥንቡሱ ፊላና ሰበረው ጋኑን

አሁን ማን ያቀዋል የሚሆነውን ሲሉ ነገሩ የደነቀው ሁኔታው ያስጨነቀው ተራ ሰው ደሞ፣

እንደው ዝም ጥርቅም

ቀን የሚወልደው አይታወቅም። ይልና አትናገሩ፣ አትገዙ፣ አትጮሁ፣ ኡኡ አትበሉ ሲሉን አፋችንን ከርክም፣ በራችንን ጥርቅም አርገን መኖር ነው። መስፍሰፍ መዘባረቁ ለምን? ምን ሊፈይድ ብለን ብንተወውም ነገሩ፣

ብሸሸው ብሸሸው መከራው አይለቀኝ

ደሙ ተፈናጥሮ ልብሴን አበላሸኝ። እየሆነ የዛሬ ዘመን ሰው ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት ይላል። ያልበላውንም ሲያክ ይስተዋላል። እንዲህም ያስብላል፤

እረ ሰው እረ ሰው ሰው አስቸገረኝ
ቢናገሩ አፈኛ ዝም ቢሉ ሞኝ።

ድሮ ድሮ አርሶ በሌውን የቅርቡ ሹመኞች አጥቢያ ዳኛና ምስለኔ እሮይታ ሲነሱት ዱሩ ቤት ማለት ሲከጅል፤

ሱሪዬን አውልቄ እንልድማያ ታሰሁ
ቀን የወጣ እንደሆን እታጠቃታስሁ።
ምስለኔ ልጥ ላጠ ጭቃ እንጨት ቀረጠ ጉጃ ሲሆኑብኝ
ሸተት ይኸን ጊዜ ሳያዋቅሩብኝ።
እረ ተውኝ ጭቃ ልቀቁኝ ምስለኔ አትድረስ ተደጀ
ገንዘቤን ጨርስህ ትጠፋለህ በጀ። ሲል አሁን አሁን ደሞ፤
አህያው ገጣባ በሬው መቀናጀ
ብርቱ ሰው አድካሚ እንደምንሽ ጉጀ

ማለት ሲጀመር፤ ደባስ ብሎ አሞቱ የፈሰሰውን በፍርሃት ቆፈን የተኮራመተውን እንዲህ ይሉታል።

ዐመለኛ ዶሮ ቀፍቅፉ ቀፍቅፉ
ሴቶች ብቻ ሆኑ ኩኩ የሚል ጠፋ
ማሽላ እሸት በልቶ ደሞ ማቲጉላ
ወኔው ቀዝቃዛ ነው እንደ ቁልቋል ጥላ
እናቱ ቀቅላ እቱ እየመተረች እያለችው ብላ
ወኔው ቀዝቃዛ ነው ጉዳይም አይሞላ ይሉታል።

እንጀቱ እርር ኩምትር ያሰው፤ ነገር ያስመረረው፤ ይከፍለው ሽልንግ፤ ይጉርሰው ቂጣ፤ ይለብሰው ሸማ የቸገረው ነጭ ጉግ አምጣ ጥቁር ውትት ውሰድ ብሰው ፈጥርቀው ሲይዙት መውጫ ቀዳዳ ማጣቱን ግራ የገባው መሆን በዚህ መልክ ይናገራል።

ላሚቱ ጠቶ ታም እላባው ዕውር
እንዴት ያለ ቀን ነው የሚያደናግር
ያስገርማል እዚ ይገስ አያስቅም
ጠጣ ትትጉዙትዝ ዝገጀር ሜት ቲቶም
ጅብ ራሱን ታሞ አህያ ትታከም፡፡
ነገሩ ያላማረው መናገርም ያስፈራው እልጉምጉሚ.
የኛ ዘመን አልፎ አሁን በሰው ዘመን
እንዝታችን ደፍተን እንደ ጤፍ በመመን
ላገኘ ነው በማለት ሞትኩኝ በሰቀቀን
ሀይ ሀይ እሉቱ የምጠብቀው ቀን
ደስ ያሰው ደስ ብሎት የከፋው ከፍቶታል
ይኸን ጊዜ ቤቴን በርባሪ ገብቶታል፡፡
እንዴት ያረጉታል የዕድልን ጉንባሳ
አሮጌ ቤት አደል በባላ አይነሳ ይልና ሰጠቅ አርጉም፣
ሠላሳ ኮሚቴ ሠላሳ ኮፒ አለው
በሠላሳ ኮፒ እየሰቀሰቀ
ድሃም ተሰደደ ሐብታሙም አለቀ
ውሃ ማቆር ሥራ በብዛት ሠርተናል
ጉድጓዱን ቆፍረን ጅቦች አቁረናል
ሰው ባደባባይ የሆዱን ሳይናገር
ተከታትሎ አለቀ እላው እግር በግር
እምላክ የሰም መሰል ታሰበት እገር
ዝም በሉ እየተባልን እንዳንናገር
እትዬ ማሚቴ ውሽማሽ ማን ማን ነው
አይስፈለፍም የዝምታ ቀን ነው፡፡

ጊዜው ደህና ነበር የተደላደለ

ሹሞቹ በሱና ድሃ ተበደለ

አሉቅታም ወንዝና ሹመ ብዙ አገር

ጥጅም አያወጣ ድሃም አያኖር። ሲል መድረሻ ያጣው ከርታታ፣ ኔሉ ደም ነሩ ሁሉ እየባሰ ወቅቱም እየከፋ የሚሄድ መሆኑን ይህን መሰለናኝ ይናገራሉ።

ውሻ ቲዘልቅበት ጅብ ዘሮ ይሸሻል

ይነጋል ብንለው እያደር ይመሻል።

ውሃ ቅልቅል እዩ አሻቅቢ አይወጣም

የባስ ቀን እጁ የተሻለ አይመጣም።

የዘመኑ መከፋት፣ የሁቀኛ መጥፋት የበረከት ማጣት ያስጨነቀ ከበበው፣ ችግር እንደ መርግ የተጫነው ዕዳ ያጉበጠው ብሶቱ፦

እንዲህ ያስ ዘመን ዘመኑ ገሰባ

የታመመው አይሽር የወጣው አይገባ።

ምን ያስ ዘመን ነው የዘመን ወልጋዳ

ስፍተንም ማስነንም ሆነናል ባለዕዳ

እነሱ በበሉ እነሱ በጠጡ በስማ ጀራችን

አልወርድልን አለ ዕዳው ተጀርባችን።

መገን ያገሬ ሰው እየው ጉዳችንን

አልወርድልን አለ ዕዳው ተጀርባችን

በሮቼን አምጡልኝ አርጀ እበላቸው

ደሞ እንደ መሬቱ ሳይካፈሏቸው

ጊደሯም ተሸጠች ሙክቱም ተነዳ

አላስቀምጥ ቢለኝ የማዳበሪያ ዕዳ። ይላል።

ስለዚህ እንደ በደላችን እንደ ኃጢአታችንና ስንፍናችን ብዛት ሳይሆን

እንደ ቸርነትህ ይቅር በሰን ማስት ተገቢ እንደሆነ ሸሑ እንዲህ በማለት ነበር የተናገሩት፦

ዱአን በቀኝ እጁ ጨብጦ መያዝ
የዛን ቀን ይወጣል ከብዙ መዘዝ
እየዋ ልንገርህ እንዳትል ፍዝዝ
የሐበሻ ልጆች ተዉ ዱአ አድርጉ
ተከፉ ተደጉ ያወጣል በወጉ
ስሥቻይቱ ዑዲኒያ ሁሴም አደግድጉ
ዱአን የጠበቀ አያይም መከራ
ነቢ ተናግረዋል የወይባው ሙሽራ
በዱአ ተጥናና ላንተ እንዲበጅህ
ለሰው ትተርፋለህ እንኳን ለራስህ፡፡
የዑባዳ ራሱ ዱአ ነው ብለዋል
ሙኩል ኢባዲቱ ብለው ተናግረዋል
በሰማይ ቀበሌ መሊኮች ቲያወጉ
ባጤ መባል ቀርቶ ይባላል በደርጉ
ያኔ ተዱአ እንዳትዘናጉ
መሬትና ሹመት እንዳትፈልጉ፡፡

ቁርዐን መድኃኒት ነው
ዱአ መትረየስ ነው
ሙኸፍ እንባ ነው
ዐደብ እንዳጥር ነው
አጥር ተተጣሰ ሁሉም መፍረሱ ነው፡፡

እሱ፡፡ በጾም በጸሎት በፍቅር በትህትና፣ በየዋህነት በትዕግስት፣ ተጠምዶ መኖሩ ከሐሣር ወደ ክብር፣ ከረሃብ ወደ ጥጋብ እንደሚያሸጋግር ስማያዊና ምድራዊ ክብር እንደሚያጐናጽፍ ዓይን ያላየውን ጀ

ነው። ሌላው ሁሉ ዕዳው ገብስ ነው። አሳሳቢው፣ መላ ያጣው የእርስ በርስ መተሳሰቅ ነው ያሉት በዘመን ተሻጋሪ ስንኞቻቸው እንዲህ ነበር።

ፈረንጅ ፈረንጅ አለኝ አበሻ መሬቱ
የፈረንጁስ ነገር አለው መመለሻ
እኔን የቸገረኝ አበሻ ባበሻ።

እዎ የወንድማማች እልቂት አስቸጋሪ ነው። ይህም የታየው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ከወረዱ በኋላ ነው። ሰዎች ግርማዊነታቸው ቢወርዱ ኢትዮጵያ ትበጠበጣለች ይባል ነበር። ይኸው እኛ ሥልጣን ላይ ብንወጣ ምንም አልሆነች አገሪቱ ሰላም ነች ሲሉ ሌላው ፍርሃቱ ሲበረታበት፣ ችግሩ ሲያይልበት ሽሎ እንዳሉት እየየውን አበዛው። እንጉርጉሮውንም ተያያዘው። ትንሽ ታይቀይም፦

የፓፓ ቆቡን ደፍቶ ባናቱ
ወቴ ጸሰ ይላል ከነዝተቱ
የደረጉ መኪና ሽሯ የለበሰው
ተማሪውን ሁሉ ወደቱ አደረሰው። አሉ።

ነገሩም ከረረ፣ ጦሩም አመረረ፣ ወጣቱም ደነበረ እንዳሞራም በረረ። የሞተም ሞቶ የታሠረም ታስሮ ሰውም እንዲህ አለ።

የደርጉ መኪና ሽራ የለበሰው
ተማሪውን ሁሉ አፈር አለበሰው
የተማሪው ደብተር አልጠፋም ተገኘ
እመሐል ፒያሳ ላይ በደም እየዋኘ።

ካሉ በኋላ ከድጡ ወደ ማጡ ሄድን ኧረ ይቅር በሰን ሲሉ፦

ኃይሌ ማረኝ ማረኝ ኃይሌ ማረኝ ማረኝ
የደረጉስ ነገር ምንም አላማረኝ።
ቀላጢያችን ሜዞ ግብራችን ብር ታምሣ
አባ ታጠቅ ኃይሌ እባክህ ተነሳ።

ለሜን ቤገምድርን ነፋስ ወዘወዘው
ለላስ ቅጠል ኖሯል ደግፎ የያዘው
ፖሊስ ሌባ ሆነ ጦር ሠራዊት ፈራ
አገሬ ጉድ ሆነች ቀና በል ተፈሪ
ነፃነት እጥቶች ከምሠለጥን
በኃይለ ሥላሴ ባላገር ልሁን

ማለትን አዘወተረ፡፡ እነሆ ሆ፣ ብሎ ያወረዳቸውን እኒህን በታሪክ ፊት የተረጋገጠና የገነነ ስም ያላቸውን ንጉሠ ነገሥት ከላይ በተባለው መልክ ሲያነሳቸው ንጉሡም "አገርና ታሪክ አይሞትም የታሪክንም ክብር የሚጠብቅ ትውለድ ነው፡፡" ያሉትን የሚያዘክር ነው ወጣቱ ያሰው፡፡ በሠሩት ወጣቱን ለማስተማር የወጡ የወረዱትን የሥልጣኔን ሙራ የፈነጠቁትን ኢትዮጵያን በዓለም ላይ የሚባትን ክብር ያጐናጸፏትን ተከብረው ሕዝባቸውን ያስከበሩትን፣ ዓለም ያደነቃቸውና ያስደነቁትን የነፃነት አባት የሆኑትን ገናና ንጉሠ ነገሥት ታላቅነት ለመግለጽ ቄሱ ስም፣ ክብርና ዝና እያወሳ እያወደሰ እንዲህ ይል ነበር፡፡

ተማሪው፤ አበባ ይዘን ተሸልመን
ሰላምታ እንስጠው ላዲስ ዘመን
ስሙ ይታወቅ ባለም ሙሉ
ኃይለ ሥላሴ ጠቅል በሉ
በጠቅል ጊዜ ያልተማረ
ማዘኑ አይቀርም እያደረገ
ቶሎ ቶሎ ተጋገዙ
ፀሐይ ወጣ ሥራ ያዙ ሲል

ካህኑ ደግሞ፤ ምንጨም ተፈሰቀ በተራራው ላይ
በተሉ ውጥተን እንቀዳም ወይ

መሰላሉም ሳለ መወጣጫችን

ኃይለ ሥላሴ ነው አባታችን:: ይላል

ኮሪያ ዘማቹ ጦርም፣

አባ ጠቅል ኃይሌ የኢትዮጵያ መሪ

እናት ኢትዮጵያ በጣም በጣም ኩሪ ሲል

ሌላውም፣ መንግሥትን ለዳዊት ቡራኬም ለሴም

እንዳንት የተሰጠው አንድም ሰው የለም

እንደ ማቱሳላ እንደነ አብርሃም

ዕድሜህን ያርዝመው እምላክ ዘላለም ይላል::

ሸህ ሑሴን ጅብሪልም የግርማዊነታቸውን ታላቅነት ገና በጥዋቱ እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት::

ለሚካኤል ልጆች ይዣለሁ ትግያ

ልጅስ ተወለደ ተመኮንን ጉያ

ቁሜ አልሃምዱ ቁጭ ብዬ አተህያቱ

ተፈሪን ተፈሪን አለች መሬቲቱ

ተፈሪ የሚሏት ትንሿ ወጠጤ

የኋላ የኋላ ትባላለች አጤ::

እናገረዋለሁ እርጌ ተልክ

ሸዋ ላይ ይባላል በተፈሪ እምላክ

ኢትዮጵያ አገራችን ራሷን ተሠርታ ተብላ ልክክ

ተቀብታዋለች ቤሌምበር በምሥክ

ትሸታቸዋለች ሰርማ ሰቁርክ

በሰማይ ጠያራው በመሬት ላይ ታንክ

እየመጡ ቀሩ እያሉ ልክክ

ኃይለ ሥላሴ ነው ባሏማ በልክ

በኋላ፣ የ1928ቱን የጣልያን ወረራና የአምስት ዓመቱን ስደት መለ

ያመለከተውም፣

የሀገሽ መሬት ምን ያሸብርሻል
ይመጣል ተፈሪ አሁን ያረጋሻል
ሁተኛው ደሴ በጠባሲት ኩስ
ጌደ ያሉት ዕቃ መጣ ተመልሶ
ተወደቀ ወደ ተፈሪ አባ ነፍስ
ላይሙት ላያህይ ሁሉን ሸኝ ቀዲር
ተመልሶ ገባት ያበሻን ምድር
ኃይሊሥላሴማ ተፈሪ አባ መላ
ዐርባ ዓመት ይገዛል አበሻን በሙሉ።

ይሉና፣ ሰጠቅ አርገውም ከልጅነት እስከ ሹመት እንደ ተናገሩት ሁሉ ከሥልጣን ስለ አወራረዳቸውም እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት፣

እኛ አፈር በገባት ባንድ መቶ ዓመት
ተፈሪ ዓይኑን ታሞ ይገዛል መሬት
ሰማኒያው ያልቅና ቲሆን ሦስት ዓመት
ተማሪ አፈረሰው የተፈሪን ቤት
ጀበብ ጀበብ አለ ወታደር ወጣት
በታተነውሳ የተፈሪን ቤት
ገና ታትወጣ የተፈሪ ሱሪ
በገጠር ይዘምታል የሚሉት ተማሪ

ሲሉ ጊምባዎችም፣

አህያ መጣች ተጭና እንጆድ
ክፉ ቀን መጥ ቷል የሚያጣክድ አሉ።

ሺሉም ቀጠል አርገው እንዲህ አሉ።

ባይሆን ቀኑ ቲደርስ ዐርባ ዓመት ቲሞላ

የገዛ አሽከሮቹ ያዝ አርገው በመላ
ታልጋው ያወርዱታል በችግር ሲቆላ
ተዛም ያቀምሱታል
ታልጋው እምዘግዝገው ምድር ይጥሉታል
በፊት መቃ መሥራት እንዲህ ያንገላል
ሕልቁን እንደ ቀጣው ችግር ያቀምሱታል
መስከረም አንድ ቀን ድንገት ይይዙታል
ሳመት አሥራ አምስት ቀን ቲቀረው ይሞታል
የገዛ አሽከሮቹ ያላደጋቸው
በዙፋኑ ባልጋው ያሞናደላቸው
ታልጋው ያወርዱታል ጓሊል ሰልኗቸው

ሲሉ ሽሑ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ስህገር ዕድገት ስወገን ኩራት አያሌ ተግባራት መሥራታቸውንና በሰላም የማረፊያ ጊዜያቸውን አሰበው፣

እንግዲህ አገሬ እኮራብሻለሁ

ያሰብኩትን ሁሉ ሠርቸብሻለሁ የሚቡት ፋታ ሳያገኙ ሥልጣናቸውንም እንደሚይጡ ሽህ ሁሴን ጅብሪል እንዲህ ሲሉ ነበር የተናገሩት፡፡

በሰማይ በራሪ በምድር ተሽከርካሪ
ወት እንዴት ደረስ ልጃችን ተፈሪ

በማስት እምጥ ይሁን ከምጥ የተቀበሩበት ወይትና እንዴት እንዳልታወቀ ይናገራሉ፡፡ ይህ ሲነሳ አንድ ነገር ያቃጭልብናል። እነ ወሎየ ከደሴ ወደ አዲሳባ ያቀናል፡፡ ወደ ወንድሙ ቤት፡፡ ወንድምየውም መጣሁ ሳይለው ዱብ ዕዳ የሆነበት የወንድሙ አመጣጥ ያስደነግጠውና የአባትን የእናቱን የዘመድ አዝማዱን ሁኔታ ሲጠይቀው ደህና ናቸው ይለዋል፡፡ ይመሽል ይተኛሉ፡፡ አዲሳቤው በዓይኑ እንቅልፍ ሳይኳል ይነጋል፡፡ ወፍ ሳይንጫጫ ይነሳና ወንድሙን ይጠብቃል። ከእንቅልፉ አልነቃም፡፡ ግራ ቢገባው ተነስ ቁርስ ደርሷል ሲል ይቀሰቅሰዋል። እውሰኛቸውን ከበሉ በኋላ በል ሥራ መሄዴ ነው። ለምን ድንገት

እንደመጣህ አልነገረኝ አልክ ቢለው፣ የመጣሁትማ የግርማዊነታቸውን መቃብር አይቶ ልመለስ ነው ቢለው ቅጥል ይልና እስስ ከልጅ ኢያሱ አጠገብ ነው ቢለው የልጅ ኢያሱ መቃብር ወዴት ነው? ሲለው እኔ ወት አውቄ ሲል ይመልስለታል።

ያም እስ ይህ የንጉሡ አሟሟት ሳይታወቅ፣ መቃብራቸውም ሳይገለጥ በዝም ዝምታ ታለፈ። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ሸሑ እንዲህ ያሉት?

ልጅ ኢያሱ ንግሥ በሸዋ መሬት
ጥቅልል አርጉ ይዞ ያያቱን ግዛት
በኋላ እንደገና አሳይ ሹቱበት
ዘኒ ሆነ ብለው በቀንም በሌት
ታልጋው አስወረዱት በሥራው ብዛት።
ባሽከሮቹ ጥፋት ደሞም ባጋፋሪ
ዘውዱ ቲዞር አየን ወደ ልጅ ተፈሪ ይሉና ለጠቅ አርገውም፣
ቀጥላ ነገሠች ዘውዲቱ እሚኒት
እምሳያ የለሳት መልኳን ትታይዋት
የራስ መኮንን ልጅ ተፈሪ ሚሉት
መቃ ሥራ ሠርቶ ገሎ ቀበራት
ሦስት ህመቱን ገዛች ያቺ ቆንጆ ሴት
እቤት ውስጥ ቀብሮ መደብ ሠራባት
በመቃ ይሞታል መች ቢቀርለት
በዘውዲቱ ጡር መቃ በሠራበት
ጥቂት ያቀምሱታል ክስረት የበዛበት
በሱ ጊዜ ያለው ሹማምንት ባላበት
ቱራ ያድኑታል ሁሉን በያለበት።
ኃይሌ መቃ ሠርቶ በዘውዲቱ ራሳ
ተዚያችው መደብ ላይ ቢሞትባትሳ

ጊታችን መች ነው ጀዛ የሚረሳ

ዘውዱን ተራሱ ላይ ሱሱን ቀምተው

ሀመድ ያሰብሱታል ቅመሰው በሰው

ባለ ብዙ መላ ባለ ብዙ ሐብት

ደርጉች ያወርዱታል ከእልፍኙ በኩራት

በንግሥት ዘውዲቱ መቃ በሠራበት

ታልጋው ወርዶ ታስሮ አልቅሳ ይሞታል

በራሱ ጡር ውሎ መቃ ቀይቶታል። ካሉ በኋላ ሕዝቡ መከራው እንደሚጠና ሰላሙ እንደሚጠፋ፣ ቁም ስቅሉን እንደሚያይ፣ ነገሩ ሁሉ መላው የጠፋ እንደሚሆንበት እንደ ደረቆት እንደሚታመስ፡-

እንዲህ ሀዳ ሀዳ እዱንፓ ትታልቅ

እማሹም አይደክም ታማሹም እያልቅ

ታምሰን ታምሰን ምጣዱ ቲሰማ

ታይጉዳ አይቀርም ትልቁ ከተማ

ብለው ነበር ሸሁ። ምን እያየን ነው? ሁሉም ይናገረው፣ ምን ይባል ምን ሸህ ሁሉን ጅብረል፣

ተቴዎድሮስ አንስቶ ተፈሪ ድረስ

ዘመኑ ያበቃል የዘውድ ንጉሥ

በምርጫ ታልሆን የለም የሚነግሥ

ግን ሕሰቁን እኖነው ብዙ ቀን ቲያሰቅስ

እንዳሉት እነሆ ነጋ ጠባ እየየ ነው። ረፈደ መሸም እንጉርጉሮ ነው።

እንጉራጉራሰሁ የደላው መሰዬ

ሰሲቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብዬ

ብቻ ሆኑ ነገሩ። ሸሁም እንባ እሚያብስ ችግር እንደማያቃልል ተማሪም እንደሚመራ፣

እፉኚያ ታልቅና ትትሆን ምልፈት
ይበረካከታል የመንደር ሹመት
ጭቃ ሹም ይቀራል ፊት የነበሩት
አበሻን ይመራል ተማሪ እሚሉት

ብሰው ነበር ሆነ። ነገሩ ስይ መቧጠጥ ነገር ማሳመጥ የሰው መቀላወጥ ቻ ሆነ። ዘመቻና ሰፈራ መዋጮና ትጣት በዛ። ጉዳዮች ሁሉ የኮሚቴ ሥራ ሆነ። ሰውም እንዲህ ማለት ጀመረ። ባፋቸው ትምርት በጃቸው ታምራት ሚሠሩት የተናገሩት ሰምሮ ከቀ.ኃ.ሥ. በኋላ በወየው ወየው አለን። ነገሩ ለጤ ተሞቀ በማን ይሚገቱ መሆኑ ነው።

የሐብታም ልጅ ቀረ ብሩ ግን ዘመተ
የድሃ ልጅ ኸደ እየወተወተ
ኮሚቴ ቲባላ የሰውም ትንፋሽ
እንጀራው አለቀ ተልባው ታይታሽ
አንዱን ብንሸመው አንዱን ብንሸር
ታሰ ብር አይኸድም የኮሚቴ እግር
ያሳማ ኮሚቴ የጅብ ሊቀመንበር የጠጣ ጠሐፊ
ኸረ ተይ አንቺ ቀን ቶሎ ቶሎ አለፊ
አቶ ዐረቂ በፊት ቂስ ብሩ እያብራራ
ይኸን ያላመጣ መሬት ሳይመራ።
ኮሚቴና ካድሬን ጣለብን እግዚር
አምላክ የለም መሰል ታሰበት አገር
አሻቅቤ ባየው ሰማዩ ቀለለኝ
አንተንም ሰፈራ ወሰዱህ መሰለኝ
መሬት ባንቺ ደሞ ምን ኃጢያት ኑሮብሽ
ኮሚቴ እንደ ሰጦ ያገለባበጠሽ
እባክህ አምላኬ ነፋሱን መልሰው

ወንድሙን ወንድሙ ሽጦ ታይጨርሰው
አላሻግር አለኝ ይኸ ትንሽ ፈፋ
መቸም ባገር አልኖር ኮሚቴ ታልጠፋ
መይገማን ትሰምደው አይወማ መጣብኝ
አይወማን ትሰምደው አይሰማ መጣብኝ
ተደገሙትማ የከርሞን አይቸ
ገዳም እገባለሁ ቆቤን አስፍቸ
እኔ በኢገማ ሚስቴ ባይኢሰማ
የሞተ ሰው መልካም ይህንን ሳይሰማ
እንዲት ጊደር ሽጬ ኢገማ ከፍዬ
የናት አገር ጥሪ የድርቅ ከፍዬ
እንዲት ብር ተርፋኝ ጥሬ ጨሌው ልገዛ ዓይኔ ቲቅለበለብ
መንጭቀው ወሰዷት ላስተማሪ ቀለብ
የዘንድሮውስ ቀን መራር እንደ ጌሾ ሆምጣጣ እንደ እምባጮ
ብንወልደው ሚሊሺያ ብንዘራው መዋጮ
እንዲህ ያለ ዘመን የዘመን ቁረንጮ
ወልዶ ለዘመቻ ሠርቶ ለመዋጮ
ሁለት ችጋራሞች እንደኛው መላጣ
ሰኞ ተሰብስቦ ማክሰኞ ብር አምጣ
ሾልቦ ለደርግ አባል ላዳ ላቃጣሪ
እኔን የተረፈኝ የናት አገር ጥሪ
እንዝመት ታላችሁ ላኩን መተከል
ምንድ ነው ሠፈራ ዶሮ ይመስል
እንዝመት ታላችሁ እንዝመት ሁመራ
እንዝመት ተላችሁ እንዝመት አሥመራ

ተምን የመጣ ነው የሚጨት ስፈራ
እያልኝ ስሙልኝ ዘንድሮ ጉዱን
ሦስት እህል ዘራኊት ዐርባ ባምሳዩን
ወይ አልተጣላን አልተነጋገርን
ሰተት ብለው ገብተው ቤት አፍርሱ አሉን።
ኧረ እናንተ ሰዎች ለቆመው አልቅሱ
ሁለት ግሞች አሉ ጠንራ እሚያፈርሱ
ወንዱም አሳረሰ ሴቱም አሳረሰ
እንደ ጥንብ አሞራ ቤት እያፈረሰ
እናበቅል ነበር ሠርገኛ ተነጭ
መኪና ወስደው በሳው ተቀማጭ
ምን እንኳን ቢርበው ጅብ አይበላም ቆስጥ
እንደምንም ብሎ ቀበሌ መመረጥ
ጥበቃ ጓድ ነብሩ ፍርድ ሸንጐ ሚካ ሊቀመንበር ገደል
አልሰማም ወይ ደርጉ ገበሬ ሲበደል
የሞተውም ሞቷል ያለውም ተጣልቷል
ዝምድና ሊታጠብ ውሃ ተወዝቷል
አይኢሰማም ይሉናል
አይኢወማም ይሉናል
ጉልበታችን ደክሚል አንዱ ይበቃናል
አምራችና ጋሪ ሁለቱ አንድ ናቸው።
ዓይናቸው ታልጠፋ ማረፊያም የሳቸው
የቤት ሊቀመንበር የሴት ፍርድ ሸንጐ
እንግዲህ ደህና ሁሉ ድስትና ሙጉጉ
ድስትም ቶሎ ፍላ ምጣድ ቶሎ በማ

ሴቱ ተሸክፎ ቆሟል እንደማማ
እሷም ቸኩላለች አሰባት ሰብሰባ
እምቢ ብለህ እንደሁ ኋላ ሰዳ እንዳትገባ
ታነክትሃለች አፈሙዝ አንግባ
ቅዳሜም ታረሰ እሑድም ታረሰ
ሚካኤል ታረሰ ገብርኤልም ታረሰ
ትዝብቱ ቀረ እንጂ አምራችም ፈረሰ
እሰጥ አገባ ነበር ሙግታችን
ራቦር በመጣፍ ሠላሳ ዓመታችን
ደርግ ደመና ነው ኮሚሽን ካፊያ ነው
እንጀቴን ያራሰኝ መካነ የሱስ ነው
እናንት ጨዋ ሰዎች በቅሎ ነበራችሁ
እናንት መኪንንቶች ፈረስ ነበራችሁ
ደኸያችሁ መል አህያ ገባችሁ
ያመተየስ ልጅ የወሰቴ ልጅ
ሞዴል ቤት ተሠርቷል መጥተህ እየው እንጂ
ብድር አመላለሱ እንደዚህ ነው እንጂ
እነ አባተ ዓለሙን እያማረራችሁ
ሰሊት የሚበሉ አባል መረጣችሁ
እንዲህ ያለ ዘመን ዘመነ ደንቆሮ
ምሑር ወደ ጫካ ወቴ ወደ ቢሮ
ጠላም ይጠጣና ይፈሳል አምቡላ
ሥጋም ይበላና ይጣላል አጥንቱ
ዓይኑን ያፈጥና ይቀራል ትዝብቱ
እንዲህ ያለ ዘመን ዘመነ ግርምቢጥ

ውሻ ወደ ሠርጾ እህያ ወደ ሊጥ
አረ እነዚህ ሹሞች ምንኛ ቀበጡ
በሰኔ ዘመቻ በሐምሌ ብር እምጡ
ሃምሳም ሜዞም እሱ ስሚን አሳንሰው
የከረምንበትን ወሰዷት ጨርሰው
መቸም ተይዣለሁ በብዙ ኮሚቴ
እኔ አረዳሁሽም ወልደሽ ተኪ እናቴ
አሁን የሚሠራው ባዲሱ መደሻ
ይጠቅመን ይሆን ወይ ለኛ ለህበሻ
ኧረ እነ ኮሚቴ የናንተስ መቃብር እንዲህም አልነበር
በታች አጋም አርጉ በላይ ቀጋ ነበር።
ኮሚቴ እሚባለው ኃይለኛ ጋሜ ነው
ትናንትና በሌቱ ዛሬም እማረው
እነሱም አደሱ እኔ ነኝ ደንቆሮ
አርጀ ቢበላስ እንደ አሬራች ዶሮ
እንደው በደረቁ እያዋየኒቸው
እምንነድ ዱር ጣሉኝ ርሁሻ መስያቸው
አቶ ዐረቂ በፊት ቂስ ብሩ ተኂሳ
ይኸን ያላመጣ መሬት አያገኝም ቀረ በመሐላ
ተሊቀመንበሩ እስማማለሁ ብዬ
እንዲህ ተጠሐፊው እስማማለሁ ብዬ
ሚስቶን አስደፈርኳት እህቴ ናት ብዬ
ባባቴ ቤት ሙማ እንዳልበላሁበት
በናቴ ቤት ጠጄን እንዳልጠጣሁበት
ኮሚቴ መጣና ኽርም አጣሁበት

ስሊቀመንበሩ ዐሥር ብር አጥቸ
ለሰባት ኮሚቴ ሰባት ብር አጥቸ
አላገር ማሸላ ከረሙ ልጆቸ
እየበሉ ሙማ እየጠጡ ውስኪ
ማንን ለመምሰል ነው የሰበሱት ካኪ

ዘመን ተለውጦ ታሪክ ተገልብጦ፣ ግንባሬን ላረር ደረቴን ለጦር እግሬን ለጠጠር ይል የነበረ ተዋጊ ጠላቱን ቆንጥር ለቆንጥር ያሳድድ የነበረ ተሳዳጅ ሁኖ፣ አሳሪው ሲታሰር ታሳሪው ሲያስር ማየቱ እጅግ ያስገርማል። ነገሩ ሱሚ ተራ ተራ የሚሉትን ያዘክራል። ጀምበር በማዘቅዘቋም ዘሃርም በመዞሩ ቆራጥ ተዋጊ ይል ለነበረው ጦር ገበሬው እንዲህ አለ።

እነ እንቁላል ቁርሱ እነ ሥጋ ጥብሱ
ወረታ ሲተኮስ ዳንግላ ደረሱ
እገር አማን ሆኗል በሉ ተመለሱ
እነ ዳቦ ቁርሱ አረቂ ትራሱ
ሐሙሲት ሲተኮስ የትም አልደረሱ
እጃቸው ተያዘ ሲተረማመሱ
ምክር ቤት በጋሪ ኢሠፓ በፈረስ
ይሽቀዳደማሉ ዳንግላ ለመድረስ
ይጠላለፋሉ እኔ ልፈርስ እኔ ልፈርስ
ቀበሌ በበቅሎ ደህንነት ባህያ ምክር ቤት በፈረስ
እሽቅድድም ያዙ ዳንግላ ለመድረስ
አወይ አያ ኢሠፓ እግዚአብሔር ያጥናህ
ወረታ ሲተኮስ ማርቆስ የገባህ
እነ እንቁላል ቁርሱ ውስኪ ነው መክሰሱ ሻጋሻ ነው ትራሱ
ሐሙሲት ሲተኮስ ወደቤት ደረሱ?

እናሸንፋለን ስትሉ ከርማችሁ
ወያኔ ስትመጣ ወዲት ደረሳችሁ
አገር ደህና ሁኗል ግቡ ሰፈራችሁ
ዲስኩሩን ቀጥሉ እንደ ልማዳችሁ
እንዲህ አገር ሲደላደል
ባለሥልጣን ሁሉ ገባ ገደል፡፡
አወይ አያ ኢሠፓ እግዚአብሔር ያጥናህ
ሐሙሲት ሲተኮስ ማርቆስ የገባህ
የጥቁር ሰው ዘሩ ይባላል ሀበሻ
ማርቆስን አረጉት የፈሪ መሸሻ
አገር ሲረጋጋ እንዲህ ሲደላደል
ኧረ እነ ኢሠፓ የዘለሉት ገደል
አንት የጣና ድልድይ የጉጃም ንጉሥ
ያን ሁሉ ወታደር ወዴት አደረስህ
እነ ቆስጣ ቁርሱ እነ ጉመን ጥብሱ
የኛ ወታደሮች በላት ተጠበሱ
ሙቶ አለቃ ሮጠ ሻለቃም ሮጠ
ኰኔኔር ሮጠ ጀኒናር ሮጠ
ሕዝባዊ ሠራዊና ጣና ላይ ቀለጠ፡፡
አባትየው ደፋር ልጁ ፈሪ ቢሆን
እናቱን ጠይቋት ዘር ቀላቅላ እንዳይሆን
የበሮቹ ጭራ ዝምብ አይከለከልም
መዋጋት ነው እንጂ መሸሹ አይቸግርም
እንደ ዛሬው ሳይሆን ፍርጠጣ ሳይበዛ
ወረታ ከተማ የነበረሽ ለዛ

Scanned with CamScanner

ሸምብራ እሸቱ እንጂ አይበላም ሥሩ
ወረታም ጆዳ ነው ጠንክረው ተሠሩ
ታንክ ቢደረደር መትረየስ ቢያጓራ

ወረታ የቀረ ደሃና ባንዲራ:: ተብሎ ካበቃ በኋላ ባለድሉቹ ሲደላደሉ፣

ስማችን ወያኔ ስዳባችን ቅማላም
የደርግን ወታደር ነዳነው እንደላም
መላሰቸው ምላጭ ልብሳቸው እድፍ
ትልልቁን ሁሉ ነዱት እንደ ጉርፍ
በሬዬንም ሽጬ ልጆንም ሰጥቼ
ጋብዬንም ሽጬ ሱሪየን ሳስማማ
ኢህአዴግ መጣልኝ በነጠላ ጫማ::
ይኸው የነበረ እስከትሎ ውሻ
ከእንግዲህ ቀረሰት ሞፈር ዘመት እርሻ
የዘንድሮ ነፋስ ወደላይ ነፈሰ
ዱርዬ ቁጭ ብሎ ኢሠፓ ታፈሰ
ሠርቼ እንዳልበላ ኢሠፓ ፈረሰ
ሠርቶ እንዳልባላ ኢህአዴግ ደረሰ::
የበላህም ብላ የጠጣህም ጠጣ

ከዚህ የበለጠ ምንም ቀን አይመጣ:: ሲሉ ገምባዎችም ስለት መሥጋት ቀን መፍራት ቀረልህ ሲሉ፣

እህያ መጣች ተጭና ስንጋ
እርፉህ ተቀመጥ ስሲት እትስጋ አሉ::

ቅጠል በላ ቢሄድ ግንድ በላ ይመጣል ይሉ ዓይነት ሆነና ሰው፣

እንተ እቅሰው ስሰው

እያመጣ ቆለለው ሆነና ነገሩ እንዲህ ያስብል ጀመር:-
የምቀኛን ምላስ ይንቀለው በለጋው
እያደገ እየለ እሾህ የሚወጋው
እሾህ ብቻ ሆኗል እግሬን ብዱበሰው
እንዴት መላወሻ መሄጃ ያጣል ሰው::
አወይ ያገሬ ሰው እየው ጉዳችንን
አልወርድልን አለ ዕዳው ተጀርባችን
ልጅም አምጡ ቢሉን ልጅም ሰጠናቸው
እህል ስጡን ቢሉን እህል ሰጠናቸው
ቤቱን ስጡን አሉን ጠገራው ቀርቷቸው
እጅ መንሻ ፈላጊ ከፉ ዳኛ መጥቶ
ድሃው ተሰደደ የሚከፍለው አጥቶ
ጊደርዋም ተሸጠች ሙክቱም ተነዳ
አላስቀምጥ ቢለኝ የማዳበሪያ ዕዳ
አንድ በሬ ነበረኝ የማልበው የማርሰው
አስራት መጣ ቢሉት ታሞ ተኛ እንደሰው::
ምን ያለ ዘመን ነው የዘመን ወልጋዳ
ለፍትንም ማስነንም ሆነናል ባለዕዳ
አይዞች ሙሃቻዬ አይዞሽ ብርብራዬ
እበካብሻለሁ ቢተርፈኝ ተዳዬ
ጊዜው ጥሩ ነበር የተደላደለ
ፈራጁ በዘና ድሃ ተበደለ
ምን ሊሆነኝ ጉጆ ምን ሊሆነኝ ቤት
እንግዲህ በሐብቴ ታላዘዝኩበት
ጊደሯም ተሸጠች ሙክቱም ተነዳ

አላስቀምጥ ቢለኝ የማዳብሪያ ዕዳ
ቀን ይወጣል ብዬ ብጠብቅ ባስጠብቅ
እንኳን ቀን ሲወጣ ጨለማ ነው ድቅድቅ

ሲል ባላገር፣ ጋዜጠኛ ደሞ እንዲህ ሲል ያስነብባል፡፡

መሬትም እንደ ዕቃ ኸደ ተወደነ
የኛ የነበረው ዛሬ የሰው ሆነ
ሄዷል ተወድኖ ተሸብሎ በሰው
ትውልድ ካቦ ሆኖ ሰቦ ካልመለሰው፡፡

ሰውየው ሰዎች ሲስቁ ሳቀ አሉ፡፡ ምነው ምን ሰምተህ ሳቅህ? ቢሉት፣ መቸም ተናንቶ ክፉ ነገር አይወጣም ብዬ ነዋ አለ ፈርቶ፡፡ ከሹምና ከጥልቅ ፊት ዘወር ነው ይባል የለ እሱም ዘወር ሲል እንዲህ ነበር ያለው፡፡

ሐምሊ ግብስብሱ መስከረም እራሱ
ባልና ሚስት እንኳን ቀርቷል መጓረሱ
አውጣኝ አውጣኝ ሆኗል ሁሉም ለየራሱ
በወያኔ ጊዜ መሬት ያገኛችሁ
ዲቡን አታፍርሱ ይረጋ መስሏችሁ፡፡
አህያ መጣች ተጭና ግልድም
የተጠጋ ሰው እንዴት ይለድም
ወንድማችን ሞቶ ሆነን ሀዘን ላይ
ቤታችን ተቃጥሎ ቁመን ባመድ ላይ
እንታረቅ ቢሉ ሆድ ይሽራል ወይ

ሲል ጊምባ ደሞ፣ አህያ መጣች ተጭና ቁና
ተጋደል ይልቅ እርቁን ተውና፡፡

ይላል፡፡ ከዛሬ ነገ ያልፍልኛል፣ አልፍ ሲሉ አልፍ ይገኛል ብዙ የሚያስበው ጀምበር በወጣች በጠለቀች ቁጥር ከትሮው ፈቀቅ ያላለው ወደ

ነበት ያሽቆለቆለው ሺ ቢታሰብ ያው በገሊ እንዳለችው ድመት የሆነበት፣

መልኩም ተለውጦ ተተልከሰከሰ
ታምናው ተታችምናው የዘንድሮው ባለ፡፡
ይነጎል እያለ ሰው ሁሉ ያወጋል
እንኳንስ ሊነጋ እያደር ይመሻል
ያምናን ቀን እማሁት ሳፈ ለከት የለው
የዘንድሮው መጣ እጅ እግር የሌለው
ሳምላክ የምነግረው ምሥጢር ስላለኝ
ቀን ያልፋል ብለውኝ በመጠበቅ ላይ ነኝ
የውሃን ጉደሎ ውሃ ይሞሉታል
የጠጅን ጉደሎ ጠጅ ይሞሉበታል
የቀንን ጉደሎ እንዴት ያረጉታል

ይልና ለጠቅ በማድረግ፣

አልቅሱ እንሳቀስ ጊዜ ያመጣውን
ሳቅና ጨዋታ ድሮ የቀረውን
አንቺ ለቅሴቱ ምን ጊዜም ቤቱ ነሽ
አቀስልሽኝ እንጂ እኔንም ጨምረሽ፡፡
የድሮ ዝሬ እርሶ ይለምናል
የዘንድሮ መንግሥት ወራርሶ ይበላል
የመጣውም መጥቶ ተስፋ ታስቀረጠን
ከዝንጀሮ ቆንጆ ምኑን አስመረጠን
ያልሞተበት የለም ያልጉተተ እሬሳ
ጨዋታ አይደለም ወይ ሐዘን የሚያስረሳ
ሽምብራ ብዘራው ሆነ አሉ በርበሬ
ቅመሙ ተሸዋ ጭብጨባው ተትግሬ

ይኸን ቀማምሜ ብወቃቅጠው
ድንግርግር ብሎኛል ቀኑንም አሳቀው
ለዱአ መስለፍ ይኸን ጊዜ እኮ ነው
ወንድም ተመራሬት ጥንብን በሩቅ በለው።

መጠለያ ጉጆ መቀመጫ በርጩማ ያጣ፣ ቢርበው የሚያጉርሰው፣ ቢበርደው የሚያለብሰው አጥቶ ሰማይ የተደፋበት ግራ ተጋቢ፣

ወይ እንደ ቀበሮ አልገባሁ ተጉሬ
ታገሬ ላይ ሁኘ ናፈቀኝ አገሬ።

ሲል ነበር ያስመረረው። ኑሮ ያደነባበረው፣ ብረር ብረር ያለው፣

አንተ ያገሬ ውሃ አረንጓዴ አትልበስ
እጠጣህ ይሆናል ምናልባት ብመለስ

ሲል ወላጁ ደሞ፣

ደህና ብትመለስ ደህና ብቆይህ
ከሽብር ይበልጣል የማሜውትህ

ይላል። ሲላው ሆድ የባሰው ደሞ፣

አገራችን ታሞ ተኝቶ ባልጋ ላይ
ትተነው መጥተናል ሞት ሽረቱን ታናይ
የሚጓዘው በዛ ወንዝ የሚሻገረው
እዚያ ሊያልቅ ይሆን ወይ ከዚህ የሚሸሸው
በእንዲህ ያለው ዘመን ቲመሽ ተወልጄ
ጅቡን ጋሽ እላለሁ ውሻውን ወዳጄ
አተር ሽምብራውን ዝም ብለሽ አቅርቢው
እኛም አይተነዋል የታመሰው ቀን ነው
ተስፈቱ ነው ወይ ሲሠራ የጠፋው
እንቡ አለ ሞሰቡ ያልበላ እየገፋው

ያልታወቀ ሐኪም ተኛ ተደብቆ
ብዙ ሰው ጨርሷል ጉሮሮውን አንቆ
ኧረ ወገኖቼ እዩት ጉዳችንን
አልወርድልን አለ ዕዳው ተጀርባችን
በቀይ ሽብሩ በብሔራዊ ውትድርናው

በአርሻ ስብሉ በግብርናው ሲያማር የነበረው ሁሉ፣
መርዶ አይሉት ምሥራች አይመች ለወሬ
መንግሥቱ ኮብሉ ገባሉ ሐራሬ::

ሲል ቆይቶ ነገሩ ሁሉ አላምረው ሲል የወደዱትን ሲያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ እንዲሉ ሆነና ገበሬው መልሶ፣

እንደ ኮራ ኺደ እንደ ተጀነነ
አንድነት ወይም ሞት እንደ ተማጠነ::
ስንዴው በሄልኮፐተር በቆሎው በጆት
መንጌ ኃይለማርያም የድሆች አባት
መንጌ ኃይለማርያም አይሙት አይበላሽ
ሰተራበው ስንዴ ሰጠገበው ኮላሽ::
መንጌ ኃይለማርያም ምን ምንህ ይረሳል
ብርድልብስህ አለቆ ኬሻህ ይሰበሳል
መንጌ ኃይለማርያም የብረት ምሰሶ
የጠፋውን አገር አቀና መልሶ

በማለት በስንዴው ነው፣ በመሬት ነፃ መስጠቱ፣ በብርድ ልብሱ ነው፣ ከቶ በምኑ ነው የምትረሳው? በማለት ያሞጋግሱታል::

ያም አለ ይህ ከንጉሡ ከሥልጣን መውረድ በኋላ ብዙ ብዙ እጅግ ብዙ ተብሏል:: ግርማዊነታቸውም የኛ ዘመን እዚህ ላይ ያበቃል:: የናንተ ይጀመራል ሆኖም ግን የኢትዮጵያን አንድነት የማትጠብቁ ከሆነ የናንተ

ይወቀስና የኛ ስም ይነሳል ያሉት አባታዊና መሪያዊ ትንቢት ዛሬ ላይ ሆኖ ለሚያየው እውነት በስድሳ ስድት ዓመተ ምህርት የተባለው ሁሉ ቀርቶ ነው? ያስብላል። ጊዜ እንዲህ ያረጋል ባንድ ራስ ሁለት ምላስ ይባል የለ?

ዘመንን በዘመን የሚያድስ ፈጣሪ የመንግሥቱ ወራሾች የሰሙ ቀዳሾች ያረገን ዘንድ ሞልቶ ከረፈው ዕድሜ እንዲያድስን የምንሰምነው ገበሬው የሚናገረውን ምሑሩ የሚያስነበበውን ለመመልከትና፣

ዕድሜ ያሰውና የዘገየ ሰው

አይቀርም ይደርሳል ልቡ ካሰበው።

የሚለውን ለማወቅ ነው። ቡተስፋ ተሻድር ነፍሴ ይባል የለ? አዎ የዜሩና የወሰደ ተስፋ አይቀርጥምና፣

ሰታምር ሠራና ሰታምር አቆጠኘ

ድንቅ ነው ፈጣሪ ይህንን አሳየኘ

ማለቱ ተመስገን ነውና። ሺሑም ባንድ ወቅተ ማተብ አብቱ፣ ሃይማኖት ሰውጡ በተባሉ ጊዜ፣

ደጋውም ቁንጫ ቆላው ረምጫ

የሰይድ አሽከሮች አጣን መቀመጫ።

እንዳሉት ሁሉ እንደ ሰብ የጠስጡበት እንደ ጉመን የተቀረደለት መሬታቸው ሲሄድ ቤት ሲፈርስ ሕዝብ ሲታመስ ማኅበራዊ ሕይወት ሲቃወስ፣ ድሃ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ የሚል ሲጠፋ፣ ድህነት ሲዘፋ ወኝ መናገር ቢሳን እንጉት ደፍቶ ቤት ዘግቶ፣

እንጉራጉራለሁ የደላው መስዬ

ሰሲቱ እንዲነጋ ቀኑ እንዲመሽ ብሎ ማለት አይለነውም።

ምንም ይሁን ምን ሰው በየዘመናቱ ሁሉ ይሉው ይናገረው አያም፡ ብዙም ብሏል እያለም ነው። ለአብነት ያህልም፣

ፉቱ የሞቱት ሰዎች መቸ ተበላሹ

ይኸን ቀን ሳያዩት ደግ ጊዜ ሸሹ

እዳኙቱን ውሻ ነከሰቻት በግ

[illegible]

[illegible]

[illegible]



Scanned with CamScanner

ላሙ ውተት የለው
በሬው ሻኛ የለው ቻኛው ቀጠሮ አብገር
እንግዲህ አብቅቷል ዓለም አትናውገር
እኔን ቆማጣ ቲሉ
መሄጃ አጣ ሰው ሁሉ። እንዳሉት፣
ወዳም ወዲህ ቃጣን
መጠጊያ መሸሻ አጣን
ያንተው ነው ሁሉም ሥልጣን
ምን ባልን ምን በወጣን
እኛ አልበላን አልጠጣን
ተበላው ጋር አትደባልቀን
ኧረ ባክህ ለየት አርገህ ነጻ አውጣን
እስቲ እንተባበር ለዚች አንዲት አገር
ዋልታና መከታ ብንሆናት ማገር።

የሚለው። ተንጉሡ አንሳስና አወዳደር ድረስ ያለውንና ሹሙም ይደርሳ
ያሉትን አቅርበናል። ከንጉሡም በኋላ ሕዝቡ ያለውን ሙሻዖ ሆ
ለቅምሻ አሳይተናል። አሁን እኛን የሚበጀን፣

ዝግ ይሁን የበላው በር
በዱአ እንተባበር
ፍጡራን ቲሸበር
ታንወድቅ ታንሰበር
ሰላም አውጣን በሰላም በር።

ማሰቱ ነው። ወይ ደሞ፣

ወፈር አርገህ በጥብጥ ውሃ እንዳታስመታ
ርቅዝ እንድታገኝ ተላይኛው ጌታ።

አለዛ፣ እኔ ሰሉ ብየ ስለፉ ስለፉ



Scanned with CamScanner

ታጥቆ ብድግ አለ ሊዶለኝ አፈፋ
ሳዳቸቹ መጀን ሁለት ዓይኑ ይጥፋ
የጠሳ ተራራ አይበቅልም ቡን
የወደድከው ይክዳህ ዱበርቲ መጀን እንሳለን።

ሸሑም፣
ሸንበቆ ቢረዝም ቅል አያንጠለጥል
ርግማን በዛና ሰው ወዳጁን ቲጥል
ነገር ቲቅመዘመዝ ቲሻገር እንደ ትል
ምነው ዘመድ ወዳጅ ዱኣ አትል ዱኣ አትል

ይላሉ። ስለዚህ እኛም፣

መቃም ነው ማስቃም ነው ሆኖ በሸርጡ
አሉን ቁጥቦች ጥሪ እሚያዳምጡ።
ኑ! ግቡልን እንጂ አይባሉም ውጡ።

እንዲህ ተሆነ፣

አሚን የአሚን ልጅ አሚን የወደደው
የዘራው ይበቅላል ያድጋል የወሰደው

እሚባለው እንዲሆንልን ጊምባዎች፡-

አህያ መጣች በቀስታ ብላ
ዱአህን ቀጥል አዳሜ ሁላ
አህያ መጣች ተጭና ዱላ
ዱአህን ቀጥል አትበል ቸላ

ያሉትን ልብ በማለት አገራችን ገበሬው አርሶ የሚያመርትባት፣ ነጋዴው የሚያተርፍበት፣ የታመመው የሚሸርበት፣ ያጣ የሚያገኝበት፣ የተጣላ የሚታረቅበት፣ የወጣ ባማን የሚገባበት፣ በላው ተበረድ የሚሆንበት እንዲሆን በዱአ መተባበር ነው። በጾም በጸሎት መጽናት ነው። ጸሎት ብርታትን ይሰጣል። ጉልበትን ያበረታል። ክንድንም ያጠነክራል።

በአሸናፊነትም ያዘልቃል። እንግዲህ እንዲህ እንዲህ ዓይነቱን ስናይ እናት አገር ኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ማማ፣ የስበባት ማኅፀን፣ በመሆኗ በፊደሏ የምትኮራ፣ በታሪኳ የምትጠራ፣ በቆራጥ ልጆቿ የምትከበርና የምትታፈር ከመሆኗም በላይ ዘመን ተሻግረው በሌላ ጀምበር ዘልቀው የሚሆነውንና የሚፈጠረውን መናገርና ማስተማር የሚችሉ ታላላቅ ሊቃውንት አባቶች እንደነበሯት ድርሳናት በነቃሽነት ይቆማሉ። የእበውን አስገራሚ፣ አስደናቂና አስተማሪ አባባሎች በመሸከፍ አሻራቸውን ማደስ ከኛ ይጠበቃል።

ጀንበሯ አላዘቀዘቀችምና እስቲ ወደ ውጭ ብቻ ሳይሆን ወደ ውስጥም ለማየት እንሞክር። ነገ ሳይሆን ዛሬውኑ!! እበውን ለመቃኘት ጓዳ ጕድጓዳውን ለመቧጠጥ፣ ለመፈታተሽ እንሞክር። የሰው ወርቅ አያደምቅ ነውና!!

## ዐምደ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀያትህ ይቆይ | ዕድሜህ ይርዘም፣ ዑምርህ ይርዘም |
| ሀልቅ | ፍጥረቱ ሰው |
| ለበይክ | አቤት ማለት |
| ሐጃ | ጉዳይ፣ ተከር የሚፈጸም፣ የሚሞላ |
| ሐቻ | ዘለዓለም |
| መውሪድ | የወንድ አገልጋይ፣ ካዳሚ |
| መቆዘም | ማዘን፣ መተከዝ፣ አንገት መድፋት |
| መጀን | መከታ አድርኤለሁ |
| መናቁብ | ታሪክ ንግግር |
| መርሃባ | እሺ፣ በጉ፣ በጀ |
| መኸለቅ | መወሰድ፣ መፈጠር |
| መቅራት | መማር ፊደል መቁጠር፣ አሊፍባ ማለት |
| መጾረር | መቆጣት፣ ማኩረፍ |
| መቅራብ | ክብት ግባት |
| መከወን | መሰብሰብ፣ መሸከፍ |
| መፈየድ | መፈጸም፣ መተከር |
| ሙሃቻ | ቡሃቃ /የሊጥ ማቡኪያ |
| ማጀት | ጓዳ |
| ሰደቃ | ምጽዋት፣ ተስካር፣ የነፍስ ይማር |
| ሰበር | ረጋ፣ ጨመት ያለ ቻይነት፣ ታጋሽ፣ አደብ ያለው |
| ሲር | ምሥጢር |
| ሶላት | ስግደት |
| ሸረጥ | መሰስ፣ ዘወር፣ ገሸሽ፣ ለቀቅ ሲያደርግ |
| ሸክክ | ተጠራጠረ |
| ሸሊላ | እሺ፣ በጀ ይሁን ማለት እርስዎ እንዳሉ |
| ሸዋትህ ይለምልም | ዘርህ ይባረክ ሸህወት |
| ቀልብ | ልብ አእምሮ አቅል |
| ቀዬ | ግቢ፣ በራፍ፣ የደጃፍ አካባቢ |

| | |
|---|---|
| ቃዲ | ሹም የሸሪአ ዳኛ |
| ቅዋ | አቅም ቀድር ጉልበት |
| በቀተ | ስደት |
| በጌ | ሜዳ |
| ቱፍታ | ምርቃት |
| አረዳ | ስፈር ቀበሌ አደባባይ |
| አድኒያ | ዓለም ሲሳይ እርዝቅ |
| አውልያ | ውቃቢ ባላህ ትዕዛዝ |
| አውገረድ | የትዳር ጓደኛ /ሚስት/ |
| ኢልም | የተማረ ቀለም የገባው |
| እሰላማይላኩም | ጤና ይስጥልኝ |
| ኢማን | እምነት |
| ከሰዋ | ግርዶሽ |
| ከራማ | ታምራት፣ የሚያሳይ መንፈስ |
| ከተበ | ዳፈ /ጻፈ/ |
| ከይር | ሰላም ደህና |
| ካዳሚ | ሴት አልጋይ |
| ኸሊቅ | ፈጣሪ አላህ አንድዬ |
| ወልይ | ጠንቋይ |
| ወዳጃ | ጸሎት ዱአ |
| ወሰሜ | በቂምሃ ሰዓት /ጸሎት/ ጫት መቃም በሚጀመርበት ወቅት ተሰይተው የሚቀመጡበት |
| ወፍቅ | ተስማሚ ስጦታ |
| ዝሁር | ከስድስት እስከ ሰባት ሰዓት ድረስ |
| ደረሳ | የተማሪ ቃልቻ /ተማሪ/ |
| ጀባ | እንካ /ምርቃን/ |
| ጀነት | ገነት፣ መንግሥተ ሰማይ |
| ጡሌ | የውኃ መያዣ ቅል |

## የሕዳር መዘክር

1. መንግሥቱ ለማ፣ መጽሐፍ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ፣ አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም. ገጽ 5
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 5
3. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 10
4. አለቃ አጽመ ጊዮርጊስ፣ የጋላ ታሪክ /ያልታተመ/
5. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ. /አዲስ አበባ፣ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት፣ 1941 ዓ.ም. ገጽ 54
6. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 53
7. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 54
8. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 137
9. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 137
10. ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም. ገጽ 45
11. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ ጥ.ሥ. ገጽ 165
12. ከበደ ተሰማ /ጥ.ሥ.፣ ገጽ 46
13. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ ጥ.ሥ.፣ ገጽ 51
14. ከበደ ተሰማ፣ ጥ.ሥ. ገጽ 51
15. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 47
16. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 47
17. ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፣ አማርኛ እኔ ከነመፍቻው፣ /አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1958 ዓ.ም. ገጽ 11
18. አባ ኪዳነማርያም ጌታሁን፣ ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ፣ /አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1955 ዓ.ም.



Scanned with CamScanner

## ዋቢ መጻሕፍት


1. መንግሥቱ ለማ፣ መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ኃይሉ ወልደ ታሪክ። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም.
2. መንግሥቱ ለማ፣ የግጥም ዓይነት ሥራቱ፣ ሥርዓቱ
3. ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል፣ አማርኛ ቅኔ ከነመፍቻው። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1959 ዓ.ም.
4. ዓለማየሁ ሞገስ፣ የአማርኛ ግጥምና ቅኔ ማስተማሪያ። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1954 ዓ.ም.
5. አለቃ አጽመ ጊዮርጊስ፣ የጋላ ታሪክ ያልታተመ።
6. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ። አዲስ አበባ፣ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት፣ 1941 ዓ.ም.
7. ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ። አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም.
8. አባ ኪደነ ማርያም ጌታሁን፣ ጥንተዊ የቆሎ ተማሪ። አዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1955 ዓ.ም.
9. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ አጼ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት
10. ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ አጼ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት
11. ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ



- ለኔ ማለት ቀርቶ ሲባል ለኛ ለኛ [illegible]
  እባክህ [illegible] አታቋርጠው ቀኛ።

- በእንዲህ ያለው ዘመን በተመናመነው
  አውጣኝ አውጣኝ ብለህ ጌታህን ለምነው።

- [illegible]
  እንዲህ [illegible] አገር ሆነ ባዶ።

- [illegible]

- [illegible]

- [illegible]

[illegible]

ዋጋ 91.50ብር
(15USD)




Scanned with CamScanner